# አእመረ ኢትዮጵያ

# Think Ethiopia

**(ቅጽ አንድ)**

**አዲስ አበባ፤ ኢትዮጲያ**

2018 ዓ.ም

©**አእመረ ኢትዮጵያ** Think Ethiopia
**(ቅጽ አንድ)**

**የውስጥ ገጽ ቅንብር - መርሃጽዮን ጌታቸው - 0902938910**

# በኢትዮጵያ ላይ ያተኮሩ መጻሕፍት ዳሰሳዎች መድበል
# A Compendium of Book Reviews on Ethiopia

## ርዕሰ አርታኢ

**ዳዊት በዛብህ**

## ተባባሪ አርታኢዎች

**ቢኒያም አቡራ**

**ወልደጊዮርጊስ ይሁኔ**

**የሺጥላ ይገዙ**

**ሲራክ ወንድሙ**

**መኮንን ደፍሮ**

**ዮዲት አማኑኤል**

## አባላት ያልሆኑ ዳሰሳ አቅራቢዎች

**መሰለ ተሬቻ**

**ጻጋዬ አዳም**

**አንዋር ሙሰማ**

# ማውጫ

መግቢያ......................................................................7

## 1. ግለ ታሪክ እና ትውስታ

-የሚሳም ተራራ.........................................................13
-“ሕይወቴ፥ ለሐገሬ ኢትዮጵያና ወገኖቼ ኢትዮጵያውያን ዕድገት
የነበረኝ የሥራ ጥማት፥ ከ1917-1967 ዓ.ም”.........................19
-አንዳፍታ ላውጋችሁ....................................................33
-Thomas A. Lambe: A Missionary Doctor and Entrepreneur...........37
-ብር ሕይወቴ.............................................................39
-አባት ዐልባ ሕልሞች...................................................45
-ባንዲራ ሳይኖረኝ እንዳልሞት: ኢትዮጵያ፣ ከንቱ ሕልሜ እና ሰቀቀኔ....49

## 2. የፈጠራ ጽሑፎች

-ፀሀይ ከጨለማዬ ምን አለሽ.........................................55
-ከደመና በላይ..........................................................61
-ሀገር ያጣ ሞት..........................................................67
-ስለ ትናንሽ አለላዎች...................................................77
-ወድቆ የተገኘ ሀገር.....................................................85
-በተለይ አስራ አንደኛው...............................................89
-ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ....................................99

## 3. ሥነ መለኮት እና ፍልስፍና

-ግርባብ [ያደግሰው]....................................................111
-‹ዮቶር› ኮብላይ ካህን.................................................119
-የሕግ ፍልስፍና.........................................................125
-የኢትዮጲያ ረቂቅ ፍልስፍና..........................................145
-Borrowing Freedom...................................................151
-የእከይ እና ስቃይ ጣጣ.................................................153

## 4.ጥናት እና ምርምር


-ምሁሩ…………………………………………………………………161
-ሆህያተ ጥበብ፤ ለጸሐፊያን፥ ለተርጓሚያንና ለአርታዕያን……………167
-ድብቁና ያልተነገረው የአይሁዳውያን እና የኢትዮጵያውያን ታሪክ…173
-The Teshome Habte Gebriel Reader………………………183


## 5. የሕይወት ክህሎት


-"የፈረንጅ ሚስት"……………………………………………………189
-የልብ ጠጋኙ ማስታወሻ………………………………………………193
-የኔ ማስታወሻ…………………………………………………………199
-ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ………………………………………203
-የትዝታ ፈለግ…………………………………………………………209

# መግቢያ

የመጻሕፍት ዳሰሳ ከጥንታዊ ዘመን ጀምሮ በተለያዩ መልክዎች ይታይ ነበር። በጥንታዊ ግብፅ፣ ግሪክና ሮም ውስጥ ምሁራን የሌሎችን ጽሑፎች በመተቸትና በማወደስ ይገልጫሉ ነበር። እንደ ፕላቶና አርስጦትስ ያሉ ፈላስፎች የሌሎችን ሐሳቦች በመገምገም ይፅፉ ነበር። ነገር ግን ዘመናዊ የመጽሐፍ ዳሰሳ በ17ኛውና 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአውሮፓ በተለይ በእንግሊዝና ፈረንሳይ በመጽሔቶች (journals) መልክ ተጀመረ። እንደ "The Monthly Review" (1749) እና "Edinburgh Review" ያሉ መጽሔቶች መጻሕፍትን በስፋት መገምገም ጀመሩ። በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ በጋዜጣዎች ውስጥ የመጽሐፍ ዳሰሳ ተወዳጅ ሆነ፣ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ በሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና አሁን በበይነ መረብ (እንደ Goodreads፣ Amazon፣ ብሎጎች) በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዳሰሳዎች ይጻፋሉ። የመጽሐፍ ዳሰሳ ቀዳሚ ጠቀሜታ አንባቢዎችን መምራት ነው። በየዓመቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍት ሲወጡ፣ አንባቢ ጊዜውንና ገንዘቡን ለሚገባው መጽሐፍ እንዲውል ዳሰሳ መመሪያ ይሆናል። ጥሩ ዳሰሳ የመጽሐፉን ጥንካሬና ድክመት፣ ዋና ሐሳብ፣ የጸሐፊውን ዘይቤና የሥራውን ተፅዕኖ በግልጽ ያስረዳል። በተለይ ለተማሪዎች፣ ምሁራንና ተመራማሪዎች የተወሰኑ መጻሕፍት ጠቃሚ መሆናቸውን ለመወሰን ይረዳል። በተጨማሪም ዳሰሳ አዲስ ወይም ያልታወቁ ጸሐፊዎችን ወደ አንባቢ ይደርሳል። ረጅም ጊዜ በሚቆይ መልኩ ደግሞ የመጽሐፍ ዳሰሳ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ መዝገብ ይሆናል። የአንድ ዘመን ዳሰሳዎች ያን ዘመን ማኅበረሰብ ምን እንደ ሠራ፣ ምን እንደ ወደደ፣ ምን እንደ ተችቷል ያሳያሉ። ለምሳሌ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፉ የቪክቶሪያ ዘመን ዳሰሳዎች ዛሬ የዚያን ጊዜ ሥነ ምግባርና የፖለቲካ አመለካከት ለመረዳት ያገለግላሉ። በመጨረሻም ዳሰሳ ደራሲያንን ያሻሽላል፣ አንባቢዎችን ይወያዩበታል፣ የሥነ ጽሑፍ ውይይትን ያበለጽጋል። ስለዚህ መጽሐፍ ዳሰሳ መጽሐፍና አንባቢ መካከል ድልድይ ብቻ ሳይሆን የሥነ ጽሑፍ ባህል ዋና አካል ነው።

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ዓለም ታሪክ ውስጥ በጣም ተደማጭነት ያላቸው ዳሰሳ አቅራቢዎች መካከል ቨርጂኒያ ዉልፍ (Virginia Woolf)፣ ጆርጅ ኦርዌል

(George Orwell)፣ ሃሮልድ ብሉም (Harold Bloom) እና ሚቺኮ ካኩታኒ (Michiko Kakutani) ይጠቀሳሉ። ቨርጂኒያ ዉልፍ በ1920ዎቹና 30ዎቹ ውስጥ በThe Times Literary Supplement ላይ የጻፈቻቸው ዳሰሳዎች (በተለይ "The Common Reader" ስብስብ) ዛሬም እንደ ሥነ ጽሑፍ ዳሰሳ ምርጥ መመዘኛ ይቆጠራሉ። ጆርጅ ኦርዌል ደግሞ በ1940ዎቹ የጻፋቸው ተችሯማና ቀጭን ዳሰሳዎች (እንደ "Politics and the English Language" እና በTribune ዓምድ) የፖለቲካ ግንዛቤን ከሥነ ጽሑፍ ጋር በማገናኘት ታይቶ የማይታወቅ ተፅዕኖ ፈጥረዋል። ሃሮልድ ብሉም በ"The Western Canon" (1994) እና በበርካታ መጽሐፍት ላይ ባደረጋቸው ዳሰሳዎች የሥነ ጽሑፍ ሥልጣን (canon) መፍጠር ላይ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ሚቺኮ ካኩታኒ ደግሞ ከ1983 እስከ 2017 በThe New York Times ዋና የመጽሐፍ ዳሰሳ አቅራቢ ሆና በመሥራት ፑሊትዘር ሽልማት አግኝታለች፤ ጽሑፎቿ በተለይ ዘመናዊ ልቦለዶችን (እንደ ሳልማን ሩሽዲ፣ ካዙኦ ኢሺጉሮ) በጥልቀት የተተነተኑ ናቸው። በዘመናዊ ዲጂታል ዘመን ደግሞ የዩቲዩብና ብሎግ ዳሰሳ አቅራቢዎች ተወዳጅነት አግኝተዋል። ከእነዚህ ውስጥ በጣም ታዋቂዎቹ Better Than Food (ክሊፍፎርድ ሊ) — በጥልቀትና በፍልስፍናዊ አቀራረብ ይታወቃል። Daniel Greene በተለይ ፋንታሲና ሳይንስ ፊክሽን (Brandon Sanderson፣ Robert Jordan) ላይ ያተኮረ ሲሆን Merphy Napier በማንጋ፣ በልቦለድና በክላሲኮች ላይ ሚዛናዊ ዳሰሳዎች በማቅረብ ታዋቂ ነው። በሌላ በኩል Jack Edwards በወጣቶች ዘንድ በጣም ተወዳጅ፣ በወቅታዊ መጻሕፍት ዳሰሳውና በቀላል ቀልዱ ይታወቃል። እነዚህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮች ያሏቸው ሲሆኑ የመጽሐፍ ገበያን በቀጥታ ይነኩ ዘንድ የደረሱ ሲሆን ብዙ መጻሕፍት "BookTube effect" ተብሎ በሚጠራው ምክንያት ታዋቂ ይሆናሉ። ስለዚህ የመጽሐፍ ዳሰሳ ከተለምዷዊ ጋዜጣ እስከ ዲጂታል ሚዲያ ድረስ በመለወጥ ዛሬም የአንባቢዎችን ምርጫ ይቀርፃል።

የመጽሐፍ ዳሰሳ ለግለሰብ እውቀት እድገት ትልቅ ሚና ይጫወታል። መጽሐፍትን በማንበብ ሰው አዲስ እውቀትና ተሞክሮ ያገኛል፣ ሃሳቦች ስለሚፍታቱ የማሰብ ችሎታ ይጨምራል፣ ችግር ፈቺ ችሎታና ክህሎት ይዳብራል። በተለይ በአፍሪካ ሀገራት የመጽሐፍ እጥረት በመኖሩ ምክንያት

ብዙ ልጆች የማንበብ ችሎታ እያጡ ነው። በአፍሪካ ሀገራት የመጽሐፍ ዳሰሳ ለትምህርትና ማህበራዊ እድገት ዋነኛ መሳሪያ ነው። መጽሐፍት በቤት ውስጥ በመኖር ልጆች የማንበብ ባህል ያዳብራሉ፣ የቋንቋ ችሎታቸው ይጠናከራል፣ በትምህርት ቤትም የተሻለ ውጤት ያስመዘግባሉ። በሀገራቱ ያለው ድህነትና የመጽሐፍ እጥረት የልጆችን የእድገት ደረጃ ይቀንሳል። በዓለም ባንክና ዩኔስኮ ሪፖርቶች መሠረት መጽሐፍት የልጆችን የስሜት ብስለት በእጅጉ ያሻሽላል። በዚህም ምክንያት የመጽሐፍ ዳሰሳ ባህል ማሳደግ ለአፍሪካ ልጆች ትልቅ የእድገት ዕድል ይፈጥራል።የማንበብ ባህል ያለው ህብረተሰብ የተሻለ የሥራ እድል ያገኛል፣ ጤናና ግብርና እውቀትን በመጠቀም ሕይወትን ያሻሽላል፣ ድህነትንም ይቀንሳል። በኮሪያና ሲንጋፖር ያሉ ሀገራት የእድገት ሚስጥር የማንበብ ባህል መሆኑ ይታወቃል። በአፍሪካም መጽሐፍትን በማሰራጨትና ቤተ መጻሕፍት በመገንባት የማንበብ ባህል ማሳደግ የሀገራቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያፋጥናል። ስለዚህ የሃገርኛ መጽሐፍት ዳሰሳ ለአፍሪካ የወደፊት ተስፋ መሠረት ነው። የመጽሐፍ ዳሰሳ ለኢትዮጵያ እድገት ትልቅ ጠቀሜታ አለው። በኢትዮጵያ የአዋቂዎች የማንበብና የመጻፍ ችሎታ በ2022 ወደ 60% ገደማ ደርሷል፣ ነገር ግን ብዙ ልጆች ያነበቡትን ለመረዳት ይቸገራሉ። የመጽሐፍ ዳሰሳ የማሰብ ችሎታን፣ ቋንቋ አጠቃቀምንና ችግር ፈቺ ችሎታን ያዳብራል። እንደ Ethiopia Readsና Read@Home ፕሮጀክቶች መጽሐፍትን በማሰራጨት የልጆችን የማንበብ ችሎታ በእጅጉ እያሻሻሉ ነው፣ ይህም የግለሰብ እውቀትን ለማሳደግ ይረዳል። የመጽሐፍ ዳሰሳ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት መሠረት ነው። የማንበብ ባህል ያለው ህብረተሰብ የተሻለ የሥራ፣ የጤናና ግብርና እውቀት ያገኛል፣ ድህነትንም ይቀንሳል።

## ምዕራፍ አንድ

# ግለ ታሪክ

*ርዕስ፡ የሚሳም ተራራ*
*ደራሲ: ፍቅረማርቆስ ደስታ*
*ዘውግ: ግለታሪክ*
*ገፅ: 224*

ጋሽ ማሞ ውድነህ "ማንም ሰው ቢሆን የተደበቀ ነውር አለው፤ ለማንም የማይናገረው። በዚህም ምክንያት ትክክለኛው ትምህርት ከሰዎች ወደ ሰዎች ሳይተላለፍ ይቀራል።" ይላል። "የሚሳም ተራራ" የተሰኘው የፍቅረማርቆስ ደስታ ግለ ሕይወት ታሪክ ወ ግለ ማስታወሻ መጽሐፍ፥ ሽቅብ ቁልቁል በተናጠው የሕይወት እንስራ "ለጥቂት-አፍታ" የተከፈተ ባለ-224 ገጽ ትፌ ነው። በትፌዋ ቀዳዳ አፎት ላይ የተንቸረፈፈው ወተት እንግልቷን ሲያሳብቅ፥ ፕስስስ ብላ የወጣችው ትንፋሽ ደግሞ ሰው ሰው ትሸታለች። የሚሳም ተራራ የግለ ሕይወት ታሪክ (autobiography) እና የግለ ማስታወሻ (memoir) ቅይጥ ነው።በመጽሐፉ ውስጥ የግለ ማስታወሻ ባሕርይ በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ይስተዋላል። አንደኛ፥ ዐብይ መንስዔው ከድርጊቱ ይልቅ ለድርጊቱ ያለው ምልከታ መሆኑን ያሳያል። ለአብነትም የወላጆቹን ታሪክ ከማተት ይልቅ በአስተሳሰባቸው ውስጥ ታሪካቸውን መግለጽ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ከአክስቱ የሻረግ ድርጊት ይበልጡኑ ፍካሬው ግዘፍ እንዲነሳ በብዕሩ ይተባል። ከ"ዳራ" እርቅ አውራጅነት ይልቅ፥ የማኅበረሰቡ የ"እንግዳ አይሳሳትም!" ብሂል ይልቃል። ሁለተኛ፥ ከሕይወት ሰፌድ ውስጥ ሊያስተምሩ የሚችሉትን የተረክ ሰበዞችን በአብዛኛው ይመዛል። ይህንንም በጋሽ መሐመድ ምክረ-ሐሳብ፥ በበርናርድ ሾው የመጨረሻ የጣር ወቅት ንግግር፥ በአባቱ በበርቲ "የጥቁርና የነጭ ተቃርኖ" ፍቺ፥ ከማያ አንጀሎ የፍርግርግ ውስጥ ወፏ ዝማሬ እንደዚሁም በሚጠቅሙ እንቅፋቶች ውስጥ እንመለከታለን። በተለይም የሀገራችንን ኹናቴ ከታላቁ ባለቅኔ ሆሜር ጽሑፍ ጋር በማሰናሰል፥ በሥነ-ጽሑፋዊ ንቡር ጠቃሽነት (literally allusion) ሥነ-ዘዴ በመጠቀም፥ ትምህርታዊ ሁዳድ በማበጀቱ፥ የግለ ማስታወሻዊነት ዘር ሲያጎነቅል ይታያል። በሦስተኝነት ደረጃ ደግሞ በከፊል የጊዜ ቅደም ተከተል ተፋልሶን እናስተውላለን። የመጽሐፉ መዳረሻ አከባቢ ላይ የጎልማሳነት ዘመኑን ተረክ ከሀዲዱ ፈቀቅ አድርጎት"ሰባተኛ ሲ" በተሰኘ

ንዑስ ርዕስ የልጅነት ዘመኑን የተረክ ፋርጎ እመሃል ውስጥ ይዶለዋል። "ሕለተወርቅ"ን ይተዝታል። "ምሳዬ ነው!" ባዩ የልጅ ተስፋሁን ታሪክም የጊዜ ቅደም ተከተሉን ነድሎ ይገባል። ከዚያም ያቆመውን የጎልማሳነት ዘመኑን ፋርጎ ይቀጥላል። በእነዚህ እና መሰል ኹናቴ ተረኮቹን ማቅረቡ መጽሐፉ በአንድ ወገን የግለ ማስታወሻነት (memoir) ምዳቤ ውስጥ እንዲፈረጅ አንደርድሮታል።

በሌላ ጎኑ ደግሞ "የለም ይሄ የግለ ሕይወት ታሪክ (autobiography) መጽሐፍ ነው" እንድንል የሚገፋፉን ነጥቦችም ይስተዋልበታል። አንደኛ፥ መጠነኛ ቅደም-ተከተል መኖሩ በጮርቃነቱ ከእምዬ እና ከአያይ ጋር በነበረው መስተጋብር አሃዱ ብሎ፣ የጉርምስና ወራቱን በተቀፀል አሳብሮ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኬሚስትሪ ክፍለተ ትምህርት የተማሪነት ሰርጥ አልፎ፣ "ጂንካ ገንዘቤን እንካ-እኔን አትንካ" በተባለለት ኩርባ ታጥፎ፣ የሐመርን እና የኦሞ ወንዝ ትሩፋታዊ ማኅበረሰብ ሕይወት ከደጅ እስከ ጓዳ-ጎድጓዳ አስሶ፣ ተምሞ፣ ከትቦ፣ የሀገረ አሜሪካ የወለፈንዴነት (absurdity) ሕይወት ወለል ድረስ የተሰናሰለ ቅደም-ተከተላዊ ድርዳሮሽ እናገኛለን። በዚህም የግለ ሕይወት ታሪክ (autobiography) ዘውድ ይደፋል።

ሁለተኛ፥ በዘመናት ውስጥ በደረሰበት የአስተሳሰብ በድራ ራሱን በራሱ መመዘኑ ተጠቃሽ ነው። በእንቦቀቅላነቱ "ባልና ሚስት ከአንድ ወንዝ ይቀዳሉ ማለት ምን ማለት ነው? ወንዝ ውስጥ ያለው ውኃ አይደል?። ይላታል እምዬን። በጉርምስናው ወራቱ ባሳለፈው የወኅኔ ቤት አበሳ ደግሞ "ሰው ደግ፣ ሰው ክፉም እንደሆነ ያን ቀን ገባኝ" ሲል እናገኘዋለን። በወጣትነቱ ደግሞ "የምፈልገውን ሳላውቅ በወላጆቼና በመምህራን መሪነት አሁን ያለሁበት ድረስ ደረስሁ። አሁን አውላላ ሜዳ ላይ ብቻዬን እንዳለሁ ነው የሚሰማኝ። ከተፈጥሮ ጋር መገናኘትና መግባባት እፈልጋለሁ" በማለት በደረሰበት የዘመን በደራ የራሱን መሐለቅ ያስቀምጣል። በዘመነ ጎልማሳነት ደግሞ "ነፍሴ ሌላ ጋ ናት፤ ሥጋዬ ግን ታክሲ ይነዳል፤ ..." በማለት ሕይወቱን ያኂሳል። በዚህም የመጽሐፉ ቅንብብ ውስጥ የግለ ሕይወት ታሪክ መንፈስ ያረብባል።

ሦስተኛ፥ በግለ-ፍተሻው ሥነ ልቡናዊ (psychological) እና ፍልስፍናዊ (Philosophical) ይዘት ያሳርፋል። ገና ብላቴና ሳለ "ፈጣሪ ሁላችንንም ከፈጠረ ለምን ክፉና ጥሩ ሆንን?" በማለት የግብረ-ገባዊ ፍልስፍና (moral philosophy) መጠይቅ ያነብራል። ለሽምግልና ለተላኩ ሰዎች የሚቀርብላቸውን ጥያቄ ሞግቶ፣ የቶልስቶይንና የጋሽ ሀዲስ ዓለማየሁን የትዳር ሕይወት ተቃርኖን አንጽሮ፥ የራሱን አስቸጋሪ የትዳር ቆይታውን ከአያቱ ምክር ጋር አሰባጥሮ ከትቧል። ለብዙ ሥነልቦናዊ እንድምታና ፍካሬ ተጋላጭ በሆነ መንገድ።በአራተኛነት የምናገኘው ደግሞ የጅማሮውም፣ የማጠንጠኛውም ሆነ የመዳረሻው ማዕከል ባለታሪኩ በመሆኑ "የለም ይሄ የግለ ሕይወት ታሪክ (autobiography) መጽሐፍ ነው" እንድንል ይገፋፋናል። ትልልቅ አበርክቶት ያስቀመጡ ጉምቱ ሰዎች የሕይወት ታሪካቸውን ባለመጻፋቸው ብዙ አጉድለውናል። ሥራዎቻቸው የሚጠናው አንድም ከራሳቸው ግለ ሕይወት ታሪክ በመነሳት በመሆኑ ሥራዎቻቸውን በሙላት ለመገንዘብና ለመፈከር ስንቸገር ዳክረናል።

አንዳንድ ታሪካቸውን የጻፉ ሆኑ ያጻፉ ሰዎችም ኩነኔ-አልቦነታቸውና የጽድቃቸው አያሌነት እጅጉን የትየለሌ ስለሆነ የደመና ጭብጦነት ይጠናወተዋል። ተደራሲውም እንዲህ መሰል የግለሰብ ታሪክ ሲያነብ፥ እነርሱ የደረሱበት ማማ ላይ የማይወጣ እንዲሁም የማይቀዳጁት ድል እየመሰለው ይብሱኑ በቀቢጸ ተስፋ እንዲናውዝ ያደርገዋል። ፍቅረማርቆስ በ"የሚሳም ተራራ" መጽሐፉ፥ ከሕይወቱ የፈሰሰውን ማር ብቻ ሳይሆን የሚደማውንም ቁስል ያስቃኘናል። ምንም እንኳ "ሾላ በድፍን" ቢሆንም የአባቱ የወላጆቹን አለማወቅ ጉዳይ እንደ አቡሰዲቅ ጊዜ እየጠበቀ የሚያገረሽ ቁስል አልነበረም ለማለት ይቸግራል። የእጦት አዘቅቱ ምን ያህል ናዲር እንደነበር የአክስቱ የሻረግ መቀነት ያወሳል። ባሕርዳር ወኅኒ ቤት ውስጥ አያሌ ጊዜ ሞት ማንቁርቱን ሊያፈርጥ በደጁ አድብቷል። መልከ ቀናውን ወዳጁን ከጓሮ እንደበቀለባቸው አትክልት ቀንጥሰውበታል። ነጻነትን ፍለጋ መጻተኝነትን አስመርጠውታል። ይሄ ሁሉ የሕይወት አቀበት ግን አልያዘውም፤ አልጠላውምም። እንደውም የሚሳም ነው ይላል።

የአረብኛ ሙዚቃ አንቆረቁራለሁ ብሎ መሳለቂያ መሆኑ ... በስንግ ውበት መሻት የተነሳ ጂንካ ላይ የገመጠው የፍቅር ቃሪያ ማቃጠሉ ... ውኃ ውኃ

ማሰኘቱ ... በሐመር ቀዬ ሳለ በእባብ መነደፉ ... በሞት እና በሱ መካከል አንድ ስንዝር መቅረቱ ... ከሐመር አከባቢ በነጮች ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ መባረሩ ... መጽሐፉን እንዲያሳትምለት የተማጸነው ሰው በንግግር ልምጭ መጋረፉ ... ማስለቀሱ ... በቀላሉ የማይወጡት ዳገት ነበር። ግን የሚጠላ አይደለም። የሚሳም አቀበት ነበር - ለፍቅረማርቆስ። የገዛ ፍቅረኛውን "የኔ ናት ወይስ አይደለችም?" በሚል ቁጤማዊ መፍገምገም ዳክሯል። ብርሃን ባለው ጨለማ ውስጥ። የአባቷን ቁጡነት ለማስከን በተደረገው የተጣደፈው የትዳር መንገድ፥ ማጎቶት አልባ ማንደጃ ላይ ተጥዷል። ወደ ሀገረ አሜሪካ ተሂዶ የተጀመረው አዲስ የሕይወት መንገድ ግን ከጉብታም፣ከኮረብታም ላቅ ያለ ተራራ ሆኗል።

በአሰቃቂው የክረምት ወቅት በአንድ የስልክ ጥሪ ቤት የለሽ መሆኑን አረዳችው። በርሃብ፣ በብርድ፣ በብቸኝነት ናወዘ። ሻንጣውን እየጎተተ ሲጓዝ የሚያዩት ሐበሾች ሰገራ እንደነካው እንጨት ተጸየፉት። ይሄ ትልቅ የሕይወት ተራራ ነው። የቁስለ-ጎመራ የፈጠረው ተራራ ነው። የቁስል ተራራ! እውን ግን ይሄ የሚሳም ተራራ ነውን? የፍቅረማርቆስ ደስታ መልስ "አዎ" የሚል በመሆኑ ነው መሰል ብዙዎች በብርድ፥ በርሃብ፥ በብቸኝነት እና በሱስ ከሞቱበት የቤት የለሽነት ሕይወት ተነስቶ መስተንግዶ ተምሮ፣ ሠርቶ፥ ወደ ታክሲ ሹፌርነት አድጎ፥ የሦስተኛ ድግሪውን ለማጠናቀቅ ጥቂት ምዕራፍ የቀረው እጩ ዶክተር ሆኗል። "ካልተናገርነው የተዳፈነ ሕመም በላይ የሚያም ሕመም የለም" በሚል መርህ ያገኛትን ዕድል ተጠቅሞ።

የሚሳም ተራራ ስሙር መጽሐፍ ነው ሲባል አንደኛ እጅግ ግላዊ የሚባሉ ሁነቶችን በማካተቱ ነው። ሄነሪ ኖዌን "እጅጉን ግላዊ ነገር እጅጉን ዓለም-አቀፋዊ ነው" ይላል። ለዚህም ነው አንዲት የአይሁድ ልጃገረድ የነበረችው አና ፍራንክ የጻፈችው የዕለተዕለት ማስታወሻ፥ አፍሪካ ውስጥ ያለ አንድ ወጣት ሲያነበው ስሜት የሚሰጠው። ለዚህም ነው የፍቅረማርቆ ደስታ እጅግ ግላዊ ነገሮቹን እያነበብን እንባችን የሚመጣው። ሁለተኛ ተገቢነቱ ያመጣው የመጽሐፉ አጓጊነት ነው። ፍቅረ ማርቆስ ደስታ አንጋፋ ከሚባሉ ደራስያን አንዱ መሆኑ እና በትልቅ የስኬት ደረጃ ላይ መድረሱ፥ የሕይወት መንገዱን መከተቡ የተገቢነት ጥያቄ መልስ ይሰጣል። ሮይ ፓስካል ግለ ሕይወት ታሪካቸውን መጻፍ ያለባቸው ሰዎች በሕይወታቸው ለትልቅ ስኬት የበቁ

ሰዎች መሆን አለባቸው” ይላል። ይሄ ሐሳብ ውሃ የሚያነሳው የሰው ልጅ ምስጢርን ለማወቅ ካለው ጉጉት ጋር እንደሚቆራኝ ስናውቅ ነው። የዚያኔ አጓጊነቱ ላቅ ይላል። ለዚህ ደግሞ ከባለታሪኩ ጋር ያለን ትስስር መሠረታዊ ጉዳይ ይሆናል። ከፍቅረማርቆስ ኢትኖግራፊክ ድርሰቶች ጋር የመንፈስ ትስስር በመኖሩ የመጽሐፉን አጓጊነት ከጅማሬው በይኖታል። ሦስተኛ ግለ ሕይወት ታሪክ የሌሎች ሰዎችንም ተረክ እንደ ገባር ስለሚጠቀም፥ ጸሐፊው ራሱን ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ መልክ የሚያቀርበው፥ ሌሎችንም ትናንሽ መጻሕፍት አቀናጅቶ ስለሆነ ሰዎችን የማወቅ እና የመረዳት አቅሙ የመጽሐፉን ክብደት ይወስነዋል። “እንዴት እንደሚነበብ ካወቅህ እያንዳንዱ ሰው መጽሐፍ ነው” ይባልም የለ። በዚህ ረገድ ፍቅረማርቆስ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ለቁጥር የሚያታክቱ ትናንሽ መጻሕፍትን ለግሶናል ማለት እንችላለን። የተረክ አመራረጡ፥ ወሽኔ የሚያሰኝ የስዕላዊ ገለጻው፥ ቃላትን የማዘዝ አቅሙ፥ ቃላትን ለአዲስ ፋይዳ የሚያውልበት መንገድ፥ ውስብስቡን ነገረ-ዓለም አፍታቶ ቀሊል በሆነ መንገድ ማንበር፥ ከቻርጌ ቃላትን አሮጌና ገጠሬ ቃላትን በሴማው በሴማው የሚያስገባበት መንገድ … አጃኢብ ስለሆነ የመጽሐፉን ስሙርነት አለመመስከር እብለት ነው። የሕትመት ጥራቱም ሳይዘነጋ። የሌላውን ተደራሲ ሐሳብ ባላውቅም በኔ ዕምነትና የንባብ ደረጃ መጽሐፉ ላይ ከፍተኛ ጥድፊያ አስተውያለሁ። በጥድፊያውም ለተደራሲው የተተወ የማሰቢያ አውድማ ተለቅቋል። ነጻ ቀጠና መኖሩ ቢያስመሰግንም ነገር ግን አንዳንድ መብራራት ያለባቸው ጉዳዮችም አብረው ተዘልለዋል።ይህም አላስፈላጊ እንደምታ ሊያመጣ ይችላል፤ ልቦለድ አይደለምና። ለአብነትም ያህል የእምዬ እና የአያይ ታሪክን ማንሳት እንችላለን።

**ዳሰሳ አቅራቢ: ቢኒያም አቡራ የመጀመሪያ ዲግሪ በጋዜጠኛነት እና ተግባቦት ያለው ሲሆን "የባለቅኔዋ ሶሪት" እና "ወደ ፍቅር ጉዞ" የተሰኙ መጻሕፍት ደራሲ ነው።**

*ርዕስ፡ "ሕይወቴ፥ ለሐገሬ ኢትዮጵያና ወገኖቼ ኢትዮጵያውያን ዕድገት የነበረኝ የሥራ ጥማት፥ ከ1917-1967 ዓ.ም"*
*ደራሲ፡ ደጃዝማች ወልደ ሰማዕት ገብረ ወልድ*
*የህትመት ዓመት፡ ጥር 2012 ዓ.ም)*
*ገጾች፡ xxvii + 636*

## ●● እንደ፡ መግቢያ፡ ቢያሻህ ●●

*ወገን ይህቺ የሳንባ ቆልፍ ነገሯን እንደምን ከርመሃል? እኔስ ያቺ የነገርኩህ የደዌዋ ክፉ ወቅት ደርሳ ነገሯ በልቤ ላይ እስክትኩረፈረፍ በደጃዝማች ወልደ ሰማዕት እምላለሁ መፅሐፍ ማንበቡን አልተውኩም። ዛሬ አስኪ በዚህ ወሳኝ የሕይወት ምዕራፍ ላይ ቆመን "ሕይወቴን" እንዳሰው። ይኸውም ደጃዝማች ወልደ ሰማዕት ገብረ ወልድ፤ "ሕይወቴ፥ ለሐገሬ ኢትዮጵያና ወገኖቼ ኢትዮጵያውያን ዕድገት የነበረኝ የሥራ ጥማት፥ ከ1917-1967 ዓ.ም" (አዲስ አበባ፤ መንኩሳ ማተሚያ ቤት፥ ጥር 2012 ዓ.ም)፥ ገጾች xxvii + 636፥ በ365 የኢትዮጵያ ብር፤ ለአንባቢ ያቀረቡት የግለ-ታሪክ ድርሳን ነው።*

*ደጃዝማች በ20ኛው መ.ክ.ዘ በኢትዮጵያ ከተነሱት እጅግ በቁ የሕዝብ አስተዳደር አገልግሎት መሪዎች ግንባር ቀደሙ ናቸው። እኚህ ሰው ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ተራ ሰራተኛነት (ከመስከረም 1951-የካቲት 1951)፣ የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት የፀጥታ ዳይሬክተርነት (ከየካቲት 1951-የካቲት 1951 ዓ.ም)፣ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር የአስተዳደር ዳይሬክተርነት (ከመጋቢት 1952-መስከረም 1955 ዓ.ም)፥ የወላይታ አውራጃ አገረ ገዢነት (ከመስከረም 1955-መጋቢት 1963 ዓ.ም)፥ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዘት መክትል ገዢነት (ከመጋቢት 1963-ሕዳር 1965 ዓ.ም) እና የወለጋ ጠቅላይ ግዛት ገዢነት (ከሕዳር 1965 ዓ.ም-1967 ዓ.ም) በችሎታቸው የበቁ ናቸው።*

*ደጃዝማች ከግል ጥቅም ይልቅ የኅበረተ-ሰቡን ጥቅም አስቀድመው የልውላኑና ልዕልታቱን የምልጃ ጣልቃ ገብነት እንኳ ሳይቀበሉ የበላይ አለቆቻቸውን ሳይቀር የሚዠልጡ ብቁና ቆምጫጫ አስተዳዳሪ ናቸው። ታዲያ እኚህ የደጃዝማች ወልደ ሰማዕት የቅጣት ብትር ያረፈባቸው ጠልፎ ጣይ ባለስልጣናት አይተኙላቸውምና በየደረሱበት የተዛባውን የአስተዳደር*

ስርዓት መስመር አስይዘው ኡፈይ ብለው ወደ ዋናው ሥራ ከመግባታቸው በሰውር እጆቻቸው እያሽቀነጠሩ ከሐገር ሐገር በእንክርት ነገር ግን በየደረሱበት ደግሞ የርትዕ ፍትህን ሲያሰፍኑ የኖሩ ... የፉካሬ እየሱሱ ቴዎድሮስ አይነት ሰው ናቸው። መቼም የዳኛች ወልደ ሰማዕት መንፈስ የማትሞት ነች ... መልሳ አፈር ልሳ ትነሳለች። ይህነ ግለ-ታሪክ ሥታነብ ይብላኝ ለኢትዮጵያ ሰው ሳይማር ለሚሰለጥንበት የቢሮ ተንኮልና ክፋት ማለትህ አይቀርም። ... ይኸውም የኢትዮጵያ ቢሮክራትና ሹም ከግል ጥቅሙ ውጪ ሐገራዊ ተልዕኮ የሌለው ጉፋያ ነው። የኢትዮጵያን የአስተዳደር ሥርዓት ታሪክ በአግባቡ አጥንቶ ለማዘመን የሚፈልግ መንግስት በኢትዮጵያ ተነስቶ ቢሆን ኖሮ ለእኒህ ሰው ሐውልት ይተክልላቸው፥ አደባባይ ይሰይምላቸው ነበር። የእኔ ግን ዋና ዓላማ ሰውዬው የተነፈጋቸውን ማኅበረሰባዊ እውቅናና ዋጋ ለማስመለስ ዘመቻ መክፈት አይደለም። የኢትዮጵያ ሰው እኒህን ሰው ጠንቅቆ ያውቃል። እውቅና ቢነፈጋቸው ሰውዬው ለግዜው አጨብጫቢ ቲፎዞ ባይኖራቸው፥ የኢትዮጵያን የአስተዳደር ታሪክም መርምሮ ለማጎልበት የተነሳ ትውልድ ባለመገኘቱ ነው። ወደ ፊት ግን ልግመኛ ያልሆነና የአስተዳደር ታሪኩን ፈትሾ ለማወቅና ለማሻሻል የሚሻ ትውልድ ሲነሳ የእኒህን ሰው አስተዳደራዊ አበርክቶ ተገቢውን እውቅና ይሰጠዋል። ይልቁንም ይህ የእኔ ዳሰሳ በይበልጥ የሚያተኩረው በዚህ ግል-ታሪክ ውስጥ የተመለከቱና ለ20ኛው መ.ክ.ዘ የኢትዮጵያ ታሪክ አጠናን አዲስ መረጃን ሊፈነጠቁ የሚችል ደራሲው በግለ-ታሪካቸው ያካተቷቸውን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የልምድ ማስረጃዎች በታሪክ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ለተሰማሩ/ለሚሰማሩ ምሁራን አፅዕኖት ማመላከት ነው። ይህንንም ድርሳን “አቃቂር” ያላወጣሁለት ደራሲው ያዩትንና የሰሙትን የአስተውሶ መረጃ ተጠቅመው ያዘጋጁት ግለ-ታሪክ እንጂ እንደ የታሪክ ድርሳን ተውስታቸውን በሌሎች የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች መዝነው ያቀረቡት ባለመሆኑ ነው።

ስለሆነም አሁን ስለ ግለ-ታሪኩ አወቃቀር ልመልስህና አንዳድ ነጥቦችን ለመላክትህ። በአጠቃላይ ይህ የደኟች ወልደ ሰማዕት በቅፅ አንድ (ነት) ያሳተሙት ግለ-ታሪክ በ17 ምዕራፎች፣ 200 በሚሆኑ ዓብይትና ንዑሳን ርዕስት፣ በመፅሐፍ የፊት አካላት (ምስጋና፥ መቅድምና መግቢያ) እና

በመፅሐፍ የጀርባ አካላት (የተቀፅላ አባሪዎች፥ የዋቢ መፅሐፍት ዝርዝርና የመጠቁም ማውጫ) ተዋቅሮ የቀረበ ከመሆኑም በላይ 135 በሚሆኑ ፎቶግራፎች፥ የአከባቢ ማመላከቻ ካርታዎችና የምስክር ወረቀቶች በማበልጸጊያ አባሪነት የቀረቡበት ነው። በተለይ የዚህ ግለ-ታሪክ ድርሳን ከ135 በላይ አባሪ ምስልች የበልፀጉ ነገር ደጃዝማች ከመለስተኛ ሁለተኛ ተማሪነት ግዜያቸው ጀምሮ በፎቶ ማንሳትና አጥቁሮ ማጠብ ብልሃቶች የተካኑ ሰው በመሆናቸው ምክንያት ነበር። በተለይ ፎቶን አጥቁሮ የማጠቡን ብልሃት የተማሩት ደግሞ ከታዋቂው ጋዜጠኛ ዳሪዮስ አባት አቶ ሞዲ ነበር። አቶ ሞዲ በአጼ ምንልክ፥ በልጅ እያሱ፥ በንግስተ-ነገስታት ዘውዲቱና አልጋ ወራሽ ተፈሪ ዘመነ መንግስታት የታወቁ የቤተ መንግስት ፎቶ አንሺ የነበሩና በ1910/11 ዓ.ም የሕዳር በሽታ መቅሰፍት ግዜ ለሕይወታቸው ሳይራሩ አዲስ አበባ በየቤቱ እየዞሩ ሟቹን በመቅበር፥ ታማሚውን ውሃና ምግብ እያቀረቡ በማስታመማቸው የህዝብ ባለውለታነት ኢትዮጵያዊ አድርጎ ያስቀራቸው የሕንድ (ደጃዝማች የፐርሽያ ይላሉ) ተወላጅ ሰው ናቸው። ዛሬ በዚህ የሳንባ ቆልፍ (ኮቪድ-19) መቅሰፍት ዋዜማ ላይ ሆነን የእኒህን ሰው የሕዳር በሽታ መቅሰፍት መልካም ስራ እናስባለን/እንዘክራለን።

## ●● የግለ-ታሪኩ አፅመ ታሪክ ●●

ይህ ግለ-ታሪክ የወልደ ሠማዕት ገብረ ወልድ ዋልተንጉስና የቤተ-ሰቦቻቸው ነው። ወልደ ሠማዕት የተወለዱት በቀድሞው የሐረረጌ ጠቅላይ ግዛት ሐምሌ 19፣ 1917 ዓ.ም ነው። ይኸውም ግለ-ታሪክ የ20ኛውን መ.ክ.ዘ የኢትዮጵያንን ምሁር ወገን እና ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት ታሪክ በከፊል የሚወክል ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያን የ20ኛው መ.ክ.ዘ የአስተዳደር፥ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ተቋሚዊ ሥርዓት ታሪክ የሚያጠኑ የታሪክ ምሁራን ይህን ግለ-ታሪክ በማገናዘቢያነት እንዲያመሳክሩ በአንክሮ እመክራለሁ።

የዳጃች ወልደ ሠማዕት ግለ-ታሪክ እንደ ምን የ20ኛው መ.ክ.ዘ ኢትዮጵያን ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት እና ማህበራዊ ታሪክ የከፊል ወካይ ሊሆን እንደሚችል እንደ ሚከተለው አመላክታለሁ። የደጃች ወልደ ሰማዕት አባት (ግራዝማች ገብረ ወልድ ዋልተንጉስ) ለፍትህ ግንባራቸውን የማይመልሱ ቆፍጣና ዳኛ እና አስተዳዳሪ ናቸው። የወልደ ሰማዕት ሴት ዓያት

(ወ/ሮ ፃድቄ ወልደ ሚካኤል) የስመ ጥሩ ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል የአባት ወገን እህት ናቸው። ራስ መኮንን ደግሞ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት በ19ኛው መ.ክ.ዘ ማገባደጃ ሲጀመር ከተነሱ ብቁ አስተዳዳሪዎች ዋንኛው ናቸው። በ20ኛው መ.ክ.ዘ የተነሱ የበቁ አስተዳዳሪዎችና ምሁራን (እነ አለቃ አጥሜ ጊዮርጊስ ገብረ መሲህ፣ ደጃች ተሰማ እሸቴ፣ ዶ/ር መላኩ በያን፣ አቶ ባሻወረድ ሐብተ ወልድ፣ ፊታውራሪ ተክለ ኃዋሪያት ተ/ማርያም፣ … ወዘተ) የዕውቀትና የአስተዳደር ብልሃት አደላዳይም ናቸው። ደጃች ወልደ ሰማዕት የዚህ የራስ መኮንን የአዋቂነትንና የአስተዳደር ብልሃት ባህል የመጨረሻው ወራሽ ነበሩ ለማለት ይቻላል። ታህሳስ 1967 ዓ.ም የደጃዝማችነት ማዕረግህን ጣል አልጥልም የማይረባ ንትርክ ከስራቸው በጡረታ ሲሰናበቱ ይህ በዘመናዊ የኢትዮጵያ የአስተዳደር ታሪክ ውስጥ በክፋትና ሴረኝነት ተተብትቦ መልካምነቱ ተውር ትውር ይል የነበረ የርዕትና ፍትህ አገልግሎት ታሪክ እስከ ወዲያኛው ተዳፍኖ ያለ ወራሽ የቀረበት አሳዛኝ ታሪክ በዚህ የወልደ ሰማዕት ግለ-ታሪክ ተወክሏል። ዛሬ የኢትዮጵያ የአስተዳደር ስርዓት የአገልግሎት የስራ ሥፍራ መሆኑ ቀርቶ የጉቦኞች፣ የጠልፎ ጣይ ሴረኞች እና ነገር ቆርጠው መወሰን የማይችሉ privileged bureaucrats እጅ ላይ ሙሉ ለሙሉ የወደቀበትን ሁኔታ ልብ ያለ የዚህን ግለ-ታሪክ ውክልና መረዳት አያዳግተውም።

የዚህም ግለ-ታሪክ የ20ኛው መ.ክ.ዘ የኢትዮጵያ ማህበራዊ ታሪክ ውክልናውም ይህ ነው። ደጃች ወልደ ሠማዕት በድኅረ ጣልያን ወረራ መልሶ የቆመውን የኢትዮጵያን ንጉሰ ነገስት መንግስት የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግስት እንደ ነበር ያለ ቅንጣት ጥርጠር የተቀበሉ ሰው ናቸው። ከዚህም የተነሳ በፍፁም ሀቀኝነትና ታማኝነት መሀል አገር ከዳር ሳይሉ አስተዳደራዊ አገልግሎት ሲሰጡ ኖረዋል። ሥለግትር ሐቀኝነታቸውም አለቆቻቸውን ሳይቀር በኃላፊነት (የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ተጠባባቂ ሚንስትሩን፥ የአልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ወገንተኛ፥ የበላይ አለቃ የሚሆኗቸውን አቶ እሸቴ መኮንን የአንድ ወር ደሞዝ እንደ ቀጡና ሚንስትሩም በዚሁ ሰበብ ስራ እንደለቀቁ ለምሳሌ ከገፅ 154-160 ተመልከት) ተጠያቂ እያደረጉ ቅጣት እስከ ማከናነብ ደርሰዋል። በዚያም ባላጋራን እያበቀሉ ባልተገባ ተጠልፈው ሲወድቁና ሲነሱ በሚጠሏቸው ሰዎች መንጋጋ ሲላመጡ ኖረዋል። ስለሕዝባዊ አገልግሎታቸው

ቀን ከሌት በስራ ከመጠመድም ልጆቻቸው እንኳ ተወልደው ሲያድጉ በቅርበት ለመከታተል እድል አልነበራቸውም። በስራቸው ብቃት ከተራ የአገር ግዛት ሚንስቴር ሰራተኝነት ተነስተው የአገር ገዥነት የስልጣን ዕርካብን የተጎናጠፉት እኒህ ሰው፤ የ66ቱን የአባዮች የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ በጡረታ ሲገለሉ ግን፣ በ20 ዓመት የጉብዝና የስራ አገልግሎታቸው ዘመን በጉቦና ንቅዘት ያላዳበሩት ኑሮ እየተገዳደራቸው የተሸለሟቸውን ሜዳዮች እና የእጅ ሰዓቶችን ጨምሮ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች እየሸጡ ኑሮን ሊገፉት ሲውተረተሩ በግለ-ታሪካቸው ይነበባል። ከድጡ ወደ ማጡ ይሆንናም የ1983 ዓ.ም የኢህአዴግ የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎም በዲቪ ሎተሪ ሐገር ጥለው ስደትን ሲሹ ከመታየትም፤ በ1980ዎቹና 1990ዎቹ ልጆቻቸውና በቁርባን ያገቧቸው ባለቤታቸው ፈተዋቸው በአሜሪካንንና በእንግሊዝ የስደት ኑሮ ሲያያዙት፤ አገራቸውን በፅናትና በሐቀኝነት ያገለገሉት ደጃች ወልደ ሰማዕት መልሰው በስተ እርጅና የላጤነት ሕይወት አንድ ብለው ሲጀምሩት በዚህ ድርሳን ቀርቧል። ይኸውም በ20ኛው መ.ክ.ዘ ያሉ አንኳር አንኳር የኢትዮጵያውያን ማህበራዊ ታሪክ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም የተቋማትና ተቋማዊ ስራዓት ግንባታና ልግመኛ የለውጥ ሂደት፣ በየተቋማቱ የተሰገሰገው የቢሮክራት (የኢትዮጵያ የልሂቅ ወገን) ተፈጥሮና ተቋማዊ ጠባይ፣ የዘመናዊ ትምህርት ይዘትና እድገት፣ የጋብቻ፥ የቤ-ተሰብ፥ የሞትና የሐዘን ሁኔታዎች፣ ሰደትና የቤተሰብ መበትን ... ወዘተ ርዕሰ ጉዳዮች ከሞላ ጎደል በዚህ ግለ-ታሪክ የተካተቱበት ነውና በተለይ ይህ ድርሳን ለማህበራዊ ታሪክ ተመራማሪዎች ጠቃሚነቱ የጎላ ነው ማለቴ ስለዚያ ነው። ... የደጃች ወልደ ሰማዕት ግለ-ታሪክ በይበልጥ ለኢትዮጵያ ማኅበራዊ ታሪክ ምርምር የጎላ ጠቀሜታ ይኑረው እንጂ ፖለቲካን ጨምሮ ለሌሎችም የታረክ ዘርፎች ታሪካዊ ጥናት አስፈላጊና አዲስ የሆኑ መረጃዎች የተካተቱበት ነው። ከዚህ ቀጥዬ በዳጃች ወልደ ሰማዕት ግለ-ታሪክ ውስጥ የተመለከቱ በማኅበራዊም ሆነ የስርዓተ መንግስት ታሪክ ተመራማሪዎች እስከ ዛሬ በተጠኑትም ሆኑ ወደፊት በሚጠኑት ጥናቶች ውስጥ አፅዕኖት ሊሰጣቸው የሚገቡ እንግዳ ጉዳዮችን እጠቁማለሁ።

## ●● የታሕሳስ፡ 1953 ዓ.ም፡ የመንግስት፡ ግልበጣ፡ ከግርግር፡ ወደ፡ ድንግር ●●

እስከ ዛሬ ስናውቅ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ቀናኢነት ያላቸው ፀሐፍት የታሕሳስ 1953ቱን የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ዋጋ ሲያሳጡት "ግርግር" ብለው ሲጠሩት፤ የ1950ዎቹና 60ዎቹ አባይ ማርክሲስት ትውልድ ደግሞ ይህን ሙከራ ከምንም በላይ አልቆ የተራማጁ ዓይን ገላጭ ክስተት ተደርጎ ሲቀርብ ነው። ለቀ.ኃ.ሥ መንግስት እጅግ ቀናኢ አመለካከት ያላቸው ደጃዝማች ወልደ ሰማዕት ደግሞ ለ"ግርግርነትም" የማይበቃ፣ በይበልጥ የምዕራባውያን ስውር ሴራ የተከፈነ፣ የራቱዎች "የድንግር"ድርጊት አርገው ያቀርቡታል። ከዚህም የተነሳ ደጃዝማች ወልደ ሠማዕት ይህ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራና በሙከራው የተሳተፉ ሰዎች ታሪክ በታሪክ ፀሐፍት ተዛብቶ ቀርቧል፣ ይህንንም ግድፈት መጪው ትውልድ አፅዕኖት ሰጥቶ፣ መረጃዎችን በበቂና በአግባቡ መርምሮ ተስተካክሎ መቅርብ እንዳለበት ደጋግመው ይመክራሉ።

እንደ ደጃች ወልደ ሰማዕት ይህ "የታሕሳስ ድንግር" ከጥንስሱ እስከ ድፍርሱ ታርሞ ሲቀርብ እንደ ሚከተለው ነው። የመፈንቅለ መንግስቱ ዋንኛ አቀናባሪዎች ምዕራባውያን ናቸው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የኢትዮጵያ አስከፊ የጭሰኝነት ሥርዓት ይተች ስለነበር፤ ከ1940ዎቹ አጋማሽ አንስቶ ንጉሰ ነገስቱ ይህ የጭሰኝነት ስርዓት እንዲወገድ አጥብቀው ያስቡበት ነበር። ነገር ግን ለባለ መሬቶች የሚከፈል የብድር ብር ከምዕራባውያን መንግስታት ለምነው ማግኘት አልተቻላቸውም። በጨረሻም ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የተፈለገው ብር (400 ሚሊዮን ሩብሊስ) በግዜው ሶቭዬት ሕብረት ተብሎ ይጠራ ከነበረው የዛሬው ሩስያ መንግስት በ1951 ዓ.ም በብድር ተገኘ (ገፅ 142 ተመልከት)። ይሄ ከሶቭይት ሕብረት የተገኘ ብድር ግን የምዕራባውያን ሀገሮችን ለክፉ ሥጋት ዳረገ። ለዚህ ደግሞ ዋንኛው ምክንያት ኢትዮጵያ በዚህ ብድር ሰበብ ወደ ኮሚኒስቱ ወገን ልትቀላቀል ትችላለች የሚል ነው። እንግዲህ የዚህ ስጋት ዕጢ ለሁለት ዓመታት ሲጎለብት ይቆይና ነው በስተመጨረሻ የታሕሳስ 1953ቱን መፈንቅለ መንግስት በተለይ በእንግሊዝና በአሜሪካን ኢምባሲዎች ከጀርባ ሆኖ ገፋፊነት ወለደ።

እንደ ደጃች ወልደ ሰማዕት ከኢትዮጵያ በኩል በዚህ መፈንቅለ መንግስት የተሳታፉት ሰዎች አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት ምንም የረዥም ግዜ ኅብረተሰባዊም ሆነ አገራዊ ዓላማ የሌላቸው የዋሆች ወይ ስሜት-ነድ ጅብደኛ የምዕራባውያን ተላላኪዎች ናቸው። ይኸውም አምብሮ ከመንግስቱና ግርማሜ ንዋይ የግል ስብዕና አቀራረብ የሚታይ ነው። መንግስቱ የወር ደሞዙን ሳይቀር ለተቸገሩ ሰዎች እርዳታ፣ የቀረውን ደግሞ በቻቻ ዳንስ ፣ ከልዕልት እስከ ተራዎቹ ወይዛዝርት ሴት አውልነት … ወዘተ ሲዘራ ሚውልና ደሞዝ ሲመጣ በብድ ተመላሽነት ከመቶ ብር ባላይ መቀበል የማይችል ብኩን፥ በሥራውም ዝርክርክ ሰው ነው (ለዓብነት ገፅ 179፣ 200-201 ተመልከት)። ግርማሜም እንዲሁ ምንም እንኳ በስራው ብቁ ቢሆንም ከመጀመሪያው አእምሮውን በኮሚኒስት አብዮት በክሎ “እነኝህን የፊውዳል ቆሻሶች ማስወገድ” በሚል ፈሊጥ ደም እንደ ሸተተው ጅብ አቅሉን ስቶ አጋጣሚ ሲጠብቅ ኖሮ ድንግት አጋጣሚውን ሲያገኝ በመፈንቅለ መንግስቱ ዘው ያለ ነብራራ ነው። በግዜው ለሚያስተዳድረው የጅጅጋ አውራጃ 300.000 ሺህ ብር ጠይቆ ተፈቅዶለት ነገር ግን ገንዘቡን በማግኘት ሂደት ስለተጉላላ በዚያ ምሬት ነው ንጉሰ ነገስቱ ወደ ብራዚል የሄዱበትን አጋጣሚ ተጠቅሞ ወንድሙን ከምዕራባውያኑ ጋር በመሆን አሳምኖ ያለ ረዥም ግዜ ዕቅድ መፈንቅለ መንግስቱን ጠንስሶ እንዲተገበር ያደረገው። ይሄ ብቻ አይደለም። በመፈንቅለ መንግስቱ የተሳተፉት እነ ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ፣ ጀነራል ፅጌ ዲቡ … ወዘተ በጀነራል መንግስቱ ነዋይ እጅ ሕይወታቸው ተይዞ ተገደው እንጂ ፈቅደውና ወደው አይደለም። ሴራውም አይሆኑ ሆኖ በሶስት ቀናት ውስጥ ሲከሽፍ ጢሰኝነትን እንዲያጠፉ ከሁሉ ባላይ ኃላፊነት የተሰጠው የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ሚኒስትር ጀነራል ሙሉጌታ ቡሊ የተገደሉት በምዕራባውያኑ ሴራ፤ 20 የሚጠጉት የኢትዮጵያ ትልልቅ የአገር ባለውለታ ባለስልጣናት የተረሸኑት በአቅለ ቢሱ ግርማሜ ነው (በአጠቃላይ ስለ ታሕሳስ 1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ከገፅ 166-204 ተመልከት)።

… እውነቱ ደጃዝማች ወልደ ሰማዕት እዳቀረቡት ሆኖ ኋላ የተነሳው ማርክሲስት ዓባይ ትውልድ አውቆ ለፖለቲካ ርዕዮቱ የኃልዮት መሰረት ይሆነኛል ብሎ በቅጥፈት፣ ሳያውቅ በመናጆ ዳተኝነት የዚህን መፈንቅለ መንግስትና በእርሱም የተሳተፉ ገለሰቦችን ዛሬ በታሪክ በምናወቃቸው የለውጥ

ፋና ወጊነት "አደናግሮ" አቅርቦት ከሆነ ይህ ድርጊት የክፍለ ዘመኑ ታላቅ ሴራ ተደረጎ መቅረብ የሚችል ነው። ... የኢትዮጵያን ዘመናዊ የፖለቲካ ታሪክ ያጠኑ ወይ የሚያጠኑ ምሁራን ይህንን የዳጃች ወልደ ሰማዕትን የግለ-ታሪክ መስራጃ በጥንቃቄ መርምረው እና የመረጃው ዋጋ መዝነው አጥርተው እንዲያቀርቡ አበክሬ እጠይቃለሁ። ነግር ግን ይህ መፅሐፍም በኦፌሴል በሚመረቅበት መድረክ ደጃዝማች በዚህ ጥያቄ መፈተን ይኖረባቸዋል የሚል አስተያየት አለኝ። በዚህም ብቻ አይደለም ደጃች ወልደ ሰማዕት መጠየቅ የሚኖርባቸው። በዚህ መፈንቅለ መንግስትና በአጠቃላይ የንጉሰ ነገስቱን መንግስት ከውስጥ ገዝግዘው በመጣል ልዑል ዕምሩ ኃይለ ሥላሴ የነበራቸውን ጉልህ ሚና መረጃዎች በግልጥ ቢያመላክቱም ሸፋፍነው አልፈዋልና መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ይኸውም ነገር እንዲህ ነው ...!!

## ●● ነገረ፡ ዕምሩ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ ●●

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ልዑል ዕምሩ ኃይለ ሥላሴ የቅርብ ዘመዳሞች ከመሆናቸውም ጭቃ-ቦክ አብሮ አደጎች ናቸው። በቀ.ኃ.ሥ የአላጋ ወራሽነት ዘመን ርስተ-ጉልትነቱ ከራስ መኮንን ቤተሰብ በሆነው የሐረርጌን ጠቅላይ ግዛት ገዢነተን ከመሾምም፤ የአልጋ ወራሹ ሥልጣን በወሎ፣ በትግራይና በጎጃም በየተራ ቅንቅን ገጥሞት መረጋጋት ባጣ ቁጥር፤ በእነኚህ ስፍራዎች ሁሉ በገዢነት እየተሾሙ ስልጣናቸውን ያረጋጉላቸው ልዑል ዕምሩ ናቸው። ልጅ እያሱን ከስልጣን አውርዶ ራስ ተፈሪን አላጋ ወራሽና ባለ ሙሉ የመንግስት እንደራሴ በማድረጉ ንቅናቄ ዕምሩ ዋንኛ ሚና ተጫውተዋል። ቀ.ኃ.ሥ እቴጌ መነንን በልጅ እያሱ አቅራቢነት በህይወት ከነበሩት ባላቸው ከራስ ልዑል ሰገድ መንትፈው እንዲያገቡ ሲደረግም ልዕል ዕምሩ የጠላፊ ግብረ ኃይሉ መሪ ነበሩ። ለዚህም ነበር ከጣልያን ወረራ በፊት በአገሪቱ ከነበሩት 6 ብቻ ልዑላን አንዱ ሆነው መስፍንነትን የተጎናጠፉት። የጣልያን ወረራ ተከስቶ ንጉሰ ነገስቱ በስደት ሐገር ጥለው ሲሄዱም ልዑል ዕምሩ የመንግስቱን ዙፋን ወደ ጎሬ አዙረው ጦሩን አስተባብረው እንዲመሩ ታምነው የእንደራሴነት ውክልናው የተሰጣቸው ሰው ነበሩ። ነገር ግን ከጣልያን ወረራ በኋላ በቆመው የቀ.ኃ.ሥ መንግስት ውስጥ፣ ለአጭር ግዜ የጎንደር ገዥ ከመሆናቸው በስተቀር፣ ቀ.ኃ.ሥ ዕምሩን ለረባ ስልጣን ሲያበቋቸው አይታይም። ይልቁንም ከ1938 ዓ.ም ጀምሮ መጀመሪያ በአሜሪካን፣

ቀጥሎም በሕንድ አምባሳደርነት ከአገር ከማራቅም፣ ከታሕሳስ 1953 ዓ.ም መፈንቅለ መንግስት ... በኋላ ደግሞ ጭራሹኑ ከመንግስቱ ስራ በጡረታ አሰናብተው ቤት ሲያስቀምጧቸው እናውቃለን። እኔም ከቶ እነኝኝ ሰዎች የተቃቃሩት በምን ይሆን በማለት ሆዬን ሲበላኝ ኖሯል። በተለይ ደግሞ ገና የአሜሪካን አምባሳደር ሳሉ በአልጋ ወራሹ አስፋ ወሰን ወጪ ግርማሜ ንዋይን መልምለው አሜሪካ እንዲማር ያደረጉበት ሁኔታ፣ በኋላም የሕንድ አምባሳደር ሳሉ ይህንኑ ግርማሜ ቀጨኔ የሚገኘውን ቤታቸውን ከውስኪና ከሴቶች ጋር አደላድለው በመስጠት “የቀጨኔ ክለብ” የሚባለውን ኮሚኒስት የመንግስት ተቃዋሚ ግብረ ኃይል አቋቁሞ እንዲዶልት ያደረጉበትን ሁኔታ፤ ግርማሜ ንዋይ የጎላ ሚና በነበረው በታሕሳስ 1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ደግሞ እርሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትር፥ አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ደግሞ ሕገ መንግስታዊ ንጉሰ ነገስት ተደርገው የቀረቡበትን አኳኋን ሳይ፤ በኋላም ደርጉ መጥቶ ንጉሰ ነገስቱን ከስልጣን ሲያወርድ “ብር አውሮጳ ባንክ ለክፉ ግዜ ይሆናል በሚል ያስቀምጡ ነበር” በሚል ለደርጉ ጥቆማ አድርገው ከመስበላትም፥ ንጉሰ ነገስቱ ከሥልጣን እንዲወርዱ እነ ደበላ ዲንሳ ሲጠይቁና ንጉሰ ነገስቱ ሲያንገራግሩ “ጃኖሆይ አሁን ሁሉም ነገር አብቅቶለታል” ብለው የመጎተት ያህል አግባብተው ከዙፋኑ ሲያወረዷቸው .... ወዘተ ሳይ የእነኝህ ሰዎች ቅንቅን ሥሩ ጥልቅ ሊሆን እንደሚችል እጠረጥር ነበር።

አንባቢ ሆይ ... ይህ የደጃዝማች ግለ-ታሪክ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዚህ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ለዘለቀ የንጉሰ ነገስቱና የልዑል ዕምሩ ስውር የሥልጣን ቅንቅን ምስጥር በስተመጨረሻ መልስ የሰጠ ነው። የዚህም ሚስጥር አቀራረብ እንዲህ ነው። በ1929 ዓ.ም ልዑል ዕምሩ በጣልያን ተማርከው አንድ የጣልያን ደሴት ላይ በእስር እንዲቆዩ ይደረጋል። በዚያም በእስር ላይ እንዳሉ አንዲት በፈረንሳኛ የተፃፈች የማርክሲስት ከሚኒስት መፅሐፍ ያነቡና በኮሚኒዝም ሥርዓት ፍቅር ይያዛሉ። ይኸውም ትኩስ ፍቅር ያመናቅር ይሆንባቸውና መለስተኛ መፅሐፍ እስከ መፃፍ ያደርሳቸዋል። ከዕስር ተፈተው ኢትዮጵያ እንደ ተመለሱም በግስጋሴ ቤተመንግስት ሄደው ለንጉሰ ነገስቱ መፅሐፏን እንዲያነቡላቸው ይሰጧቸዋል። ንጉሰ ነገስቱም አንብበውም “በትፈልግ እራስህ አሳትመው” ብለው ገሸሽ ያደርጓቸዋል። ከዚያ ግዜ ጀምሮ ልዑል ዕምሩ ዕንቅልፍ አጥተው ከወታደር እስከ ተማሪ ተራማጅ

ማርክሲስት የመሰላቸውን (ደጃች ወልደ ሰማዕት ሳይቀር ካኪ ስለሚለብስ ኮሚኒስት መስሏቸው) በስውር አደራጅተው የቀ.ኃ.ሥን መንግስት ገዝግዘው ይንዱታል (ሥለ ዕምሩ ይህ ታሪክ ገፅ 172-177፣ 524-551 ተመልከት)።

ይህንን ግልጥ ማስረጃ እያዩ ደጃዝማች የልዑል ዕምሩን ሚና ባይገልጡት .... እኔ አግዛቸዋለሁ። አንባቢ ሆይ ታህሳስ 1953 ዓ.ም መንግስቱና ግርማሜ ሞክረው ካላሳኩት እስከ መስከረም 2፣ 1967 ዓ.ም መንግስቱና አጥናፉ መርተው እስካሳኩት የወታደሩ መፈንቅለ መንግስት፤ በ1950ዎቹ ተወልዶ 1960ዎቹ ፍሬ ስላፈራው የማርክሲስት ሌኒኒሰት ... ግራ ዘመም የኢትዮጵያ ፖለቲካ .... አባቱ አንድ እርሳቸው ልዑል ዕምሩ የመሆናቸውን ነገር ዕመን እንጂ አትጠራጠር። ሰኔ 21፣ 1966 ዓ.ም ደርጉ ተመስርቶ በቀጣይ አምስት ዓመታት ውስጥ እጅግ በሰከነ ብልሃት ጓድ መንግስቱ ኃ/ማርያም የንጉሰ ነገስቱን መንግስት እና በራሱ በደረጉ ውስጥ የነበሩ የበላይ አመራሮችን ደረጃ በደረጃ አስወግዶው ሙሉ የሥልጣን ዕረካቡ ላይ በብቸኛ አሸናፊነት የወጡበትን ... ብዙ የግዜው ሰዎች ግለ-ታሪካቸውን ፅፈው መላምት ሰጥተዋል። አንድ በብዙዎች ተደጋግሞ የሚጠቀሰው መላምት ጓድ መንግስቱ የግቢ ምንስትር የነበሩት የደጃች ከበደን ተሰማን ምክር አግኝተው ነው ከማለትም እንደውም ከነ አንካቴው መንግስቱ የከበደ ተሰማ ልጅ ናቸው እስከ ማለት የደረሱ ነበሩ። አሁን ልዕል ዕምሩ ተገቢው የታሪክ ስፍራቸውን እየያዙ በመምጣታቸው ይህ መላምት ያበቃለት ይመስላል። ይልቅስ ምቾት የሚነሳው በታህሳስ 1953 እና መስከረም 1967 ለውጦች ልዑሉ ሲያወቁ ለውጡ የበላቸው ጓዶቻቸው ነገር ነው። ያም ቢሆን ለመረዳት አዳጋች አይደለም። አብዮተኛ ስትሆን በተለይ ደግሞ የማርክሲስት ሌኒኒስት ከቆምክለት ዓለማና አብሮህ ከሚቆም ጓድ ውጪ ወደጅ ዘመድ፥ ይልኙታ፣ ውለታ ... አይኖርህም። ይህ ደግሞ በዓለም አብዮተኞች መንደር ሁሉ የታየ ነው።

## ●● ነገረ፡ ፕሮፌሰር፡ መስፍን፡ ወ/ማርያም ●●

ፕሮፌሰር መስፍን የአገር አድባር ናቸው። ነገር ሁሉ ከፍቶ በዘመነ ኢህአዴግ ደጃች ወልደ ሰማዕት እንኳን በዲቪ ሎተሪ የአሜሪካን የስደት ኑሮ ሲሹ (የቁርባን ባለቤታቸው ወግድ ወዲያ ከዚህስ አገር ኑሮ ስደት የሻላል ብለው

በስተ እርጅና ኑሮአቸውን በአሜሪካ ሲደርጉ) ... ፕሮፍ መስፍን ወይ ፍንክች ከኢትዮጵያ ውልፍት አላሉም። በዚህም አገር ሽማግሌ ሳያጣ ቀረ ... አንባቢ ሆይ የመስፍን ወለታ ብዙ አለብህ። ፕሮፌሰር መስፍን ግን ይተቻሉ። በፕሮፌሰር ሽብሩ ተድላ፣ "ከጉዛምን ማሪያም እስከ አዲስ አበባ" ግለ-ታሪክ ውስጥ ፕሮፌሰር መስፍን በ1953 መፈንቅለ መንግስት ቀንደኛ የመፈንቅለ መንግስቱ ደጋፊ ሆነው ሰልፍ ሲመሩ ታገኛቸዋለህ። ከዚያ ወዲህ በተነሱት በደርግና የኢህአዴግ መንግስታትም በቀንደኛ ተቃዋሚነት ታገኛቸዋለህ። ... ከግዜ ወዲህ ደግሞ የስራ ባልደረቦቻቸውን (በተለይ የታሪክ ምሁራኑን እነ ፕሮፌሰሮቹን እነ ታደሰ ታምራትን፣ መርድን ...ወዘተ) ስራዎቻቸውን እያነሱ ሲያገጣብሩ ታያቸዋለህ። እኝህ ሰው በእሳት የተፈተኑ የግማሽ መዕተ ዓመት ተቃዋሚ ናቸው፤ ንጉሳዊውን፣ ከወታደራዊው ደርጉ፣ ከዘውጌኛው ኢህአዴግ ሳይለዩ። መስፍኔ ግን በተቃወሙት ሥርዓተ መንግስት እግር ሊተኩት የሚፈልጉት ሥርዓተ መንግስት እና የሥርዓተ መንግስት እሳቤ ምን ይሆን? የዚህ ጥያቄ መልስ ለዘመናት ሲያብሰከስከኝ አሁን የደጃች ወልደ ሠማዕት ግለ-ታሪክ ውስጥ አገኘሁት። የመስፍኔ እውቀት ንባባዊ እንጂ ተግባራዊ አይደለም። ይህን ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሳይቀሩ ጠንቅቀው ያውቁት ኖሯል። በሕዳር 1965 ዓ.ም ደጃች ወልደ ሠማዕት የወለጋ ጠቅላይ ግዛት ገዢ ሆነው ሲሾሙ ሹመቱን ለመቀበል አንድ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣሉ፤ "በስሬ የሚሾሙ ሹማምንትን እኔ እንድሾም የሚፈቀድልኝ ከሆነ ብቻ ሹመቱን እቀበላለሁ" የሚል። ይኸውም ተፈቅዶላቸው ሹመቱን እንደ ተቀበሉ ፕሮፌሰር መስፍንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ድረስ በመሄድ ምክትል ገዢ እንዲሆኑ ይለምኗቸዋል። ከብዙ ልግመት በኋላ ሹመቱን ይቀበሉና ጃኖሆይ ጋር ሹመቱ ለመጽደቅ ይቀርባል። ለካስ ተቺነቱን አይተው ከዚያ በፊት የጋንቤላን አስተዳደር እንዲያቀኑላቸው ከሙሉ ሥልጣን ጋር አገረገዥነት ቀ.ኃ.ሥ ሹመዋቸው መስፍን በተግባራዊ ዕውቀት ዕጦት ለግመው ገፍተውባቸው ነበርና ጃኖሆይ ስለመስፍን ሹመት እዚህ ሲሉ አስተያየት ይሰጣሉ፤ "ጥበቡም ሐብቱም ያላቸው አገሮች የሰሩትን እያየና የፃፉትን እያነበበ ከመናገርና ሌሎች የሰሩትን ከመንቀፍ በስተቀር የሚሰራ ሰው አይደለም። ..." (ገፅ 457 ተመልከት)።

ደጃች ወልደ ሠማዕት ግን የነጉሰ ነገስቱን አስተያየት ባለመቀበላቸው ሹመቱ ፀደቀና ... መስፍን ሹመቱን ተቀብለው ወደ ስራ እንዲገቡ ሲጠበቁ መጀመሪያ መኖሪያ ቤቴ ይታደስ አሉ። ቤቱ ሲታደስ የተሰጠኝ ላንድሮቨር አሮጌ ነውና አዲስ ካልተገዛ አሉ። ከየካዝናው ብር ተለቃቅሞ መኪናው ተገዝቶ ሲሰጣቸው ደግሞ መኪናው ኢንሹራንስ የለውም ብለው ለገሙ። መኪናው ኢንሹራንስ ሲወጣለት እንደ ምንም ሲለግሙ በሹመት ቦታቸው ተገኝተው ዞር ዞር ብለው ከተመለከቱ በኋላ ሰነዱ ተዝረክርኳል፣ ሰራተኞቹ ከ5ኛ ክፍል ያለፉ አይደሉም .... ወዘተ ምክንያቶችን ዘርዝረው ማመልከቻ ለአገረገዢው ፀሐፊ ወርውረው ወደ አዱ ገኒ መሰስ ብለው ተመለሱ። በዚህም የፕሮፍ መስፍን የሹመት ነገር እልባት አገኘ ...። ፕሮፍ መስፈኔ ግን ይህቺን የሹመት ታሪክ ለስልጣን አልጓጓም አይነት የስነ-ምግባር ብቃት አላብሰው እያቀረቡ ሲኩራሩባት ስንሰማ ኖረዋል። እንደ እወነቱ ግን መስፍኔ የንባባዊ ምሉዕነት አራማጅ ሰው እንጂ የተግባር ዕውቀት ባለቤት አይደሉም። ይህችን ደስ የማትል ዕወቀት ለሰጡኝ ደጃች ወልደ ሠማዕት የከበረ ሰላምታ አቅርበናል።

## ●● ነገረ፡ ወለጋ ●●

የዳጃች ወልደ ሰማዕት የወለጋ አገረ ገዢነት ሹመት ነገር ከተነሳ የአገረ ግዛቱ ባላባቶች በየ አጥቢያቸው የነበራቸው ያልተገደበ ሥልጣን መቼም የሚገርም ነው። የዚህም ነግር አኳኳን ከብዙው በጥቂቱ እንዲህ ነው። እኛ ወለጋን ስናውቀው ከጣልያን ወረራ ግዜ አንስቶ በመአከላዊው መንግስቱ ተበዳይነት እገነጠላለሁ ሲል ነው። የJohn Spencer, Ethiopia at Bayን ስታነብ የተባበሩት መንግስታት እ.አ.አ በ1945 እንደ ተመሰረተ የጠቅላይ ግዛቱ ባላባቶች የመገንጠል የወል ደብዳቤ እስከ ማስገባት መድረሳቸውን ታውቃለህና የዚህ ጠቅላይ ግዛት ችግር ምን ይሆን በሚል መቆዘምህ አይቀርም። ይህ የተገንጣይነት አዝማሚያ ግን ከአስተዳደር በደል የተነሳ እንዳልሆነ ይህንን የደጃዝማችን ግለ-ታሪክ ስታነብ ታውቃለህ። ይኸውም እንዲህ ነው። ደጃዝማች በየሚሾሙባቸው አከባቢዎች ሁሉ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የተሾሙበትን ጠቅላይ ግዛት ችግሮችና ዕምቅ የኢኮኖሚ ትሩፋቶች ለወራት ተዘዋውረው የማጥናት ከጥናቱም ተነስተው የተግባራወዊ ምላሽ የመስጠት ጠባይ ነበራቸው። ለአንድ ወር ከአስራ አምስት

ቀናት የወለጋን ጠቅላይ ግዛት ያልተነኩ የኢኮኖሚ ትሩፋቶችና ያሉ የአስተዳደር ችግሮችን ተዘዋውረው ባጠኑበት ወቅት የየአጥቢያው ባላባቶች የነበራቸው ሥልጣን ከሌሎች ጠቅላይ ግዛቶች ሁሉ በተለይ ያልተገደበ ሆኖ አግኝተውት ነበር። ነብሰ ገዳይ ወንጀለኛ እንኳን ያለ ያጥቢያ ባላባቱ ፈቃድ በፖሊስ እጁ አይያዝም ነበር (ከገጽ 482-485 ተመልከት)። አንባቢ ሆይ 20ኛው መ.ክ.ዘ የወለጋ ሊህቃን ከአስተዳደራዊ በደል ከሚመነጭ የተገንጣይነት ጥያቄ ከየት መጣ ነው? ... መልሱን ሳትደክም እኔ እነግረሃለው። እ.አ.አ ከ1904 ዓ.ም ጀምሮ በጠቅላይ ግዛቱ የተነዙት ምሲዮናውያን የፈጠሩት የባህል ተነጣይነት መንፈስ ውጤት ነው!! ለዚህም መረጃ ደጃዝማችን ከልብ አመሰግናለሁ። በመጨረሻም ዳሰሳዬን የማበቃው መፅሐፉ የሕትመት ቀለም ጥራት የማጣቱን፣ ግለ-ታሪኩም በአንድ ቅፅ ተጠናቅሮ መቅረብ ሲገባው በሁለት ቅፅ ተንዛዝቶ የመቅረቡን ነገር በመተቸት ነው። ከሳንባ ቆልፍ ጠብቆ ለነገ ሰው ይበለን!!

Reviewer: Mesele Terecha has a PhD in Medical History and is a Bibliophile

*ርዕስ: አንዳፍታ ላውጋችሁ*
*ደራሲ: ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር)*

የታሪኩ ባለቤት ይህን ምርጥ ግለ ታሪክ ሲጀምሩ ብዙ ሰዎች የሕይወት ታሪክህን ጻፍ ሲሏቸው "በታሪክ አጋጣሚ ከታላላቅ ሰዎች መሃል በድንገት የተገኘ ተራ ሰው ምን ታሪክ አለው" እያሉ ሲከላከሉ መኖራቸውን ይጠቅሳሉ። ይሁንና በፈረንጅ አገር ሳሉ እስከ 17 ዓመታቸው ጫማ ያለማድረጋቸውን ለፈረንጆቹ ሲነግሯቸው እና ማመን ሲሳናቸው ምናልበት ሕይወቴ ቢጻፍ ይጠቅማል ማለታቸውን ያወሳሉ። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በግንቦት 24, 1924 ዓ.ም. በሸንኮራ/መንዝ ከአባታቸው ግራዝማች ኃይሌ ወልደየስ እና ከእናታቸው ወይዘሮ አሰገደች ወልደ ዮሐንስ ተወለዱ። በልጅነታቸው በሸንኮራ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ትምህርታቸውን ጀመሩ። በተለምዶ በወቅቱ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በግዕዝ ቋንቋ፣ በቅዳሴና በመጻሕፍተ ቅዱሳት ላይ ያተኮረ ነበር፣ ይህም ለጌታቸው የግዕዝ ቋንቋ ፍቅርና ጥልቅ ግንዛቤ መሠረት ጥሎላቸዋል። በ1940ዎቹ መገባደጃ ላይ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በቅድስት ሥላሴ ቤ/ክ ትምህርት ቤት ተምረዋል። አባታቸው ቀደም ብለው መጥተው ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ባለ መቃብር ቤት ተቀምጠው ሲያስተምሩ ስለነበር ከአባታቸው ጋር እዚያው መቃብር ቤት ብርዱን እና "ሌላውንም" ችለው ኖረዋል። አባታቸው የመቃብር ቤቱን ጣሪያ "የቄሳር መንግስት መልዕክተኛ" በሚል ጋዜጣ አስውበውት ስለነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የአማርኛ ፊደል ማንበብ የጀመሩት ያኔ ነበር። በ1952 ዓ.ም. ወደ ግብፅ ተጉዘው በካይሮ በሚገኘው የኮፕቲክ ቲዎሎጂካል ኮሌጅ በባችለር ኦፍ ዲቪኒቲ ተመርቀዋል። ከዚያም በአሜሪካን ዩኒቨርሲቲ (ካይሮ) በሶሻል ሳይንስ ተመርቀው በ1962 ዓ.ም. ከጀርመን ኤበርሃርድ-ካርልስ ዩኒቨርሲቲ በሴሚቲክ ፍልስፍና ዶክትሬታቸውን አግኝተዋል። ይህ የትምህርት ጉዞ በግዕዝ፣ በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በግሪክና በሌሎች ሴሚቲክ ቋንቋዎች ላይ ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው በ1960ዎቹ መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ (አሁን አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ መምህርነት ማገልገል ጀመሩ። ለአስር ዓመታት ያህል በዚህ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን አስተምረው፣ በተለይ በግዕዝ ቋንቋና በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ጥልቅ ትምህርት ሰጥተዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ በርካታ የምርምር ጽሑፎችን አዘጋጅተው በኢትዮጵያ እና በውጭ መጽሔቶች ላይ አሳትመዋል። ከዋና ሥራዎቻቸው አንዱ የግዕዝ የእጅ ጽሑፎችን መዝግቦ መጠበቅ ነው። ከ5,000 በላይ የግዕዝ ጽሑፎችን በማይክሮፊልም ቀድተው በማስቀመጥ፣ እነዚህ ቅርሶች እንዳይጠፉ አድርገዋል። ይህ ሥራ በተለይ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ጥንታዊ መጻሕፍትና ጽሑፎች ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ትልቅ ጠቀሜታ ነበረው። በተጨማሪም፣ ከ18 በላይ መጻሕፍትን በግዕዝ፣ በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛና በሌሎች ቋንቋዎች ተርጉመውና ደርሰው አሳትመዋል። ከእነዚህ መጻሕፍት መካከል በግዕዝ ቋንቋ ላይ ያተኮሩ ጥናቶች፣ የኢትዮጵያ ታሪክና የቤተ ክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ትንታኔዎች ተካተዋል። ፕሮፌሰሩ የፊሎሎጂ (Philology) ሊቅ ናቸው። ፊሎሎጂ የቋንቋዎችን እና የጽሑፎችን ታሪክ፣ መዋቅር፣ እና ዝግመተ ለውጥ የሚያጠና የጥናት መስክ ነው። ይህ ዘርፍ ጥንታዊ የእጅ ጽሑፎችን፣ ሰነዶችን፣ እና ሥነ ጽሑፎችን በመተርጎምና በመመርመር የባህል፣ የሃይማኖት፣ እና የታሪክ ግንዛቤን ያጎለብታል። በፊሎሎጂ አማካኝነት የቋንቋዎች አመጣጥ፣ የቃላት ለውጥ፣ እና የሰዋሰው ሥርዓቶች ይጠናሉ፣ እንዲሁም የጥንት ሥልጣኔዎችን ቅርስ ለመጠበቅና ለመረዳት ይረዳል። ለምሳሌ፣ የግዕዝ ጽሑፎችን በመገምገም የኢትዮጵያ ታሪክና ባህል መተንተን ወይም የላቲንና የግሪክ ጽሑፎችን መተርጎም የፊሎሎጂ አካል ነው።

የደርግ መንግሥት በኢትዮጵያ ሥልጣን ሲይዝ፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው በፖለቲካዊ ምክንያቶች ቅርቃር ውስጥ ገቡ። በዚህም ምክንያት ከቤታቸው ሊያስሯቸው ከመጡት የደርግ ወታደሮች ጋር ሌሊት ሙሉ ተታኩሰው መጨረሻ ላይ በግንብ ዘለው ሲያመልጡ አከርካሪያቸው ላይ በገባች አንድ ጥይት ተመተው ወድቀው ተይዘዋል፤ በዚህ ምክንያት ወደ እንግሊዝ ለመሰደድ ተገደዋል። ከዚያ በመቀጠል ወደ አሜሪካ ተጉዘው በሴንት ጆንስ ዩኒቨርሲቲ (ሚኒሶታ) መምህርነት ተቀጥረው እስከ ጡረታቸው ድረስ በዚያ ሠርተዋል። በውጭ ሀገር ቢሆኑም፣ ለኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ጥናት

ያደረጉት ሥራ አላቆመም። በተለይ በአሜሪካና በአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች የኢትዮጵያ ጥናትን ለማስፋፋት ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ፕሮፌሰር ጌታቸው በሐምሌ 5, 1956 ዓ.ም. ከወ/ሮ ምሥራቅ አማረ ጋብቻ ፈጽመው ስድስት ልጆችን አፍርተዋል። ቤተሰባቸው በሥራቸው ዘመን ሁሉ የቅርብ ድጋፍ ሰጪ ሆኖ ቆይቷል።

በተጨማሪም፣ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችና ሴሚናሮች በመሳተፍ የኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ ለዓለም ማስተዋወቅ ችለዋል። ፕሮፌሰር ጌታቸው ለሥራቸው በርካታ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ተቀብለዋል። ከእነዚህ መካከል፡ -የማካርተር ጂኒየስ ሽልማት (1988 ዓ.ም) በኢትዮጵያ ቅርሶች ጥበቃና በግዕዝ ቋንቋ ጥናት ላደረጉት ልዩ አስተዋፅኦ ተሰጥቷቸዋል።የኤድዋርድ ኡሌንዶርፍ ሜዳል (2014 ዓ.ም.) በኢትዮጵያ ጥናትና በሴሚቲክ ቋንቋዎች ላደረጉት ምሁራዊ ሥራ እውቅና የተሰጣቸው ነው።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ስለ ደቂቀ እስጢፋኖስ የጻፉት ሥራ በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እና ሥነ መጻሕፍት ላይ ያተኮረ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ነው። ደቂቀ እስጢፋኖስ በ14ኛው እና 15ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተነሳው፣ በአፄ ይሥሐቅ (1406–1421) ዘመን በአባ እስጢፋኖስ የተመሰረተ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነበር። ይህ እንቅስቃሴ በተለይ በአጽዋም፣ በጸሎት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እና በመነኮሳት ሕይወት ላይ ያተኮረ ነበር። አባ እስጢፋኖስ በአፄ ይሥሐቅ ፍርድ ቤት ውስጥ ሃሳባቸውን በመግለጽ ተደንቀው ቢሆኑም፣ በኋላ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ተቃውሞ ገጥሟቸው ተወግዘዋል። ይህ መጽሐፍ የደቂቀ እስጢፋኖስን ታሪካዊ እና መንፈሳዊ ጠቀሜታ በጥልቀት ይዳስሳል። ፕሮፌሰር ጌታቸው በኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጽሑፍ እና ታሪክ ላይ ባላቸው ሰፊ ዕውቀት፣ የደቂቀ እስጢፋኖስን እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እና ማኅበረሰብ ውስጥ ያለውን ሚና በማጥናት በዝርዝር ይተነትናሉ። ይህም የእንቅስቃሴውን መነሻ፣ የተፈጠረበትን ሁኔታ፣ እና በተለያዩ ነገሥታት ዘመን ያጋጠመውን ድጋፍና ተቃውሞ ያጠቃልላል። የፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ሥራ በግዕዝ እና በአማርኛ የተጻፉ ጥንታዊ መጻሕፍትን በመመርመር የደቂቀ እስጢፋኖስን ትምህርቶች፣ የአምልኮ ሥርዓቶች፣ እና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያላቸውን ተፅዕኖ በማጉላት

ይታወቃል። ይህ ሥራ በተለይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ እና ባህላዊ ታሪክ ለማጥናት ለሚፈልጉ ምሁራን እና ተማሪዎች ጠቃሚ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች፣ ሥነ ጽሑፍና ታሪክ ጥናት ላደረጉት አስተዋፅኦ የማይጠፋ ውርስ ትተዋል። የግዕዝ ቋንቋን በማጥናትና በማስተማር፣ በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ጥንታዊ ጽሑፎች በመጠበቅ፣ የኢትዮጵያን ማንነትና ቅርስ ለዓለም አስተዋውቀዋል።

የእነርሱ ሥራ በተለይ በአፍሪካ ጥናትና በሴሚቲክ ቋንቋዎች መስክ ለሚማሩ ተማሪዎችና ምሁራን መነሻ ሆኗል። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ ላይ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ለትውልድ ትውልድ የሚተረክ ነው።

## Reviewer: Editor in Chief of Think Ethiopia

*Title: Thomas A .Lambe: A Missionary Doctor and Entrepreneur*
*Author: PaulE.Balisky*

A couple of years ago I was sipping coffee at 'Lambe cafe' infront of Pasture research institute with my friends and an altercation arose about the meaning of the word 'Lambe'. None of us knew what it meant that day. So years went by and I heard Doctor Messele Terecha talk about him and other missionary doctors on Sheger Radio. Surprisingly, I bought his biography two days after and it is immersive to say the least.

The young Presbyterian Missionary doctor came from America to spread the good news. Interestingly, his missionary colleagues called him a '*loose canon'* on the ship, they were right. While he was on a medical mission near the Sudan border the spanish flue broke out. So, the ruler of Qellem, Dej Birru, invited him to heal the sick. While he was at Sayo and thinking about moving to Gore( Illubabora), something happened. A beetle was fatally waged in the ear of Ras Nadew at Gore. Frightened by the near death experience, his vassals brought him to Dr.Lambe and Lambe manages to take out the dead insect to the disbelief, awe and relief of Ras Nadew. Surprisingly, Ras Nadew adamantly believed Doctor Lambe saved his life and wrote a letter to Alga werash Teferi Mekonen so that the new king might take advantage of his healing Power and the rest is history.

Dr Thomas Lambe was called to Addis Ababa and became the most revered and loved Doctor in town for nearly half a

century. However, the reason why I am writing this review is to underline how much ostracized he was by his own people. He was fired from the Presbyterian church and the Sudan Interior Mission (SIM) for establishing the Abyssinian Interior Mission, instituting the Teferi Mekonen Hospital and not administering the finance according to the Missionary protocol.

He engineered the most elaborate and novel plan to raise funds for the Construction of the Hospital but his own missionary friends accused him of embezzling the funds. That's why the Missionary HQ in America considered him as a reckless cow boy and he laments this in his own Auto - biography 'A Doctor without a country', for an American who died in Jerusalem after his retirement, he was indeed a persona non grata for Christ. Fortunately, Emperor Haileselassie loved him like a brother but his tragic fallout with the Emperor after the Italian invasion sends him into a great depression because the king suspected him of having a secret complicity with the Fascists. Sadly, he suffered a grave injustice in the hands of Fascists during the occupation. Such was the life of a doctor without a country.

**Reviewed by the Managing editor of Think Ethiopia**

*የመጽሐፍ ርዕስ፦ ጎብር ሕይወቴ*
*ጸሐፊ፦ ፕሮፌሰር (Emeritus) ባሕሩ ዘውዴ*
*የገጽ ብዛት፦ 313*

የዳሰሳችን መዳረሻ እንዲሆን እሳቸው "የሦስቱ ሚዛን" ያሉትንና የሕይወታቸው ፍልስፍና (መመሪያ) የኾነውን ዘዴ በመከተል የመጽሐፍ እጥርጥሩን እንሰድራለን። "...ከዩኒቨርሲቲ ተማሪነቴ ጀምሮ የሕይወቴ መመሪያ አድርጌ የወሰድኩት "የሦስቱ ሚዛን" ያልኩትን ነው። እነሱም አካዳሚያዊ፥ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ...አካዳሚዊው ሙያዊ ተግባሬ ነው፤ ማሕበራዊው ለሕይወቴ ጣዕም የምሰጥበት፥ ፖለቲካዊው ደግሞ የዜግነት ግዴታዬ..." ገጽ 94 ልጅነታቸው ምን ይመስል እንደነበር በሚተርኩበት ሥፍራ (ከገጽ 1-10) የአባታቸውን ዘውዴ ወልደሃናና የእናታቸውን አዳነች ቦባስ የትውልድ ሐረግ ይዘረዝራሉ። የባሕሩ (ፕሮፌሰር) አያቶቻቸው በአካባቢያቸው የተከበሩ አዛውንቶች እንደነበሩ፤ በእናታቸው ወገን በኩልም በተለምዶ በከበሬታ አጠራር "ንጉሥ" ተብለው ይጠሩም እንደነበር ከትውስታቸው ያስቃኙናል። ለሐይማኖታቸው ቀናዒና በመልካም ምግባርም ይታወቁ ነበር። የሶዶ ጉራጌ የኾኑት ቤተሰቦቻቸውም በአጠቃላይ የጉራጌ ብሔረሰብ አባል ከመኾንም ከየትኛው ጎሳና "ቢጤ" (ንዑስ ጎሳ) እንደኾኑ ማወቅ ልክ እንደ እስራኤላውያን "እስራኤላዊ" ከመባል አልፎ የየትኛው ወገን (ነገድ) መኾናቸውን ማወቅ እንደሚገባ ኹሉ በእሳቸውም ቤተሰብ ዘንድ ይኽ ልማድ ያለ መኾኑን ይመሰክራሉ።

መለያቸው በማሕበራዊ ሕይወት የጠበቀ ትስስር፥ ለሐይማኖት የተሰጠ መኾን ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮም ጋር የነበራቸው ቁርኝት አስገራሚ ነው። በልማድ የአየሩን ኹነት በመረዳት የሰጡት ትክክለኛ አስተያየት ምን ያኽል ከተፈጥሮ ጋር የተሳሰረ ሕይወት እንዳላቸው ያሳያሉ። (ገጽ 4) ሌላ ደግሞ ገጃ (ጌጃ) በሚባለው አካባቢ የነበረው በተለያዩ የሥራ መስክ የተሰማሩ ሰዎችና ብሔረሰብ አባላት አብረው ተሰባጥረው መኖራቸውም የልጅነት መዋዕላቸው ትውስታ ናት።

ከገጽ 11-32 የእሳቸው (ባሕሩ) ውልደት፥ የትውልድ ቦታና ዘመን፥ እንዲሁም የስም አወጣጥ (አሰያየም) እና ሌሎችንም የቤተሰብና የልጅነት

ሕይወታቸውን የሚያስቃኙበት ክፍል ነው። የእሳቸው አባት ጋሽ ዘውዴ ልጆቻቸውን ደስታን ባለመንፈግ ነገሮችን (አንዳንድ ድርጊቶችን) ባለመከልከል ይልቁን በሥራ ትጋትን በማሳየት የራሳቸውን እጣፈንታ በራሳቸው እንዲወስኑና ምርጫዎቻቸው ብልሃት የተሞላበት እንዲሆን አድርገው ማሳደጋቸውን ከምስክርነታቸው እንገነዘባለን። ይኽም የታሪኩ ባለቤት በኾኑት በጋሽ ባሕሩ ሕይወት በተለይም የአካዳሚው ዓለም ልኅቀት የታየ ነው።

ከአያቶቻቸው የተላለፈው ልማድም በክፍሉ መንጸባረቁን ማስተዋል ይቻላል። ይኽም በሥራ ትጉ መኾን፥ የራስን ወገን ማወቅን (ታሪክ)፥ ከሌላውም ብሔረሰብ ጋር ተሰባጥሮ በሰላም መኖርን፥ ለሐይማኖት የተሰጠ ልብ ያለው መኾንና በዋናነት ደግሞ የሴቶች ሚና በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ የተብራራ መኾኑን ልብ ይሏል። (የባለቤታቸውን ብርቱነት ለማየት ከገጽ 161 ጀምሮ እስከ መጽሐፉ መደምደሚያ ድረስ የጻፉትን ማንበብ በቂ ነው።) ለአሁኑ ግን የእናታቸውን አዳነች ቦባስ በገጽ 15 ላይ ቤተሰብንና ቤትን መሠረቱ የጠበቀ እንዲሆን ያደረጉትን ተጋድሎ የዘከሩላቸውን ማሰብ የተሻለ ነው። በዚህም “ሴት ያመነ ጉም የዘገነ”፥ “ሴት ድብ ትፈራለች፥ አጥር ትመዛለች”፥ “ሴት ለቤት፥ ወፍጮ ለዱቄት” የሚሉትንና መሰል ሴትን የሚያንኳስሱ አጉል የንግርት ልማዶች በተግባር ያፈራረሱና በሴቶች ላይ ተደራጅተው ሴቶችን ከሚመዘብሩ “ፌሚንስቶች” የላቁ ፌሚንስት መኾናቸውን “ለጨለማ ጊዜ መብራት ለመከራ ጊዜ ብልሃት” ኾነው አሳይተዋል! በዚህ ጠንካራ ቤተሰብ ውስጥ መገኘታቸው (ጋሽ ባሕሩ) የሕይወታቸውን መጻዒ ዕድል መወሰኑ ሳይታይ የተፈታ ህልም ነው።

በመቅደም ላይ የመጽሐፋቸው ዒላማ ወጣቱ መኾኑን እንዲህ ይገልጻሉ፡- “ይህ ግለ ታሪክ በተለይ ዒላማ ያደረገው በተለይ ወጣቱን ትውልድ ነው።” በቀለም ትምህርት የተሻለ ቦታ መድረስን ለሚሻ ወጣት በተለይም በማሕበራዊ ሕይወት በእጅጉ ለተሳሰረና ምሣሌን ለመመልከት የሚያማትረው ይህ ክፍል አስተማሪ ኾኖ አግኝቼዋለሁ። ለትምህርት፥ ንባብ፥ እና መጻሕፍት ያላቸው ፍቅር ይስባል። በእርግጥ ይህ ጥልቅ የማወቅ ረሃባቸው (አርስቶትል በሜታፊዚክ መጽሐፉ መግቢያ “All men by nature desire to know” እንዳለው) ከትጋታቸው ጋር ተሰናስሎ የኾኑትን እንዲሆኑ

አድርጓቸዋል። በተለምዶ "ቀለሜ" የሚባሉ ዐይነት ተማሪም እንደነበሩ ከዜና መዋዕላቸው እየጨለፉ ያቀመሱንን ላጣጣምን እሙን ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ከተማሩበት የተስፋ ኮከብ ትምህርት ቤት፥ ለጥቀውም የመሰናዶ ትምህርታቸውን እስከተካታተሉበት የልዑል መኮንን (አዲስ ከተማ) ትምህርት ቤት ድረስ በትምህርት (ዕውቀት) ልኅቀት፥ በትምህርት ቤቱ ውስጥም ኾነ ውጪ ባሉ ገጠመኞች የክስተቱ አካል (በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ) በመኾን ኹለገብ ተማሪ እንደነበሩም አሳይተዋል።

በተለይም በኢኮኖሚ የተመቻቸ ካልሆነበት ቤተሰብ ለተወለደ፥ ለትምህርት ሳይሆን ለንግድና ለተለያዩ ነገሮች ከሚኾን ሥፍራ መገኘታቸው፥ እንዲሁም ሲኒማ ገብተው ፊልሞችን ቢመለከቱም፥ እግር ኳስ ማየትም መጫወትም ውስጣቸው ቢሆንም፥ ከተለያዩ ፈሽታ ገለጻዎች ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ያላቀቡ ሆነውም ሚዛናዊ ሕይወት ምን ይመስላል የሚለውን የሚያስነብቡ ሕያው መጽሐፍ ናቸው። ብዙዎች የገለጹላቸውን ትዝብት ማለትም የመርካቶ ልጅ ለትምህርት እንደማይሆን፥ ጉራጌ ለንግድ እንጂ ለትምህርት ፍቅር እንደሌለው፥ የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪ በዓለምአቀፍ ተቋማት ላይ ትልቅ ተሰሚነት ያለው መሆን ይቅርና አገር ውስጥ ካሉት ትምህርት ቤቶች ለመወዳደር ብቃት የለውም የሚለውን፥ እንዲሁም ጎበዝ ተማሪ ሲባል አንድን ነገር ብቻ የሚያሳድድና በሌሎች የሰነፈ ነው የሚሉትን አመለካከቶች ያጠሩ ምሁር ናቸው።

በኃላም የቀዳማይ ኃይለ ሥላሴ (አዲስ አበባ) ዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውን፥ ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች ይልቅ የታሪክ ትምህርትን እንዲመርጡ ያደረጋቸው ምክንያት፥ የአስተማሪዎቻቸውን ብቃት፥ ጊቢ ከመግባታቸው በፊት በነበራቸው የትምህርት ዘመን የባሕር ማዶ ቋንቋን በባለቤቶቹ (native speakers) የመማራቸው (ሲጠብቅ) ያለውን አዎንታዊ ፋይዳ፥ ፖለቲካዊ ተሳትፎና በጊዜያቸው የነበሩ አሳቢያንን ግብር ይተነትናሉ። (ከገጽ 33-84) የድኅረ ምረቃ ትምህርታቸውን የት እንደተከታተሉ፥ የትምህርት እድሉን ያገኙበት መንገድ፥ እዛው በነበሩበት ወቅት የነበራቸውን ቆይታ በመተረክ ለምርምር ሥራቸው የተዘዋወሩበት ሥፍራም ይተነትናሉ። የፖለቲካ ተሳትፎአቸውም እንደ አብዛኛው የወጣት ግለት (passion) ካልተረጋጋ-ፍላጎት (turbulence) ጋር ተጣምሮ በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ በጊዜ

ሂደት ደግሞ በልምድና ዕውቀት እየተሳለ ከጃንሆይ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አሻራቸውን እያስቀመጡ አሉ።

"ከመሬት ላራሹ" በመቀጠል "ድኽነት ወንጀል ወይ?" በሚል የተጋጋለውን ሰላማዊ ሰልፍ በመንግሥት ግበረ-ኃይላት መበተኑን በመግለጽ በጊዜውም የነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጥምቀት ተቋዳሽ መኾናቸውን አሳይተዋል። በድኅረ ምረቃ ትምህርታቸው ወቅት በነበራቸው ስብሰባና የውጪው ዓለም የፖለቲካ ርዕዮተ-አለማዊ እንቅስቃሴ ነፋስ ውስጥ እሳቸው በማርክስ ዕሳቤ ተጽዕኖ ስር እንደነበሩም ከጽሑፋቸው መረዳት ይቻላል። ቀዳማይ ኃይለ ሥላሴ ተወግደው ወታደራዊው የደርግ ሥርዓት አገሩን ከተቆጣጠረ በኃላ የድኅረ ምረቃ ትምህርታቸውን አጠናቀው በተመለሱ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ በቁጥጥር ስር ውለው ለአምስት ዓመታት እስር ቤት እንደነበሩም ተርከዋል። እስር ቤቱ መልካም ሥፍራ ባይሆንም የጊዜው መትረፍረፍ ለቋንቋ ክሂሎት ማሳደጊያና ለበርካታ መጻሕፍትና ሌሎች ጽሑፎች ንባብ እንዳገዛቸውም ገልጸዋል። ይሁን እንጂ የጋሽ ባሕሩ መታሰር ለብዙዎች ጭንቀት በተለይም ለቤተሰቦቻቸው ጥልቅ ኃዘን ነበር። የዚህ ደግሞ ምክንያቱ እስር ቤቱ የእስረኛ መብት የሚከበርበት ሥፍራ ሳይሆን በሕግ ከለላ ውስጥ ሆነው የሕግ ጥሰት (የማይገረሰሰው ሰብዓዊ መብት እንኳን ያ ኃይል ከፈቀደ የሚገረሰስበት ወቅት) የሚካሄድበትና ትክክለኝነት ሚዛኑን የሚደፋው ለእውነት ወይንም በእውነት ሳይሆን ኃይል ወዳለበት መሆኑም ነበር።

እስር ቤቱ ውስጥ ይካሄድ የነበረውንና ከእነሱ (ከደርግ) አስተሳሰብ ውጪ ሌላን አሳብ የሚያቀነቅን እሱ ይቅርና ያቀነቅናል ተብሎ የሚታሰብ እስረኛ እንዴት "እንደሚንከባከቡት" የቆንጂት (ትርሲት) ተክሉን ማስታወሻ ላነበበና የበዓሉ ግርማን ኦሮማይ "የማሳቅ" ና "ስየላ" ቃላት ለሚገባው በደርግ ሥርዓት እስረኛ አያያዝ ምን ይመስል እንደነበር ከጋሽ ባሕሩ ምስክርነት ጋር ማመሳከር ይችላል። ይኽም ሥርዓቱ በባሰ ጭቆና የተተካ መኾኑን ለመገንዘብ ቀላል ነው። ታላቁ የመካከለኛው ዘመን ፈላስፋ ቅዱስ ቶማስ አኳይናስ አንድ ጨቋኝና አፋኝ (Tyrant) መሪን በኃይል የጣለ ቡድን ከመጀመሪያው የባሰ ጨቋኝ ሊሆን እንደሚችል የሰጡት አስተያየት የጃንሆይ መነሳታቸውና የደርግ መተካት ትልቅ ማሳያ ነው። ከእስር ከተለቀቁ በኃላ በደርግ ዘመነ መንግሥት እንኳን የዘር ፖለቲካው ቅጥ አንባሩን ማጣቱን መስክረዋል (ቢያንስ

መፋፋሙን)።በመቀጠልም በኢሕአዴግ ዘመን የነበረውን ትሩፋትና ክፍተት አብራርተዋል። በጊዜውም ለታሪክ ትምህርት እድገትና መስፋፋት የራሳቸውን ሚና ለመጫወት መሞከራቸውን ከጽሑፋቸው እንረዳለን። በአሁኑም መንግሥት (በብልጽግና ፓርቲ ዋና ሊቀመንበርና በኢትዮጵያ መሪ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ አማካኝነት በተከፈተላቸው እድል) የራሳቸውን አስተዋጽኦ ለማሕበረሰባዊ ሳይንስ ጥናት እድገት ለማበርከት እየታተሩ መሆናቸውንና በአገሪቱ የትምህርት ተቋማት የታሪክ ትምህርት እንዲሰጥ ያቀረቡት ባለስድስት ነጥብ መደምደሚያ አሳብ ያለው ጽሑፋቸውም ቅቡልነት ማግኘቱን መስክረዋል። በስተጨረሻም በአህጉራዊ እንቅስቃሴ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ አብራርተዋል።

**የመጽሐፍ ዳሰሳ በየሺጥላ ይገዙ (የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ምሩቅ፥ የአራተኛ ዓመት የሥነ-መለኮት ተማሪ፥ የ26 ዓመት ወጣት፥ የአዲስ አበባ ነዋሪ)**

*የመጽሐፉ ርዕስ፦ አባት ዐልባ ሕልሞች*
*ደራሲ፦ ማስረሻ ማሞ*
*የገጽ ብዛት፦ 340*

ኢትዮጲያችን ኩሪ እኛም ባንቺ እንኩራ ካልንበት ቅንፍ ወጥተን ኩራታችንን የምንመረምርበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ማስረሻ ማሞ ብሔራዊ ኩራታችንን ለመመርመር የራሱን ሕይወት "በግለ ታሪክ ተረክ" ሰድሮ መሰዋዓት አድጎልናል። በአዲስ ነገር ጋዜጣ የስንቱን ፊልም እና ድርሳን ሲገመግም እንዳልኖረ ዛሬ ተራው ደርሶ ራሱ ባለሳምንት ሲሆን የጻፈውን ልንዳስሰለት የተገባ ነው። ማስረሻ ወደ ተረኩ ከመግባቱ በፊት በመቅድም፣ ምስጋና እና አበርክቶት ያሚሙቃል እኛን ደግሞ ስለሚጠብቀን ጉዳይ ያዘጋጀናል። ደራሲው መጽሐፉን ለማዋለድ ሰበብ የሆነው የኮሮና ወረርሽኝ በሀገረ ኔዘርላንድ ላንቃ እና ትናጋውን ቆልፎ ከሞት አፋፍ አድርሶ ከመለሰው በኃላ ያገኘው አብርሆት ነው። ሁሉም ሰው የሚሞት ሲመስለው በዚያች ቅጽበት የሕይወቱን ፋይዳ ይመዝናል። ይህ ደራሲው ራሴን አክሜቤበታለሁ የሚለው መጽሐፍ የእርሱ ትውልድ ያልታከመ እና ያልሻረ ሕመም ማሳያ እንደሆነ ይነግረናል። ሳይካትሪስቱ ዶክተር ዳዊት አሰፋ "የሁሉ" በተሰኘ መጽሐፉ ያልታከመ Collective trauma ሲቆይ እና ሲመረቅዝ Intergenerational trauma ሆኖ ትውልድ እንደሚሻገር ያወሳውን እና እስከዛሬ እነ አዳም ረታ በኤልዛቤል የነገሩንን ማስረሻ ነፍስ ዘርቶበት በራሱ ሕይወት ስለተረክልን ምስጋናዬ የላቀ ነው።

መጽሐፉ የሚጀምረው ባለታሪኩ እማማ ደንሳ እግር ስር ተቀምጦ እንዝርታቸውን እያሾሩ ልቃቂት ሲያመርቱ የሚወረውሩትን ቃላት እየለቃቀመ እና ከሰዕብናው ጋር እየሰፋ ሲተርክልን ነው። ሴትዮዋ ከሸማ ውጪ አይለብሱም በሸክላ ብቻ እንጂ አያበስሉም። አፈር ስለሆንን ወደ መሬት ጠጋ ብለን እንኑር የሚለው ፍልስፍናቸው "ሸክላ ሰሪ በገል ይበላል" ይሉት ብሂል ስድብ እንዳይመስላቸው አድርጓል። ልብሳቸው የተሰራበትን ድርና ማግ ሲነግረን በድርና ማግ መሃል ያለውን ልዩነት የማያውቅ የኔ ዓይነቱ ከተሜ አምስት የማግ ዓይነት በግርጌ ማስታወሻ ሲጻፍለት ሊደነግጥ ይችላል።እንግዲህ እንዲህ በደቃቅ እውነታዎች የሚጀምረው መጽሐፉ

"መናጢ እና መናኛ" ሰዎች ግለታሪካቸው ሊጻፉ አይችሉም የሚለውን "የሚያቃጥል ታቦት" እሳቤ ውድቅ ያደርገዋል። ታሪኩ ሲቀጥል እና ሲቀጣጠል እንደ ዘበት ጣል የሚደረጉልን "የባለጅ ቃላት" የዕደ ጥበብ ማዕከል ወደ ሆነው የቀጨኔ ማህበረሰብ ስነ ልቦና ማዕከል ይዘውን ይነጉዳሉ። ለምሳሌ 'ማፈፍ' ያልደረቀ የሸክላ ጭቃን ቅርጽ የማስያዝ ሂደት ሲሆን ማስሬ "ሕይወትን ማፈፍ" ብሎ የስነ ጥበብ ቃል ያደርገዋል። "ቋንቋ መግባቢያ ብቻ ነው" የሚሉ ደናቁርት ቃላት ሊሸከሙ የሚችሉትን ስነ ልቦና ይህን ድርሳን በማንበብ ብቻ ማረጋገጥ ይችሉ ነበር።

ተራኪያችን በሕጻንነቱ ከእኚህ ሴት ቤት ከእናቱ አስጨከነች ጋር ወደ አክስቱ አባዬ ጣፈጥ ቤት ለመሄድ ይገደዳል። እናቱ አክስቱን ለማገልገል ጠላ እና አረቄ እየጣለች እና እያወጣች ስትዳክር አስር ዓመት ይሆናታል። ታድያ ድንገት እህቷ ስትሞት የእህቷ ልጅ ባል አስጨን ከቤታችን ውጪ ብሎ ያሰቃያታል። እንግዲህ እዚህ ጋ ወደ ኦሪትም የሚሳበው የቀጨኔ ማህበረሰብ የሕገ ልቦና ሽንጎ ሐተታ ዘምክንያቱን የሚሰጠው በመደበኛው ሕግ ልጅ እያለች እህት ባትወርስም ሐብቱን ያፈራችው እህት ሜዳ መውደቋ ለህሊና ተቃራኒ እንደሆነ ጠቅሰው የሩብ ግማሹን ሐብት እንድትካፈል ይፈርዱላታል። በዚያ ሀብት መለስተኛ ጎጆ ቀልሳ ስትኖር ጠላ ለመጠጣት "ማደያውን" የሚሞሉ ደንበኞቿ የሚፈጥሩትን መስተጋብር ለአንባቢ እተዋለሁ። ማስረሻን አባት ዓልባ ያደረገው ጉዳይ የሚመነጨው እናቱ አስጨ ልጆቿን አባት ዓልባ ላለማድረግ የመሠረተቻቸው ትዳሮች ምኞት ስለነፈጉት ነው። በመጽሐፉ የእናቱን ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን የመላው ባለጅ ማህበረሰብ ጠንካራ ሴቶችን እናይበታለን። ወንዶቹም ቢሆኑ "ከሞያ ጉድጓድ" እስከ አደባባይ "ሸማ አልባሽነት" የተካኑ ናቸው። ይሁንና ማህበረሰቡ ለሴቶች እንደሚያደላ "በጎባይ" እና "ጥፍሮዬ" ስርዓቶችን ብቻ በማየት መፍረድ እንችላለን። በባለጅ ስርዓት ለጋብቻ ስርዓት "እንጀራ እንዲቆርሱ" ሽምግልና የሚላኩት ሴቶች ሲሆኑ የስርዓቱን የሚያምር ስዓላዊ መግለጫ ከመጽሐፉ ያገኙታል። የጥፍሮዬ ስርዓት ሴቷ በሰርጓ ዕለት ክብረ ንጽህና ካላት ለክብሯ የሚደረግላት የመዝናኛ ስርዓት ነው። በጥፍሮዬ የሚወጡት ግጥሞች ወሲብ ቀስቃሽ ቢሆኑም ያን ዕለት ሴቶቹን ማንም አይናገራቸውም፥ ግጥሞቹ እንደ

"ሌቱም አይነጋልኝ" እንደ ወረደ ቀርበዋል እናማ ወዳጄ መጽሐፉን ገዝቶ መኮምኮም ነው።

የባለታሪኩ የማንነት ጥያቄዎች እየጎረመሰ ሲሄድ ፍልስፍናዊ በሆነ መንገድ እየተገለጡ ይሄዳሉ። በአንድ ወንበር የሚቀመጡ የሃይስኩል ጓደኛው የቀጨኔ ማህበረሰብ አባል እንደሆነ ሲነግረው በነጋታው ዴስክ ሲቀይር እና እነሱ ቡዳ እና ማታ ማታ ወደ ጭራቅነት እንደሚቀየሩ ሲነግረው ምድር ዓለሙ ዞሮበት ጥያቄውን ለእናቱ ይዞ ይመጣል " እንዴት ሰው ሌላ ሰውን ይበላል?" ይላታል። ማስረሻ በእናቱ፣ ባልንጀሮቹ እና ባስተማሪዎቹ ውስጥ ሆኖ ጠበቅ ያለ ፍልስፍና ሲናገር ከእነርሱ ይልቅ እሱን እንሰማዋለን።በሀገረ አሜሪካ ኢሳቤል ዊልክርሰን የተባለች ጥቁር ደራሲት በ2020 ያሳተመችው Caste: The Origins of Our Discontents የተሰኘ መጽሐፍ የአሜሪካን ማህበረሰብ እንደ ህንድ እና ናዚ ጀርመን በካስት እንደሚመራ የጻፈች ጊዜ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ Caste system እንዳለ ለመፈተሽ 8 ነጥቦች አስቀምጣ ነበር።በወቅቱ አሜሪካን በሚያህል የነጻነት ሀገር አሁንም Caste system እንዳለ ማስመሰል የግራ ዘመሞች ሴራ እና የ Woke culture ጣጣ ተደርጎ ብዙ ሁከት ተነስቶ ነበር። የሀገራችን ባለጆች የደረሰባቸውን መገለል አስታኮ ማስረሻ እንደ ዊልከርሰን እዚህ ሀገር Caste system እንዳለ አረጋግጫለሁ ቢለን ምን ይውጠን ነበር? ምክንያቱም ደራሲው የኢ/ ኦ/ ተ/ ቤ/ክ የባለጅ ማህበረሰብ ለክህነት አይበቃም በማለቱ ቄሶቹ እነርሱ በሰሩት ልብሰ ተክህኖ እያጌጡ እነሱን ማሸማቀቃቸውን በእግረመንገድ ሲጠቅሰው እንጂ ነገሩን ከመሠረቱ ሰርስሮ ሲነግረን አናይም ግን ያላየውን ጽፏል ለማትም የማልደፍረውም "ከባለቤቱ ያወቀ" እንዳይሆን ነው።

የደርግ ዘመን መጨረሻ ያመጣው የፓለቲካ ትኩሳትን እንዴት በትኩስ አቅሙ ከመነን ግንብ እስከ ቀጨኔ ጫካ እየተሽሎከሎከ እንደተወጣው እናይበታለን። የምስራች የምትባል ዓይኑካውን ሲያወሳ ለሴቶች የነበረውን ፍርሃት አልደበቀም ብቻ ሳይሆን "ጥፍሬን ያልበኛል" ሲል እያዋዛ ያጫውተናል። በኃላ ንዑስ ከበርቴ ሲሆን በፒያሳ ሆድ ውስጥ ሲዝናና ዓይነ ጥላው ይገፈፍለታል። የሚገርመው የጠቀሳቸው ቤቶች በሙሉ በሰሞንኛው "ኮሪደር ልማት" ፈርሰዋል። ብሶት የወለደው ኢህአዴግ አዲሳባን ሲቆጣጠር እንደ ፊልም አክተር ሲያደርገው ከጥይትም ለጥቂት ተርፏል። ማትሪክ

ወድቆ ሙሉ ለሙሉ የሽማ ንግድ ውስጥ ገብቶ ገንዘብ የማግኘት እና የማጣት ሂደት ውስጥ ይገባል። የነጋዴ ነገር ሆኖበት ድራፍት እየለጋ የቦሊውድ እና ሆሊውድ ፊልም ሲኮመኩም ቅልጥ ያለ Existential dread ውስጥ ይዘፈቃል። አንድ ቀን ሻይ ባረቄ እየጠጣ ሳለ የተወዳጀው ሳቂታ ግለሰብ እያሳሳቀ አምስት ኪሎ " ሕብረት አምባ" ይወስደዋል ቀስ እያለ በወንጌሉ ይሳብና "ጌታን ያገኛል" በቀላሉ "ሜንጤ" ይሆናል። በዚህ ምክንያት እንደዚያ የሚወዳት እናቱ አስጨ ከቤት ስታባርረው አንድ ጥያቄ ያነሳባታል፦ "አንቺ ቡዳ ተብለሽ ተወግዘሽ ኖረሽ ሌሎችን ሜንጤ ብለሽ እንዴት ትጸየፊያለሽ?" እናቱ ይህን አመክንዮ መሻገር ስላቃታት እየከበዳትም ቢሆን ትታረቀዋለች። በ Protestant Christianity ዓለም ሲቆይ የ90ዎቹ የኑፋቄ ወጅብ ከካሣ ኬራጋ እና "የእግዚአብሔር መንግስት" ጋዜጣ ጋር ያገናኘዋል።ለጥቂት ጊዜም የካሣ ኬራጋ አድናቂ ሆኖ እንደነበር ከቃላቱ እንረዳለን። ይሁን እንጂ አባት ዓልባ የነበረው የቀጨኔ ልጅ አባት ያገኘና ከወዳጁ ዳኘነት መኮንን ጋር አዲስ ባገኙት ሕይወት መረጋጋት ሲጀምሩ መጽሐፉ ድንገት ይቋረጣል። በመሠረቱ እኔ በሕንጸት ቆይታዬ Christian lierature የለም እያልኩ ብኖርም እንዲህ ዓይነቱ ዘውግ ካለ ይህ መጽሐፍ በሀገራችን የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም። ለማስረሻ ማሞ ግን "አባት አግኝተህ እንዴት አባት የለኝም ትላለህ ?" ብዬ ልጠይቀው እፈልጋለሁ።

**ዳሰሳ አቅራቢው፡ ዳዊት በዛብህ በሕግ እና ፍልስፍና የማስተርስ ዲግሪ ያለው ሲሆን የThink Ethiopia ማኔጂግ ኤዲተር ነው።**

*ርዕስ:- ባንዲራ ሳይኖረኝ እንዳልሞት: ኢትዮጵያ፣ ከንቱ ሕልሜ እና ሰቀቀኔ*
*ጸሐፊ:- ቫርትኬስ ናልባንድያን*
*ዘውግ:- ግለ ታሪክ*
*ገፅ ብዛት፡- 182*

በአጠገቤ ባለፈች ቁጥር ብርሃናማ ፈገግታዋ ያስገርመኝ ነበር። ኤሊስ ናልባልዲያን በአአዩ የሕግ ትምህርት ቤት የሕግ ፍልስፍና አስተማሪ እንደሆነች ያወቅሁ ዕለት ሴት ልጅ ፍልስፍና ስታስተምር ለማየት እንደጓጓሁ በዓመቱ ሌላ ሃበሻ ተመድቦብን ትምህርቱን በቸልታ እንደተለመደው አጓጎለው። ከዓመታት በኃላ የሕግ ፍልስፍና የተሰኘውን መጽሐፌን በፌስቡክ ሳስተዋውቅ አይታ ስድስት ኪሎ ግቢ ባለፈች ባገደመች ቁጥር የምትሰጠኝ ፈገግታ ትዝ ብሏት ይመስለኛል በውስጥ መስመር አወራን፤ በብዙም አበረታታችኝ። ኤሊስ ናልባንድያን በኢትዮጵያ የተወለደች ሶስተኛ ትውልድ አርመናዊ ናት። እኔም በተራዬ የአባቷን ቫርትኬስ ናልባንድያን "ባንዲራ ሳይኖረኝ እንዳልሞት" የተባለ መጽሐፍ ለማስተዋወቅ ስትጥር ስለረዳኃት በድጋሚ በፊትገፅ መዘውር አወጋን። የኤሊስ አባት ቫርትኬስ ናልባንድያን የታላቁ ሙዚቃ አቀናባሪ ናርሲስ ናልባድያን ልጅ እና የዳሰሳችን ሰበብ የሆነው መጽሐፍ ደራሲ ናቸው።

መጽሐፉ የሚጀምረው በታህሳሱ ግርግር ውጥንቅጥ ነው። በግርግሩ ምክንያት መላው የአርመን ቤተሰብ አራት ኪሎ በሚገኘው ቤታቸው መሽጓል። አልፎ አልፎ የሚሰማውን የጥይት ድምጽ ለመርሳት ቫዮሊን ይጫወታሉ። በግርግሩ ማግስት መፈንቅለ መንግስቱ ባይሳካም የንጉሡ ስልጣን በመነቃነቁ ነጭ በሙሉ ከመንግሥት መስሪያ ቤት ተባረረ። ከዚያን ቀን ጀምሮ እስከዛሬ መላው ቤተሰብ ዜግነት ይሰጠን እያለ እየተማጠነ ይገኛል። "እናንተ ዜግነት የምትጠይቁት መሬት ለማካበት ነው" በሚል ሰበብ ማንነት የተነጠቁት አርመኖች ሰቆቃቸው የሚጀምረው በ1915 በቱርክ በተፈጸመባቸው የዘር ማጥፋት ነው።

"Armenian Genocide, campaign of deportation and mass killing conducted against the Armenian subjects of the Ottoman Empire by the Young Turk government during World War I (1914–18). Armenians charge that the campaign was a deliberate attempt to destroy the Armenian people and, thus, an act of genocide. The Turkish government has resisted calls to recognize it as such, contending that, although atrocities took place, there was no official policy of extermination implemented against the Armenian people as a group."

*(Source Encyclopedia Britannica)*

አርመኖች በዘር ማጥፋቱ ምክንያት በመላው ዓለም ቢሰደዱም ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የጀመሩት ግን ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው። ቫርትኬስ የዚህን ስደት ውጤት እና የሀገር አልባነት ስሜት በመጽሐፋቸው መግቢያ ላይ ይገልጹታል።

"አንዲት የዕድሜ ባለጸጋ አርመን ከዚህ አለም በሞት ከመለየታቸው ከጥቂት ወራት በፊት የኢትዮጵያ ዜግነት እንዲሰጣቸው ለኢሚግሬሽን ቢሮ በድጋሚ አመለከቱ። መንቀሳቀስ እንኳን እንደተሳናቸው የታዘበው ጉዳዩ የሚመለከተው የቢሮ ኃላፊ በሁኔታው ተደንቆ፣ "እማማ ግን ይኸ ዜግነት ምን ያደርግሎታል?" ብሎ ቢጠይቃቸው "ባንዲራ ሳይኖረኝ እንዳልሞት ብዬ ነው ልጄ" ብለው መለሱለት። ጭው ባለ በሶሪያ በረሃ፣ በዴይር-ኤል-ዞር አጠገብ በዘር ማጥፋት ጭፍጨፋው እናት አባታቸውን አጥተው፣ እነርሱ በተአምር ተርፈው፣ በአንድ ስሙን በማያውቁት ሰው እርዳታ በሊባኖስ ውስጥ በሚገኝ የዕጓለ ማውታ ማሳደጊያ ማዕከል ውስጥ ተጥለው፣ በመጨረሻም በሙሽርነት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት እኚህ አረጋዊት ዕድሜያቸውን ሙሉ ዜግነት (ባንዲራ) አልባ ሆነው ኖረዋል። ሲሞኙት የኖሩትን ዜግነት በተሰጣቸው ጊዜ በፊታቸው ላይ ይታይ የነበረው የኩራትና የትምክህት ስሜት በምንም ዋጋ ሊተመን የሚችል አልነበረም። ከፋም

ለማም፣ ባንዲራቸውን በኢትዮጵያም፣ በአፍሪካም እጅግ ረቂቅ ትርጓሜ ተሰጥቶት የሚኖረውን የኢትዮጵያን ባንዲራ አገኙት" (ገጽ 1-2)

ጸሐፊው ቫርትኬስ በአባታቸው ጥላ ስር ያደጉ ብቻ ሳይሆን የአባታቸውን ቁጭትም ይጋራሉ። አባታቸው ያዘጋጁት "አፍሪካ" የተሰኘው ህብረ ዝማሬ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሰረት ለመሪዎች ሲቀርብ እርሳቸው እንዳይታዩ ተሸፍነው በምልክት ለሌላ ሃበሻ እንዲያሳዩ የተደረገው በዘረኝነት ምክንያት መሆኑን ያስረዳሉ። ንጉሱ ለአርመኖች ከለላ የሚሰጡት ምንም እንኳ ፎቶው ቢጠፋም ልጅ ኢያሱ እንዲወድቅ ያደረገውን ብቸኛ ፎቶ ያነሱት አርመናዊ ፎቶ አንሺ በመሆናቸው እንደነበርም ይነግሩናል። ቫርትኬስ ቆጵሮስ የሚገኘው ሚኞት የአርመኖች ትምህርት ቤት ለመማር ከሄዱበት ቀን ጀምሮ ወደ አ.አ ተመልሰው የቤተሰባቸውን ቢዝነስ እስከተረከቡበት ቀን ድረስ ባንዲራ አልባ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ተራ የዜግነት አገልግሎት ለማግኘት በኢትዮጵያ መንግስት ቢሮክራሲ የሚደርስባቸው እንግልት ሲያስከፋቸው እንደኖሩ በቀላሉ እንረዳለን። በኢሕ አዴግ ዘመን እንደውም አንዱ የቀበሌ ሠራተኛ መታወቂያቸው ላይ ብሔራቸውን አማራ ብሎ እንደሞላው እያዋዙ ይነግሩናል። በርግጥ የናልባንድያን ቤተሰብ ከሸገር እስከ ቢሾፍቱ መሬቶችን ገዝተው ቤቶችን ገንበተዋል። ስደት ቋሚ ቅርስ የመያዝ ጥቅምን ጨምሮባቸዋል።

የዚህ ድርሳን ዋንኛ ችግሩ ትርጉሙ ንባብ አደናቃፊ ከመሆኑ የተነሳ ራሳቸው ቫርትኬስ በአማርኛ የጻፉት እንጂ አማርኛ በሚችል ሰው የተተረጎመ አይመስልም። ይሁን እንጂ ለሀገራችን ሰፊ አገልግሎት የሰጡ ዋና ዋና አርመኖችን ማወቅ አስችሎናል። ዲክራን ኤቤያን (የአጤ ሚኒሊክ ዘውድ ሰሪ)፤ ሚናስ ኬርቤክያን( መሃንዲስ)፤ ሳርኪስ ቴርዚያን (የእንፋሎት ባቡር ሰሪ)፣ ባግዳሳሪያን( የሚኒሊክ ሳንቲም ያተሙ)፣ ቦያጂያን ቤተሰብ (የሀገሪቱ ከፍተኛ የነገስታት ፎቶ ክምችት ባለቤት)፣ እስክንድር ቦጎሲያን (ሰዓሊ) እና ወዘተ በሃገራችን የማይረሳ ውለታ የዋሉ ናቸው።አርመኖች ከአብዮቱ በኃላ ከአዲሳባ እስከ ቢሾፍቱ ያላቸው ትርፍ መሬት እና ቤት ተወረሰባቸው። እነ ናልባንዲያን የመረጡት የአራት ኪሎ ቤታቸውን በመሆኑ ቀይ ሽብርን በቅርበት ያውቁታል ብቻ ሳይሆን ሁለቱ ቮልስ መኪኖቻቸውን ደርጎች እንደልባቸው መጠቀም ብቻ ሳይሆን ገፋ ሲል እነሱንም እንደ ሹፌር

ያሰሯቸው ነበር። ቫርትኬስ በተለያዩ ንግድ ቢሰማሩም ከደርግ በኋላ በቆዳ ንግድ እና ማምረት ከመጠመዳቸው እና ካዩት መከራ የተነሳ ዘርፉን "ሰቀቀኔ" ብለውታል። ይሁን እንጂ በንግድ ብቻ ሳይሆን ለኦሮሚፋ ከላቲን ይልቅ የአርመን ፊደላት ይቀርባሉ በማለት የሰሩትን ምርምር ያጋሩናል። በበኩሌ ከራሳቸውን ግለ ታሪክ በፊት እንደ ከተማ ይፍሩ ልጆች የአባታቸውን ግለታሪክ ቢጽፉ የተሻለ ነበር። ቫርቲኬስ አሁን በአዲሳባ የአርመን ማህበረሰብ መሪ ሆነው በሰንበት እያስቀደሱ ይኖራሉ። ኤሊስ ደግሞ ከሀገር ውጪ አንዱ NGO ውስጥ ትሰራለች፤ የሕግ ፍልስፍና ማስተማሩን የተወችው ይመስለኛል።

Reviewer:- Think Ethiopia's Editor in chief.

## ምዕራፍ ሁለት

# የፈጠራ ጽሑፎች

*የመፅሐፉ ርዕስ:- ፀሀይ ከጨለማዬ ምን አለሽ*
*ደራሲ:- እሱባለው አበራ*
*ዘውግ:- ረዥም ልብወለድ*
*ገፅ ብዛት:- 254*

**ቀለም በቀንድ (በብልቃጥ) ሳለ ጨለማ ነው፤ በተፃፈ ጊዜ ግን ብርሀን ነው። ቀለም በቀንድ ሳለ ድዳ ነው፤ በተፃፈ ጊዜ ግን መላሰኛ ነው። ቀለም በቀንድ ሳለ ጭምት ነው፤ በተፃፈ ጊዜ ግን እንደሰከረነው። ሁሉንም ይለፈልፋል። ከዘነብ ኢትዮጵያዊ፣ መፅሀፈ ጨዋታ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ ከመፅሐፏ ማለፊያ እግረ መንገዳችንን ጨልፈን እነሆ በረከት...**

**ደራሲው ከዚህ በፊት ያልተሞከረ አዲስ " ማህሌታይ" በተባለ የድርሰት አፃፃፍ ስልት እንደፃፈው በመፅሀፍ ማሳረጊያ ላይ ይነግረናል።**

**ይህ መፅሀፍ በኢትዮጲያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ሶስት የዜማ ስልቶች ባህሪ በግዕዝ ወመቋሚያ፣ ዕዝል ወጸናጽል፣ አራራይ ወከበሮ በተወከሉ ሶስት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን በዋናነት ጦርነት፣ ቀቢፀ ተስፋ፣ ፀፀት፣ ህላዌ፣ ነፃፍቃድ፣ በጥልቀት ይዳስሳል። በመጀመሪያው ማለትም በግዕዝ ወመቋሚያ በተወከለው ክፍል ደራሲው የግዕዝን ዜማዊ ባህርይ በመመሰል በዚህኛው ክፍል ጠንካራና ጠጣር ፍልስፍናዎችን ትዝብቶችን በሶስተኛ ተራኪ መደብ ሁሉን አወቅ** (omniscient) **አንፃር ይተርክልናል።**

**በሰማይ አይታረስ ንጉስ አይከሰስ ዘመን ሁሉም ነገር ቀዝቃዛ ይመስላል። በስሜት ተካልበው ከደጃቸው ያኖሩት ባዕድ፣ ከመጡበት መንገድ የሚነፍሰው ንፋስ ከቀልብ ያልተረገጠ ዳናቸውን እያጠፋ መነሻ ቢስ አድርጓቸዋል፣ ከትላንት ሲያሻግሯቸው የነበሩ ድልድዮችን አፈራርሰው ዳግም በትውስታ እንዳይመለሱባቸው ሆነዋል፣ ትዝታቸው ደብዛው ጠፍቶ ድንገት ከየትም እንደመጡ፣ ግር በተሰኙ ህዝቦች የተመላች ከተማ፣ ማንም በማንአለብኝነት ህመምና ጉስቁልናውን ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ባላየ ባልሰማ የሚተላለፍባት በውል ያልተቃኘን የዘመን መልክ በዚህ ባልታወቀው ሶስተኛ መደብ ተራኪ ከየጓዳው መጋርጃውን እየገለጠ ትዝብቱን ያስቃኘናል። አበይት ከሆኑት**

የፍልስፍና ዘርፎች ዲበአካላዊ (metaphysical) የሆኑ ጥያቂዎችን እያነሳ ሲብሰለሰል እናገኘዋለን። ለምሳሌ በገፅ 31 ላይ እንዲህ ይላል።

"ይህ አለም ፈጣሪና መጋቢ አለውን? ወይስ የሰው ልጅ የመለኮት ስራ ሳይሆን ከአጽናፈ ዓለሙ ጋር ወደ መኾን የመጣ የዐቢይ ፍንዳታ ክስተት ውጤት ነው?አምላክ የሰውን ልጅ ፈጠረ ወይስ የሰው ልጅ አምላክን? በማለት የሰው ልጅ የህላዌን ወለፈንድነት (Absurdity) ለማምለጥ የሸሸገባት ድንኳኑን ህልው መሆን አለመሆኗን ተያያዥ ህልቆ መሳፍርት ጥያቄዎችን እያነሳ የሰውን ልጅ መሰረተ ሚስጥር ለመፍታት ሲበረብር ይታያል።"

## ነፃ ፍቃድ (free will)

በነፃ ፍቃድ (Free will) እና በተወስኖዋዊነት (determinism) ጽንሰ ሀሳብ በፍልስፍና፣ በሥነ መለኮት እና በስነልቦና ውስብስብና አከራካሪ ሲሆን በፍልስፍናው ዘርፍ ዲበአካላዊ (metaphysics) ላይ የተመሰረተው ነገረ ህላዌ (existentialism) ስር የሚዳሰስ እሳቤ ነው።

በነጻ ፍቃድ ላይ በርካታ ቁልፍ አመለካከቶች አሉ፡

**- ነፃ ፈቃድ:**

የሰው ልጅ ሙሉ በሙሉ በውጫዊ ሁኔታዎች ወይም አስቀድሞ የተወሰነ የክስተቶች ሰንሰለት ሳይወሰን በነፃነት ምርጫ እና ውሳኔ የማድረግ ፍቃድ አለው የሚለው አመለካከት።

**- ተወስኖአዊነትት (Determinism)**

የሰዎች ድርጊቶች እና ምርጫዎች ጨምሮ ሁሉም ክስተቶች የሚወሰኑት በቀደሙት ክስተቶች እና በተፈጥሮ ህግጋት ነው የሚለው አመለካከት ነው። ምርጫችን ከቁጥጥራችን ውጪ የሆኑ ነገሮች ውጤት ተደርጎ ስለሚወሰድ የነጻ ምርጫን እና የሞራል ሃላፊነትን ይፈታተናል። ሌላኛው...

**- ተኳሃኝነት (compatiblism)**

ነፃ ምርጫን እና ተወስኖአዊነትን ለማስታረቅ የሚሞክር የመካከለኛ ደረጃ እይታ ነው።

ታድያ በፀሀይ ከጨለማዬ ምን አለሽ መፅሐፍ ላይ ከተነሱት አያሌ ጭብጦች ውስጥ ነፃ ፍቃድ አንደኛው ነው በመፅሐፉ በገፅ (41) እንዲህ ሲል ይጠይቃል።

በምልዕተ ዓለሙ ውስጥ የሰው ልጆችን ዕድል ፈንታ የሚወስን ኃይል አለ? የተፃፈው ይፈፀም ዘንድ ግድ አይደለምን? ወይስ ነገረ ፍርቱና እና የአርባ ቀን ዕድልም ያረጀ ያፈጀ የአቅመቢሶች ተረት ነው? ይቀጥልናም...

በነፃ ፍቃድ መኖር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ የመሸከም ነገር በሰው ልጅ እጅ ላይ ብቻ እንዲወድቅ ይኾናል። ኋላፊነትን በመውሰድ ውስጥ ተጠያቂነት ይከተላል። ቀናው ሲፀድቅ፣ ስሁቱ ደግሞ በስጋውም በነፍሱም ይኮነናል።ነገር ግን በደግም፣ በክፉም ከሞት በኋላ እስከዘላለም የሚፀና ፍርድ ለመቀበል የአንድ ሰው እድሜና ህይወት በቂ ነው? ብሎ በገፅ 41 ነፃ ፍቃድ፣ እጣፈንታና የለት እንጀራ ብሎ በሰየማት ንዑስ ርዕስ ስር መብሰልሰሉን ይቀጥላል።

ሁለተኛው ክፍል በዕዝል ወፅናፅል ይወከላል። በዚህ ክፍል ተራኪው ከሶስተኛ መደብ ወደ አንደኛ መደብ ተራኪነት ሽግግር ያደርጋል።

## ሽግግር (transcend)

ይህ የተራኪውን የስብዕና ሽግግር በአንድ ግለሰብ አንፅሮተ አለም ምልከታ ከመነሻ ተነስቶ ወደምንምነት የሚሸጋገርበትን መስመር ተከትሎ የተራኪውን በልጅነት ያለውን የህላዌ አረዳድ (ከነገሮች ሁሉ መለኪያነት ማዕከላዊነት) ተነስቶ ቀስ በቀስ እየተገፈተረ ከጨዋታው ሜዳ እስከወጣበት የወጣትነት ጊዜው ያደረገውን የህይወት አረዳድ ሽግግር አስፍሯል። በህይወት ዘመናቸው በቅድስና ተመላለሱ ስለሚላቸው የተራኪው ስለ ካህኑ የማደጎ አባቱ እንዲህ ሲል ይመሰክራል።

“ጠባያቸውና ምግባራቸው ጠንካራ ነው። ከአለም ፍቃድ ራሳቸውን አግልለዋል። የንጽህናን ዝናር ታጥቀዋል።” (ገፅ 55)

ሆኖም ህይወት መልኳን እየቀየረች ጀንበር እያዘቀዘቀች ስትመጣ ቀስ በቀስ እምነቱ መፈረካከስ ተስፋውም መሟጠጥ ቢጀምርም በዚህ ክፍል ጭላንጭል ብርሀን ማየት የተሳነው አይመስልም።

- **ቀቢፀ ተስፋ**

በመፅሀፉ የሚዳሰሰው ሌላኛው ጭብጥ ቀቢፀ ተስፋ ነው። በህይወት መድከም እና ስለወደፊት ምስል ከሳች አንዳችም ነገር ማጣት ተስፋቢስነት ነው።

የሁላችንም የልብ ጓዳ ቢበረበር ቢያንስ ለአንድ ጊዜ በዚህ አይነት ስሜት ውስጥ አልፈናል።

- **ኢምንትነት**

በውጪው አለም ያለውን ትርምስ ሽሽት ወደ ውስጥ የሚደረግ ጉዞ እና በውስጣዊ አለም ከተንሰራፋው ጥልቅ እና አስፈሪ ጨለማ ጋር መፋጠጥ..0 በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ተራኪው ከመታዘብ እና ከመብሰክሰክ ያለፈ እዚህ ግባ የሚባል እንኳን ተሳትፎ እንደሌለው ሲረዳ የማይቀረውን የህይወት ስንክሳር ይጋፈጣል። ተራኪያችን በስተመጨረሻም የሰው ልጆች እድል ፈንታቸው በእጃቸው ላይ እንዳልሆነች ከእነሱ ቁጥጥር ውጪ መሆኑንና ሌሎች በነሱ ላይ አቅም እንዳላቸው ሲገልፅ እንዲህ ይላል።

“በድንገት ከእንስሳ በታች እንደሆንኩ እንዲሰማኝ ሊያደርጉኝ የሚችሉ ሰዎች ደጃፌን በየትኛውም ቅፅበት ቢያንኳኩ ላስቆማቸው አልችልም። ኢምንት ነኝ።” (ገፅ 109)

በመጨረሻም አራራት ወከበሮ የተወከለው የመፅሀፉ ሶስተኛ ክፍል ህልው በመሆናችን የማይቀርልን የህይወት ድለቃ ህማም ሲቃኝ፡-

- **ጦርነት**

ዛሬ እያለፍንበት ያለውን የህይወት ምስቅልቀል በትክክልም የዚህኛውን ዘመን ትውልድ ወካይ ተደርጎ የተገለፀው አንደኛ መደብ ተራኪ የጦርነትን አሰቃቂነት ይነግረናል። በዚህ ውስጥ እልፍ የተረሳ እና ችላ የተባሉ የግለሰብ ህይወቶች ሰሚ የሌላቸውን የጣር ድምፆችን ያወጣሉ። ለመኖርህ በህይወት

መገኘት ብቻ ዋስትና አይሆንም። በሌሎች ሀይልን የተጎናፀፉ ባለጡንቻዎች ለመኖርህ ማረጋገጫ ካልሰጡህ በስተቀር። ድንገት አንድ ጠዋት የጦር መሳሪያ ጥይት በቤትህ ጣሪያ አናት ላይ ሲርከፈከፍ ትነቃለህ። ገና ህይወትን በመጀመሪያክ ሰአት ይመጣና ለአላማዬ ተማገድልኝ የሚል ጉልበተኛ ደጅህን ይቆረቁራል፣ እጣፈንታህን ይወስንልህል። የዘመኔን ወጣት ምስቅልቅል ስነልቦናው፣ ፍርሀቱ፣ ተስፋ ቢስነቱ፣ የዛለ መንፈሱን ይወክላል። ህይወት ይሏት ፍዳ ተጭናበት አሳሩን ይበላል። ተራኪው በዚህኛው ክፍል የገፈቱ ቀማሽ ነው። ታድያ ይህ የማይሽር ጠባሳ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ ገና ከእናታቸው ማህፀን ብቅ እንኳን ላላሉት ለመፃዒ ትውልዶች እጣፈንታቸው ዛሬ እየተሰራላቸው እንዳልሆነ ማን ደፍሮ መናገር ይችላል?

## የ ያ ትውልድ

ከተማዋ ትታመሳቸች ብዙ ነገሮች መናድ ይጀምራሉ። ሀገሬው ሰማዩን ሲያርስ ንጉሱን ሲከስ ይውላል። ወጣቱ ያነገባትን ተስፋ ይዞ በስሜት እየተመራ በአንድ አቅጣጫ ብቻ የለኮሳት እሳት መልሳ ራሱን ትበላዋለች። አብዮት ልጆቿን በላች የተባለለት የ60ዎቹ ትውልድ ገፅታ ልብ ይሏል።

## ጥላ (shadow) ሲገፈፍ

አንድ ግለሰብ ለመካድ ወይም ለመጨቆን የሚሞክረውን ንቃተ ህሊና የሌለውን፣ የተጨቆነ እና ብዙውን ጊዜ የማይፈለጉትን የእራስ ገጽታዎችን ይወክላል።

የግል ጥላው ልንገነዘበው ወይም መጋፈጥ የማንፈልገውን የራሳችንን ማንነቶች ያቀፈ ነው። ለምሳሌ ተቀባይነት የሌላቸው ግፊቶች፣ ምኞቶች ወይም በማህበራዊ ደረጃ የማይፈለጉ ባህሪያት ወዘተረፈ... ጁንግ እንደሚለን እነዚህ ማንነቶች ባልተቀበልናቸውና በካድናቸው ቁጥር በኛ ላይ ሀይል እያገኙ እና ከቁጥጥራችን እየወጡ ተገቢ ወዳልሆኑ ድርጊቶችን እስከመፈፀም ሊያደርሰን ይችላል። ስለዚህ ጥላን ማቀናጀት የጁንግ የግለሰባዊነት ፅንሰ-ሀሳብ አስፈላጊ አካል ነው - የግል እድገት እና ራስን የማወቅ ሂደት። ጥላውን በመቀበል እና በማዋሃድ ግለሰቦች የበለጠ ሙሉ፣ ትክክለኛ እና በስነ-ልቦና የተዋሃዱ እንዲሆኑ ያስችላል። ይለናል።

ማህበረሰብ የተዋቀረበት ጠንካራ መሰረት መፈረካከስ ሲጀምር። ግለሰብ በደህና ጊዜ ሸሽጎ ያኖራት ነውሩ የሚፈራው እና የሚገዛለት ነገር ሲያጣ ከጓዳ ወጥቶ አደባባይ ላይ ርቃኑን ይቆማል። እንግዳ ማንነቶች ብቅ ብቅ ማለት ይጀምራሉ። ስርአት አልበኝነት፣ ስግብግብነት፣ ሌብነት፣ ጭካኔን የመሳሰሉ የሰው ልጅ አውሬያዊ ባህሪዎች ጥርሳቸው አግጥጠው መታየት ይጀምራሉ። ይህም ማህበረሳዊ መልክ ሲይዝ እኛን ይመስላል። መፅሀፏ ቆም ብለን እራሳችንን እንድናይ ትጋብዛለች።

### የሰፈሩ የተከበረ አድባር።

ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ትልቅ ቦታ የሚሰጠው እና ማንነቱን የመሰረተበት አንድ አይነኬ አይመረመሬ አድባር አለው። በወለፈንዴነት የምንመላለስባትን ህይወት ትርጉም የምትለብሰው በዚህ አድባር በኩል ነው። ይኸን አድባር የወከሉት ካህኑ የተራኪው የማደጎ አባት ናቸው።

### የቅድስና ምሳሌ እሳቸው ናቸው።

እሳቸው የሰፈሩ አድባር ናቸው፣ የማይናዱ የሚመስሉ የማህበረሰብ ዕሴት ናቸው፤ እልፎች የተመረኮዙመት ተሰባሪ የማይመስል ምርኩዝ ናቸው። በጊዜ ጉልበተኝነት ከዕለታት በአንዱ ቀን የዚህ አድባር መገለጫ እንደቅርፊት ከላዩ ላይ እየተገፈፈ ድራሹ ይጠፋል። የተጠለሉበት ቤት ምሰሶው የጊዜ ፈርጣማ ክንድ ሲያርፍበት ይዘማል። ከዕለታቶች በሌላኛው ቀን ደግሞ የጊዜ አውሎ ነፋስ ጣሪያውን ገንጥሎ መጠለያ አልባ ቤተኛ ያደርገናል። በመጨረሻም ማገሩ ይወድቃል። ያ ባለግርማ በምልአት የቆመ የሚመስለው ዋርካ ዳግመኛ እንዳንጠለለው ሆኖ ይፈርሳል። ድንገት በዙሪያችን ባዶነት ያረባል።

### የመጨረሻው መጀመሪያ ነጥብ

ይሄ መፅሀፍ ከፈጠራ ልቦለድነት ከፍ ያለ ኮርኳሪ፣ መተከዣ የሚሆኑ ጥልቅ ሀሳቦችን ይዳስሳል። ስነፅሁፋዊ ውበቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። ሁሉም ሊያነበው የሚገባ መፅሀፍ ነው። ይህን ውብ ድርሳን የሰጠንን እሱባለውን እጅ ነስተናል።

Reviewer:- Yodit Ammanuel is an associate editor at Think Ethiopia .

*ርእስ፡- ከደመና በላይ*
*ጸሐፊ፡- ጃርሶ ሞት ባይኖር ኪሩቤል*

ጃርሶ ሞትባይኖር ኪሩቤል ተወልዶ ያደገው እዚሁ አዲስ አበባ ቀበና አካባቢ ነው። በተለይም "አስኮ ጌታሁን" የተሰኘችው ስምንት አጫጭር ልብ ወለዶችን የያዘችው መፅሐፉ እጅግ ታዋቂ ናት። በቀድሞው አጠራሩ "የጀርመን ድምፅ ሬድዮ ጣቢያ" በአሁኑ "ዶቼ ቨለ ራዲዮ" ደግሞ፣ ከ1973 እስከ 1992 ድረስ 44 የአጫጭር ልብ ወለድ ታሪኮቹ በራሱ ተራኪነት ለአድማጮች ተላልፈዋል። ከነዚህ ውስጥ ስምንቱ እዚሁ መፅሐፉ ውስጥ ተካተዋል። "የአዲሳባ ልጆች"፣ "ስምንተኛ ዲ"፣ "ጆርዳን" እና የመሳሰሉት ናቸው።

በነገራችን ላይ ምትሃታዊ ስነፅሁፍ እና የአፃፃፍ ስልት የምናውቅ አይመስለኝም።ስለምትሃት በደረቁ መፃፍ እንደ ሃሪ ፖተር እና ናርኒያ መሰል ድርሳናት ተምኔታዊ ዓለም በመገንባት ሊከወን ቢችል እንኳ የአፃፃፍ ስልቱን ራሱን ምትሃታዊ ማድረግ ግን የተለየ ክህሎት ይጠይቃል። የጃርሶን አዲሱን ድርሳን ሲያነቡ ቃላቱ ራሳቸው ከወረቀቱ ላይ እየበረሩ ወደ ዓይንዎ ሲሰርፁ ሊታዘቡ ይችላሉ። የጃርሶ አጫጭር ተረኮች ውስጥ ያለው ገፀ ባህርይ በአውሮፓ የሚኖር ሰዓሊ እና ደራሲ ነው። የራሱን ስም በየታሪኮቹ ስንቅር ስለሚዶላቸው እውን ታሪክ ይሁን የልቡናው ውልደት ግራ ያጋባል፣ ምትሃትም አይደል? ለምሳሌ ከሳላሳ ዓመት በፊት ቀበና ወንዝ ስለሚያውቃቸው ሴት ሲያወራ አብረውት አንዱ አውሮፓ ቤተመጻሕፍት የተቀመጡ ይመስላሉ።

"በወጣትነት ዘመኔ፤ የስነ-ጽሑፍን አድማስ: እየቃኘሁ፤ በለጋ አዕምሮ፤ በጉጉ: መንፈስ፤ ህይወትን፣ "ልወቅሽ-ታውቂኝ"፤ እያልኩኝ: ስፍጨረጨር፤ ዙሪያዬ: ሁሉ፤ በግጥም: ውበት፣ በቃላት: ኃይል፤ ሊገለፅ: እንዲችል: ብዬ፤ ከሃሳብ፣ ከፊደል: ጋር: ስሟገት: ሳለሁ፤ እቤታችን: ከሚመጡት: የእናቴ: ወዳጆች: አንደኛዋ፤ ስሙኒም፣ ሽልንግም፣ የእህል: ዱቄቱንም፤ እንጀራውንም፤ አስቋጥራ: ከምትሸኛቸው: መሳኪን: አንደኛዋ: "እመት: ደስታ" ይሰኙ: ነበር። "እመት: ደስታን" አይቶ፤ ለሥዕል: የማይመኝ፣ ድም፣ ሰምቶ: "ምን: ይሆን: የህይወታቸው: አይነትና: ጠረን?" ብሎ: የማይመሰጥ:

ከያኒ: አይገኝም። እንዲሁ: ሲያዩዋቸው፤ ተመራመሩኝ፣ ፈልጉኝ፣ እሹኝ: የሚል: አይነት: ፊደል: ከላህያቸው: ይነበባል። እኔም: ሆዬ፤ እንኳን: ደርሰውብኝ፤ ፈልጌ፣ አስሼ፣ የምመራመር: አይነት: በለስ: በመሆኔ፤ "እመት-ደስታ" ብዬ: በመሰየም÷ ከግጥም: ወደ: ስድ: ጽሑፍ: ዓምድ: የተሻገርኩበትን፤ የመጀመሪያዬን: ተረክ በአፍላው: እድሜዬ: ጻፍኩኝ። ከረዥሙ: በአጭሩ፤ ቀበና: ወንዝ: ዳር፤ ሀኪም: ሜዳ: ከሚሰኘው: መንደር: በታች፤ ጭቃ: ምርግ፤ አንዲት: ክፍል: ቤት: ተዘግተው: የሚኖሩ፤ አፅመ-ርስታቸውን: ፍርደ-ገምድል: ዳኛ፣ በግፍና: በውሸት: ምስክሮች: ተነጥቀው፣ ራሳቸውን: የሳቱ፤ የተረፈች: ህይወታቸውን፤ ከጨለማ: ክፍላቸው፤ እሳቸው: እራሳቸው፣ አንዴ: ዳኛ፣ አንዴ: ጠበቃ፣ አንዴ: ከሳሽ፣ አንዴ: ተከሳሽ: በመምሰል: ተውኔት፤ የገዛ: ድምፃቸውን ሲያዳምጡ፤ ወፍ: ጪጪ: ጪጪ: የሚልላቸው:ሴት: ነበሩ።"

*ገፅ 102*

ዋናው ገፀባህርይ ጠልሰም ቢጤ የሆኑትን እና የመሀከለኛው ዘመን የቤተስኪያን ስዕሎችን በየአውሮፓ ከተማ የጥናት ጉባኤ እየተገኘ የሚመረምር ደብተራ ወይ ያፈረሰ ቄስ ይመስላል። ከእነዚህ ከተሞች ሆኖ በናፍቆት ወለድ ቁጭት ስለሀገሩ (ቀበና) ሲፅፍልን ግን ምታት ነገር በየመሃሉ እየከተተ ስልቱን ያለማምደናል። ቃላቶቹ ፍልስፍና ወለድ ስለሆኑም ጭምር ብዙ ያመራምራሉ።

"የእመት: ደስታን: ሕይወት: መርምሬ፤ ፅፌ: ያስነበብኳቸው ሁሉ፤ ለጊዜው: በጥልቁ: ነበር: መንፈሳቸው: የተነካው። የመሬትን፣ የርስትን: ነገር፤ ቁጣና: መከራ፣ ጣጣ፣ ግፍን: በደልን: አስታወሳቸው። ይህ: የሆነው፣ ሳይጋነን÷ ከ33፣ከ34: ዓመታት: በፊት ነበር። ጊዜ ተተክቶ፣ ሰባት: ባህር፣ ሦስት: ውቂያኖስ፣ 60 ወንዞች: አቋርጬ፤ ብዙ: የብስ: እግሬ: ረግጦ፣ ብዙ: ብዙ: ነገር፤ ሰው: እንደሆነው: ሆኜ፣ አይሆነው: ሆኜ፤ ዛሬ: እዚህ: አካል: ሰውነቴ: ካለበት: እንግሊዝ: ምድር፣ ሎንዶን፤ እንደገና: እመት: ደስታን: አገኘኋቸው። አብሮኝ: የኖረን፤ የልማድ፣ የአመል: ሙያ፤ እንደወትሮው: ሁሉ: ከአንድ: ቤተ-መጻሕፍት: ጥግ: ይገኙ፤ ስቸከችክ፤ እመት: ደስታ፤ በቀጥታ: ወደተቀመጥኩበት: መጥተው፤ ካልጠፉ: መቀመጫ፣ ካልጠበበ:

ቦታ፤ እየገፋፋኝ፤ ከመደርደሪያው: መጽሐፍ: ለማውጣት: ይታገላሉ። የጸሀፊ: አንጎል: አንዳንዴ፤ ያለፈ: ትውስታውን፤ የሌሊት: ህልሙንና የቀን: የእውኑን: ትእይንት: ስለሚያጠናግር፤ እራሴውኑ: መላልሼ: በመጠየቅ: "እውን: የማየውን: እመት: ደስታን: ነውን? ከሆነስ: እንዴት: ሳያረጁ? ደሞስ: ምንስ፣ ነፋስ: ቢነፍስ: ነው፤ ከቀበና: ወንዝ፣ ከስንት: ባህር: ባሻገር: ከሎንዶን: ምድር: ያሳረፋቸው? ደሞስ: ከ30: ዓመታት: በኋላ: እንደገና፤ ቦታ: እርስት: ብለው፤ ከእኔ: ጋር: መጋፋት: ምን: አመጣው?" እያልኩ: ስጠይቅ፤ እንኳን: የዘንድሮ: አቅለቢስ: ሰው፤ ድሮም: ቢሆን: ሰው: ይመሳሰላል: እና፤ "ድንገት: ተመሳስለውስ: ቢሆን? አማርኛ: ተናጋሪ: በግንባሩ: አይለይም። ፈረንጁም፣ አፍሪካውም፣ ጃማይካውም: የሚናገረው: ነው: ዛሬ....." እንዲህ: እንዲህ: እያልኩኝ: ሳሰለስል፤ ድንገት: ነጠቅ: ብለው: ከአጠገቤ: ሄዱ። አስቤ: ሳልጨርስ፤ ደሞ: ተመልሰው: መጡ፤ እና: ያልጠፋቸውን: መጽሐፍ: ፍለጋ፤ ከንቱ: ይባዝኑ: ጀመር።"

*ገፅ 103*

ጃርሶ ያለ ማብራሪያ የሚጥላቸው አባባሎች አሉት። ለአብነት "ዓለም የወደዳትን ጥሬ ከብስል ታላምን" የሚለውን ፈሊጥ እስካሁን እየተመራመርኩበት ነው፣ በብቃት ላብራራልኝ ወሮታውን እከፍላለሁ። ጃርሶ ከደራሲነቱ ባሻገርም ሠዓሊና የሙዚቃ ባለሙያ ነው። በልጅነቱ የካቶሊክ ኃይማኖት ተከታይ፣ በወጣትነቱ ኢ–ዓማኒ፣ ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ደግሞ የአይሁድ (Judaism) እምነትን የሚከተለው ጃርሶ፣ የሙዚቃ ሥራውን በአብዛኛው ለመንፈሳዊ ዓላማ እንደሚጠቀምበት ይናገራል።

"ከቶ: ምንድነው: ነገሩ? "ፊደለ:ፈጠረ: ነው። ፊደል:ፍጥረት:ነው። እና: አንድ: ናቸው" ብለው÷ መምህራችን: ጥንት: ያስተማሩኝ: ከአንጎሌ: ደወለ። የሰላሳ: አራት: አመቱ: ፊደል፤ ቀንና: ኮከብ: ቆጥረው: ተመልሰው: ወደእኔው: መጡብኝ: ይሆን?÷ ተነስቼ: ወደ: ውጭ: ወጣ ብዬ: አየር: ተቀብዬ: ስመለስ፤ የሉም። ከተቀመጥኩበት: ወንበር: : ሎሚ: አኑረዋል። ምንድነው: ብልሀቱ? ሎሚዋንም: የሀገርቤት: ሎሚ: እንደሆነች: ጠረኗ: ነገረኝ። እመት: ደስታ: እራሳቸው: ናቸው፣ ሎሚ: ከመዳፋቸው: አይጠፋም: ነበር፤ ትዝ: ይለኛል። እሳቸው: ናቸው! ደንቃራ: እንዳይሆን: ጠረጠርኩኝ።

ሎሚዋን: እያሻሸሁ: ሳሽታት: ተመልሰው: መጡ። ይግረምህ: ብለው፤ የባሰውን: ከጉልበቴ: ጋር: ይታሸሹ: ያዙ። ምኞታቸው: ግን: ያሮጊት: አልመስልህ: አለኝ። ከአካሄዳቸውም: የልጃገረድም: አይነት: ነገር: ይመስላል።

በቃላትኛ: ብልሀት: በጉልህ: "እመት: ደስታ" ብዬ: ጽፌ: ከፊት: ለፊቴ: አኖርኩት: ጽሑፉን: አንብበው፤ ድንገት: መልስ: ቢሰጡኝ።እንዳላየ: እየለዩ: መጽሐፍ: ፍለጋቸውን: ቀጠሉ። እንደ: ድብብቆሽ፣ ሳውቅዮሽ: እየተጨዋወትን: ሰአቱ: ገፋ። ፊቴን: ወደመስኮቱ: መለስ: ባደርግ፤ አንዲት: ዘለግ: ያለች፣ ፀጉረ: ረዥም: ወጣት: መጣችና፣ "እማማ: ደስታ: የት: ጠፍተው: ኖረዋል! እኛ: ላይ: ታች: ስንፈልግዎ። ይኸንን: ሎሚ: ለምን: ለሰው: ሰጡት?" በማለት: በአለንጋ: ጣቶቿ: ወደ: እኔ: ጠቆመች። አተኩረው: አዩኝና: "የእኔ: ሎሚ: አይደለም" አሏት። እንግሊዘኛቸው: የሀገሬው: ነዋሪ: ቃናና: ጥራት: አለው። አይ: ተመሳስሎ: ነው። ምን: እንዴት: ቢሆን፤ የቀበና: ወንዝ: ባልቴት፤ እመት-ደስታ: እንግሊዝ: ምድር: ደርሰው?! አይ: የማይመስል: ነገር: ነው።

"የእኔ: ወንድም: ሀበሻ: ነህ?" ብለው: ሲያናግሩኝ፤ እግሮቼ: ተሳሰሩ፣ ከንፈሬም: ቀረፈዱ። እንዴት፣ ምን፣ እንደምመልስ: ጠፋኝ። ጥቂት: አምጬ፣ "አዎን" የሚል: ቃል: ከውስጤ: ወጣ። ፈጠን: ብለው: ሄደው: ወንበር: አመጡና: ከአጠገቤ: ተቀመጡ። "እዚህ: ሰፈር: መሬት: ይመራሉ: ንግስቲቱ: የሚል: ጭምጭምታ: ሰምቼ: የመጣሁ: ሀገር: ጎብኚ: ነኝ። ምትረዳኝ ነገር: ቢኖር?" ከተጎናፀፉት: ወርቃማ: በፍታ: ስር: ከደረታቸው: ላይ: የተጎበጎበ የመሬት: መልከአ-ምድር: ንቅሳት: ነገር: ታየኝ። "እማማ: ደስታ: አይደሉም: እንዴ!" ስል: ብጮህ፤ "እኔስ: መሆኑን: ነኝ። አንተ: ማን: ትሰኛለህ?" አሉ: "እኔንማ: ሊያስታውሱኝ: አይችሉም። ዘመኑ: እሩቅ: ነው። በርስት: የተነሳ..." ብዬ: ሳልጨርስ፤ እጃቸውን: አንስተው:- "በቃ! በቃ! በቃ!÷ የመሬት: የርስትን: ነገር: አታንሳብኝ": አሉና: ጉንጬን: በስሱ: ዳሰስ: አድርገው: ሲሄዱ፤ ተከትዬ፣ "እንዴ! ምንድነው: ነገሩ!፤ ምን: የተባለ: ንፋስ: ነው: እዚህ: ያደረስዎት?" ስል: ጮህኩኝ። መሀረባቸውን: አውጥተው: ገፃቸውን: እየደባበሱ፣ "ርስት: ፍለጋ: ነው: ንፋስ: አይደለም" አሉና: በፈገግታ: "ደሞስ: ቢሆን: ሠማህ: ወይ: ወገኔ: ንፋስ: አበቦችን: ከማሳመም: ሌላ: ምን: ተግባር: አለው: ብለህ!" ብለውኝ: ተሰወሩ። ያንን: ምሽት፤

በቴሌቭዥንም፣ በራዲዮም፣ ከምስራቅ: የመጣ: ሀይለኛ: አብሎ: ንፋስ፤ እጅግ: ብዙ: የእንግሊዝ: ገጠሮችን: እንዳወከ፤ ከየአቅጣጫው: ተነገረ፣ ተሰማ።"

*ገፅ 104-105*

ጃርሶ ሞትባይኖር ኪሩቤል፣ ከኪነታዊ ሕይወቱ ውጪ ፖለቲከኛም ነበር። ከ19 60ዎቹ መጀመሪያ እስከ 70ዎቹ አጋማሽ የኢሕአፓ አባል ሆኖ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርጓል። እንደምታውቁት ጠልሰም ምትሃታዊ የደብተራ ስዓል ክህሎት ቢሆን ጃርሶ ደግሞ አዲስ ጠልሰማዊ የስነፅሁፍ ዘርፍ አስጀምሯል። ይዘቱ ብቻ ሳይሆን የተፃፈበት ቋንቋ እና ክህሎት ራሱ ምትሃታዊ በመሆኑ አዲስ ዘርፍ ቢሆን ማጋነን አይሆንም። የተራቀቁ የአውሮፓ ከተሞችን የኑሮ ዘይቤ እና ታሪክ በዱሮ አማርኛ መተረክ መቻል በራሱ ምትሃትን ይጠይቃል።

እስቲ ከምትሃት ነክ ታሪኮቹ ሁለቱን ጀባ እንበላችሁ

## አንደኛ

". . .በማግስቱ ከየብርሌው የሚዋኘው የየኔታ ጭራ ንቃይ ለደንበኛው ሁሉ ሲታይ ጉድ እየተባለ ይወራ ጀመረ። ከጉሮሮአቸው ተጣብቆ በትንታ የሚረብሹ ደንበኞች ጩኸት ማሰማት ጀመሩ። “እንዴ! ወለላ ምንድነው ነገሩ? በሰንበሌጥ ይሁን ቃጫ አለቅን'ኮ! . . . ወለላ ሁለት ጠላ ጠማቂዎች በሽልንግ ቀጥረው ጋኑን፣ ደንበጃኑን፣ ማጣሪያውን፣ ነጠላውን ጥድት አስደረጉት። የየኔታ ጥሩነህ ጭራ ብናኝ ከወዴት እንደሚመጣ አልታወቀም። ከብርሌ ሁሉ ተሰግስጎ ይታይ ጀመር። . . . አቶ ታመነ ጠጋ ብሎ “ወለላዬ፣ የእኛ ሰው ለምን አይን ተፈጠረብህ ብሎ ነው የሚቀና። ለምን እርስዎ?” አላቸው። “የእጀ-ሰብ ፀላኢ የሚያውቁ ወዳጅ አሉኝ። ነገ ምሽት . . . ጠጅ-ሣርና አሪቲ ከቤቱ ነስንሰው የእጁን መደኅሚያ ቋጥረው ይጠብቁኝ” ብሏቸው ወጣ ። . . . በማግስቱ ይማሩ ጉንዶ እና ስልቻ ዙሪያውን እንደ ሲባጎ የየኔታ ጭራ ቋጥሮት ተገኘ። "

*የየኔታ ጥሩነህ ጭራ (ከገጽ 28 - 29)*

## ሁለተኛ

"እትዬ: ማሚቴ: ገብሬ፤ ዛር: ስላለባት: ሽቱ: ትጠጣለች። እትዬ: ማሚቴን: የሚያውቃት: ሁሉ: በሽቱ: ጠጪነትዋ: ያውቋታል። ጠረኗ: የባህር: ዕጣን: እና: ሉባንጃ: ነው። ሽቱ: ተቀብታ: አታውቅም። "የሰው: እንኳን: ሲሸተኝ: ትንፋሼ: ያበረክትብኛል" ትላለች። "ትንፋሼ" የምትለው: በቀን: የምትቆጥረው፥ ሃያ: አንድ: ሺህ: አንድ፥ የማይጨምር፣ የማይቀንስ: እስትንፋሷ ነው። እንደ: መጥፎ: ዐመል: አብሯት: የአረጀ: ልማድ: በመሆኑ: ስትቆጥረው: እንኳ: አያስታውቅባትም። ሁለት: አንጎል: የአላት: ይመስል: በአንደኛው: ሃሳብና: ንግግር: ስታካሂድ: በሌላኛው: ትንፋሿን: ትቆጥራለች። እትዬ: ማሚቴ: የሠፈራችን: ትዕንግርት: ነበረች።"

*የሊባኖስ ሽቱ (ገጽ 87)*

በተረፈ ጃርሶ ከሸገሯ የወግ እመቤት መዓዛ ብሩ ጋር ያደረገው ቃለምልልስ እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ Youtube ውስጥ ገብታችሁ እንድትሰሙት እንመክራለን። ይህን መጽሐፍ ለሕትመት እንዲበቃ ያደረጉትን ጋሽ ክብሩንም እጅግ እናመሰግናለን። በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ ደራሲው የጨረሳቸው እና በቅርቡ ለሕትመት የሚበቁ የረጅም ልቦለድ መጻሕፍት እንዳሉት ቢጠቅስም ይኸው ዓመታቱ እየነጎዱ ስለሆነ ቢፈጥን ይበጀዋል።

ክብረት ይስጥልን የቀበናው ጃርሶ ሞት ባይኖር!

The Reviewer is the managing editor of Think Ethiopia

*የመጽሐፉ ርዕስ፡- ሀገር ያጣ ሞት*
*ጸሐፊ፡- ሄኖክ በቀለ ለማ*

## መግቢያ

ሀገር ያጣ ሞት (2013) በሄኖክ በቀለ ለማ የተጻፈ ረጅም ልብ ወለድ ነው። ይህ ማለፊያ የድርሰት ሥራ የአንባቢን ነፍስ እንደ ሾተል የሚሸነትሩና የቆምንበትን እውነት የሚከልሱ ሆምጠጥ ያሉ ዐሳቦች (serious issues) በነጠረ ቋንቋ እና በውብ ገለጻ (description) የቀረቡበት ነው።

ሀገር ያጣ ሞት አንገብጋቢውን የሰው ልጅ ህላዌ የሚፈክር ልብ ወለድ ሲሆን በዘውጉ (genre) አስማተ ዓለም (magical realism) ብለን የምንጠራው ነው። አስማተ ዓለም ልብ ወለድ ከእውናዊ (realism) ልብ ወለድ የተለየ ነው። እውናዊ ልብ ወለድ ለክሱት ህላዌ ታማኝ (faithful) በመሆን በተለየ መልኩ በኅብረተሰብ ሡራሽበ የአኗኗ እርከን ወይም የመደብ ተዋረድ የታችኛዉን መደብ (low socitial class) በሚወክሉ ተርታ ሰዎች (ordinary people) ላይ በማተኮር የዕለት ተዕለት አኗኗራቸውን የሚያስቃኝ ነው (ኬኔዲ እና ጊኦያ፣ 2002)። በምድረ አሜሪካ የእዉናዊ የሥነ ጽሑፍ ንቅናቄ ዐቢይ አቀንቃኞቹ ሄነሪ ጀምስ እና ማርክ ትዌን ናቸዉ (ማክሚሼል፣ 1985)።

የእውናዊ ልብ ወለድን በተመለከተ ለመጀመሪያ ጊዜ የጻፈው ግሪካዊው ፈላስፋ አርስቶትል ነው። አርስቶትል ፖይቲክስ በተሰኘ ሥራው እንደሚነግረን፣ የኪነ ጥበብ ሥራ በገሀዱ ዓለም ያለ፣ የነበረ እና የሚኖር እውነታን በመዳሰስ ለአንባቢ ወይም ተመልካች መሬት የወረደ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል (አርስቶትል፣ 1920)።

ማጊ አን ቦዎርስ ማጂካል ሪያሊዝም በተሰኘ ሥራዋ ውስጥ እንደ ጻፈችው፣ የአስማተ ዓለም ልብ ወለድ ልዩ ጠባይ ተራኪ ህልውናን በተመለከተ አስማታዊ እና ገሀዳዊ አተያዮችን አንባቢ በእኩል ደረጃ እንዲቀበል መሳመኑ ነው (ቦዎርስ፣ 2004)። በተጨማሪም፣ አስማተ ዓለም ልብ ወለድ ከእውናዊ ልብ ወለድ የሚለይበት ልዩ ጠባዩ በተለየ መንገድ

አስማታዊ እና ገሀዳዊ የሆኑ ፍፁም ተቃራኒ ኩነቶችን በአንድ አጋምዶ በማቅረብ አንድ አዲስ አንጻር መፍጠሩ ነው (ቦዎርስ፣ 2004)። እንደ ቦዎርስ (2004) ገለጻ፣ በአስማተ ዓለም የኪነት ሥራዎች ውስጥ 'አስማት' ምስጢራዊነትን (mystery)፣ እንግዳ ኩነትን (extraordinary happening) ወይም ልዕለተፈጥሮን (the supernatural) የሚገልጽ አቻ ቃል ነው።

ሄኖክ የአስማተ ዓለምን የአተራረክ መንገድ (narrative mode) የተገበረዉ እንደ አድባሬተረትም እንደ አፈ.ታሪክም የተሰኘ ርዕስ በተሰጠዉ በልብ ወለዱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ትረካ ዉስጥ፣ በእግር በፈረስ ይፈልግሃል ሞት የተሰኘ ርዕስ በተሰጠዉ በልብ ወለዱ ሁለተኛ ምዕራፍ ትረካ ዉስጥ፣ ሳቃችን ራሱ የእንባችን አሽከር ናት የተሰኘ ርዕስ በተሰጠው በልብ ወለዱ አራተኛው ምዕራፍ ትረካ ውስጥ፣ ትዝታ እንደእንጀራ በትናንሽ ዓይኑ የተሰኘ ርዕስ በተሰጠው በልብ ወለዱ ዘጠነኛ ምዕራፍ ትረካ ውስጥ፣ ካፒታሊዝም ይፋፋምብን የተሰኘ ርዕስ በተሰጠው በልብ ወለዱ አሥረኛ ምዕራፍ ትረካ ውስጥ ነው። ደራሲው በሀገር ያጣ ሞት ውስጥ የፈጠረው ታሪክ አስማተ ዓለማዊ ቢሆንም ዋና አትኩሮቱ ተጨባጩ የሰው ልጅ ኑባሬ (concrete human existence) ነው።

ሄኖክ በሀገር ያጣ ሞት የሚግተን ደረቅ እውነት ምሬቱ የሚያንገሸግሽ ነው። ይህም፣ ድርሰቱ በቃናው መራራ እንዲሆን አድርጎታል። ይህ ሥራ ትልሙ የተዋጣለት ነው፣ የአንባቢን ልብ የሚሰቅል። ትረካው የተተረከው በሦስተኛ መደብ አዋቂ ኩሉ እና በአንደኛ መደብ የትረካ አኳያ ነው። የትረካው መቼት ሄላ-ገነት እና "ሀገር" ነው።

የሄኖክን ሀገር ያጣ ሞት በኪናዊ ደረጃዉ ከፍ ያለ ሥራ ሆኖ እንዲገኝ ካደረጉት ነገሮች መከከል አንዱ የተዋጣ የገጸባሕርይ አሳሳሉ ነው። ድርሰቱ ውስጥ የቀረቡ ገጸባሕርያት ሥነ ልቡና አሳሳል ግሩም ነው። እነዚህ ምናባዊ ገጸባሕርያት በገሀዱ ዓለም በሥጋ ተገልጠው አብረውን እንደሚኖሩ ሰዎች ልባችን ውስጥ ልዩ ሥፍራ ይዘው የሚኖሩ ናቸው። የመልከ የነፍስ ህመም ልባችን ዘልቆ የሚሰማ ነው። የፍቅር ቀዝቃዛነት ከትውስታችን ዶሴ የማይፋቅ ነው። የዱና ገራገርነት እንደ ዘበት እንዳንረሳት የሚያደርግ ነው። የደስታ ጌታ

የሞት ፍርሀት በአንባቢ አእምሮ ተመዝግቦ የሚኖር ነው። ዕድለ ጠማመውና ከርታታው ዕድሉ ቀና ትውስታችን ውስጥ ቤቱን ሠርቶ የሚኖር ነው። በድምፀ መረዋዉ አዝማሪ ሐዋዝ ላይ የተፈረደዉ ኢ-ርቱዕ (unjust) ፍርድ እያንገበገበን የሚኖር ነዉ። ሕይወት ፍቅርን ብላ የከፈለችው መስዋእትነት አጀብ ሲያስብለን የሚኖር ነው። ዕድለ ቢሱ ጤናዉ አንጀታችንን እያላወሰ ሲታወሰን የሚኖር ነው። የተስፋ ቢሱ ተስፋ አሰቃቂ አሟሟት ውስጣችንን እንደረበሸ የሚዘልቅ ነው። የደራሲው ሄኖክ በትዝታ ባዛኝነት አይረሴ ነው። በእዚህ ድርሰት ውስጥ የተሳሉ ገጸባሕርያት የየራሳቸውን ቀንበር ተሸክመው የሚውተረተሩ ናቸው። አንዱ የሌላው መከራ ፈታይም ነው።

ሀገር ያጣ ሞት ሄኖክ ሀገራችን ኢትዮጵያ ያለችበትን ወቅታዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ ያሳየበት ሥራ ነው። ወደድንም ጠላንም ሀገራችን እኛ ዜጎቿ ብሩህ ተስፋ ሰንቀን ልንኖርባት የማንሻ የግፍ ምድር ናት ይለናል ሄኖክ። ይህን ሐተታውን ከትላንት ጀምሮ የተከፈተ በር የተሰኘ ርዕስ በተሰጠዉ በልብ ወለዱ አምስተኛ ምዕራፍ ትረካ ዉስጥ የሚከተለውን ይነግረናል።

ሀገር ላይ መኖርና መበርከት የሚያሳስበው ማንም። አይደለም ሰው ቀርቶ እንሰሳቱም ከሞት በኋላ ያለውን ይናፍቃሉ። አህዮች ጠግበው እንዲናፉ በተሰማሩበት ሜዳ ጥርስ ይሳበራሉ።

“በጎች ጎመን በመገዝገዝ የዶለዶሙ ቢላዎችን ፈልገው ይታሻሉ። ከብቶች ሲታረዱ ነፍስ-ውጪ፣ ነፍስ-ግቢ አይንፈራገጡም። በደስታ ቆዳቸውን ይገፍፋሉ ወፎች እንቁላላቸውን ከጎጆ፟ቸው በእርግጫ ወደ መሬት ይፈጠፍጣሉ። እባቦች ሰርጡን፣ ድንጋይ ለድንጋይ መሹለክለክ ትተው የሰዎች እልፍኝ ውስጥ ይገኛሉ። እናታቸውን ብትቀዉራቸውም እስከምትደግማቸው አቀባብለው ይጠብቃሉ። በጀርባህ ጋለል ብትል ሰማይህ ላይ ራሱን የሚከሰክስ ኮከብ በሽ ነው።”

(ሄኖክ፣ 2013፡ ገጽ 103)

ከላይ የቀረበው የደራሲው ሐተታ ለሙግት የሚቀርብ ነው።

የሄኖክ ሀገር ያጣ ሞት ሕይወት ተንታኝ ልብ ወለድ ነው። ይህም ትንተና ሕይወትን ጠልቀን በውል እንድንረዳ ያደርገናል። በሕይወት እና በልብ ወለድ መሐል ያለው ቁርኝት ጥብቅ ነው። "ልብ ወለድ ሐይወትን መረዳት እንድንችል ይረዳናል፣ ሕይወትም ልብ ወለድን መረዳት እንድንችል ያግዘናል" (ሾልስ፣ ኮምሊ፣ ክላዉስ እና ሲልቨርማን፣ 1991)። ሄኖክ በሀገር ያጣ ሞት ውስጥ የዳሰሳቸው ሴማዎች (themes) በርካታ ናቸው። ይህ ኂሳዊ መጣጥፍ በተመረጡ ሦስት አንኳር ሴማዎች ያተኮረ ሲሆን እነሱም ሀላዌ፣ ዕጣ ፈንታ እና ሞት ናቸው።

**፩. ህላዌ**

ሕይወት ሄኖክ በሀገር ያጣ ሞት በጥልቀት የፈከረው አንኳር ርዕሰ ጉዳይ ነው። ሕይወት የሞት ተፃራሪው ፅንፍ ነው። ሕይወት ለሄኖክ በጊዜ ስፍር የተቀነበበ ተራ ቴአትር መተወን ነው። ታዲያ በሕይወት መድረክ ላይ የተተወነ ማለፊያም ሆነ መናኛ ቴአትር ዓላማው ቀይቶ በሞት የሚፈርስ ስለሆነ ፋይዳ ቢስ ነው። አፍራሹ ደግሞ ፈጣሪ ነው (ሄኖክ፣ 2013)። እንደ ሄኖክ አተያይ፣ የሕይወት የአዙሪት ጉዞ አታካች ነው። ለሄኖክ፣ ራስን የማጥፋት (suicide) አንዱ ዐቢይ መንስኤ ይህ መታከት ነው። ተስፋ ለእዚህ ሐተታ በዋቢነት የሚጠቀስ ገጸባሕርይ ነው። እጅና እግሯ የ'ሷ በሕልሜ 'ሚመጣዉ የተሰኘ ርዕስ በተሰጠዉ በልብ ወለዱ ዘጠነኛ ምዕራፍ ትረካ ዉስጥ በራሱ አንደበት የሚከተለውን ይነግረናል። ባለፈው ሳምንት ነበር ጨክኜ የሞትሁት። ጸሎተና ፍቅሯን ምድር ላይ አንከርፍፌ — ወይ ሳልቋጥር፤ ወይ ሳልፈታው። መላ ያላሉት ፍቅር ከሞት ወዲያም ተከትሎ እንደሚያስጨንቅ ማን ነገረኝ ታዲያ? መኖርና መተንፈስ መሃል ምን የሚያህል ልዩነት አለ? መሰንበትና መኖር ለምን አንደመንታ ያምታታሉ? እግዜር ራሱ መኖር ለታከተው መሹለኪያ ቀዳዳ ለምን አላበጀም? ሁላችንም መኖር እንደማያጓጓን ማወቅ እንዴት ይሳነዋል?

**"የሞት ፍርሀት?"**

"ሞትን እፈራዋለሁ? አ! አ! ይልቅ መረሳትን ነው የምፈራው። ነገ ውስጥ ዕድል ፈንታ ማጣትን ነው የምፈራው። ነገ የማልተነፍሰው አየር ይነፍሳል፤ ነገ "አበጀህ!" የማልለው "አጠፋህ!" የማልለው ንጉሥ ይነግሣል፤ ነገ

የማልጠለለው ዝናብ ይዘንባል፤ ነገ የማልሰማው ወሬ ሀገሩን ያዳርሳል። የምፈራው ይህንን ነው። የምፈራው መብነንን ነው። ነገ ተስፋ ማን እንደሆነ ትርጉም የማይሰጥበት ጊዜ ይመጣል። የምፈራው እርሱን ነው።”

‘ተቀበል ሐዋዝ!’
“እግዚሐር ሲፈጥረኝ መች አማከረኝ ... ሃሂ”
“ድገመው!”
“እግዚሐር ሲፈጥረኝ መች አማከረኝ ...”
...
“ሞትን መቼ ፈራሁ መኖር ግን ታከተኝ!”

ታዲያ የእኔን ሞት ምን ልዩ አደረገው? ማንስ ሲሞት ማንስ ሲለቀስለት አይደል የከረመው? ማንስ መሞቱን እርግጥ አድርጎ አሟሟቱን ሲመርጥ አይደል የሚከርመው? ... በፍቃዱ የሞተ ሁሉ አሟሟቱን መርጧል።”

*(ሄኖክ፣ 2013፡ ገጽ 163-164)*

## ፪. ዕጣ ፈንታ

ዕጣ ፈንታ ሌላኛው በሀገር ያጣ ሞት ውስጥ የተፈከረ ማዕከላዊ ሴማ ነው። ሄኖክ የዕጣ ፈንታ (fatalism) አስተምህሮ አራማጅ ደራሲ ነው። ዕጣ ፈንታ ዲበአካላዊ አስተምህሮ ሲሆን የግለሰቦች ድርጊያ እና ኹነት ነፃ ቢመስልም ቀድሞ የተወሰነባቸው ፍፃሜ በሕይወታቸው መፈፀሙ አይቀሬ ነው የሚል እሳቤን ይሰብካል (ሶሎሞን፣ ማርቲን እና ሂጊንስ 2012)። ለሄኖክ፣ የሰው ልጅ በሥልጣኑ ከዕጣ ፈንታው ወሰን ጋት ፈቀቅ ማለት የማይችል ፍጡር ነው። ይህን እምነቱን የድርሰት ሥራው ውስጥ በሳላቸው ገጸባሕርያቱ ሕይወት አማካኝነት አሳይቶናል። ዱና መፃኢ ዕጣዋ ቀድሞ መወሰኑን የምታምን ሴት ናት። ሳቃችን ራሱ የእንባችን አሽከር ናት የተሰኘ ርዕስ በተሰጠዉ በልብ ወለዱ አራተኛ ምዕራፍ ትረካ ዉስጥ በራሷ አንደበት የሚከተለውን ትነግረናለች፣

“ዕድል ፈንታ ይከተለኛል። በልጅነቴ ተተንብዮልኛል።”

*(ሄኖክ፣ 2013፡ ገጽ 89)*

ይህም እምነቷ ቀቢፀ ተስፋ ዓለሟ ላይ ቤቱን የሠራባት ሎሌ (passive) አድርጓታል። የዕጣ ፈንታዋ ተላሚ ማን እንደሆነ ግን አልነገረችንም። የዕድል ፈንታ እምነት ባለንበት እንድንረግጥ የሚያደርገን ትብታብ ነው። አክላ ከትላንት ጀምሮ የተከፈተ በር የተሰኘ ርዕስ በተሰጠዉ በልብ ወለዱ አምስተኛ ምዕራፍ ትረካ ዉስጥ የሚከተለውን ብላለች፡

*"ዱና ሐዋዝ ነኝ። በሰማይና በምድር መሃል በሀገር ሰው ፍቃድ የሚበጅ መጭ ያለ ታሪክ እስካለ ድረስ መራጭ አይጠፋም። ተመራጭና ምራጭ ጎዳናውን ማጣበቡ አይቀርም። እኔ መርጬ የ'ግዚሐር ቅሪ መሆኔን ግን አላስታውስም። ጠማማ ዕድሌና ሽፋፋ ዕጣፈንታዬ ናቸው አነፍንፈው የተከተሉኝ። ታዲያ ምን አቅም አለኝና "አትከተሉኝ" እላቸዋለሁ?"*

*(ሄኖክ፣ 2013፡ ገጽ 95)*

ሌላኛው ሰው የሚኖረው የተጻፈለትን ነው የሚለው እምነት አራማጅ ገጸባሕርይ በጊዜ የተመሰለው ሽማግሌ ነው። ይህ ገጸባሕርይ እያንዳነንዳችን የምንኖረው በውጫዊ ኃይል ተተልሞ ያበቃ ሕይወትን ነው ይለናል። ሽማግሌውም እንደ ዱና የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ ጸሐፊ ማን እንደሆነ ገልፆ አልነገረንም። ይህንንም ከላይ በተጠቀሰው ምዕራፍ ዉስጥ ከመልከ ጋር በሚየደርገው ምልልስ እንደሚከተለው ይነግረናል፡

"ከእዚህ ወዲህ ለሥልጡንነቴና ለዘመናይነቴ እንዴት ግድ ሊኖረኝ ይችላል? የማስበው ይህን ውርደቴን አንቀርቅቤ ከዚህ ዓለም ብን ብሎ ስለመጥፋት ብቻ ነበር።

እየተንደረደርሁ ሄጄ "ጊዜ" የተባለውን ሽማግሌ ክንድ አፈፍ አደረግሁት።

"ውሰደኝ ... ውሰደኝ ... የተወሰኑ ዓመታት ወደ ኋላ መልሰኝ ... አሁኑኑ ... አሁንን መኖር አልፈልግም! ውሰደኝ እባክህ! ሕይወቴ ላይ ማስተካከል ያሉብኝ ነገሮች አሉ!!"

"ዛሬን እንደማያውቅ ነው የምትኖረው ... ምን ይረባሃል?"

"ይሁን!"

"ብወስድህም የሠራኸውን ስሕተት ደግመህ ትኖረዋለህ ልጄ"

"አላደርገውም!"

"ከዕድል ፈንታው ማንም አያመልጥም!"

"ግድ የለህም! ከዚህ ቦታ አጥፋኝ ብቻ!!"

*(ሄኖክ፣ 2013፡ ገጽ 93-94)*

ከዱና እና ጊዜ ከተባለው ሽማግሌ ሌላ ዕድሉ ቀናም በዕጣ ፈንታ የሚያምን የሄኖክ ገጸባሕርይ ነው። ለዕድሉ የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ ጸሐፊ ማን እንደሆነ በግልፅ ይነግረናል፣ እሱም ፈጣሪ ነው። ይህ የእድሉን ቀና አተያይ የሥነ መለኮት ልኂቃን አርባ ቀን ዕድል (predestination) ብለው ይጠሩታል። እነዚህ ልኂቃን እንደሚነግሩን፣ የእያንዳንዳችን ድርጊያ እና በሁለንታ ውስጥ ያለ ሁሉም ኩነት በፈጣሪ የሚታወቅና በሥልጣኑ የተከወነ ነው (ሶሎሞን፣ ማርቲን እና ሂጊንስ 2012)።

እንደ ሄኖክ አተያይ፣ የሰው ልጅ የዕድል ፈንታ ሎሌ ከሆነ በግብሩ ተኮናኝ የሆነ ማንም የለም። ሁሉም ሰው ንፁህ (innocent) ነው።

### ፫. ሞት

ሞት በሄኖክ ሀገር ያጣ ሞት ውስጥ የተዳሰሰ ሦስተኛው ማዕከላዊ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ሞት የሰው ልጅ ፈፅሞ የማያመልጠው ዕጣው ነው። ለሄኖክ ሞት የሰው ልጅ ከፈታኙ (tragedy) ሕይወት እፎይ የሚልበት መልካም ዕድል ነው። ሄኖክ እንዲህ ጽፏል፣

"ሕይወት ተፈርዶብኛል። ሞቴ ናፍቆኛል"

*(ሄኖክ፣ 2013፡ ገጽ 52)*

ደራሲው በእግር በፈረስ ይፈልግሃል ሞት የተሰኘ ርዕስ በተሰጠው የልብ ወለዱ ሁለተኛ ምዕራፍ ውስጥ በቀረበው ስንት ስጦታ ነው ሕይወት የሚያህለው? የተሰኘ ንዑስ ርዕስ በተሰጠው ትረካ ውስጥ በቀረቡት ከሰውነት ወደ አማልክትነት በተለወጡት ደስታ ጌታ ሕይወት አማካኝነት ቁልጭ አድጎ

እንዳሳየን፣ ለሰው ልጅ ትልቁ እርግማን መዋቲነት (mortality) ሳይሆን ዘላለማዊነት (immortality) ነው።

በእርግጥ የሰው ልጅ መዋቲ ነው። መዋቲነት መልካም ፍርቱና ነው፤ ምድራዊ ኑሮን ለቀመሰ ሰው እንደ አማልክት ዘላለማዊ ሆኖ መዝለቅ እጅግ አታካች ነውና። ሄኖክ የሚከተለውን አትቷል፣ "መኖር ሰልችቶኛል። ሞቴን የት አገኘዋለሁ?" (ሄኖክ፣ 2013፡ገጽ 52)። እንደገናም፣ ሄኖክ ከንፈር ላይ ተኝቶ ጥርስ መሃል መንቃት የተሰኘ ርዕስ በተሰጠው የልብ ወለዱ ሦስተኛ ምዕራፍ ውስጥ ከላይ የተነሳውን ነጥብ ዳስሷል። ይህን ነጥብ የምትነግረን ፍቅር ስትሆን ሐተታዋም የሚከተለው ነው፡-

"ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ጎዳና የለውም። አንዳንዶች መንገዳቸው የተቃና ነው። ምንም ፈተናና መሰናክል የለውም። ሽር ብሎ መምጣት ሽር ብሎ መድረስ ብቻ ነው። የአንዳንዶች ደግሞ እሾህና አሜኬላ የሞላው ይሆንና ደምተው፣ ቆስለው ይደርሳሉ። እንደ እኔ አይነቶች ደግሞ አለን። ሰዎች የሚራመዱበትን መንገድ ባልጠና ትከሻችን ተሸክመን የምንኖር። እንደ ጥርብ ድንጋይና እንደ መረሬ አፈር ሳንሰስት የምንረገጥ። ለሰው "ሃይሎጋው ሽቦ", "አቧራው ጨሰ" የምንሰለቅ። ሰማይና ምድራችን ተጠቅልሎ ካልተወረወረ መከራችንና ኀዘናችን ማብቂያ የለውም። ዕንባችንና ስብራታችን ስፍር የለውም። የምንጠብቀው አፅናኝ መሢህ የለንም። "ነገ ይወጣል" ብለን ተስፋ የምናደርገው ብራ ቀን የለም። ሞቴን አፍጥነው ከማለት ውጪ የምንሳልለት ርእይና ትልም የለንም። ተግተን የምንንገሸገሸው ሀሞት እንጂ እየቆጠብን የምናጣጥመው ጥፍጥና የለንም። ሕይወት እንዲህ ሲሆን ሞት ተስፋ ይሆናል"

(ሄኖክ፣ 2013፡63)።

### ማጠቃለያ

ሀገር ያጣ ሞት ሄኖክ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የራሱን አሻራ ያሳረፈበት ሸጋ የፈጠራ ሥራ ነው። ይህ ድርሰት ያልተበረዘ፣ ያልተከለሰውን ቱባውን የባላገሩን ኢትዮጵያ ሕይወት የሚቃኝ በመሆኑ እኛን እኛን የሚሸት መሆን ችሏል። ድርሰቱ ደራሲው ለውጫዊ ዓለም ገጽታ (nature) እና ዉበት

(beauty) ***ያለውን ስሜተ ስሱነት*** (sensibility) ***ያስተዋልንበትም ነው። ፍልስፍናዊ ድርሰት የሆነው ሀገር ያጣ ሞት አይደፈሬው ፈጣሪ ላይ ጠንከር ያለ ተጠየቅ በማንሳት ረገድ ከሌሎች የድርሰት ሥራዎች ልቆ የሚገኝ ነው። ድርሰቱ ያላወሳው፣ ያልዳሰሰው የሕይወት አንግልም የለም። በእዚህ ሥራ ሕይወት ከነንፍጡ፣ ከነጉድፉ፣ ከነተቃርኖው ተፈክሯል። ድርሰቱ የሕይወት ዥንጉርጉር መልክ ባማረ ኪነት የቀረበበት መሆኑ ደግሞ ጥበባዊ ፋይዳውን ከፍ ያደርገዋል።***

**Reviewer:- Mekonen Defro has a Masters Degree in Philosophy and currently writes as guest art critic for the weekly Addis Admas magazine, he is also an associate editor for Think Ethiopia.**

*የመጽሐፉ ርዕስ፡- ስለ ትናንሽ አለላዎች*
*ደራሲ፡- ዮናስ አድማዉ*

# ስለ ትናንሽ አለላዎች፡ የሐበሻ ስንክሳር

## መግቢያ

ስለ ትናንሽ አለላዎች (2011) በዮናስ አድማዉ የተጻፈ ረጅም ልብ ወለድ ነዉ። ይህ የልብ ወለድ ድርሰት በአማርኛ ቋንቋ ከተጻፉ በጣት ከሚቆጠሩ ሸጋ የልብ ወለድ ሥራዎች መካከል አንዱ ነዉ።

ዮናስ በቋንቋ መራቀቅን የተካነ፣ በልብ ወለድ የሚፈላሰፍ በሳል ደራሲ ነዉ። በእዚህም ምክንያት ነዉ ስለ ትናንሽ አለላዎችን ጠጠር ያሉ ፍልስፍናዎች የተፈከሩበት ሥራ ሆኖ ያገኘነዉ። ፈላስፋ ልብ ወለድ ደራሲ የሚኖርበትን ማኅበረሰብ የጋርዮሽ ንፅረተ ዓለም መዋቅሮች (communal belief systems) የመንቀስ (criticizing) አልፎም የመናድ (deconstructing) ክህሎትን የታደለ ነዉ። ፍልስፍናዊ ልብ ወለድም በተነበበ ቁጥር አዲስ ትርጉምን የሚፈጥር ነዉ።

ዮናስ ተራ የሚመስሉ ጥቃቅን የሕይወት ገጾችንና ኹነቶችን በርቀትና በዝርዝር በሸጋ አተራረክ አጉልቶ በማቅረብ አንባቢ ጉዳዩን ልዩ አፅንኦት ሰጥቶ እንዲመለከተዉ የማድረግ ክህሎትን የታደለ ደራሲ ነዉ። በሕዉስታ (sensation) የምንቀዳዉን የነገሮችን ቀለም፣ ሽታ፣ ጣዕም፣ ድምፅ፣ ልስላሴና ሻካራነት እና ሙቀትና ቅዝቃዜ ዘርዝሮ መተረክ (detailed narration) የበሳል ደራሲ ሙያዊ ክህሎት ሚዛን ነዉ።

በዮናስ ስለ ትናንሽ አለላዎች ዉስጥ የተዳሰሱ ዋና ዋና ሴማዎች የጊዜ ህልፈት (change)፣ ፍቅር (love)፣ ሞት (death)፣ ባይተዋርነት (estrangement)፣ ትዝታ (reminiscence)፣ የሕይወት ወለፈንድነት (absurdity)፣ ወረት (faddism)፣ ክህደት (infidelity) እና ይሉኝታ (shame) ናቸዉ።

ይህ ኂሳዊ መጣጥፍ ከላይ በጠቀስሁት የዮናስ አድማዉ የልብ ወለድ ሥራ ዉስጥ ከተዳሰሱት አያሌ ጭብጦች መካከል ጥቂቶቹን መርጦ የሚዳስስ ነዉ። እነሱም የሕይወት ከንቱነት፣ የአርነት እና የወሳኛዊነት ተግዳሮት፣ የሐበሻ ማንነት እና ፍቅር ናቸዉ።

## ፩. ሕይወት ወለፈንድ ነዉ

ልክ እንደ ታዋቂዉ ደራሲ እና ፈላስፋ አልበርት ካሙ፣ ለዮናስ የሰዉ ልጅ አንገብጋቢዉ ጥያቄ የሕይወት ትርጉም ነዉ (ዮናስ፣ 2014)። ካሙም ዘ ሚዝ ኦፍ ሲሲፈስ በተሰኘ የፍልስፍና ሥራዉ እንደ ጻፈዉ፣ ተጨባጭነት ከሌላቸዉ ከንቱ ጥያቄዎች ይልቅ ፍልስፍና ቅድሚያ ሰጥቶ ሊመልስ የሚገባዉ ወሳኙ ፍልስፍናዊ ተግዳሮት ራስን መግደል ነዉ (ካሙ፣ 1955)። ራስን መግደል የፍልስፍና አንገብጋቢዉ ጥያቄ ከሆነዉ ከህልዉና ጥርጉም ጥያቄ ጋር የተሰናሰለ ነዉ።

ለዮናስ የሰዉ ልጅ ሕይወት ወለፈንድ (meaningless) ነዉ። የእዚህ የዮናስ እሳቤ ዐቢይ ምክንያቱ፣ የሰዉ ልጅ በሞት በቅፅበት እድሜ ትቢያ የሚሆን መዋቲ መሆኑ ነዉ። ለካሙ፣ ከሞት በተጨማሪ የሕይወት ከንቱነት ምንጩ በድግግሞሽ የተሞላዉ አታካቹ የሰዉ ልጅ ህላዌ ነዉ (ኮፕልስተን፣ 1994)። ዮናስ የሰዉ ልጅ በሕይወት ከንቱነትና በአታካች የዉሃ ቅዳ ዉሃ መልስ ኑረት ሰበብ ራሳችንን ከመግደል የሚታደጉን ብዙ ማባበያና መሸንገያ ተዉኔቶች አሉን ባይ ነዉ። በብዙ ጥበብ የተራቀቀዉ "አማልክቱ የሰዉ ልጅ" አይቀሬ ዕጣ ሞት የካበዉን ሁሉ በአንድ ጀንበር የሚንድ ከሆነ የህልዉና ትርጉም እንዴት ናላ የሚያዞር ጥያቄ አይሆን? ሰዉስ ጉያዉ ሸጉጦት በሚራመደዉ ሞት እንደ ጧት ጤዛ በቅፅበት እንደሚረግፍ እያወቀ እንዴት ብሎ በሕይወት ፍቅር ሊወድቅ ይችላል?

ዮናስ ሕይወት ወለፈንድ ነዉ ቢልም ራስን መግደልን ለእዚህ ተግዳሮት መፍትሄ አድርጎ አያዝም። በተመሳሳይ መልኩ ካሙም ራስን መግደልን አያበረታታም። ዮናስ ለከንቱነት ስሜት ተግዳሮት ግልፅ መፍትሄን ባይጠቁምም ካሙ ግን ከላይ በተጠቀሰዉ ሥራዉ መፍትሄዉን ጠቁሟል። በእዚህ ሥራዉ ካሙ እንደሚነግረን፣ የከንቱነት ስሜት መፍትሄዉ ራሱን

የወለፈንድነት ስሜትን በፀጋ ተቀብሎ (lucid recognition) እስከ ዕለተ ሞት መዝለቅ ነዉ።

### ፪. ሰዉ ትናንቱን ነዉ፡ አርነት እና ወሳኛዊነት

የአርነት እና የወሳኛዊነት ተግዳሮት በዮናስ ስለ ትናንሽ አለላዎች የተዳሰሰ ዐቢይ ዲበአካላዊ ርዕሰ ጉዳይ ነዉ። ዮናስ በእዚህ ሥራው እንደሚነግረን፣ ሰዉ ያለፈ ሕይወቱ ስንክሳር ሥሪት ነዉ። በሌላ አነጋገር፣ የዛሬ ሕይወታችን በትናንት ታሪካችን ግዞት ሥር የወደቀ ነዉ። ዮናስ ድርሰቱ መግቢያ ላይ የሚከተለዉን አስፍሯል፡

"ሰዉ ትናንቱን ነዉ። "ወሰን" የተባለዉ ኢትዮጵያዊ ጎረምሳ ከመወለዱ አስቀድሞ፣ ማለት መወለድን የሕይወት መጀመሪያ አጥቅ አድርገን — ሌላ ቀደምት አጥቅ ሊኖር እንደሚችልም ሳንዘነጋ፣ በሚፈጠሩ ተከታታይ የማህበራዊ ክንዋኔዎች መሰናሰል የተፈጠረ ስብዕና ነዉ። ቢሞት ምን ይሆናል? አናዉቅም። ሲኖር ግን ያለፈበት ልጅነቱን ይመስላል።"

*(ዮናስ፣ 2014፡ ገጽ 8)።*

ከላይ የቀረበው የዮናስ አተያይ አንድምታው እኛ እያንዳንዳችን በትናንት ሕይወታችን እግር ብረት የተጠፈርን ነን የሚል ነዉ። ይህ አይነቱ እሳቤ ለወሳኛዊነት (determinism) ቦታ ይሰጣል። እዉን ሰዉ የትናንቱ ሎሌ ነዉ? ፈረንሳዊዉ ኤግዚስቴንሻሊስት ፈላስፋ ዠን-ፖል ሳትረ በፍፁም አይደለም ይለናል። እንደ እሱ እሳቤ፣ ሰዉ ትናንቱን ነዉ የሚለዉ እሳቤ ለአርነት ቦታ የሌለዉ እሳቤ በመሆኑ የተወገዘ ነዉ። እንደ ሳትረ እሳቤ፣ ሰዉ ትናንት በገነባዉ ማንነቱ ላይ ስልጣን ያለዉ ፍጡር ነዉ (ሳትረ፣ 2018)። በሌላ አነጋገር፣ እኛ እያንዳንዳችን በራሳችን ላይ አቢዮት በማካሄድ የትናንት አሻራ ያረፈበት ማንነታችንን የማፍረስ ሥልጣን አለን። ይህን ሂደት ሳትረ ሽግግር (transcendence) ብሎ ይጠራዋል። ካሙ እንደ ሳትረ ሁሉ እያንዳንዱ ግለሰብ ዕጣ ፈንታዉን ለመወሰን ፍፁማዊ አርነትን የተጎናፀፈ ነዉ የሚል አቋም ያለዉ ፈላስፋ ነዉ (ተምኮ እና ሆፍ፣ 2001)።

ከላይ የዳሰስሁትን የሳትረ አተያይ ግብዝነትን (bad faith) የሚቃረን አተያይ ነዉ። ቡሽ ዠን-ፖል ሳትረ፡ ኪይ ኮንሰፕትስ በተሰኘዉ በስቴቨን

ቸርችል እና ጃክ ሬይኖልድስ አርትኦት በተደረገዉ ሥራ ዉስጥ በቀረበዉ ሰልፍ ሜኪንግ ኤንድ አሊኔሽን፡ ፍሮም ባድ ፌዝ ቱ ሪቮሉሽን በተሰኘዉ ሥራዉ እንዳብራራዉ፣ ግብዝነት የሰዉን ልጅ ነባራዊ ሐቆች አርነት (freedom) እና ዚቅ (facticity) በመካድ የሚገለጥ ተግባር ነዉ። አርነትን የተጎናፀፈዉ ግብ አልቦዉ (contingent) የሰዉ ልጅ ዓለም ዉስጥ እንደ ግዑዝ ባለበት ረግቶ እንዲዘልቅ ያልተፈጠረ፣ በተቃራኒዉ ራሱን እንዲቀርጽና ትልሙን እንዲቀይስ የተኮነነ መሆኑን በይሁንታ የሚቀበል ፍጡር ነዉ (ቡሽ፣ 2013)።

ሰዉ ያለፈ ሕይወቱ ስንክሳር ሥሪት ነዉ የሚለዉ የዮናስ እሳቤ በሃያኛዉ ክፍለ ዘመን የተነሳዉን የኦስትሪያዊዉን የሥነ ልቡና ሊቅ ሲግመንድ ፍሮይድ ፍካሬ ልቡና ነባቢ አእምሮ (Freud's psychoanalysis) የሚጋራ እሳቤ ነዉ፣ ምንም እንኳ በሳርተር በፅኑ ቢተችም። ለሳትረ ሰዉ የትናንቱ ዉጤት ነዉ የሚለዉ የዮናስ እና የፍሮይድ እሳቤ ግብዝነት ነዉ። በግብዝነት ዉስጥ የወደቀ ሰዉ በልዩ ልዩ ኃይሎች ቀድሞ የተበጀ ቋሚ ማንነት (fixed identity) አለኝ ብሎ የሚያስብ ነዉ (ሳትረ፣ 2018፤ በርናስኮኒ፣ 2006)። በተጨማሪም፣ ሮበርት ሲ. ሶሎሞን ፍሮም ራሽናሊዝም ቱ ኤግዚስቴንሻሊዝም፡ ዘ ኤግዚስቴንሻሊስትስ ኤንድ ዜር ናይንቲንዝ ሴንቸሪ ባግራዉንድስ በተሰኘዉ ሥረዉ እንደ ጻፈዉ፣ ሳርተር ከሥነ ልቡናዊ ተወስኖሻዊነት (psychological determinism) ነባቢ አእምሮዎች (theories) ዉስጥ አንዱ የሆነዉን የፍሮይድን ፍካሬ ልቡና ነባቢ አእምሮ ሚዛን የሚደፉ ምክንያት አቅርቦ ፋርሽ ያደረገ ፈላስፋ ነዉ። ፍሮይድ ኢ-ንቁ ኅሊና በንቁ ኅሊና ላይ ይሰለጥናል ብሎ ያምናል። በመሆኑም፣ ነባቢ አእምሮዉ ለሰዉ ልጅ ነፃ ፈቃድ ቦታ የለዉም። በተቃራኒዉ፣ ለሳትረ፣ እያንዳንዳችን የቀደመ ታሪካችንን በሥልጣናችን የመሻር ኃይሉን የታደልን ነን (ሶሎሞን፣ 2001)። ለሳትረ፣ ሥነ ልቡናዊ ተወስኖሻዊነት ርትእ ባለመሆኑ በፅኑ የሚወገዝ አንዱ የግብዝነት መገለጫ ጠባይ ነዉ (ሳትረ፣ 2007)። ሮበርት ሲ. ሶሎሞን (2001) ከላይ በተጠቀሰዉ ሥራዉ እንደ ጻፈዉ፣ አንድ ግለሰብ በቀደመ ባሕርይዉ፣ በቀደመ ኹነቱ፣ በአካባቢዉ ተፅእኖ ታስሬያለሁ የሚል እምነት ከገነባ በግብዝነት ዉስጥ መዉደቁን

ያመላክታል። ለምን ቢባል፣ ያለፈ ስብዕናችን ነጋችንን የመወሰን ኃይል ስለሌለዉ።

ሳትረ ኢ-ንቁ ኅሊና (unconscious mental states) አለ የሚለዉን የፍሮይድ የፍካሬ ልቡና ነባቢ አእምሮ አይቀበልም። እንደ ሳትረ እሳቤ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ ጭቆናዉን (repression) በተመለከተ ደንበኛ ግንዛቤ አለዉ (ስቴቨንሰን እና ሐበርማን፣ 2009)። የሳትረ የግብዝነት ትወራ የኢ-ንቁ ኅሊናን ቅዠትነት የሚያስረግጥ ነባቢ አእምሮ ነዉ፣ ግብዝነት እዉነታዉን እያወቁ ራስን የመደለል ተግባር ስለሆነ።

## ፫. የሐበሻ ማንነት

ስለ ትናንሽ አለላዎች ደራሲዉ በመቅድሙ እንደገለፀዉ የሐበሻን ሕይወት ወርድና ቁመት በሳላቸዉ ገጸባሕርያት ዉክልና በጥልቀት የሚፈክር ስንክሳር ነዉ። ዮናስ እንደሚነግረን፣ ሐበሻ በአፉ በታሪኩና አባቶቹ ባጎናፀፉት ነፃነቱ የሚኮራ መሆኑን የሚደሰኩር፤ በገሀድ ግን ኅሊናዉ በፈረንጅ ባሕል ቅኝ የተገዛ ሎሌ ነዉ። ሐበሻ ድህነቱን ከአድማስ ማዶ ተሰዶ ሊያራግፍ የሚመኝ፣ በአፉ ሀገሬን እወዳለሁ የሚል፣ በገሀድ ግን እትብቱ የተቀበረበትን አፈር ሽሽት የባሕር ሲሳይ መሆንን የሚመርጥ የሩቅ ሀገር ናፋቂ ነዉ። ሐበሻ በድንቁርናዉ ሰበብ የሌላዉ ዓለም ህዝብ ጅራት የሆነ ህዝብ ነዉ። ድንቁርና ዮናስ ያክላል፣ የብሔራዊ ቁርቁዝናችን (poverty) እና ክሽፈታችን (collapse) ዋናዉ ምክንያት ነዉ። ሐበሻ አመፀኛ ነዉ፣ በሦስት ገመድ መሬት የወንድሙን ደም የሚያፈስ። ሐበሻ ወንድን አምላኪ ሴትን አኮሳሽ (sexist) ነዉ። ሐበሻ በተዉኔት መልካም ስሙን የሚገነባ ግብዝ ነዉ። ሐበሻ ቂመኛ ነዉ። ሐበሻ የሰዉ ሥጋ እርም የማይል ሐሜተኛ ነዉ።

## ፬. ፍቅር

ዮናስ እንደሚነግረን፣ ፍቅር የ"ሰዉነት" ልዩ መገለጫ ጠባይ (idiosyncratic essence of man) ነዉ። ይህ ለሰብአዊ ፍጥረታት የተቸረ ስሜት ሌሎች በሁለንታ ዉስጥ የሚገኙ ፍጥረታት ማለትም እንስሳት፣ እፅዋት እና አእዋፍት ፈፅመዉ የማያጣጥሙት ልዩ ስሜት ነዉ። የፍቅር ስሜት፣ ዮናስ ያክላል፣ ቅዱስ ስሜት ነዉ። ፍቅር እና ናፍቆት የአንድ

ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸዉ። እነዚህ ሰብአዊ ስሜቶች በሰዉ ልጅ ልብ ዉስጥ ቤታቸዉን ሰርተዉ ዘመናትን ተሻግረዉ የመጡ እፁብ ስሜቶች ናቸዉ።

## ፳. የትዉልድ ክሽፈት

ዮናስ በልብ ወለድ ሥራዉ ዉስጥ የሳለዉ ዋና ገጸባሕሪ ወሰን ጫኔ የተባለ ምሁር ወጣት ነዉ። ይህ ገጸባሕሪ ጭምት፣ አፍቅሮ ያመለካትን ሴት ከንፈር እንኳ ለመሳም ያልበቃ ዐይነ አፋር፣ ጥገኛ (dependant)፣ ሥራ ፈት (unemploy)፣ ባይተዋር (alienated) እና ምኩን (loser) ነዉ። ወሰን የድህረ ደርግ ትዉልድን የሚወክል ገጸባሕሪ ነዉ። ወሰን ለምን መከነ? የገጸባሕሪዉ ክሽፈት ሰበቡ የአገሪቱ ክሽፈት ነዉ። ደራሲዉ በገጸባሕርዩ ሕይወት ገልጦ የሚያስቃኘን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሀገሪቱ ነባራዊ አዉድ ደንቃራነት ወዲያ ወዲህ እንዳይፈናፈን የመጠፈሩንም ሐቅ ነዉ። እያንዳንዱ ደሃ ኢትዮጵያዊ በሀገሩ ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች እግር ብረት ተጠፍሮ በገባበት አረንቋ እንዲዳክር የተኮነነ ዜጋ ነዉ። ማምለጫ የለም። የአባቶቹ ገፈት ቀማሽ ነዉ። አባቶቹ የቀናች ሀገር አላወረሱትም። ዮናስ የሚከተለዉን ጽፏል፡

"የአለፉትን ሶስት አመታት ከአደገበት ቤት ወጥቶ ዩኒቨርሲቲ በጥሶ የእናቱ ጓዳ ሲመለስ የሰዉ ሀገር ሄዶ ያሳለፋቸዉ ሶስት አመታት፣ የጠቀለለዉ ድግሪና ያፈራቸዉ ጓደኞቹ እንደህልም ቀለም አልባ፣ እንደክረምት አግባ ከንቱ ሆኑበት። ሲሄድ ትልቅ ሻንጣ ይዞ ሲሸኝ ያስታዉሳል። በመሐል ብዙ የሚረቡም የማይረቡም ሰዎች እየሄዱ መጥተዋል። እንደሰመመን ያስታዉሳል። ቀጥሎ ጥቁር ካባና ቆብ አጥልቋል። ሊናገር ይፈልጋል – "የት ልንደርስ ነዉ እንዲህ የሚያጣድፉን?" ሊል ይፈልጋል ግን ቃላት ከአፉ አይወጡለትም። በቅጡ በማያዉቀዉ ትምህርት፣ በቅጡ በማያዉቀዉ አኳኋን ተመርቆ ሲወጣ ለክፉም ለደግም የማይነቃ በድን ሆነ።"

*(ዮናስ፣ 2014፡ ገጽ፣ 26)።*

ከላይ የቀረበዉ የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ የድህረ ደርግ ትዉልድ ራዕየ ቢስ የሆነበት ዐቢይ ሰበብ ነዉ። በግል ሩጫዉ የትም የማያደርሰዉ ከንቱ ድካም መሆኑን ያዉቃል። የርትእን መጓደል ጠቅሶ ቢያምፅ፣ አርነት መገፈፉን ቢጠይቅ የጥይት ሲሳይ እንደሚሆን፣ መከራና እንግልት እንደሚደርስበት ጠንቅቆ ያዉቃል። ታዲያ የእዚህ ትዉልድ ጭላጭ ተስፋ ምንድር ነዉ? የእዚህ ትዉልድ ብቸኛ ተስፋዉ ስደት ነዉ።

## ማጠቃለያ

የዮናስ ስለ ትናንሽ አለላዎች ይህ መጣጥፍ ያልዳሰሳቸዉ በርካታ የህልዉና ገፆችና አንኳር ጥያቄዎች (big questions) የተዳሰሱበት ኪናዊ ይዘቱ የላቀ ድርሳን ነዉ። ይህ ድርሰት ኋላ ላይ በተጻፉ በሌሎች ልብ ወለድ ደራሲያን ሥራዎች ላይ ተፅእኖ ማሳረፍ የቻለም ነው።

Reviewer: Mekonen Defro is a senior editor at Think Ethiopia

*Title: ወድቆ የተገኘ ሀገር*
*Author: Yiftusera Mitiku*
*Genre: Fiction*

This is a book about a young woman who went through hell because of the EthioEritrean war. Losing her father early on her childhood, she grew up in a small rural town with her beloved brother and mother. Her deep seated anguish begins as her brother is recruited to serve the Army, in fact he volunteered. Devastated with the news her mom starts to drift into an unknown state of mind which becomes even more exasperated as the brother returns from the war Shell Shocked. "shell shock," or what is now adays more commonly referred to as "post-traumatic stress disorder" (PTSD), is a complex and serious condition that can affect individuals who have experienced traumatic events, particularly those related to combat or warfare.Originally identified during and after World War I, "shell shock" was a term used to describe the psychological and emotional trauma experienced by soldiers exposed to the intense and relentless bombardment of artillery shells. The term "shell shock" specifically evokes the harrowing impact of the environment of war and the overwhelming psychological effects of constant artillery fire.

This condition can manifest in individuals who have undergone or witnessed traumatic events, such as military combat, natural disasters, violent assaults, or accidents. PTSD can lead to a range of symptoms, including flashbacks, nightmares, severe anxiety, and emotional detachment, among others, which can significantly impair a person's daily

functioning and well-being. The term "shell shock" conveys the profound disorientation, emotional turmoil, and psychological distress experienced by individuals subjected to the extreme stressors of wartime, highlighting the profound and enduring impact of such traumatic encounters on the human psyche. But, people who are near and dear to these persons also suffer an emotional anxiety at par or even worse than the original victims.

Masresha battles his PTSD after his return from the war, which leaves him and his mom in a series of miseries. His mother begs and implore every supernatural power known to her at the cost of becoming a witch herself. The narrator of the book is the sister and she tries so hard to find and rescue her brother as he suddenly disappears from their house, he seems to exhibit a severe dementia as he talks about the lamb he saved in the middle of one battle forgetting the entirety of the war. The lamb, I believe, represent his innocence. The sister becomes an elementary school teacher but she sadly and relentlessly search for him putting her own life on hold.

Yiftus book is small but her narration, choice of words and purpose leaves you breathless. The book illuminates how wars can rip apart not just nations but families in ways that cannot even begin to be described in human words.Even the title of the book **ወድቆ የተገኘ ሀገር** says a lot about the indifference of leaders as they start wars as they please thinking of their citizens as expendable pawns in a game of war. How many shell shocked men do we have in this country begining from the 1974 revolution upto the recent

ENDF/TDF war? It is my understanding that we live in a shell shocked country.

**The Reviewer: Dawit Bezabih is the managing Editor of Think Ethiopia**

*የመጽሐፉ ርዕስ፡- በተለይ አስራ አንደኛው*
*ጸሐፊ፡- ይፍቱሥራ ምትኩ*
*የገጽ ብዛት፡- 106*

በ106 ገፆችና በስምንት ርዕሶች የተከፋፈለ ኖቭሌት ቅርፅ ያለው መፅሀፍ ቢሆንም በውስጡ በያዘው ቀለማም መልከ ብዙ የህይወት ፈርጅ ድንቅ መፅሀፍ ያደርገዋል። በሰው ልጆች የእጣ ፈንታ ዳረጎት ላይ የተቋጠረች ህልውናን ባስመለከተ በሰፊው ለመዳሰስ የተነሳው ይህ የመፅሀፍ ጭብጥ በኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍ ውስጥ ሁሌም እንግዳ ሆኖ ከሚታየው lower class የማህበረሰብ ደረጃ ላይ ቆሞ ታንቲራ ይገጥማል።

በሌላ መልኩ የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ማህበረሰባዊ እሳቦት፣ የስነ ልቦና ዳር፣ የልቦና ውቅርና መሰል የተዘነጉ የሚመስሉ ግን መጋረጃው ቢገለጥ አፍጥጠው የሚገኙ እሴቶች ላይ ትኩረት አድርጓል።ገፀባህሪያቱ በተረካቸው የሚነኩት ነጥብና ቀዝቃዛ ስሜት አኗኗራቸው ካደረሰባቸው ጉስቁልና ጋር ተዳምሮ የመፅሀፉን መዳረሻ በቀዝቃዛ የስስ ስሜቶች ሙሌት እንዲታጀብ ሆኗል። እስኪ ለአመል መንሳፈፋችንን እናቁምና ከላይ የጠቀስኳቸውን ነጥቦች በጥልቀት ለመረዳት እያንዳንዱን ገፅ እንግለጥ....ተራኪያችን ማቲ ናት። ህፃን። በኖረችበት ቀዬ የረባ ስም የላትም። እናቷ ጥላት ስትሄድ ያገኘቻት አኬ የምትባል አሳዳጊዋ በምትጠራት ስም እንቀጥል..! አካላቴ ትላታለች አሳዳጊዋ። ካለ ህይወት መደላድል በወጣትነት የስሜት ትኩሳት ዘላ የገባች አንድ ሴት እንዳይሆን ሆነና አረገዘች። ያን ሲያውቅ ባሏ ጥሏት ጠፋ። እሷም ፈለጉን በመከተልና ራሷን ነፃ አድርጋ ከህይወት ጋር ለመታገል ስትል የሶስት ዓመት ሞሳ ልጇን የትም ጥላ ጠፋች። ተራኪያችን ከአሳዳጊዋ ጋር የምትገናኘው እንደዚህ ነው። መንደሯ ብዙ በሚናፈቁ አለላዎች የተሰራች ሌማት ትመስላለች። እድገቷንም በባይተዋርነት ጎዳና ላይ እየተረማመደች የሰፋችው ከዚሁ ዳርቻ ነበር። አንድ ቀን ከአቻዎቿ ጋር ሱዚ እየተጫወተች እያለ ያቺ የምትወዳት የሰር በሰዎች ተደግፋ ወደ ቀየዋ ስትገባ አየች። በአይኗ ያየችው ነገር ልቧን ብቻ ሳይሆን እሷንም በምህዋሩ ላይ ሰቅሎ ዝም አለ። ድንጋጤ ሲፈጠር የምድር ህግጋት ውላቸውን ይስታሉ መሰለኝ የመሬት ስበት ቀረ። ሽቅብ ሰማይ ጉና አየሩ ላይ ቀረች።...

## ጀበና!

በመፅሀፉ የመጀመሪያ ርዕስ ስር የምንመለከተው ታሪክ መልከ ብዙ ነው ለእኔ ጠቅላላ ታሪኮችን በአንድ እሽም አድርጎ ከመያዙም ባለፈ ለቀጣይ የጭብጥና የታሪክ ነገራ መንገድ ትንቢት የሚሆን ይመስለኛል። ህይወትን በአንዲት ጀበና የመሰራትና የማለቅ አፅናፍ የያዘ ስሁት ልቦለዳዊ እውነታ ነው።ይህ ጀበና በሚል ርዕስ ስም የነቃው ታሪክ በመኖር ቀለም ዳር Relative context የሚቃርመው የመሳሳብ ህጎችን እንዳፀና የሚገልፅ ጎሕ አለው። ቀደምት ሊቃውንቱ ሞት ሙትን ይስባል እንደሚሉት ደሀ ከደሀ ይሳሳባል። ሀብታም ከሀብታም ይዋደዳል። ይባላል። ገና በውልደት ጅማሮ ማህበረሰብ የውበት መለኪያውን የሰቀለበት ቆጥ ስር መልከ ጥፉነት active ሊያደርግ ከሚችልበት ውሎ ገፍቶ ያወጣል።

"....እናቴን አልመስል አባቴን....ኬት ወጥቼ እንደሁ፥ አባቴም ሁለት ሶስት'ዜ ማን ጎበኘሽ እያለ ታንቲራ ሲገጥማት ትዚ'ለኛል በልጅነቴ። ..."

ይህ ከባድ የስነ ልቦና ልምሻ ከመሆንም ባለፈ በscientific wey of biological knowledge ብንሄድ ሌላ ትርጉም ያለው የ Gene ግኝትና ስነ ተዋልዷዊ ጥያቄዎችን በብዙ ቤተሰቦች ላይ የሚፈጠር ጥያቄ ነው። በተለይ ልጇ እከሌን መስላለች በእከሌ ትወጣለች አይነት እምነት ላለው ማህበረሰብ... የሆነው ሆነና የሰር በመልከ ጥፉነቷ የተገፋች ሆነች። ፈላጊም ጠያቂም ጠፉ። አባቷ ቆማ ከምትቀር አለና ከአንድ ሽፍታ ጋር ሊድራት ተስማማ። ዳስ ተጣለ። ሰርጉ ተደገሰ። ቀየው ሞቅ ደመቅ እንዳለ መሸ። ሙሽራው ቢጠበቅ የውሃ ሽታ ሆነ። የሰዓቱ መግፋትና የሙሽራው መዘግየት ያሳሰባቸው ቢጠይቁ ተጋቢው በመንገድ ላይ እያለ ከሽፍታ ጋር ተታኩሶ መሞቱን ይሰማሉ። ደስታ ነው ያሉት በሀዘን ተቀየጠ። የነገ ተስፋዋ ከሰባራ እድል ጋር ተሰብሮ ቀረ።...በኋላ ላይ በሆነ አጋጣሚ የሰር ከነ አካላቴ ጋር ትገናኝና ጓሯቸው ጀበና መስራት ትጀምራለች። ለጀበና የሚሆን አፈር ለማምጣት አካላቴን አስከትላ ተራራ ትወጣለች።ትወርዳለች። እዚህ ጋ የተራራ ትርጉሙ ምንድነው? በዚህ ድርሰት ውል ውስጥ የተገለፀው መልከ ሰብዓዊ ህፀፆች የሰርንም ሆነ አኬን ከግሪኩ የአፈ-ታሪክ ንግርት ጋር የሚያመሳስለው ነገር የለም? ስብሐት ሲሲፈስ የሚወክለው የሰውን ልጅ እንጂ ሌላ አይደለም

ያለውስ እንዲሁ ዘበት ነው? ወደ የሰር ስንመለስሲሲፈስ ድንጋዩን እየገፋ ጫፍ አደረስኩ ሲል ይመለስበታል። ድንጋዩን ተከትሎ ወደ ንቃቃቱ ይሮጣል። ከዚያ ሽቅብ ወደ ላይ እየገፋ ይወጣል። አሁንም ይመለስበታል።ሲሲፈስ ተመላሹን ድንጋይ እየተከተለ ወደ ታች - እየገፋ ወደ ላይ የሚኖር የዘላለም ፍርደኛ ነው።የሰርን በዚህ የህይወት እሽክርክሪት ውስጥ ከተን ብንዳስሳት ይኸው ነች።የእምባ አለቷን በመግፋት ፈገግታ የሚናፍቃት ፍርደኛ። ከላይ እንደጠቀስኩት የእሷ የህይወት ዝቅታ የሚጀምረው ገና ከፍጥረቷ አንስቶ ነው። ማህበረሰብ የደነገገው የውበት ትርጉም መዝገብ ውስጥ ተፈልጋ ስትታጣ የእድሜ ዘመኗን እኩሌታ ለደስታ የራቀች ለሀዘን ወዳጅ የነበረች ሆና ለመቆየት ተገደደች። ያ ያመጣው መዘዝ የባል ችግር እንደየሎስ እንዲያንዣብብባት ሆነ። በስተመጨረሻም:

"ኋላ ሳድግ ' ይህቺ ልጅ ቆማ ቀረች ' ሲባል አባቴ ታንድ ሽፍታ ጋር ልጅህን ለልጀ ተባብሎልሁ መጣ። ሁለት የቸገራቸው ሲገናኙ....የሽፍታንስ ልጅ ተመልከ ጥፉ ውጭ ማን ያገባል?" መላ አካሌ ጆሮ ሆኖ ይሰማል።..

/ገፅ 18/

ዳስ ተጥሎ ሰርጉ ተደገሰ። ግን አልተሰረገም። የቤታቸው ከባቢ ደመቅ መቅ ብሎ ሙሽራውን ይናፍቅ ገባ።

ከዚያም! « ... እኩለ ሌት ሆነ ሲጠበቅ። ሙሽራው የውሃ ሽታ። '

እስቲ ወጣ በሉና 'እዩ' ተባለ ጨፋሪው...ግማሽ መንገድ እንደኸዱ ነዋሉ ' አከባቢው ሰላም አደለም' ..... 'ምንድነው? ' ቢሉ ' ሽፍታ ሰው ገሎ' ....እህ ቢሉ ሟቹ ሙሽራው።»

/ገፅ 19/

ተገፍቶ ላይ ወጥቶ የነበረው ድንጋይ ወደ ንቃቃቱ ተመለሰ። ሽፍታው ተስፋዋን ይዞባት የሄደ መሰለ። አኬ በአንድ ቦታ ተራኪያችንን አምሮትሽን በላሁ እንዳለቻት ሁሉ በሞቱ መርዶ የተስፋዋን ብስራት ቀበረ።ሁሉም በዜሮ ተባዛ። «እሜቴ የት ልደር...እካብ ላይ ብሰራ እባቡ መከራ..»ሆነ።ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደሙቀጫ።

ታሪከኛችን የሰር በተለምዶ ቀደምት የማህበረሰብ አተያይ ቡዳ እየተባለ የውርደት ስም በሚሰጠው ጫፍ የቆመ የሸክላ ስራ ባለሙያ ነች። ሊያውም ጀበና ሰሪ...በእድሷ ጥመት ሰርክ የምትብከነከነው የሰር የአምላኳን የእጅ ስራ ተምሳሌት ለምን ተከተለች? ሸክላ ሰሪስ ትሁን ሰርክ ከመቃጠል የማይድን ጀበናን ከመስራት የአበባ ማስቀመጫ ወይም ውሃ መቅጃ እንሰራ ለምን ምርጫዋ አልሆነም? በህይወት ላይ በቀለኝነቷን ማሳያ ነው? እሷ አንድ ጀበና ለመስራት ቅርጫት ተሸክማ ከረጢት ያዘለች ልጅ እግር አስከትላ ለአፈር ምርጫ ተራራ እንደወጣችው እግዜር እሷን ሲፈጥር ጥሩ አፈር ፍለጋ ይህን ያህል ደክሟል? ከአበባ ማስቀመጫ መሀል ምን ሲል ጀበና አድርጎ ፈጠራት?? ብዙ መጠይቃዊ መልኮችን በውስጡ የያዘ ስራ ነው። የእጣ ፈንታን መራር ገፅ ዘርግቶ ያስነበበን አትሮኖስም ጭምር ... ሌላው በዚሁ ዘውግ የሚታይ ሲሲፈሳዊ መልክን በጎሹ ሚስት ትረካ ውስጥ ይህን እናገኛለን።

**ቅቤ**

«««  »»» በዚህ ጥቅል ውስጥ የሚጠቀሱ ውህደታዊ የህይወት ዘለላዎች ያንኑ ያየነውን የሰው ልጅ ሲሲፈሳዊ የዘውትር ዙረት የሚያስረዱ ናቸው። ለአብነትም የጎሹ ሚስት በተደጋጋሚ በሚመታት ሾተላይ መታጀሏ አንዱ ማሳያ ነው።

ለህያው የሰው ልጅ ተስፋ ውስጥ ልጅ ምን ማለት እንደሆነ ማብራራት ትንሽ የሚቸግር ቢሆንም አገኘው ስትል ከእጇ እያመለጠ ገፍታ ጫፍ ላይ ያደረሰችው ውጥን የኋሊት ተመልሶ ሲያብከነክናት እንመለከታለን። ይህም በፈጠረው ስነ ልቦናዊ ጫና ለሁለት ዓመታት መላ ፍለጋ መባዘኗን እንዲህ ትገልጣለች።

“ኋላ እናቴ ተባሌ መከራ ወሰደችኝ፥ የሾተላይ አለ የተባለበት ሁሉ። ኑሮዋን ታትታ እንደቀልድ ሁለታ'መትጠበል አልቀረ! ተቆላ ተደጋ ተንከራተተች፥ ላይ ታች።”

*/ገፅ 52/*

ይህም መባከኗ በሰዋዊ ሀይል የማይቻል መጠየቋን ባህል በወለደው ልቦናዊ እውነት ሞግታ ቢቸግራት..

*"አሁን ፍቱን ተገኝቷል ትኽድ አሉ አንድ አዋቂ፥ ሩቃ'ገር ኸደን ያገኘናቸው። እናቴን ለብቻዋ ጠርተው እንደው ተዛ ደጋ አገር ብትወጣ...' ይሏታል፥ ምስጢሩን ሳያብራሩ። ዘበኑም እንደዛሬ አይደለም ያውቁታል መቸም፥ 'ለምን እንዴት' አይባል በስንት መከራ የተገኘ አዋቂ ሻንጣ ተሸርፎ በመኺና ኸር የለ ጨነቃት እናቴ። 'እንዴት ብዬ ተአምቻዎቼ እተያያለሁ?' ነው አንዱ ፍራቻዋ። የትም አይሄዱም' ያሉ እንደሁ የልጁ ትዳር እንዳይፈርስ። ታሪኬ መፍታት ማግባት ሆኖ መቅረቱ ላይቀር ሰቀቀኗ ያን'ዜ"*

*/ገፅ 52-53/*

ልክ በዓለማየሁ ገላጋይ ልቦለድ (ታለ) ውስጥ እንዳሉት የታለ እናት በቀን የፈለጉት እግዚሃር ዝም ሲል በጨለማ አዋቂ(ጠንቋይ) ቤት ትመላለሳለች። በዚያም ነገሩ ባይሰምርላት የአራስ ደሟን እያንጠፈጠፈች ሽቅብ ወደ ማሪያም ደብር ዞራ እንዲህ ትላለች።

*'አንቺማሪያም....አልኳት*

*"አንቺ ማሪያም እናትነትን እንደማታውቂ በኔ ጨከንሽ ምነው? ስለልጅሽ መንገብገብን ስለልጅ መታመምን እያወቅሽ?" አልኳት።*

*'በይ እንግዲ ስሚኝ ማሪያም፥ በማህጠኔ ደግመሽ ዘር እንዳታሳድሪ!' እንዳታሳድሪ!' አልኳት። የዲያ ይኸ አምባ ደሞ...ማሪያምን 'እመቤቴ፥ አዛኜቱ' ነው ስላት የኖርኩ እንግዲ።*

*ያን'ለት ግን እንደ'ኩያዬ 'አንቺ ማሪያም' አልኳት። እዝን ብዬ ነበራ። ቶሎ ቶሎ ልጨርስሎማ፥ መሸ እንዲሁ ተጎልተን፥ ብርዱ ሌላ ነው የዛሬው ደሞ...."*

*/ገፅ 55-56 /*

ማሪያም በዚህኛው አፅናፍ የተነሳችው እንዲሁ አይደለም። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮት ውስጥ ባላት ቦታ የአዛኝነት ልክ በመደረጓ (ከታሪክና ስነ ፅሁፋችን ..

-ግሸንማሪያም

- ፅዮን ማሪያም

- "ምነው እመብርሃን ኢትዮጵያን ጨከንሽባት!"

- ፀ.ገ.መ

- "ማሪያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም.."

*(አፄ ምኒሊክ 1888 የአድዋ አዋጅ)*

-አስመራ ማሪያም? (ስብሐት ገ/እግ/ር ከጥቂት ግጥሞቹ መሀል-ማስታወሻ .. ብዙ ብዙ... ወዘተ) አንድ በሞትና በህይወት መካከል ሆና ልጇን የተገላገለች ሴት ስትመረቅ "እንኳንማሪያም ማረችሽ ..ማሪያም በሽልም ታውጣሽ" ይባላል።

ይህቺ ኑሮ ግራ ጊዜ ግራ የሆነባት ሴት በደሏን የምታሰማውና ግጭት የምትፈጥረው ከእግዜር ጋር ሳይሆን ከማሪያም ጋር ነው።

አይነኬ (tabbo) ግጭትን ከቀደምት ቃላዊ ግጥም ተነስተን ብንፈትሽ ይሄኛው ትንሽ ይርቃል።ይለያል።

የ5,6,7ቱን በእሱ ፍቃድ ሮሮ የሚመስል እንስፍስፍ ጩኸት አለው።

"አንቺ ማሪያም እናትነትን እንደማታውቂ በኔ ጨከንሽ ምነው?"

በተለይ አስራ አንደኛው የልቦለድ መፅሀፍ ከስነ ፅሁፍ ንባብ አንፃር በተለይ ስነ ልቦናዊ ዳራዎችን፣ አዳዲስ ነገሮችን፣ የትረካ ጥበቦችንና በተለይ በተለይ ገፀባህሪያት አሳሳል ላይ አጠር አጠር አድርገን የምናያቸው ጎልህ ነጥቦች አሉን። አንዱን አስቀድመን እናስከትላቸው...

※ ስነ ልቦናዊ ዳራዎች

ያልተቆራረጡ ስነ ልቦናዊ ሀቲቶችን የሚጠቅስበት አንኳር ነጥብ ግጭቱን ከዲበ አካል (supre Nature) ጋር በማላተም ይጀምራል። ጊዜን የሚወቅሱ፣ ህግ አድርጎ በልቦናው ፅላት ላይ የገዘፉ ህጎችን የሚያንኮታኩቱ (ገፅ 68)፣ መፈጠራቸውን በእጣ ፋንታ ግፊት የሚረግሙ (ገፅ 18)፣ አይነኬውን በመንካት ካደረበት ዳስ ድረስ በመግባት የሚሞግቱ ድምፀቶች (ገፅ 56) ይደመጣሉ።

የግጭቱ ውጤት ውሳኔን ሲወልድ እንዲሁ ያሰረው ጊዜ ይፍታው ተብሎ ዝም ሲባል እንመለከታለን። ከጋራ ስነ ልቦናችን አንፃር ልመናችን በአንዱ አቅጣጫ ባይሰምር በሌላው ከመሞከር የምንሰንፍ አይመስለኝም። በተለይ በህይወት ላይ አብዮተኝነታችን ቀዝቅዞ ጠጠር ሲወረወርበት የማይበር ወፍ ካልሆንን በቀር…!

"ጣሪያ" በሚለው ርዕስ ውስጥ ልክ ቀደም ብለን "ቅቤ" በሚለው ርዕስ ስር እንዳየነው አገባብ ማቲዋ በጠበል አልሽር ስትል ሌላ የመዳኛ ስፍራና መፍትሔን እንዲህ ትጠቁማለች:-

"ትፍ ….ትፍ … ትፍ… ውሰዷት እዛው ተራራ ማዶ እየሱስ…"

"አይ አንቺ እየሱስ ሲባል …ማን አረገው የቤንጤ ብቻ እሱን እ?….ይሄ እጣን ባነሳችሁልኝ ለእኔስ …ታምር ነዋሉ ሚታይ እዛ…"

*/ገፅ 75/*

በተለይ በተለይ የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ሀገራዊ ስነ ልቦና በተለይም lower class ተብሎ ከሚመደበው መንደር በመውረድ ከእኛነታችን ጋር ሰርክ ከምናውቀው ቀለም ጋር ያዋሃደን ይመስለኛል። ሰዎች በጋርዮሽ ስርዓተ ማህበራቸው ውስጥ የሚወጡትን አቀበትና የወረዱበትን ቁልቁለት በቃል ድባብ ውስጥ ተነክሮ ሩቅ የሚወስድ ስራ ነው።

ሙሉ የመፅሀፉ ቁመና በአውዳመታዊ (የሰርክ) ወጎች መሞላቱ መፅሀፉ ለአንባቢው የሰጠው ቦታ ብዙ ነው። ረግቶ ያነበበ የሚገባው ነው። ገፀ ባህሪያቱንም በአንድ የሩቅ ዘመድ ጋር ከዓመታት በኋላ ተገናኝቶ እንደማውጋት ስሜት ያለው ስነዳዊ መንገዶች ይስተዋሉበታል። ለምሳሌ ጀበና ውስጥ የሰር ልታገባ ያለችው ሽፍታ ተገድሎ የሰርጓ መሰረዝ….በተለይ አስራ አንደኛው ስር አኬ የጎፋ ትዝታዋን የምታነሳበት ዳርቻ…ቅያስ ውስጥ የጎሹ ሚስት ስለልጅ እጦቷና የዓመታት መንከራተት ድርሳኗን የገለጠችብት ልክ ብዙ ብዙ..ከስነ ልቦና አንፃር የአንድ ስነ ጥበባዊ ጉዳይ መሄድ ያለበትን ልክ የሄደ እና አንጓዎቹን እንደቀልድ የፈተሸ ስራ እንደሆነ ይሰማኛል።

## ※ የትረካ ጥበብ

መፅሀፉ በብዛት ያልተለመደ የትረካ ጥበብን የተከተለ ይመስለኛል። በዜማና ትንፋሽ ተመጥነው በተሰሩ አረፍተ ነገሮችና ለታሪክ ነገራው ስሜት በሚሰጡ ቃላት የተሞሉ ናቸው። ቀለል ባለ ግን ደግሞ ውበት ባለው ሀረጎች የተወጋገሩም ጭምር...ምጥን ባሉ ገጠራዊ ቃና ሽልልል እያለች እንደምትሄድ ምንጭ ነው።

## ※ አዲስ ነገር

ነገረ ማቲን የተመለከተ የስነ ጥበብ ስራችን ውስጥ በተለይ በፊልም እና መፅሀፋችን ብዙ ስራዎች ቢኖሩም የተላበሱት ወንዳዊውን አለም እንጂ ሴታዊነት የለበትም። ወይም ሴት ልጅ ስትተርክ የሚያሳይ ስራ እምብዛም ነው። ጥቂት ከሚባሉት ውስጥ በአሪፍ ጅማሮ ነገረ ማቲን በሴት አለም ውስጥ ያየሁት በዚህ የልቦለድ መፅሀፍ ነው። ለዚህም ከሁሉ ከሁሉ ደራሲዋ ብትመሰገን አይበዛባትም።

## ※ገፀባህሪያት

=> ኮብላይ ናቸው - የረጋ መቼትና ሰፈር የላቸውም በሚያካልባቸው የህይወት ግፊት ልክ እንደ ጥንት የኢትዮጵያ ነገስታት ቋሚ ከተማ እንዳይኖራቸው አድርጓል። mobile capital city የሆነ መገለጫ የተላበሱ ናቸው። ለምሳሌ ከመፅሀፉ አንድ ቦታ የጎሹ ሚስት «እኔም ስደተኛ ሆንኩ። ጎጆ የማይወጣላት። ተባልኩ።» ትላለች። ሌላው አከላቴ ስትዳር ወደ ማታውቀው ሀገር መሰደዷ እና በተለይ በተለይ የሰር ከኖረችበት ቀየ ኮብልላ ወደነ አኬ መንደር መምጣቷ አመላካች ነው።

=> ጭምትና ህይወት በክፉ ክርኗ የደቆሰቻቸው ናቸው - በሀዘን ተሰብረው የሚቀሩ ሳይሆኑ ከገቡበት ችግር ለመውጣት በህይወታቸው የያዝዋትን አንድ አማራጭ እንኳን የሚሰዉ ናቸው ለምሳሌ። በ « ጣሪያ » ውስጥ መውለድ ያቃታት እናት በጠበልና በሌሎች ሀይማኖታዊ ስርዓት ነገሯ አልቀና ቢል በምሽት ወደ አዋቂ ቤት እስከመሄድ የተገደደችና በእሴት ደረጃ እምነት የሚባለውን dogmatic principal አፈር የሚያደርግ ውሳኔን ስትወስን እንመለከታለን።

በሌላም ቦታ በገፅ ላይ አካላቴ ታማ በጠበሉ አልሻላት ሲል እምነት ብትቀይርና ቸርች ቢፀለይላት እንደምትድን የሚመክር ጠያቂ እንደመጣባት ተመልክተናል።

እነዚህ የህይወትን መከራ፣ አሜን ብሎ ከመቀበል ይልቅ በእምቢተኝነት ድጋሚ ከዜሮ በመነሳት ለመጀመር መጣራቸው ከላይ ካየነው ሲሲፈሳዊ የሰው ልጅ ጠባይ ጋር የሰመረ ቁርኝት እንዳለው የሚያመላክቱ ናቸው። በቦታ ወሰን ተገድበው አይታዩ እንጂ ይህ አይነት የአኗኗር መንገድ በብዙሃኑ ጋር የሚታይ ቢሆንም በአንፃሩ ከቀሪው የማህበረሰብ ክፍል ጋር የሚያቃርንና መገፋትን የሚፈጥር ፈርጅ መሆኑም እሙን ነው። ሌላው ማህበራዊ መልክ ሰዎች በባህል ተገፍተውም ይሁን ውስጣቸው ባለው የጥርጣሬ ስሜት የሚቀሰቅስ (skeptic affecting) ሌላውን የማህበረሰብ ክፍል መገለል እንዲደርስበት ሊያደርጉ ይችላሉ።

ቡዳ ነው። በሚል የጥርጣሬ ስም ለብሰው የተገለሉ ገፀ ባህሪያት በዚህም መፅሀፍ ውስጥ ተገኝተዋል። አንዷ አከላቴ እንዳትሄድባት የሚነገራት የላይ ቤቷ ሴት ስትሆን ሁለተኛው ያኚ ፂማም ሽማግሌ ናቸው።ታዲያ ለሁለቱም የግዞታቸውን አርነት ያገኙ ያህል ነፃነታቸውን ስታውጅ የነበረችው አከላቴ ናት። ረጅም ዘመን አብሮ የኖረ አዋቂ ያልተረዳውን እውነት ፣ ትህትና እና ፍቅር በአንድ ጀምበር ከአንዲት የዋህ ህፃን ያገኙ ሽማግሌ ስሜታቸው ሌላ ሆኖ እንመለከታለን «ልንካዎት?» ነጭ የሚያምር ጢም አላቸው። ጠይም ሆነው ተአባቴም በጣም የሚያረጁ ይመስላሉ። ዓይን ለዓይን ተያየን። እምባ አቅርሯል አይናቸው። «የማነሽ መልዓክ ልጅ? ማነው ነጣ አውጭው ብሎ የላከሽ?» እምባቸው ወረደ። «አባቴ እንደርሶ ቆንጆ ነበረ።» አልኳቸው። «እሱ ሰው ሰውን አይበላም ብሎኛል። እላይ ቤት ያለችዋ ጎረቤታችንም ሰው እንደማትበላ አውቃለሁ።» እኔም እምባዬ መጣ። ሩጬ እቅፋቸው ውስጥ ገባሁ። «አልቴት አልቴት የምትሸች የኔ መልዓክ...»« ቡዳ እንዳይበላኝ ነውኮ።» «መች ጠፉኝ? ስም ይወጣል ተቤት ይከተላል ጎረቤት ሆኖ። እንግዲ ማን እንዳወጣልኝ ያላወቅኩት ስም አብሮኝ አረጀ ልጄ። መግቢያ መውጫ ባጣ 'አዋጅ' እል ጀመራ ቡድነቴ...» /ገፅ 67/ ከመንጋው እሳቦት የወጣች ብቸኛ የነፃነት ብርሃን..! ስለማህበራዊ መልክ ካነሳን አይቀር

እንደማህበረሰብ የምናውቃቸው አዘቦታዊ ብልጭታዎች ስር የሚመላለሱ የገፀ ባህሪያት ቅንበባ ከሁሉም ከሁሉ ለልቦለዱ የቋንቋና የስልት ጉዳይ ጥሩ ፍሰት እንዲኖረው የረዳው ያህል ይሰማኛል።

እዚህ ጋ አንባቢ ልብ ሊለው የሚገባው አንድ ነገር የገፀ ባህሪያቱ ግንባታ አዘቦታዊ ዘውግ ይልበስ እንጂ ለታሪክ መዋቅሩ የሚቀርቡት ተረኮች ማህበረሰቡን በወከሉት ነፍስ ውስጥ እንደትልቅ ገጠመኝ የሚታዩና ተቦክተው የተሰሩበት ቁም ነገር ነው። ይህም ከፍሰቱ ውጪ ለሰንሰለታዊ የልቦለዱ ቅርፅ ይህ ነው የማይባል ጉጉትን ፈጥሯል።

### እንደማጠቃለያ

የይፍቱ ስራ ምትኩ በተለይ አስራ አንደኛው ኖቮሌት ቅርፅ የልቦለድ መፅሀፍ በውስጡ ብዙ ደሳስ የሚሉ ያልተከላለሱ ያልተበራረዙ የትረካ ንጋቶችን ያሳየን ይመስለኛል። ብዙ ለሚባለው የአንባቢ ክፍል የጎላ አረዳድን የማይጠይቅ ቀለል ያለ የሀረግና የአረፍተ ነገር ምስረታን ያቀፈም ነው። መነሻና መድረሻውን በሰሜኑ የኢትዮጵያ ገጠራዊ ክፍል ያደረገ መቼት ቢኖረውም ደራሲዋ የተጠቀመቻቸው ወጎች ለታሪኩ ቀጥ ብሎ መጓዝ ውለታ ውሎላታል ብዬ አስባለሁ። በአጠቃላይ በቆንጆ ፍሰት ውስጥ የተወለደ ቆንጆ ስራ ነው።

....

**የመፅሀፉ ዳሰሳ አቅራቢ ሲራክ ወንድሙ በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ልዩ ልዩ መጣጥፍ በማቅረብ ይታወቃል። በቅርቡ ለረዥም ጊዜ የለፋበትን ስራ ለማሳትም እየተጋ ይገኛል።**

*የመጽሐፉ ርዕስ፡- ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ*
*ጸሐፊ፡- እሱባለዉ አበራ ንጉሤ*

**መግቢያ**

ይህ ኂሳዊ መጣጥፍ ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ (2012) በተሰኘ በእሱባለዉ አበራ ንጉሤ የተጻፈ ረጅም ልብ ወለድ ላይ ያተኮረ ነው። ይኸ ሥራ በርካታ ጠጣር የህልዉና ጉዳዮች በጥልቀት የተዳሰሱበት፣ የደራሲዉንም በሳልነት የመሰከረ ሸጋ ሥራ ነዉ። በእዚህ ሥራ እሱባለዉ በሥነጽሑፍ እና በፍልስፍና መካከል ያለዉ መስመር ቀጭን መሆኑን አሳይቷል።እሱባለዉ በይነቴክስታዊነት (intertextuality) (የአማርኛ ፍቺዉ የአቶ ቴዎድሮስ ገብሬ ነዉ) የተሰኘዉን የልብ ወለድ አጻጻፍ ይትባህሎች በሥራዉ ዉስጥ ተግባራዊ ያደረገ ደራሲ ነዉ። በይነቴክስታዊነት ከድህረ ዘመናዊ የልብወለድ አጻጻፍ ይትባህሎች መካከል አንዱ ነዉ። በይነቴክስታዊነት ቬርዶንክ (2002)፣ ካርተር (2006) እና ኒኮል (2009) እንደ ጻፉት፣ ቀድመዉ የተሠሩ የጥበብ ሥራዎችን በድርሰት ሥራ ዉስጥ ሰንጎ ማቅረብ ነዉ።

ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ በዘዉጉ አስማተ ዓለም (magical realism) ልብ ወለድ ነዉ። ይህ ሥራ ሕይወት የተባለ የሰዉ ልጅ መከራ (agony) በጥልቀት የተቃኘበት ድርሳን ሲሆን ኢ-ርቱዕ (nonlinearity) በሆነ የአተራረክ ዑደት የሚፈስ፣ በአንደኛ መደብ እና በሦስተኛ መደብ ሁሉን አወቅ የትረካ አንጻር የቀረበ ነዉ።

ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ በአማርኛ ቋንቋ ከተጻፉ በጣት ከሚቆጠሩ ፍልስፍናዊ ልብወለዶች (philosophical novels) መካከል አንዱ ነዉ። ደራሲዉ በእዚህ ሥራ ዉስጥ በጥልቀት የፈከራቸዉ ዐቢይ ጭብጦች ትዝታ፣ ወለፈንድ፣ ቀቢፀ ተስፋ፣ ወረት፣ የሕይወት ቋሚ ትርጉም አልባነት እና ፍቅር ሲሆኑ ይኸ ኂሳዊ መጣጥፍም በእነዚህ ጭብጦች ላይ ያተኮረ ነዉ።

## ፩.ትዝታ

የእሱባለዉ ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ከሌሎች የሀገራችን ደራሲያን የድርሰት ሥራዎች በተለየ የትዝታን (remaincence) ፅንሰ ሐሳብ በጥልቀት የመረመረ ሥራ ነዉ። እሱባለዉ እንደሚነግረን፣ ሰዉ ትናንቱን እየዘከረ እንዲኖርና እንዲናፍቅ ተኮንኗል። በመሆኑም፣ ትናንቱን መርሳት አይችልም (እሱባለዉ፣ 2012)። ትዝታ ትናንት ብለን የምንጠራዉ የጊዜ ምዕራፍ ነዉ። እንደ እሱባለዉ አተያይ፣ ትናንት ከዛሬ እኛ ቢርቅም ረጅም እጁን ሰዶ ሕይወታችንን የመዘወር ኃይል አለዉ። ትናንት ዛሬያችን ላይ የሚፈጥረዉ ተፅእኖ ኃያል ነዉ። ዘመን ሲያልፍ የኋሊት ይርቃል እንጂ አይሞትም፣ ህያዉ ነዉ። እሱባለዉ መለያየት ንውስ ርእስ እኮ ልብን እንዴት ይገስጿል? የተሰኘ ርዕስ በተሰጠዉ ትረካ ዉስጥ የሚከተለዉን ጽፏል፡-

"በሥራ አጋጣሚ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ የማዉቃትን ልጅ አገኘኋት። 'ኤል' ትባላለች። በልጅነት አፈቅራት ነበር። ሻይ ቡና ተባባልን። በጨዋታ በጨዋት ስናወራ 'ያኔ' የጻፍኩላት ደብዳቤዎች ዛሬም በቤቷ እንዳሉ ነገረችኝ። አልረሳችኝም። በእሷም ትላንትና ዛሬ ዉስጥ ዋጋ እንደተሰጠኝ በክብር አለሁ። የተጠፋፋነዉ ድንገት ነበር። አልፎ አልፎ ያለፈ ሕይወቴን በትዝታ ስበረብር ትላንቴ ዉስጥ ያልተመለሰች ጥያቄ ሆና የማገኛት እሷን ነዉ። 'ያ' ያላለቀ ፍቅር ይከነክነኝ ነበር። እና ጊዜ አልፎ 'ኤል'ን በአካል ሳገኛት 'አሁኔን' ጥያቄ ዉስጥ ከተትኩ። ትላንቴ ዉስጥ የነበረች አንዲት ትዝታ የተረጋጋ ዛሬዬን ትፈትነዋለች ብዬ አልጠበቅኩም ነበር። የጀመርኩት ግን ያልጨረስኩት የልጅነት ፍቅር ይጠራኛል። እንዴት ብዬ ልቤን መገሰጽ እችላለሁ? ኤል ምኞቴ ነበረች። ምኞቴን የመኖር ዕድል ሲገጥመኝ እንዴት ረግጬ አልፋለሁ?"

*(እሱባለዉ፣ 2012፣ ገጽ 107-108)።*

ትዝታ የሚወለደዉ ከቁስ እና ከሌሎች ሰዎች ጋር ካለን ጥብቅ ቁርኝት ነዉ። የትዝታ ድንገተኝነት እሱባለዉ እንደሚነግረን፣ ልክ እንደ ትንታ ነዉ። በመሆኑም፣ የትኛዉም ኩነት በየትኛዉም ጊዜና ቦታ ትዝታን ቀስቅሶ ትካዜ ዉስጥ ሊከተን አልያም በናፍቆት ሊያንሰፈስፈን ይችላል፣ መከሰቻ መንገዱ

ዉስብስብ ነዉ። እሱባለዉ ሕዋ ንዑስ ርእስ የጠፈር ባይተዋር የተሰኘ ርእስ በተሰጠዉ ትረካ ዉስጥ የሚከተለዉን ጽፏል፡-

*"የትዝታን ፈረስ በምን 'ቼ' ይሉታል? ወዲህ ወዲያ ሲዋልል የምናዉ አሮጌ በር 'ቼ' አያስብልም? ዝገቱና ንቅናቄዉ ከሕይወታችን አንዱ ሰበዝ ጋር በሆነ መንገድ ቢዛመድስ? የአሮጌ በር መቀርቀሪያ ... ማስታወስ ከማንፈልገዉ የክፉ ሰዉ ትዝታ ጋር ቢዛነቅስ? እንዲያዉ በባዶ ሜዳ 'እህህ' እያልን መቅረታችን አይደለምን? በዚህ ትዝታ ስንረታ ለስንተና ጊዜ ነዉ? በልጅነት የቀመስናቸዉ ኩርኩሞች በጉልምስናችን ሲታወሱን... መች ሳሳ ይላሉ? የትላንቱ ጥንካሬያቸዉ ዛሬም ባለበት አይደል?*

*ማንን በምን እናስታዉሳለን? የእንቅስቃሴዎች፣ የጠረኖች፣ የቀለማቶች፣ የድምፆች፣ የግዑዛን ቅርጾች ዉልብታ ጣፋጭ ወይም መራራ ትዝታን ይቀሰቅስብናል። ትዝታ ከየት እንደሚነሳ በዉል እንደማናዉቀዉ ነፋስ ነዉ። ሲደርስብን እንደ ስጥ እንበተናለን፣ እንተራመሳለን፣ እንረበሻለን። ለትዝታዎቻችን ያለን ስሜት እንደምናስታዉሰዉ ነገር ይወሰናል። ምናልባት እንፈግጋለን፣ እንኳሻለን፣ እንተክዛለን፣ እንናፍቃለን፣ እናለቅሳለን፣ እንቆጣለን፣ እንመረራለን። ያማረ ትላንት ለሌለዉ ሰዉ ትዝታ ምንድር ነዉ? የሚያጥወለዉል፣ እንቅልፍ የሚያሳጣ፣ ልብን የሚያከብድ፣ ጎዘን ላይ የሚጥል በሽታ አይደለምን?*

*(እሱባለዉ፣ 2012፣ ገጽ 13-14)*

ትዝታ ግለሰቦች ኩነቶችን የተረጎሙበትን ዉስብስብ መንገድ መሠረት ያደረገ በመሆኑ አሉታዊ ወይም አወንታዊ ገጠመኝ ሊሆን ይችላል። ለኩነቶች ያለን ሥነ ልቡናዊ አተያይ በአብዛኛዉ ግላዊ ነዉ።

**፪.ወለፈንድ**

**የህልዉና ወለፈንድነት** (the absurdity of human existence) **እሱባለዉ በትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ዉስጥ የዳሰሰዉ የአብዘርዲዝም ፍልስፍና ጭብጥ ነዉ። የወለፈንድን ጽንሰ ሐሳብ በጥልቀት በመፈከር በስፋት የሚታወቀዉ ፈረንሳዊዉ ፈላስፋ እና ደራሲ አልበርት ካሙ ነዉ። ካሙ እንደሚነግረን፣ ሕይወት ከንቱ ነዉ (ፖጅማን፣ 2006)። የህልዉና ከንቱነት**

ስሜት አንዱ መንስኤ በሰዉ ልጅ ፍላጎትና ለሰዉ ልጅ ፍላጎት መልስ አልባ በሆነዉ ደንታ ቢሱ ሁለንታ መካከል ያለ ግጭት ነዉ (ካሙ፣ 1955፤ ቤኔት፣ 2001፤ ፎለይ፣ 2008)። በተመሳሳይ እሱባለዉ እንደሚነግረን፣ ጨረቃና ከዋክብት ኀሊና ቢስና በዳ ፍጥረታት በመሆናቸዉ የሰዉን ልጅ ሐዘንና ደስታ አይጋሩም። ባዳዋ ጨረቃ የሰዉን ልጅ ዕንባ አታብስም፣ ባይተዋሮቹ ከዋክብት ጠፈር ላይ በመንቦግቦግ ፈንታ ጥልቅ ሐዘናችንን ተጋርተዉ ከል መምሰልን አያዉቁም። እሱባለዉ መዲናና ዘለሰኛ ንዑስ ርእስ እኔ መች መረጥኩኝ ለብቻዬ እንጉርጉሮ? የተሰኘ ርእስ በተሰጠዉ ትረካ ዉስጥ የሚከተለዉን ጽፏል፡-

"የነፍሴን ስርቅታ በጉያዬ ታቅፌ ኀብረ ሰማይ እመለከታለሁ። እንደ ጥቁር ግምጃ በተንጣለለዉ ሰማይ ላይ ከዋክብት ፈስሰዋል። በእኔና በከዋክብቱ መካከል በሚልየን የሚቆጠሩ የብርሃን ዓመታት ይዋልላሉ። የማያልቅ ሰማይ፣ ብትን ከዋክብት፣ ሽራፊ ጨረቃ ለከፋዉ ሰዉ ምንድር ናቸዉ? ማማር እንጂ ማሰብ በዉስጣቸዉ የለም። ከዋክብት የታከተን ገላ አያቅፉም። አመድ ለብሶ የተረሳን ከንፈር 'እፍፍ' ብለዉ ትቢያዉን አራግፈዉ በፍቅር አይስሙም። ዉስጡ በሐሳብ ስርዝ ድልዝ የተሞላን የራስ ጠጉር በጣቶቻቸዉ አያሻሹም። ደረቅ ሃቅ ነዉ - ጨረቃ አንጎል የላትም። ከከዋክብትም እንደ አንዱ አይደለሁም። ሕይወቴ ብርሃን የለዉም። ወደ ወስጤ ስመለከት ድቅድቅ ጨለማን አያለሁ። ያልታከተኝ ዉበት ምንድር ነዉ?"

*(እሱባለዉ፣ 2012፡ ገጽ 21)*

### ፫.ወረት

እሱባላዉ በትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ዉስጥ በጥልቀት ከዳሰሳቸዉ ጭብጦች መካከል አንዱ ወረት ነዉ። ወረት የጊዜ ህልፈት ወይም ለዉጥ ነዉ። በእዚህ ወሰን አልባ ሁለንታ ዉስጥ ያለ ነገር ሁሉ የለዉጥ ሕግ ተገዢ ነዉ። ሄራቅሊጠስ የተባለ የጥንት የግሪክ ፈላስፋ እንደሚነግረን፣ ሁሉም ነገር ኃላፊ ነዉ። በተመሳሳይ፣ እሱባለዉ በትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ዉስጥ እንደ ጻፈዉ፣ በእዚህ ተለዋጭ ዓለም ፀንቶ የሚዘልቅ ነገር የለም፣ ፍቅር ነጥፎ ጥላቻ ይነግሳል፣ ወዳጅነትም ይቀዘቅዛል፣ ዉበትም እንደ ጧት ጤዛ አመሻሽ ላይ ይረግፋል (እሱባለዉ፣ 2012)።

እሱባለዉ እንደሚነግረን፣ የሰዉ ልጅ በዕድሜዉ የከወነዉ እያንዳንዱ ተግባር በወረት እንዳልነበር ይሆናል። ጠዋት ባለፍንበት የሕይወት መንገድ ማታ ብናልፍ ከትዝታ በቀር በቦታዉ ያሳረፍነዉን ዳና አናገኝም። እሱባለዉ ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ንዑስ ርእስ መንገዳችን የተሰኘ ርእስ በተሰጠዉ ትረካ ዉስጥ የሚከተለዉን ጽፏል፡-

*"ኮቴያችን በድን መሬት ላይ ያርፋል። ዳናችን በነፋስ እየተጠረገ ከዐይን ይሠወራል። መንገዱን አቋርጠን እንዳልመጣን ያሳረፍነዉ አሻራ በዋዛ ይጠፋል። ጊዜ አልፎ እኛም እዚህ መንገድ ላይ አንድ ሰሞን ነበርን ብንል ማን ያምነናል? ጎዳናዉ ላይ ከነበርን ያሳረፍናቸዉ ዳናዎቻችን የታሉ? ከሌለንስ 'ያንን መንገድ' ሳናቋርጥ በምን ተአምር እዚህ እንዴት ደረስን? በምድር ላይ የማይጠፋ አሻራ ማሳረፍ ከባድ ነዉ። ተልከን ከሄድንበት ስንመጣ ከላኩን ሰዎች አፍ መሬት ላይ የተተፉት ምራቆች ደርቀዉ ይጠብቁናል። የምናገኘዉ ሽልማት የለም። ከመኖር የምናተርፈዉ ትዝታ ብቻ ነዉ። መንገዳችን እንደ ትዝታ ነዉ። አንዴ ብናልፈዉም አንረሳዉም። በትዉስታዎቻችን ምሪት ደጋግመን እንመላለስበታለን።"*

*(እሱባለዉ፣ 2012፡ ገጽ 88)*

እሱባለዉ ከላይ እንደነገረን፣ በእዚህ ዓለም ዉስጥ ያለ ነገር ሁሉ ተለዋጭ በመሆኑ ባለበት ፀንቶ የሚቆይ አንዳች ነገር የለም። ለእሱባለዉ ወረት ከሚሰለጥንባቸዉ ነገሮች አንዱ ፍቅር ነዉ። ደራሲዉ ይህን እሳቤዉን የሚያሳዬን ሥራዉ ዉስጥ በሳላቸዉ ገጸባሕሪያት 'ሰ' እና 'ዘ' ሕይወት ዉስጥ ነዉ። 'ሰ' እና 'ዘ' ባል እና ሚስት ሲሆኑ 'ዲ' የተባለች ሴት ልጅ ለመዉለድ ብቅተዋል። 'ዲ' 'ገ' የተባለዉ የልብ ወለዱ ዋና ገጸባሕርይ ፍቅረኛ ናት። እሱባለዉ መለያየት ንዑስ ርእስ እኮ ልብን እንዴት ይገስጿል? የተሰኘ ርእስ በተሰጠዉ ትረካ እንደሚነግረን፣ 'ሰ' እና 'ዘ' ፍቅር ያሞቀዉ ጎጆ ቸዉ በወረት ሳይፈታ በፊት ደስተኛ ሕይወት የነበራቸዉ ጥንዶች ነበሩ። ጊዜ ኃያል ነዉና የ'ዘ' ልብ ፍቅርን የማያፈልቅ ጭንጫ ሆነ፣ አቅፎት ያደረዉን የሚስቱን ዉብ ገላ ሰለቸ፣ ልቡም ሌላን ሰዉ አምልኮ ኮበለለ (እሱባለዉ፣ 2012)።

## ፬. የሕይወት ትርጉም ደራሲዉ ሰዉ ነዉ

እሱባለዉ የኤግዚስቴንሻሊዝም ፍልስፍና መሠረታዊ የህልዉና ጥያቄዎችን በልብ ወለድ ሥራዉ ዉስጥ የፈከረ ልብ ወለድ ደራሲ ነዉ። ደራሲዉ በልብ ወለድ ሥራዉ ዉስጥ አፅንኦት ሰጥቶ ከዳሰሳቸዉ የኤግዚስቴንሻሊዝም ዐቢይ ጥያቄዎች አንዱ ሕይወት በራሱ ቋሚ ትርጉም (intrinsic meaning) አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ጥያቄ ነዉ። እሱባለዉ በትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ እንደሚነግረን፣ ሕይወት በራሱ ቋሚ ትርጉም የለዉም። የሕይወት ትርጉም ደራሲዉ ሰዉ ነዉ። እሱባለዉ መዲናና ዘለሰኛ ንዑስ ርእስ እኔ መች መረጥኩኝ ለብቻዬ እንጉርጉሮ? የተሰኘ ርእስ በተሰጠዉ ትረካ ዉስጥ የሚከተለዉን ጽፏል፡-

"ሰዎች በሚያነቡት ምንባብ፣ በሚያዩት ቅርጽ፣ በሚያደምጡት ድምፀት ዉስጥ የማያቋርጥ የተርጉም ኀሰሳን ያደርጋሉ። ምክንያታዊነትን ይጠይቃሉ። ሕይወት ላይ ግን 'ለምን እንዲህ ሆነ? ለምንስ እንዲያ አልሆነም?' ብለን መጠየቅ አንችልም። ከአልተመለሱልን ጥያቄዎች ጋር እንኳዛለን። ምክንያቱም ምድር ላይ የያዝነዉ ሕይወት እንጂ ተዉኔት አይደለም። የተሰጠን ቃለ ተዉኔት የለም። ወደዚህ ምድር ስንመጣ የሕይወትን ትርጉም የያዘ ክታብ በአንገታችን አሥረን አልተወለድንም።"

*(እሱባለዉ፣ 2012፡ ገጽ 24-25)*

የሃያኛዉ ክፍለ ዘመን ታላቁ ፈላስፋ ዠን-ፖል ሳትረ ይህን የእሱባለዉ አተያይ ይጋራል። ሳርተር ኤግዚስቴንሻሊዝም ኢዝ ኤ ሂዩማኒዝም በተሰኘ የፍልስፍና ሥራዉ እንደሚነግረን፣ የሰዉ ልጅ ወደ መኖር ከመምጣቱ ቀድሞ የተበጀ የሕይወት ትርጉም የለም (ሳትረ፣ 2007)። ምክንያቱም፣ የሰዉ ልጅ ወደ መኖር መጥቶ ማንነቱን ከመፍጠሩ በፊት ምንም ነበርና (ሳትረ፣ 2007)። ለሳትረ፣ የሕይወት ትርጉም ፈጣሪዉ ህልዉናዉ ከንጥረ ባሕርይዉ ወይም ማንነቱ የሚቀድመዉ የሰዉ ልጅ ነዉ።

## ፭. ቀቢፀ ተስፋ

ቀቢፀ ተስፋ (despair) ከትዝታ፣ የሕይወት ወለፈንድነት፣ ወረት እና የሕይወት ቋሚ ትርጉም አልባነት በተጨማሪ በእሱባለዉ ትዝታሽን ለእኔ፣

ትዝታዬ ለአንቺ ዉስጥ የተዳሰሰ ጭብጥ ነዉ። እሱባለዉ ይህን ጭብጥ የዳሰሰዉ ሥራዉ ዉስጥ በሳለዉ 'ገ' በተባለ እንግዳ ገጸባሕሪ አማካኝነት ነዉ። ደራሲዉ እንደሚነግረን፣ 'ገ' ነፍሱ በቀቢፀ ተስፋ ሰማይ የተከበበ፣ ለሕይወትም ለሞትም ግድ የሌለዉ ጭምትና እጅግ ቀዝቃዛ ወጣት ነዉ፣ ገና በለጋ እድሜዉ የአገሩ ልጆች ከሐረጋቸዉ ባለመመዘዙ ጠልተዉት በካራ ወግተዉ የገደሉት። 'ገ' ሞትን እስኪናፍቅ ድረስ ጥልቅ ቀቢፀ ተስፋ ዉስጥ የወደቀዉ ሊኖርበት በማይፈልገዉ ዓለም ዉስጥ በመፈጠሩ ምክንያት ነዉ። እሱባለዉ ዘጠኝ ሞት ንዑስ ርእስ ሞት ሳይሞቱት ነዉ እሚለመድ? የተሰኘ ርእስ በተሰጠዉ ትረካ ዉስጥ የሚከተለዉን ጽፏል፡-

"ከተወለድኩበት ቀን አንስቶ በተሳሳተ ዓለም እንደ ተፈጠርኩ ይሰማኝ ነበር። የልጅነት ሕልሜ በወጣትነት መሞት ነበር። ጉርምስና አይቀርምና — በቀጠሮዉ መጣ። እኔ ግን ሳልሞት በሕይወት ቆየሁ። ለምን?"

*(እሱባለዉ፣ 2012፡ ገጽ 50)*

ገጸባሕርይዉ መኖር ኢምንት ትርጉም ካልሰጠዉ ለምን ታዲያ ራሱን አላጠፋም? ገጸባሕሪዉ እንደሚተርክልን፣ ለመሞት የነበረዉን ብርቱ ምኞት ከልቡናዉ ሰሌዳ ላይ እንዲፍቅ ያደረገችዉ በፈቃዱ ሊሞት ቀጠሮ በያዘበት ዕለት የተዋወቃት 'ዲ' የተባለች ሴት ናት። እሱባለዉ ጽድቅና ኩነኔ ንዑስ ርእስ መሆን አለመሆን የተሰኘ ርእስ በተሰጠዉ ትረካ ዉስጥ የሚከተለዉን ጽፏል፡-

"እናም ራሴን ላጠፋ በምችልበት አንድ ዉብ ምሽት ከ'ዲ' ጋር ተዋወቅኩኝ። ከሞት ያስቆመኝ ብቸኛ ምክንያት — ያ ነበር"

*(እሱባለዉ፣ 2012፡ ገጽ 64)*

አብዘርዲስቱ ፈላስፋ ካሙ እንደሚነግረን፣ ከፈቃድ ሞት የሚታደጉን ፍፁማዊና ዘላለማዊ መሆን የማያሻቸዉ ሌሎች የትርጉም ምንጮች አሉ። (ዊክ፣ 2003)

## ፮.ፍቅር

እሱባላዉ በትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ዉስጥ በጥልቀት የዳሰሰዉ ሌላኛዉ ጭብጥ ፍቅር ነዉ። ፍቅር እሱባለዉ እንደሚነግረን፣ ተመጦ እንደሚያልቅ ከረሜላ ያልቃል። በሌላ አነጋገር፣ ልባችን ለተንበረከከለት ሰዉ ያለን ፍቅር ጊዜዉን ጠብቆ ከልባችን ይነጥፋል። እሱባለዉ ወደድንም ጠላንም ይህን ደረቅ ሐቅ መሸሽ አንችልም ይለናል። ደራሲዉ በሥራዉ ዉስጥ እንዳሳዬን፣ 'ዘ' የተሰኘዉ ገጸባሕሪ የትዳር አጋሩን 'ሰ'ን የፈታዉ ለእሷ ያለዉ ፍቅር ከልቡ ተንጠፍጥፎ አልቆ ነዉ (እሱባለዉ፣ 2012)። ለመሆኑ ልባቸዉ እስኪ-ቃጠል ያፈቅሩን የነበሩ ሰዎች ለእኛ የነበራቸዉ የወትሮዉ ፍቅር ከልባቸዉ የሚነጥፍበት ዐቢይ ምክንያት ምንድር ነዉ? የእሱባለዉ ምላሽ ሌሎችን ከልክ በላይ ማፍቀር ነዉ የሚል ነዉ። ደራሲዉ የእሳት እራት ንዑስ ርእስ ራት እና መብራት የተሰኘ ርእስ በተሰጠዉ ትረካ ዉስጥ በሳላት በ'ዲ' አያት አማካኝነት እንደነገረን፣ 'ዘ' የልጁን እናት 'ሰ'ን ሰልችቶ ጀርባዉን ሊሰጣት የበቃዉ ከልክ በላይ ራሷን አሳልፋ በመስጠቷ ምክንያት ነዉ (እሱባለዉ፣ 2012)።

እሱባለዉ እንደነገረን፣ ከልክ በላይ ሌሎችን ማፍቀራችን ጀርባ የሚያሰጠን ከሆነ በምን መንገድ ፍቅር ዘላቂ ሊሆን ይችላል? እሱባለዉ እንደሚመልስልን በፍቅር የተጣመሩ ጥንዶችን ፍቅር ዘላቂ የሚያደርገዉ ሚዛናዊ ፍቅር ነዉ። ፍቅር ሚዛናዊ ከሆነ ሌሎችን ገሸሽ አድርገን ከልክ በላይ ራሳችንን አናፈቅርም፤ ራሳችንንም ራስተን ከልክ በላይ ሌሎችን አናፈቅርም። ሚዛናዊ ፍቅር በእሱባለዉ የፍቅር ፍልስፍና ዉስጥ ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠዉ ጉዳይ ነዉ። ይህ አይነቱ ፍቅር ከምንወደዉ ሰዉ ጋር እስከ መቃብር ያዘልቀናል። በተቃራኒዉ ከልክ በላይ ራስን ማፍቀርና ከልክ በላይ ሌላዉን ማፍቀር ያፈቅሩን የነበሩ ሰዎች ገሸሽ እንዲያደርጉን የሚጋብዙ፣ በእዚህም ሰበብ ፍቅርን የመሰለ ታላቅ ፀጋ ከሕይወታችን ስለሚሰልቡ ተቀባይነት የላቸዉም። እሱባለዉ ከላይ በተጠቀሰዉ ትረካ ሚከትለዉን ጽፏል፣

"ከራሳችን በላይ ሌላዉን ስንወድድ ራሳችንን እንበድላለን። በሕይወታችን ዉስጥ ላሉ ሌሎች ሰዎች ከትንሿ ልባችን ላይ ቆራርሰን የሰጠነዉ ስፍራ ብዙ ነዉ። ስለዚህም በእኛ ዓለም ዉስጥ ለእኛ የሚሆን ቦታ አጥተናል። በልባችን

የወደድነዉ ሌላዉን ሰዉ ብቻ እንጂ የገዛ ራሳችንን አይደለም። የገዛ ራሳችንን እንዴት መዉደድ እንዳለብን አናዉቅም። አልተማርንምም። ከሌሎች በላይ ራሳችንን አስበልጠን ስንወድድ ሌላዉን እንበድላለን። ራሳችንን ስንወድ ለሌላዉ ሰዉ የሚሆን ቦታ በልባችን አንተዉም። ስለዚህም በእኛ ዓለም ዉስጥ ሌሎች ሰዎች ስፍራ ያጣሉ። በልባችን አብዝተን የወደድነዉ ራሳችንን ብቻ እንጂ በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን ጭምር አይደለም። ሌሎችን ሰዎች እንዴት መዉደድ እንዳለብን አናዉቅም። አልተማርንም።”

*(እሱባለዉ፣ 2012፡ ገጽ 119)*

**ማጠቃለያ**

ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ጊዜ የማይሽራቸዉ በርካታ ህልዉናዊ ርእሰ ጉዳዮች በነጠረ ቋንቋ የቀረቡበት፣ በሥነ ዉበት ይዘታቸዉ ከላቁ የልብወለድ ሥራዎች መካከል አንዱ ሆኖ የሚጠቀስ ሥራ ነዉ። በተጨማሪም፣ ይህ ሥራ የሃያ አንደኛዉ ክፍል ዘመን የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እድገት አንድ እርምጃ ወደ ፊት መራመዱን ማስረገጫ አድርገን ከምንጠቅሳቸዉ ማለፊያ ሥራዎች መካከል አንዱ ነዉ።

Reviewer፡- **መኮንን ደፍሮ ልብ ወለድ ጸሐፊ፣ ገጣሚ እና የሥነጽሑፍ ኀያሲ ነው። የባችለር እና የማስተርስ ድግሪውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፍልስፍና አግኝቷል። በተማረው የሙያ መስክ በተለያዩ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ፍልስፍና አስተምሯል። ጸሐፊው ወደ ፊት ለህትመት የሚበቁ የተለያዩ የልብ ወለድ፣ የኢ-ልብ ወለድ እና የግጥም ሥራዎችን አዘጋጅቷል።**

## ምዕራፍ አምስት

# ሥነ መለኮት እና ፍልስፍና

*የመፅሐፉ ርዕስ፡ ግርባብ [ያ ደግ ሰው]*
*ደራሲ፡ ፍቃዱ አየልኝ*
*የገፅ ብዛት - 237*
*የሕትመት ዘመን - 2016 ዓመት*

[በሀሳብ እና በልብ ሀገር ላይ እየተመላለሰ የሕይወትን የጊዜን የነፍስን እና የፍጥረትን ተነፃፃሪ መልክ ለመፍታት እንዲኹም ውላቸውን ለመጨበጥ... ጥያቄዎችን አንስቶ እንዲኹ ጠይቆ ለመደመም አቃተን ያልናቸውን ሀሳቦች እና በምን ተረድተናቸው ያልናቸው ሁነቶች ... እንደ ተወለወለ ጥሩ መስታየት ነፀብራቅ በማያደናግር መልክ እና በለስላሳ ወንድማዊ ጨዋታ እንድንመለከት አምኃ (ስጦታ) የኾነን ግርባብ መፅሐፍ በእኔ ንባብ ይሄን መሳይ መልክ ተመልክቼበታለኹ]።

ግርባብ በ[prose poetry fable] መልክ (literary genre) የተፃፈ ኾኖ ጥልቅ የሐሳብ መጠይቁ [profundity]ው ደግሞ በ ያ ደግ ሰው አፈ ቀላጤነት የሚጠየቁት የፍልስፍና 'ሐሳቦች የተሳፈሩበት በአተራረኩ [ደግሞ በአንደኛ መደብ እና በሶስተኛ መደብ ሁሉን አወቅ የተተረከልን ግሩም ስራ ነው...በእርግጥ ደራሲው ያን ነኝ ለማለት ይሄንን የሚተው ወይም ወዲሕ ያለውን ለመጨበጥ ከወዲያ ያለውን የሚለቅ አይነት ባይኾንም ትረካዎችን አዛንቆ በማጫወት እስከዛሬ ካየኃቸው በአማርኛ ቋንቋ ከተፃፉ መፅሐፍት የተለየ የተለያዩ ጀነራዎችን በማዛነቅ (hybrid) መልክን ቀምሮ አስመልክቶኛል። እንግዲህ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የምንከታተላቸው ደራሲዎች ፀሐፊዎች እና ገጣሚያን የተለየ ቅርፅ በመፍጠር (experimental) ስራዎችን ሰርተን አዲስን ነገር እናመጣለን በሚል የሙከራ መከራ ውስጥ እንደወደቁ እና classic የኾነው የቀደሙት ጣፋጭ ዓይነትኛ ስራዎች በካልቾ ተመተው አዋራ እየለበሱ መኾኑን አንባቢ ልብ ይሏል.. ይሄ ባለበት ሁኔታ እንደዚህ ያለ ጥውም አተራረክ ያለው በተለያዩ ዘመን ላይ የሚያሳፍር ስራ በማግኘት የሚያስደንቅ ነው።

አይንን ገርበብ አድርገው እንዲኹ እንደዋዛ የጀመሩት መፅሐፍ "ወረቀት ከአድማስ እንደሚሰፋ" እያስረዳ 'ና ልጓም በሌለው ንፋስ ጀርባ ኮርቻ እንደተጫነች ላባ እብስ አድሮን ወስዶ የመጨረሻውን ገፅ ጨርሰው ካልዘጉት

በስተቀረ ለበኃላዬ ይትረፈኝ ብለው የሚያስቀምጥት መፅሐፍ አይደለም...ምናልባት ዘግተው ቢያስቀምጡት እንኳን እንደ አንድ ሰበዝ የሷቧትን ሀሳብ እንደ ጠገበ ገኛ ሲያመሰኩባት ቢውሉ እንጂ በዋዛ የምትለቅ መች ኾና...."ደግሞ እንደዚህ ተብሎ ነገር ከመሀል ይጀምራል" [መቅድም] ልብ ስፍራዋን ከመሀል እንዳደረገች ሁሉ ያ ደግ ሰው ነገርን ከመሀል ጀምሮ ሰው በኾንኩት ብሎ የሚመኘው አይነት አመኝ በደረስኩበት ብሎ የሚማልልለትን (የሚመንንበትን) ንፁህ እና ጠያቂ ማንነቱ ይዞ ያገኘውን እና የተገረመበትን ወዳጇና ገንዘቤ በማለት የምን ግዜም አስገራሚ መደነቅ የሞላቸው ጥያቄዎችን ለቀረቡት (ለተወዳጁት) ያቀርባል...ከእነዚህ መሀልም ለእኔ ሰባት ጉዳዩች ጥሩ ጥያቄ አንስተው አይነተኛ መልስ ያገኘኹባቸው ቀድሞ ሸክሞቼ ዛሬ ደግሞ ወረቶቼ (ንብረቶቼ) ናቸው...

1. ፈጣሪን፡ ጊዜ'ና ቦታን፡ ነፍስ፡ ሩህ እና ሞት (Creator, time & space, ruh, soul and death)
2. ትፍስህት: ሀሴት (pleasure) እና ውበት (beauty)
3. ምክንያት (reason) እና ግፊት ስሜት (emotions)
4. ወዳጅነት፡ (friendship) ትስስር እና ጨወታዎች (talkings)
5. ደስታ፡ ሀዘን እና ህመም (joy, sorrow and pain)
6. የመኖር ህግ'ና የአኗኗር ብልሀት ቅጣት እንዲሁም ምህረት
7. ዋጋ እና ሚዛንን (ወደር), (value,&balance እነዚህንና ሌሎች ወዝ እና ልዩ መልክ ያላቸው ሀሳቦችን አጣጥሜያለው...

ለዛሬ በመጀመሪያ ቀጥር ላይ የተነሱትን ሀሳቦች ግርባብ ያ ደግ ሰው እንደምን ጥያቄ አንስቶ በ"ዲያሌክቲክ "ሀሳብ አጋራባቸው የሚለውን እንዝለቅበት...የደራሲው በምዕናብ ሀገር ላይ እንደ ልብ የመጫወት ብቃት በትልልቆቹ የስነ ፅሁፍ እና የፍልስፍና ባለሟሎች የተመሰከረ በመኾኑ በመድገም አንባቢን አናደክምም ... ይልቅስ ደግ ሰው እያንዳንዳችን በየዋህነትና በትህትና የቆምንበትን ወይም የአምላክን ባህሪ የተጋራ ደህንኛ መልካችንን (higher self) ቁርጥ ይመስላል እንደ እንግዳ የተቀበልነው ደግ

**ሰው ሰንብቶ ተላምዶን የሾምነው እንደራሴያችን ይኾናል..ትንሽ የከረመ እነደኾነ ደግሞ እንደራሴ ያልነውን እኔ ራሴ ልንለው ይዳዳናል! ደራሲው ለነገዬ ብሎ ሳይሰስት የሰጠን ስራ ስንመለከት ሌሎች ድርሳናትን ለመስራት የማይደክመውና የብዕር ዕርፍን ጨብጦ አሁንም የሀሳብ ሁዳድ ላይ ወዲ ወዲያ እያለ እየዘራ እንደኾነ እናውቃለን....በግርባብ ያ ደግ ሰው በታኀዝቦ ከተደነቀባቸው(** wonder **) ካደረገባቸው ብዙ ሀሳቦችን መሀል ሰባት መስመር ሰጥተናቸው ለመመልከት እንዲመቹን ሰደርናቸው ከነዛ መሀል ቀዳሚዎቹ፡-**

**1.ፈጣሪ፣ ጊዜ እና ቦታ፣ ሩህ፣ ነፍስ እና ሞት ቀድመው ይመጣሉ።**

**ደራሲው ቀደም ሲሉ በተለያዩ አለማት ለትሰሩ እንደነ** [Tao te ching - laozi ] **የነ አቦይ ላዑዙ እና** [the art of war - sun Tzu] **እና ጋሼ ሰን ዙ መፀሐፍት እና ለነ አለቃ ኮንፊሺየስ** [confucius] **ውዴታ አለው። ኾኖም እነዚህ ድርሳናት ከተፈጥሮ ጋር አብሮ ስለመኖር** (harmony) **የስነ ፍጥረትን መነሾ ሀሳብ** (ideal of all existence) **ምኞትን እና መከራን** (desire and suffering) **ስነ ባህሪ** (disciplines) **ጥንቅቅ ብሎ መዘጋጀትን** (being prepared) **ታዛዝነትን ባስ ሲል ደግሞ እርስ በራስ ተገናኝቶ የተቋጠረን እና ውል የጠፋበትን የሀሳብ አለም ቋጠሮ እየፈቱ እርስ በእርስ ሲደጋገፉ እና ሲወዳደሱ የነበሩ አሳቢያን ሲኾኑ ለዚህም ኹነኛ ማሳያው ኮንፊሺየስ አቦይ ላዉዙን ለመጎበኘት የሄደበት ሁኔታን ማምጣት ይቻላል**...[the meeting of two masters] **በመባል በሚታወቀው በዚህ የሁለት ታላላቅ ፈላስፋዎች ግኝኙነት ኮንፊሺየስ ስለ ለውዙ ይሄንን ምስክርነት እንዲሰጥ አስችሎታል "በሰማይ የሚበር ወፍ በወንጭፍ ይወድቃል: በጫካ ውስጥ የሚኖር አውሬ ደግሞ በቀስት ወይም በወጥመድ ይታደናል: ባህርን ቤቱ ያለ አሳ በመረብ ይጠመዳል..:- በሳማይ ከደመናው በላይ አልፎ በጀግንነት የሚበርን ነፋስ የማይገታና የማያሸንፈው ደራጎንን ግን ምን ያደርጉታል? እንዴትም ሊያጠምዱት አይቻላቸውም መንገዱም ወደ ገነት ነው!"** [**ልክ እንደዚህ በንግግራቸውም በአሳባቸውም ላቅ ያሉ ዲያሌክቲኮችን በግርባብ መፅሀፍም**] **እናገኛለን...ላውዙም በሰማይ የሚበር መንገዱም ወደ ገነት የኾ ደራጎን የሚል ምስክርነት በኮንፊሺየስ ተሰጥቶታል...**

[As for dragons, I don't know if they can arise to the heaven along with a wind. I met with Lao Tzu today. Maybe he is like a dragon!”] (confucius about lao tzu)

እነ ጋሼ ኮንፊሺየስ እነዚህን አወዳጅተው ሲያነሱ የነገረ አምላክን (ፈጣሪን) ጉዳይ ያላስተዋሉ እና ወይም የዘነጉ ይመስላል ... በግርባብ መፅሀፍ ደግሞ ደራሲው ይህንን ክፍተት (missing link) ለመሙላት እና ሌሎችም የሀሳብ ዳናዎችን በመምዘዝ መሬታዎያንን ሰማያውያንን ሌሎችንም ከየት ወደ የት ናችሁ ብለን እንድነጠይቅ ያደረገው ጥረት የሚያስመሰግነው ነው።

## 1.1"ፈጣሪ"

"ደሞ ሰው እኮ ዝም ሲል አምላክን ይመስላል። ከተናገረ ግን ያው ሰው "ሰው" ነው" ይሄ ሀሳብ ለመፅሀፋ መቅድም እንዲኾን ደራሲው የፃፈው ነው...ዝምታ የአምላክ ዋነኛ ባህሪ ነው የቀረው ፍጥረት ሁሉ ደካማ ትርጓሜዎች ናቸው የሚባለውን የቀድሞ አነጋገር እያስታወሰ የፈጣሪን አንድ መልክ ያመላክተናል... "ያ ደግ ሰው ስለዚህ የጊዜ ቆጣሪ ማሰሪያ ነፍስ ነው እያልህ ነው? ብሎ ሰዓት ሰሪውን ይጠይቀዋል ሰዓት ሰሪውም አዎን "አላህ ጊዜ ባህሪዬ ነው ይላል: "እዚህች ጋር አስምርልኝ እንግዲህ. [ገፅ-68] በዚህ ዟሪ በተባለ ፁሁፍ ውስጥ ያለ ሰፋሪ ጊዜ ቆጣሪ የሌለውን ሰአት እንደሚመስል ተናግሮ እኛም ዘላለማዊውን ስፍር የሌለውን ጊዜ ባሰብን ግዜ ባዶ (vacuum) ኾኖ ወደ ሀሳባችን ይገባል ከባዶም ባዶ የኾነውን መቀመጫ የሌለውን ባዶ ለማሰብ በተቸገርን (ስፍራ የማይዝን ነገር ሰው ለማሰብ ይቸግረዋል) ግዜ ግን እሱ የአምላክን መልክ እንደሚመስል ይነግረናል።

"ኩብኩባ" በሚል ስም በተፃፈችው መጣጥፉ ውስጥ [ገፅ-10] እናት ዶሮ እና አባት ዶሮ ስለ መፍጠር ይህን ይነጋገራሉ:- አባት ዶሮ እንቁላሉ አንቺ ሳትኖሪ ቢፈለፈል ራሱ ራሱን የወለደ ይመስለዋል" እንደ እንቁላል ባለች ክብ አለም ውስጥ ስንቱ ነው የራሱ ፈጣሪ እንደኾነ የሚያስበው.? አምላክ ግን እዚህ ውስጥ ሙቀት ሰጪ እና አቃፊ ኾኖ ይነሳል። "እናት ዶሮ አምላክ እንደኔ ላባ አለው ማለት ነው? ያሞቃል? በሽፋኑ ፍጥረት ገምቶ እንዳይቀር ያደርጋል? አለችው "ይሄ ስለ አምላክ የተነሳ ትልቅ ጥያቄ ነው! "አባት ዶሮ በአመድ ውስጥ የተቀበረ ፍሬ ሙክክ ብሎ እንደሚበስል

ደመናው አመድ ነው ሰው ደግሞ እንዲበስል ተቀብሮ ነው ተጥሎ አይደለም አላት።" [ገፅ-11] ቀጥሎ እናት ዶሮ በምን መልኩ ሰማይ እና የሰማይ እውቀት እንደሚገለጥ ትናገራለች....እንዲኹም "ሳላህ "በሚለው የወዳጆች ጨዋታ ውስጥ [ገፅ-13] ስለ ቡቃያ አንስተው " የልቦና መድረቅ ከጨለማ ጥቁረት ከእሳት ግለት እንደሚከፋ አውስቶ ለዚህም ደራሽ የኾነው መልአክ ገብርኤል ቅዱስ ቃል "በአምላክ ረድኤት" ይዞ እንደሚመጣ እና ለልቦና መንገድ ማሳያ "ብርሀን ቃል እንደሚያዘንብ እና የሞተች ነፍስ መልሳ እንደምትለመልም ያበስረናል! ለእውቀት የአምላክን ተራዳኢነት ይነግረናል... ቃል እና ሀሳብም ብርሀን የኾነውን መንገድ ለማግኘት እንደ እግር መብራት ያሉ እንደኾነ ሀሳብ ያመጣል.. ያ ደግ ሰው ከአንዲት ዕጣን ከምትሸጥ ሴት ጋር በሚያደርገው የሀሳብ ልውውጥ ደግሞ " ከጥሩ እጣን ጥሩ ስም አብልጦ ሽታው ደስ እንደሚያሰኝ ትነግረዋለች... [ምዑዝ ገፅ-38] ያ ደግ ሰውም ሰባት ሰማያት ያክል ቆሞ የተጠቀለለ ጭስ በልቦናው እያሸተተ ሲሄድ አሰበ እናም "አኹን ከሰማየ ሰማያት የዘለቀ የአምላኬ ጥሩ መዓዛው እየሸተተኝ ነው ልሂድ ልከተለው" አፍንጫውን ወደ ላይ ቀስሮ እያነፈነፈ መንገዱን ይቀጥላል... "ወራጅ እና ቋሚ" ላይ ደግሞ ደግ ሰው ከአናጢ ጋር ሲነጋገር የአምላክ ዐሳብ ራሱን ችሎ እንጨት ይጎትታል: ወራጅና ቋሚ አቁሞ ቤት ይሰራል። ገብቶም ይኖርበታል።

እናም ሰው ሰው የአምላክ ዐሳብ ነው የሚመስለኝ ይለዋል። "ሰጪ አምላክ ንብረቱን ለማን እንደሚያሲዝ ያውቃል" (እውቀትም ንብረትም አያያዙን ላወቀበት የአምላክ ቸሮታ ነው...ይለናል [ዓለም ቀን ገፅ-74] የአምላክ እና የገበሬ መመሳሰል ከ"ሳላህ" ጋር ባደረጉት ጨዋታ እንህ ይነሳል ገበሬ አምላክን መሳይ ከመካከል የተበላሸውን አረማሞ የወረሰውን እሪያ የበተነውን ጃርት የቦጠቦጠውን እየተወ ለመልካም ቡቃያዎች ግን ለእናንተ አዲስ ጎተራ አላችሁ ይላቸዋል..."የዛፍ ብስል ወደ መሬት የሰው ብስል ግን ወደ ሰማይ ይወድቃሉ" በዚህም ደራሲው የሰማይን ዜና ለመስማት በልቡ ወደ ሰማይ የወደቀ ነው!

እንግዲህ እንዲህ እያጫወተ ደጉ ሰው ስለ ፈጣሪ በ "ነፍስና ዜማ: በመቃ: በላም እና ገመድ በምዑዝና ሌሎችም አርስት በሰጣቸው ጣፋጭ ወጎቹ ውስጥ" ፈጣሪን ሲያወሳ ተመልክተናል...በተለየ ደግሞ "መድኅኒት"

በምትለው ወግ ውስጥ ከበሽታ ጋር ተነጋግሮ "አንተም ፈጣሪን ታውቃለህን? ወይ ብሎ ይጠይቀዋል [ገፅ-60] በሽታም፡- "ሳይፈጠር ጊዜ ላይ የሚሰፍር የለም...እንኳን እኔ ድሮውንም የነበርኩት አንተም እንኳ ባቅምህ አኹን መጥተህ እንደተፈጠርህ ታውቃለህ። ችግርህ ካልተራመደ እና ካልበረረ የለም ስለምትል ነው" ብሎ (Existence of GOD)ን እንድንመረምር እንድንረዳ የሚጋብዝ ምላሽ ይሰጠዋል! በዚህም ሲበርና ሲራመድ ያላየነውን አምላክ በምን ልንመረምር እንደምንችል ያመላክተናል....ሁሉ ነገር የጀመረው ከነጥብ ነው ነጥብ ደግሞ አንድ ነው። አንድ ደግሞ አምላክ ነው። (ነቁጥ) በመጨረሻም አንድ መለዮ ሰሪ ለደጉ ሰው ይህንን ይሉታል ...."ልብ ማለት ያለብን ግን ሰማይን እንደ ቆርቆሮ ክዳን መሬትን እንደ ወለል አድርገን አምላክን ዉጪ እንዳናሳድረው ነው። ሁሉም የእርሱ ሲኾን "ያ ብቻ ያንተ ብለን አንከለክለውም" በማለት ሁሉን ነገር ለፈጣሪ አሳልፎ ይሰጣል! ያ ደግ ሰው.!

## 1.2. ጊዜና ቦታ (time and space)

ጊዜን በግርባብ መፀሀፍ ውስጥ ያ ደግ ሰው እንደ ሀገር እና ስፍራ ያነሳዋል። ጊዜ እንደ ሀገር ከታሰበ ደግሞ ተራራ ሸለቆ ጉድባ በተጨማሪም ኗሪ ይኖረዋል ...ኗሪዎቹም ሞት እና ዘመዶቹ እንደኾኑ እንቅልፍ የሞት ታላቅ ወንድም እንጉልቻ እና በሽታ የቅርብ ተጠሪዎች እንደኾኑ... ኩርባና ገደል ባለው ግዜ ውስጥ እንዲኹ ከባህር ወደ አየር ዘሎ ወጥቶ ተመልሶ እንደሚገባ አሳ...የጊዜ ሀገር ላይ ተዘዋውረው ለመምጣት ይቻል እንደኾነ አንድ ሰዓት ሰሪ እና ደግ ሰው ይነጋገራሉ...ደግ ሰው ጊዜ በጉድባው ላይ የያዛቸውን ነገሮች አራግፎ ምን እንደሚመስሉ ለመመልከት ሲጥር- ጊዜ ያለ ሰፋሪ ቀፎ እንደኾነ ይናገራል-ጊዜ የፈጣሪ ባህሪ እንደኾነ _የጊዜ ቆጣሪ ማሰሪያ ነፍስ እንደኾነ ያመላክተናል!_ጊዜ የቆመን ሰው ይመስላል መለመላውን ለተመለከተው ደግሞ ዝም ያለውን ነፋስ መትቶ ወዲህ እና ወዲያ የማይነቀሳቀሰውን ዛፍ ይመስላል-ጊዜ የሚታሰበው ትልቅ ሰው ሲነሳበት ነው ይላናል ትልቅ ሰዎች ጊዜ ስፍራ እንዲይዝ ስራ ያበጁበታል ይሄ ድንቅ አተያይ ነው!

## 1.3 ሩህ እና ነፍስ (ruh and soul)

ስለ ሩህ እና ነፍስ ልዩነት የሚያጫውተን ደግ ሰው ሩህ ከነፍስ ቀድማ በተገነባ የሰው አካል ውስጥ የምትከተት ማብሪያ (birth of life) ስትኾን ነፍስ ሰውና ቤቱን አንድ ላይ እንደማየት ስትኾን ሩህ ደግሞ ሰውዬውን ለብቻ እንደማየት ነው [ገፅ-130] ይለናል....ሰሪ የሩህን ልኬት የሚያውቅ ነውና የአካልን ወርድ እና ቁመት ይወስናል... ያ ደግ ሰው ከ አናጢ ጋር ባደረገው ጨዋታ ይህን ይጠይቃል:- "እንደነገርህ ከኾነ የአጭር ሰው ሩህ በረጅም ሰው ጀሰድ(አካል) ውስጥ ብትገባ ሰፊ ጫማ እንዳደረገ ኀተት ኀተት ትላለች። እንዲኹም ሰዎች ራስ ገዝ የማይኾኑት ሩሐቸው በሰፊው አካላቸው ውስጥ ማነሷ ነውን? ይላል..ያ ግምበኛም:- ምን እሳት እኮ ትንሹ ይበቃል እፍ ካልከው ይፈጋል። ወራጅ እና ቋሚ (ገፅ-146) አንዳንድ ሰው እሳት ብርሀን የኾነችውን ሩሑን እንደ ማሾ መብራት ጠምዝዞ አያደምቃትም ደግሞ ይገርምሀል ሩህ ፍም መሳይ እፍ ተብላ ካልፈገገች አካል ውስጥ ያለው ጨለማ የማይገፋ እንደ ተቦካ ሊጥ የዳኀሰ ነው አለው...በዚህም ሩህ የአካል ብርሀን ኾና ትነሳለች...ነፍስ ደግሞ...መልኳን እና ክብደቷን ለማወቅ ደግ ሰው ከአንድ ነጋዴ ጋር ይህቺን ቂሷ ያወጋባታል...ያ ነጋዴ:-ነፍስ ወደ ሰማይ ስትሄድ በስንት ግመል ተጭና ነው?ያ ደግ ሰው :- ነፍስ እኮ ሳትሄድ ነው የምትደርሰውያ ነጋዴ:- ሳይሄዱ መድረስ እንዴት ያለ ነው? ያ ደግ ሰው:- ቀድሞውንም የነበረ አምላክ ሳይሄድ እንደኖረ ይኖራል ! ብሎ በአስተማስሎ ይነግረናል....ነፍስ እንደ ጊዜ ማሰሪያ እንደ ህይወት ማብሪያ በተለያየ ቦታ እየተነሳች ትመጣለች ልስላሴዋ ደግሞ ከውሃም ከጥላም ይልቃል ያ ደግ ሰው:- "አሁን የምታየው የሰው አካል ዐውሎ ነፋስ እንደቆመው ዐቧራ ነው። ነፋሱ አደብ ገዝቶ መረበሹን የተወ ቀን ተንጠልጣይ አፈር ከከፍታው ይዘረገፋል:ብሎ ነፍስ በአካል ውስጥ ያላትን አስሮ ያዥ ሚና ይነግረናል። [ገፅ-78-79 አውድማ] በእነዚህ እና በሌሎች ወኀች ውስጥ የነፍስን ምንነት የነፍስን አካሄድ የነፍስን ሁነኛ ስፍራ እያዋዛ ለነገረን ደራሲ እጅ ነስተን ምስጋናን ሰድደናል!

## 1.4.ሞት

በዚህ መፅሐፍ ውስጥ አንድ የሀሳብ ማጠንጠኛ የነገር መወጠኛ ነው...በዚህም ረመጥ የሚል ርዕስ ስር ሞት እና መረሳትን በአንድ ላይ አምጥቶ ነገር ግን በዚህ ባለቤቱ ሞታበት ሁለት አመት ሀዘን ያልወጣለትን አባወራ አምጥቶ ጓዱ መረሳትን ረስቶ የሄደ ሞት የንግግሯ ውቅራት ጥሩ የሀሳብ ከተማ ይመስል የነበረውን ሚስቱን እያስታወሰ ስር ለሰደደ ሀዘን የተዳራገውን ሰው የሞትን ህመም ክፋት ተናጋሪ ያደርገዋል .... [ገፅ -51 ረመጥ]

ሌላም ደግሞ ሞት አገላብጦ አብሳይ ሞት አንዱን ወስዶ ሌላን በተራው አዲስ እንዲቆም የሚያደርግ ኾኖ ተከስቷል በዚህም የዚያ ደግ ሰው ልጆች የኾኑት ውብ አንተ እና ማማሩ ላም እና ገመድ በሚለው አርስት ውስጥ በሚለዋወጡት ዐሳብ እውነታ በሚታይ ነገር ላይ ብቻ የሚመሰረት ከኾነ ስምምነትህ ሞትን ያህል ጉድ ያቀፈ ነው ይለዋል መሞት ማለት አለመኖር እንዳልኾነና ስፍራ የመቀየርን ነገር የማይታይ ነፋስ የሚታይ ቅጠልን መግፋቱን አንስተቶ ሞትን በአስተማስሎ (metaphor) እና በአስረጂ እያዋዛ ይነግረናል...እዚህ መፅሐፍ ውስጥ ሌሎችም ብዙ እንደ አለት ይከብዳሉ ስንል ደራሲው እንደ ላባ አንስቶ እንድንነጋግርባቸው የሚያስችሉ ጉዳዮች አሉ:በመጪው ጊዜ ቀስ እያልን እነሱ ላይ እንጨዋወታለን...በመጨረሻም ":- የማየት ብርሀን በወረቀት ገላጣው ላይ አርፎ ግለቱ ፊደልን እያቃጠለ ዐሳብን ካላተነነ መፅሐፍ ዝግ ከተማ ነውና [ገፅ 109] እያነበብን ብርሀን እናምጣ ነገር በደፈናው እዳ ነው! ብሎ ሀሳብ አበጥሮ እንድናብጠረጥር የሰጠንን ደራሲ ፍቃዱ አየልኝ ምስጋናህን ውሰድ እንላለን .. ሰላም !

**የተጠቀሰሱ መፀሀፍት እና ድህረ ገፅ - Tao Te ching – laozi - the art of war- sun zu*

**ዳሰሳ አቅራቢው ጸጋዬ አዳም ገጣሚና ፀሀፊ ነው። በተለያዩ የትስስር ገፆች እና መፅሔቶች ግጥሞቹንና ፁሁፎቹን ያጋራል።**

*የመጽሐፉ ርዕስ- ‹ዮቶር› ኮብላይ ካህን*
*ደራሲ- ዓለማየሁ ደመቀ*
*ገጽ ብዛት- 190*

**ይኸ መጽሐፍ ወጥ ልቦለድ ቢሆንም በ19 ክፍሎች ተዋቅሮ የመጀመሪያው ከቀጣዩ ጋር ተሰናስሎ የቀረበ ነው። ደራሲው በአንደኛ መደብ በሁሉን አወቅ ዘዴ በገጸ ባህሪያቱ አማካኝነት በርካታ ሐሳቦችን እያነሳ፤ በጥያቄና መልስ መልኩ ይሞግታል። ጥልቀት ያላቸውን** ‹subtlety› **የፍልስፍናዊ እሳቤችን ይተነትናል።**

**ዳሰሳየ በዋናነት በመጽሐፉ ላይ በተነሱት ፍልስፍናዊ ሐሳቦች (ማለትም ስለ ጥበብ ማድነቅ፣ ጥበብን በመሻት ስለሚከፈል መስዋዕትነት፣ እውነትን ስለመፈለግ እና ለእውነት ከህቅ ስለመኖር፣ ለሰው ልጆች ሁሉ መልካም ስለማድረግ** (moral virtue), **ስለ ሥልጣኔ ብያኔ እና አተያይ፣ ስለ ዕጣ ፋንታ ወዘተ ትኩረት የሚያደርግ ቢሆንም መጽሐፉ ልቦለድ በመሆኑ የልቦለድ አላባውያን ከሆኑት መካከል የገጸ ባሕሪያት አሳሳል ደረጃ** (characterization), **የቃላት እና የዐ.ነገሮች አጠቃቀም፣ መቼት፣ የሴራ አወቃቀር እና ስለ ጭብጡ ማለትም ደራሲው ማስተላለፍ ስለፈለገው ዋና ፍሬ ነገር ምልክታየን አቀርባለው።**

**ደራሲው የመጽሐፉን መቼት በከተማ ላይ ጀምሮ ወደ ገጠር በመሄድ የገጠሩን እና የከተማውን ማሕበረሰብ የአኗኗር ይትበሃል ለመግለጽ ተጠቅሟል። የመጽሐፉ ዋና ገጸ ባህሪ ራሱን ፍለጋ በሚያደርገው ጉዞ ላይ ከከተማ ወደ ገጠር ይሄዳል። በዚህ ግዜ ነበር ካህን እና ገበሬ ከሆኑ ሽማግሌ ሰውየ ጋር የመገናኘት አጋጣሚ የተፈጠረለት። ከእሳቸው ጋር በሚያደርገው ውይይት ደግሞ ተቅበዝባዥ የነበረችው ነፍሱ ተረጋግታለታለች። ለነፍሱ መረጋጋት ሰውየው የከተማ ኑሮ ወከባ እና ግርግር የበዛበት እንደሆነ፤ የገጠሩ ደግሞ ከተፈጥሮ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ እርጋታ እንደሚታይበት እና የውስጡን ፍላጎት እና ምኞት ሁሉ ስለነገሩት ነበር። “ነፍስና ስጋችን የሚያዜሙት ዜማ ህብር ካልሆነ ውበትና ስምረት ሆነ የተቃኘ መልዕክት ሊኖረው አይችልም። ንጋት ላይ ተጋድመህ የውችን ዝማሬ ስትሰማ፤ ዛፉንና ቅጠሉን፤ ወንዙ ሁሉ በልቦናህ አብሮ የሚታይህ ተፈጥሮ በተቆራኘችበት**

ምትኃታዊ ኃይል ሳቢያ ነው” (ገጽ፣7) ከላይ የገለጸውን ሀሳብ ለማጠናከር የነፍስን ህመም፣ ጥሪና እውነት ለማወቅና ለመረዳት የልብ መናወጥ እንደሌለበት በአጭር እና ማራኪ በሆነ ዐ.ነገር እንደሚከተለው ገልጧል። “ነፍስህን ማድመጥ ስትጀምር እያንዳንዱን ቁስል እራስህ ማከም ትችላለህ” (15) ደራሲው የነፍስን እርጋታ መገኛ ቦታን ገጠር መሆኑን እንዲሁም በተፈጥሮ ከተገኘ እውቀት እና ጥበብ ሰዎች በደንብ መጠቀም እንዳልጀመሩ፤ የሰው ልጆች አብዝተው የሚያስቡት ምኞታቸውን ለማሳካት ሲሆን ለማሳካት ግን የመንፈስ እርጋታ ሲኖራቸው እንጂ በመራወጥ እና በመብከንከን እንዳልሆነ ለመግለጽ የመረጠው መቼት ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ የገጸ ባሕሪያት የአሳሳል ደረጃ ለሥራው ውጤት ማማር ጉልህ አስተዋጽኦ አለው። በዚህ መጽሀፍ ውስጥ ዋና ገጸ ባህሪ ተደርጎ የተሳለው በዕድሜ ወጣት ሲሆን ውስጣዊ መሻቱን፣ ጥበብን እና እውቀትን ፍለጋ፣ የጥበብ ጥማቱን ለማርካት የሚያደርገውን ጉዞ እናይበታለን። በዚህም የገጸ ባህሪው አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና ሥነ ምግባራዊ ደረጃው ተገልጾ የምናገኘው መሆኑ ጥሩ ጎኑ ቢሆንም ወጣቱ ዋና ገጸ ባህሪ ተደርጎ ከመቅረቡ አንጻር የገጸ ባህሪያት አሳሳል የመጀመሪያ ደረጃ መታወቂያ የሆነው ስሙ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ አለመጠቀሱ እንደድክመት ወስጀዋለሁ።

በዚህ መጽሐፍ ላይ ደራሲው ማስተላለፍ ለፈለገው ዋና ዋና ሐሳቦች ማለትም ራስን ስለማወቅ፣ ማንነትን ስለመፈለግ፣ ስለ ሰው ልጆች ተፈጥሮ፣ ስለ ዕጣ ፋንታ ... የሳለው ገጸ ባህሪ እጅግ የተዋጣለት ነው። ይህ ገጸ ባህሪ ‹ዮቶር› እየተባለ የሚጠቀስ ሲሆን ካህን እና ገበሬ ነው። ዮቶር ከስሙ ስንጀምር እንኳን በኢትዮጵያ የእውቀትና የጥበብ እንዲሁም የእምነት መሠረት አንዱ መሆኑ ይታወቃል። ዋና ገጸ ባህሪ የያዘው ወጣት በገጽ 8 ላይ “ለመሆኑ ከዚህ በኋላ እኔ ማን ነኝ? ከዚህ በፊት የገነባሁት እኔነቴስ ምን ሊባል ነው?” እያለ ራሱን ለማግኘት በሚያደርገው ከራስ ጋር ሙግት እ ጉዞ ላይ የሚያገኛቸው ሽማግሌው ዮቶር ከጭንቀቱ ስለሚወጣበት እና ወደ ዓላማው የሚደርስበትን መንገድ “በሕይወትህ ውስጥ ከሁሉም የሚበልጥብህ ነገር የቱ ነው/ያንን ከመለስክ ሌላውን ነገር ሁሉ ለዚያ ታላቅ ነገር መስዋዕት ለማድረግ መጨከን ይኖርብሃል።” (ገጽ 11-12) ሽማግሌው ዮቶር ካሕን

በዚህ ምክር ብቻ ሳይወሰን "የሰው ልጅ ሁሉ አንዱ ለሌላው መልካም መንገድ እንዲሆን ጭምር ነው የተፈጠረው" (13) በማለት ለአንዱ የስኬት መንገድ ሌሎች ሰዎች አስፈላጊ መሆናቸውን ይኽም የሰው ልጆች ሲፈጠሩ አብሯቸው ያለው ረቂቅ ህሊና እንደሚረዳቸው ነግረውታል። ደራሲው የእውቀት እና የጥበብ፤ የሰላም እና የእርጋታ ተምሳሌት አድርጎ የሳላቸው ዮቶር የተሰኙት ገጸ ባህሪ በአራቱም የገጸ ባህሪያት የአሳሳል ደረጃዎች ማለትም አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ስነ ምግባራዊ (physical, social, moral and psychological level of characterization) ደረጃዎችን አሟልተው የተቀረጹ በመሆናቸው የተዋጣላት ነው።

ከፍተኛ ጭንቀት (anxiety) ለሰው ልጆች አንዱ ትልቁ ህመም መሆኑን በዚህ መጽሐፍ ላይ የተነሳ ሲሆን የሰው ልጆችን የስኬት ጎዳና የሚያበላሽ መሆኑን እና መፍትሄውም ራስን አለማታለል ነው የሚል ድምዳሜ ያስቀምጣል። "ከጭንቀት መንገድ መፈወስ የሚቻለው እውነትን አውቆ በመቀበል ነው።" (25) ‹እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር› እንዲል የሀገሬ ሰው ደራሲው የሰው ልጆች ከዕውቀት እና ጥበብ ከሚያርቀው የስሜት ጎዳና ወጥተው በንጹሕ ህሊናቸው መርምረው የሚደርሱበት እውነት ወደ ትክክለኛ መንገድ የሚያመራ እንደሆነ፤ ይሄንንም መንገዳቸን በጥበብና በድፍረት (wisdom plus courage) መከወን እንደሚጠበቅባቸው በክፍል ሦስት መግቢያ ላይ ‹‹የትኛውንም ጨለማ በተጠጋኸው ቁጥር ልክ ወደ ኋላው ያፈገፍጋል" (26) በማለት እውነትን በመጋፈጥ፣ ለእውነት በማደር ወደ ብርሃን መጓዝ እንደሚቻል ያትታል። በመጽሐፉ ገጽ 71 ላይ "የሰው ልጅ እምነት እርግጠኝነት ይጎድለዋል" በማለት በፈጣሪ ያለንን እምነት ሙሉ እና ከጥርጣሬ ነጻ ስለማድረግ፤ ያ ካልሆነ ግን የምንሠራውን ሁሉ ለፍሬ ለማብቃት ጉልበታችን የሚያዝል ልባችንንም በተስፋ መቁረጥ በመሙላት የዓላማ እና የአቋም መናወጥ እንደሚያጋጥመን፤ ስለዚህ በሕይወት ጉዟችን ላይ ጥበብን መፈልግ፣ እውነትን ፈልጎ ለእውነት መገዛት ለሰው ልጆች ሁሉ መልካሙን በማድረግ እውነተኛ ሀሴት ይገኛል ይለናል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተነሱት በርካታ ፍሬ ነገሮች መካከል አንዱ የዕጣ ፋንታ (free will) ጉዳይ ነው። ሀሳቡ በፍልስፍናው መድረክ የዓለምን ሊቃውንት ሁሉ ሲያከራክር የነበረ ነው። "ከወራት በፊት በነበረኝ ግንዛቤ

‹የሁሉም ነገር ዕጣ ፋንታ በፈጣሪ መዝገብ ላይ ተከትቧል› የሚለው ነገር በከፊል ስቀበል በከፊል ደግሞ አይዋጥልኝም ነበር። ‹የአንድ ሰው ነፍሰ ገዳይነት ቀድሞውንም በዕጣ ፋንታው ላይ ተጽፎ ከሆነ፤ ያ ሰው ከመወለዱ በፊት የተጻፈውን ዓይነት ሰው ከመሆን ውጭ አማራጭ ላይኖረው ነው። ታዲያ በምንም ዓይነት መልኩ ነፍሰ-ገዳይነቱን ሊገታው ካልቻለና ከተጻፈው ውስጥ ጠብ የሚልም ነገር ከሌለ፤ እንደምን ነፍሰ-ገዳይ ተብሎ ከገሃነም ይጣላል?” ገጽ 160) በማለት የሰው ልጆች ዕጣ ፋንታ እንዲሁም ጥሩ ወይም መጥፎ የመሆንና ያለመሆን በፍላጎታቸው ላይ የተመሰረተ እንጂ ለእኩይ ደርጊታቸው ፈጣሪያቸውን ተጠያቂ ማድረግ ልክ እንዳልሆነ ይነግረናል። ይሄንን እምነቱን በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ የአዳም እና የሔዋንን ታሪክ እንደማስረጃ አቅርቦ ያጠናክራል። ሌላው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተነሱት ሐሳቦች መዳሰስ የሚገባው ስለ ሥልጣኔ ምንነት የተነሳው ነው። ደራሲው ስለ ዘመናዊው ሥልጣኔ ቁሳዊ መሆን፤ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በዓለም ሕዝቦች ላይ እንዳመጣ፤ ረፍት የሌሽ እና ተቅበዝባዥ፣ እርካታ እና እውነተኛ ደስታ ያጣ ወጣት ስለመብዛቱ፣ የዘመናዊው ዓለም ሥልጣኔ ከሰላምና ከፍቅር ይልቅ ለጦርነት (ለአውዳሚ የጦር መሣሪያ መፈብረኪያ) በቢሊዮን ሀብት እንደሚያባክን፡ ይህ የሆነው የዘመናዊው ሥልጣኔ ግብ ኃይልና ገንዘብ በመሆኑ ነው እያለ ያትታል። ስለመንፈሳዊ ሥልጣኔ ሲያነሳ ደግሞ “መንፈሳዊ ሥልጣኔ የተመሠረተው ፍቅር ላይ ነው። ፍቅር ደግሞ የሰብዓዊነት ቁልፍ ነው። ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው ራሱን ለፍቅር ያስገዛል” (ገጽ 37-38) በማለት ቢናገርም የመንፈሳዊነት ፍልስፍና ትሩፋቶችን ግን ስለ በጎነት እና ፍቅር በጥቅሉ ይገልጣል እንጂ እንደ ቁሳዊው ሥልጣኔ በደንም ተገልጾ አላገኘሁትም።

በዚህ መጽሀፍ ደራሲው የተነሱትን ፍሬ ሀሳቦች ለአንባቢ በቀላሉ ሊደርሱ (ሊረዳቸው) የሚችሉ ቃላትንና ዐ.ነገሮችን ገላጭ እና ማራኪ በሆነ መንገድ ተጠቀወሟል። ለምሳሌ በገት 22 እና 23 ላይ ስለ ፍቅረኛው ዕድላዊት ባህሪ እና ውበት ሲገልጽ “ዕድላዊት የነፍስ ጅረት የሚፈስባት፤ የነፍስ ዜማ የሚደመጥባት፤ የነፍስ ብርሃን የነፍስ ዛፎች እያሽኮረመመች የጮራዎች ሕብር ሆኖ የሚዳስሳት፤ እጥር ምጥን ያለች ውብ የነፍስ ከተማ ትመስላለች” እያለ በተምሳሌታዊ (metaphoric expression) መግለጹ ግሩም ያስብለዋል። ይህ

መጽሐፍ የሚያጠነጥነው አንድ ጥበብን ፍለጋ ሲል የሚወዳትን ፍቅረኛውን ትቶ ከከተማ ወጥቶ በመኮብለል፤ በጉዞው የሚያገኘውን ጥበብና እርጋታ፤ ከነበረበት ራስን ባለማወቅ እና ከዚህ በመነጨ ስሜት ከደረሰበት የመንፈስ መናወጥ በመውጣት ወደ አዲስ ማንንት ሲገባ እንዲሁም ወጣቱ ከአንድ ሕይወት ወደ ሌላ ሕይወት የሚያደርገውን ጉዞ እና የስኬት መንገድ የሚያሳይ ነው።በአጠቃላይ ደራሲው ፍልስፍናዊ፣ ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ ታሪኮችን የሚዳስስ ሲሆን በተለይም አሁን በሀገራችን እንደ ሰደድ እሳት በየክፍለ ሀገሩ፣ በየአውራጃው፣ በየመንደሩ እና በየጎጡ በቋንቋ፣ በባህል አንዳንዴም በሃይማኖት ልዩነት እየተዛመተ ስላለው የጦስ እሳቤ የሚያነሳው አሁን ላለነው ትውልዶች ጠቀሜታው ጉልህ ነው። በአጠቃላይ በግጥም ደራሲነቱ የሚታወቀው ዓለማየሁ ደመቀ በዚህ መጽሐፉ ላይ በግሩም ቋንቋ፣ በማራኪ አቀራረብ፣ ጥልቀት ባላቸው ፍልስፍናዊ ሐሳቦች አጥናክሮ ለአንባቢ ያቀረበው ይህ መጽሐፍ ለሚያነበው ሁሉ አዲስ ዓይነት እሳቤ ሊያገኝበት ይችላል የሚል ሙሉ እምነት አለኝ። መልካም ንባብ!

Reviewer: Woldegiorgis Yihunie, author of Reqiq Ethiopian philosophy **የኢትዮጲያ ረቂቅ ፍልስፍና**

*የመጽሐፍ ርዕስ፡- የሕግ ፍልስፍና*
*ጸሐፊ፡- ዳዊት በዛብህ*
*የገጽ ብዛት፡- 237*

መጽሐፉ ዘጠኝ ምዕራፎችና አርባ ሦስት ንዑስ አርዕስት ያሉት ሲሆን "ሐተታ ዘምክንያት" በሚለው ጽሑፍ ሥር (ከገጽ 5-6) የመጽሐፉ ዓላማዎች ተዘርዝረዋል።

1) አገር በቀል ወይንም ከእኛ አገር ሁኔታ ጋር የተሰናሰለና እንዲሁ ከውጪው ዓለም የተገኘውን ሕግ ከመገልበጥ ፍልስፍናዊ ጭብጡን በመረዳት፥ "ከውጭ ወደ ውስጥ" በሚደረገው ተግባር ላይ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠቁማል፥

2) ለሕግ ፍልስፍና ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ለማሳሰብ፥ ይህም ለፍልስፍና የትምህርት ክፍልም ትኩረት እንደሚያሻው ማሳየት፥

3) በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እሴትና ባሕል ሥር ያሉትን ሕግጋት በውይይት (ምክንዮአዊ ሙግት) ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፥

4) በአማርኛ (በአገራችን ቋንቋዎች) ስለ ፍልስፍና እሳቤዎች መነጋገርን (መሟገትን) እና መጻፍን ማስለመድ የሚሉት ናቸው።

ምዕራፍ አንድ ላይ ስለ ሶቅራጠስ ማንነትና እሳቤው ያብራራል። በገጽ 9 ላይ በሶቅራጠስ የተላለፈበትን ክስ፥ ወጣቶችን ማሳሳትና የግሪክ አማልክትን መንቀፍ፥ ይገልጻል። ምንም እንኳን የሶቅራጠስ መታሰር ኢፍትሐዊ ይርጊት ቢሆንም ወዳጆቹ ክሪቶና ጓደኞቹ እሱን ለማስመለጥ የዘየዱት መላም በሶቅራጠስ ዕይታ ኢፍትሐዊ እንደሆነ ያሳየናል (በተለይ በገጽ 13 ላይ)። ከገጽ 14-19 ድረስ የአፍላጦንን (Plato) ማንነትና አስተሳሰብ ያስተዋውቀናል። ፕሌቶ ነገሥታት ጥበብን የሚወዱ (አሳቢያን፥ ፈላስፋ) እንዲሆኑ በRepublic መጽሐፉ ያብራራበትን ይገልጻል። የነገሥታቱ ፈላስፋ መሆን ለፍትሕ መስፈንና ምክንያታዊነት ከስሜታዊነት እንዲያይል በዚህም ፍትሕና ትክክለኝነትን ወዳድ ሕዝብና መሪ እንዲፈጠር እንደሚያግዝ ያለውን ጠቃሚ አሳብ ያብራራል። በተጨማሪም ፍትሐዊ ከተማን ለመገንባት

የሚያስፈልጉትን የአስተዳደር እርከኖች (መደቦች) የገለጸበትን ተንትኗል (በገጽ 18)። ቀጥሎም ስለ አሪስጣጣሊስ (Aristotle) በሕግ ዙሪያ ያለውን አመለካከት ከኒኮማኪያንና ዩዴሚያን ኢቲክስ እንዲሁም ከፖለቲክስ ድርሳኑ ስለ ግብረገብ (good virtue) መካከለኝነት እሳቤውም አብራርቷል (ከገጽ 20-22)። በመቀጠልም ከገጽ (23-26) ሕግ ከሞራል ፍልስፍና ጋር ያለውን ቁርኝት ይገልጻል።

በዚህም የማሕበረሰብን ግብረገባዊ ዕይታ በThesis-AntiThesis-Synthesis አቀራረብ ያስቃኘናል። ስለ ሦስቱ የግብረገብ ዓይነትና ምንጮች (virtue, consequential, and deontological ethics) ይዘረዝራል። ከገጽ 26-29 ድረስ በሶቅራጠስና በአርስቶትል አመለካከት ምን እንደሚመስል ያስቃኘናል። ከገጽ 30-34 ድረስ የጠቀሜታውያኑን፥ የጄረሚ ቤንትሃም አመለካከት ማለትም ለብዙኃኑ ብዙ (መጠነ ሰፊ) ደስታን እንዴት በሥራ ላይ ማዋል እንደሚቻልና የዚህን (utilitarian) ሁለቱን (መርህና ድርጊት) አመለካከት ይገልጻል። ከዚህ ዕይታ የተቀዱ የግብረገብ ፍልስፍናዎች በብዙ አገራት ጥቅም ላይ እንደዋሉና ተጽዕኖው ሰፊ እንደሆነ ያሳያል። ከገጽ 34-38 ድረስ የካንትን የሞራል ፍልስፍና ነባቤ ቃል (theory) ይዳስሳል። በዚህም ካንት ስለ ሰው ልጆች ብቁ መሆን የሚያቀነቅነውን "human autonomy" ላይ የተንተራሰውን ግብረገባዊ አመለካከት ያሳያል። ከገጽ 39-43 ድረስ ስለ ፍትሕና ሕግ ቁርኝት የሚያብራራ ሲሆን እነሱንም ከእውነታ ዲበቁሳዊ ምልከታ ጋር ያስቃኘናል።

በምዕራፍ ሦስት ስለ ሕግ ተፈጥሮ ያለን የፈላስፎች አመለካከት ይፈትሻል። ከገጽ 45-48 ድረስ የሕግን ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ቁርኝት ይዳስሳል። በዚህም ሕግ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን መስተጋብር ከፈጣሪም ጋር ሊገናኝ እንደሚችል ይነግረናል። ከገጽ 48-51 ሶፊስቶች የነገሮችን ትክክለኝነት ወይንም እውነተኝነት ከስሜት ሕዋሳት ተራክቦ ጋር እና በፕሮታጎራስ ዐዋጅ "ሰው የነገሮች ሁሉ መለኪያ (መዳረሻ) ነው" በሚለው በመደገፍ አንጻራዊ ዕይታ እንዲያንጸባርቁና ከሶቅራጠስ በምን እንደሚለዩ ያሳየበት ነው።

ከገጽ 52-58 ደግሞ ከስሜት ነጻ በሆነ በተለይም ከሰው ልጆች ቁጥጥር ውጪ በሆኑት ነገሮችና መቆጣጠር በሚቻለው የውስጥ ፍል-አምሮት (passion) ልዩነት በመነሻነት በመጠቀም ያዋቀሩትን የስቶይኮች ምግባራዊ ፍልስፍና ያስተዋውቀናል። ከገጽ 58-61 ድረስ ቅዱስ አገስጢኖስ ከፈጣሪ ጋር በማገናኘት ስለ ፍትሕ የገለጸውንና የሰውና የአምላክ ከተማ ብሎ በመክፈል ያብራራውን የግብረገባዊ ፍልስፍና ይተነትናል። ከገጽ 62-65 ድረስ ቅዱስ ቶማስ አኳዬናስ ስለ ሕግ፥ ተፈጥሮና ፈጣሪ ያላቸውን ተዛምዷዊ ቁርኝት የገለጸበትን ያብራራል። በዚህም ልብ ሊባል የሚገባው የኦገስጢኖስና አኳዬናስ ልዩነት የመጀመሪያው የNeo-Platonism ተጽዕኖ ያረፈበት ሲሆን ሁለተኛው የአርስቶትል ተጽዕኖ ያረፈበት ነው። ከገጽ 65-68 ድረስ የሁጎ ግሮሺየስን በስቶይኮች ግብረገባዊ እሳቤ ተጽዕኖ የቀመረውን የዓለምአቀፍ ማሕበረሰብንና የማሕበረ-መንግሥት አመለካከት እንዴት እንዳስተዋወቀ ይገልጻል።

ከገጽ 69-71 ድረስ የፌኒስን ማንነትና የሱን በሕይወት ላይ አጽንኦት በመስጠት ያረቀቀውን ግብረገባዊ ፍልስፍና ይዳስሳል። ከገጽ 72-82 የሌዊስን ማንነት፥ የተፈጥሮ ሞራዊ ሕግን እንዴት እሱ ከያዘው ንጽረተ-ዓለማዊ ዕይታ ጋር እንደተብራራና ነገርየው በሰው ልጆች ሁሉ ያለ እንደሆነ ይህም የሞራል እሳቤ ከዲበአካላት ጥናት ጋር እንደሚገናኝ እና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚገናኙ ነገሮችን ገልጿል። በምዕራፍ ሦስት ከገጽ 83-85 ድረስ የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍናን ምንነት፥ ጥንስስ፥ ሂደትና አተገባበር ምን እንደሚመስል ያብራራል። ከገጽ 86-89 የዴቪድ ሂውምን በልማዳዊነት (ተግባራዊነት) (Empiricist) ሥነ-ዕውቀታዊ መሠረት ላይ የታነጸውን ግብረገባዊ ፍልስፍና ያስቃኘናል። በዚህም በድበቁሳዊ (metaphysical) እና ግብረገባዊ (ethical) ነገሮች መካከል ያለውን ክፍተት አጽንኦት መስጠቱንና "የሂውም መቀስ" የተባለውን ዘዴ አስተዋውቋል።

ከገጽ 89-92 ድረስ የጆን ኦስቲንን የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍናና ሕግን በተፈጥሮ ሳይሆን በሉዓላዊ አካል ማብራራቱን ያሳየናል። ከገጽ 93-99 የሃርትን የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና የኦስቲንን በመቃወም የራሱን "የቅቡልነት ሕግ" እሳቤ፥ የተለያዩ ሕግጋትን ዐይነቶችና "የማሕበራዊ እውነታ መርህ"ን እንዴት እንደገለጸ ያስቃኘናል። ከገጽ 99-104 የደርኩንን የሕገ-ሰብዕ

ፍልስፍና፥ ሕግን ፍርድ ቤቶች ከሚሰጡት ትርጉም አንጻር መመልከት፥ ተጽዕኖውና የአመለካከቱን አስከትሎ ዘርዝሯል። ከገጽ 104-108 የሃንስ ኬልስን ሰው ሠራሽ ሕግጋት የስልጣን ተዋረድ ሊኖራቸው እንደሚገባ፥ ይህም የስልጣን ተዋረድ ደግሞ የቅቡልነት ሰንሰለት እንደሚያሻው መግለጹን መሠረቱም "Groundnorm" ሊሆን እንደሚገባ ያብራራበትን አሳይቷል። ከገጽ 108-113 የፉለርን የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና ከውስጣዊ የሞራል ትስስር (ውቅር) ጋር ያለውን እሳቤ፥ መርሆቹ ሊያሟሏቸው ስለሚገቡ መስፈርቶች፥ የሃርትና ፉለርን ክርክር ያብራራል። ከገጽ 113-116 ድረስ የሳቮኒን ሕግ ከማኅበረሰባዊ ሥነ-ልቦና ጋር በማዛመድ የፈታበትንና ሕግጋት እንደማይፈጠሩ ይልቁን ሕግ አውጪው እንደሚያገኛቸው የገለጸበትንና የእሱን ተጽዕኖ አብራርቷል።

በምዕራፍ አራት ስለ ሰው ልጆች ነጻነት እና በመካከላቸው ስላሉት መስተጋብሮች የሚረቅቁት መርሆች ከማኅበረሰቡ ስምምነት ጋር ያላቸውን ቁርኝት ያስቃኘበት ነው። ከገጽ 121-125 ድረስ የማቴሪያሊስቱን ሆብስ ከሰው ልጆች ባሕርይ ጋር በማስተያየት ሕግን በሥራ ላይ ማዋል የሚቻልበትን መንገድ የጠቆመበትንና የማኅበረሰባዊ ውልን ያሳየበትን ይተነትናል። ከገጽ 125-128 የሩሶን ማኅበረሰባዊ ውል፥ ስለ ሕዝባዊ ሉዓላዊነትና ፈቃድ የሞገተውን ይገልጻል። የገጽ 129-132 የግለሰብ መብትና ነጻነት ላይ የሚያተኩርውን እሳቤ አብራርቷል። ከገጽ 133-137 የሮውልስን የፍትሕ ርትዕነትና የማኅበረሰባዊ ውልን እሳቤ ይተነትናል። ከ137-142 የሚልን የጠቀሜታዊነት እሳቤ ላይ የተገነባውን የግለሰብ ነጻነት መነሻውንና መድረሻውን ምን እንደሚመስል፥ እንዲሁም የማኅበረሰባዊ ውልና ግለሰባዊነት መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ይገልጻል።

ከገጽ 143-146 ድረስ (በምዕራፍ አምስት) ስለ ገሃዳዊ ሥነ-ሕግ፥ የተጠነሰሰበትን ምክንያት በማብራራት፥ የአሜሪካውያንና ስካንዴኔቭያው ሕግ የሚፈጠረው የመጀመሪያው በዳኞች ሲል የሁለተኛው ከገጽ 147-152 የሆልምስን ሕግ በአመክንዮ ሳይሆን በልምድ ለመፍታት የሄደበትን ርቀት፥ ምንባባዊ ትርጉምን የተቸበትን ኹነት፥ ከዊሊያም ጄምስ ጋር የነበራቸውን የአሳብ ተዋስኦ ይገልጽልናል። ከገጽ 153-155 ድረስ የፍራንክን ዳኞች በፍርድ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሥነ-ልቦና ተጽዕኖ ሊኖርባቸው እንደሚችል

ያተተበት። ከገጽ 156-160 ድረስ የፓውንድን የማኅበረሰባዊ ሕግ ጥናት፥ ሕግና ማኅበረሰብ ካላቸው መስተጋብር ጋር የተነተነበትን አሳይቷል።ከገጽ 161-164 ስለ ነቂሳዊ ሕግ ዳራዊ ዳሰሳ፥ ስለ Loving Day፥ በተለያዩ የመደብ (ጾታ፥ ቀለም) የተከፈሉትን የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ በመመርኮዝ በቀደመው አስተሳሰብ ላይ የሰጠውን ትችት ያስቃኘናል። ከገጽ 165-167 የድኅረ-ዘመናዊነት እሳቤ ከአፍራሽነትና አንጻራዊነት ጋር በመጣመር በሕግ (ፍልስፍና) ላይ የፈጠረውን ተጽዕኖ ያሳየናል። ከገጽ 167-170 የሃበርማስን ሕግን የተግባቦት ዲስኩር በማስለመድ እንዲስፋፋ ያሳሰበበትን ይተነትናል። ከገጽ 171-176 የአንስታይ ሕግ ፍልስፍና፥ እንዲሁም ይህን ሕግ ለማርቀቅ የተነሱት የአሳብ ሞዴሎች፥ በመቀጠልም ስለዚሁ ዕይታ መዳረሻም ያስቃኘናል። ከገጽ 177-178 ድረስም ሕግና ምጣኔ ሃብት ያላቸውን ቀርኝት ይነግረናል።

ከገጽ 179-182 የብዙኃን ሕግና አተገባበሩ፥ ስለ ሕግ ንቅለ-ተከላና በኢትዮጵያ ያለው (የነበረው) ቦታ፥ እና ስለ ሕግ ስርጸት ይተነትናል። በገጽ 183 የእጓለን (ዶ/ር) አሳብ (በተዋሕዶ ከበረ) በመንተራስ ኢትዮጵያ ውስጥ ለፍልስፍና ያለው ቦታ ዝቅተኛ መሆኑን፥ ይህም ለሕግ ፍልስፍና አለማደግ ምክንያት እንደሆነ፥ በአገራችን አክሱማዊነትና ላሊበላዊነት ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳለው፥ እንዲሁም በቀደሙት የሕግ መጻሕፍት ያሉትን መሉ በሙሉ ከመጠቀም ይልቅ፥ “በተዋሕዶ የመክበርን ጽንሰ-አሳብ ወደ ኢትዮጵያ የሕግ ፍልስፍና ታሪክ ቀይረን እንመረምረው ዘንድ ይገባል።” በማለት የአውሮፓን ከአገር በቀል እሳቤ ጋር አዋሕዶ ጥቅም ላይ ማዋልን እንደ መፍትሔ አሳብ በማቅረብ ይሞግታል። ከገጽ 189-192 ድረስ የዶ/ር ጀምበሬን "ከጥንታዊነት ወደ ዘመናዊነት" እሳቤ በኢትዮጵያ ያሳየውን ተጽዕኖ ይገመግማል።

ከገጽ 193-196 የእኛ አገር የሕግ ፍልስፍና መሠረቱ ምዕራባዊ ወይስ ምሳራቃዊ በሚል መጠይቅ ጥናታዊ ዳሰሳውን ያሳያል፥ ይልቁን በአፋዊ (oral) እና ማኅበረሰባዊ (societal) ኹነት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ይጠቁማል። በማከልም፥ “…ዓለም ላይ እየዞርን ሕግጋትን እንደ ቡፌ ከማንሳት የራሳችንን ሕግጋት ማምረት መቻል ይኖርብናል…” ይላል።

ከገጽ 197-204 (በምዕራፍ ስምንት) ርእዮተ ዓለም ከሕግ ፍልስፍና ጋር ያለውን ቁርኝት ይተነትናል፥ የማካቬሊን ውጤት ተኮር እሳቤ ያብራራል፥ የሄግልን አሳባዊነት (Idealism) በታሪክና አገር-መንግሥት አወቃቀር ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ይነግረናል። ከገጽ 205-207 የቶክቪልን ሲቪክ ማኅበር በመፍጠር በካፒታሊስት እሳቤ ባለው ግለሰብና መንግሥት ከመበዝበዝ እንደሚያድን የሞገተበትን አሳብ ያስተዋውቃል። ከገጽ 208-210 ድረስ የበርክን የወግ አጥባቂነት አስተሳሰብ እና Modern Conservative የተባለበትን ኹነት ይተነትናል። ከገጽ 211-216 የሃሚልተንን የፌደራሊስት እሳቤ፥ የሕገ መንግሥት አስፈላጊነት፥ ከጀፈርሰን ጋር የነበራቸውን እሰጥ አገባ፥ እና የJudicial Review አሠራርን ያብራራል። ከገጽ 216-218 የማርክሲስቶችን (ማርክስን ጨምሮ) ምጣኔ ሃብታዊ፥ ሰብዓዊ (በቁሳዊነት የተቀመረውን) እና ፖለቲካዊ ዕይታ ያስቃኘናል።

ከገጽ 219-221 (በምዕራፍ ዘጠኝ) የሕግንና ቴክኖሎጂን ቁርኝት፥ የኢንተርኔት ጥቅምንና ዳፋውን ይዳስሳል። ከገጽ 222-224 የሰው ሠራሽ አስተውሎት (AI)ን ጥንሰሳ፥ እድገትና አስከትሎት፥ እንዲሁም በዳኞች ተግባር ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ይዳስሳል። ከገጽ 224-227 ድረስ ስለ ጥላቻና ሐሰተኛ ንግግር፥ ስለ Cyberbullying እንዲሁም በ2016ቱ (የግርጎሪሳውያን አቆጣጠር) የአሜሪካ ፕሬዘዳንታዊ ምርጫ ላይ ያስከተለውን ውጤትም ይገልጻል። ከገጽ 227-230 የኢንተርኔት ወንጀል፥ የዘረመል ምሕንድስናና የክሪፕቶከረንሲ ከሕግ ጋር ያላቸውን መስተጋብርና በሰው ልጆች ሕይወት ላይ የተጋረጠውን አደጋ በስፋት ይተነትናል። ከገጽ 231-235 ድረስ ስለ ሰውና እጣፈንታው፥ ግለሰባዊና ማኅበረሰባዊ ግብረገባዊ ጠባይ መዝቀጥ፥ እውነትና ዲበአካላዊነት እንዲሁም ሥነ ዕውቀት ያላቸውን ትስስር፥ ፍትሕ በዓለምአቀፍ የሕግ ሥርዓት እንዴት እንደሚገለጽና የገቢራዊነትን እሳቤ የሚተች ጽሑፍ አስነብቦናል፥ ዴቭ።

ስለ መጽሐፉ ያለኝ አስተያየት፥

1) እጅግ በጣም ጠቃሚ መጽሐፍ መሆኑን የምመሰክረው እስካሁን በአገራችን ከተጻፉ የፍልስፍና ተኮር መጻሕፍት በሆነ አንድ ወጥ ጉዳይ ሰፋና ጠለቅ ያለ ታሪካዊና ሙግታዊ መጽሐፍ ሳነብብ ይህ የመጀመሪያውና ግሩም

መጽሐፍ ነው! የሕግን ፍልስፍና በሰፊው አስተዋውቆናልና ዴቭን (የዚህ መጽሐፍ ደራሲና በአክብሮት ለቀረበኝና በልቡ ሥፍራ ለሰጠኝ) ከልቤ ላመሰግን እወዳለሁ።

2) ይህ መጽሐፍ የታሪክ ስፋቱንና ፈርጀ ቤዙ አሳቦች የተነሱበት በመሆኑ ምናልባትም ከታሪክ ጥቂት ሰዎች ተመርጠው (ሲመረጡ በመካከለኛው ዘመን የነበረ አንድ ታላቅ ፈላስፋ አለ። ስሙም ፍራንሲስኮ ሷሬዝ ይባላል። የሱን የሕግ እሳቤ ቢጠና ምናልባትም ከመካከለኛው ዘመን በዚህ ጉዳይ ሰፊ ነገር የሚገኝበት ነውና ጥቆማዬ ከወዲሁ እነሆ) በሚገባ ተጠንተው (በተለየ primary sources ጥቅም ላይ ውሎ) ቢጻፍ (ዴቭ ቢጽፍልን) ይህን መጽሐፍ ባለ ብዙ ቅጽና ፍሰቱን ተጠብቀ ታሪካዊ የሕግ ፍልስፍናን በሚገባ እንኮመኩማለንና እንደ አሳብ ይህን እላለሁ።

3) መጽሐፉ (እጄ ላይ ያለው ሁለተኛ እትም ነው። በ2014 ዓ.ም. የወጣው) በቀጣዮቹ እትሞች በሥነ-ጽሑፍ ውበትና የውብ ቃላት ተከሽነው ቢቀርቡ መልካም ከዚህ በላይ ሳቢ ይሆናሉ በማለት እነኚህ የአጻጻፍ ማሻሻያዎች ቢኖሩት፡-

4) አሁን ደግሞ በመጽሐፉ ላይ ባሉት አሳቦች ምሉዕነትና ትክክለኝነት ላይ ያለኝን ጥርጣሬ እነሆ።

4.1) "...ሶቅራጠስ...የፍልስፍና ጅማሬና መሠረት ግዑዛዊው ዓለም ሳይሆን ራሱ ሰው መሆን እንዳለበት አስረግጦ አስተምሯል።" ምኑ ጋር ነው ይህንን ያስተማረው? በተለይ በአፍላጦን (Plato) ያወቅነው ሶቅራጠስ ስለ ግዑዙ ዓለም (Physical World or Universe or Cosmos ለማለት ነው) የሚያስተምርና የሚያውቅ (በዚህም ቲሚያስኒ ሎው ድርሳናት ተጠቃሽ ናቸው)፥ ስለ አማልክትና ረቂቅ ባሕርያት (ስለ gods, beings, Forms, asbtract entities; numbers, beauty, knowledge, propostions, belief, love, temperance, pleasure...ወዘተ በቻርሚደስ፥ ፋይሊበስ፥ ፌደረስ፥ ቲያቲተስ፥ ሪፐብሊክ፥ ፌደረስ፥ ሜኖ፥ ሲምፖዚየምና በሌሎቹም ድርሳናቱ አስተምሯል። ሞግቷል።)

ታዲያ ይህ አገላለጽ ምሉዕ ነውን? በተጨማሪ የሱን መንገድ አዲስ የማያደርገው ቀድመውት የነበሩት ሶፊስቶች የተጠቀሙበትን አካሄድ መጠቀሙ ግልጽ ነው።

ለምሳሌ፡- ፕሮታጎራስ አሳቡን የአስተዋወቀው ሰውን መነሻ በማድረግ ነው (ያው perception ላይ ቢያተኩሩም)። በዚህም የፍልስፍና ጅማሬ ሰው እንዲሆን ያሳየ ነው ቢባል እንኳን ከሱ የቀደሙት ሶፊስቶች አሉ። እነ ቴለስም እኮ ስለ Cosmos ይጠይቁ እንጂ ስለ ሰው ከያዙት እሳቤ አንጻር ፍልስፍናቸውን አንጸባርቀዋል። ሌላው ሶቅራጠስ የሚጠቀመው Socratic Dialogue ሚባለው ራሱ ከሶፊስቶች የተወሰደ ነው።

4.2) በገጽ 8 ላይ፥ "...አስተማሪው የነበረውን የአፍላጦንን ዲበአካላዊ ፍልስፍና በመተቸት የራሱን የፍልስፍና ጉዞ የጀመረው አሪስጣጣሊስ..." ይህ አባባል ለምን እንደሚደጋገም ግር ይለኛል። ምናልባትም ስለ እነሱ (Plato and Aristotle) ከsecondary sources ስለ ሚተረክ ይሆናል እንጂ የፕሌቶን መጻሕፍት አንብቦ የአርስቶትልን ለቀጠለ የሁለቱ አስተሳሰብ ተቀራራቢ እና አሪስጣጣሊስ የፕሌቶን ትቶ የራሱን የጀመረ ሳይሆን አሻሽሎና አሳምሮ ያቀረበ ብሎ ለመደምደም ያስደፍራል። ለምሳሌ የአሪስጣጣሊስ Metaphysics ድርሳኑ መጽሐፍ አንድ ላይ የፕሌቶን አሳብ ያነሳና በአብዛኛው ተስማምቶ ፕሌቶ ስላብራራው የForm እሳቤ ጉድለት (ማለትም perceptible መሆን ስለሚጎድለው) አሳይቶ መጽሐፍ ሁለት ላይ በፕሌቶ እሳቤ በመንተራስ እነኚህ Forms የሚታወቁበትን መንገድ Four Causes ያስተዋውቃል።

ሌላው ፕሌቶ ሶፊስቶችን የተቃወመበትን በመደገፍ የእሱን ዲበቁሳዊ እሳቤ ያሞግሳል፥ "...Plato was in a sense not wrong in saying that sophistic deals with that which is not...." (86, book 6)

"...Plato was not wrong when he said that the sophist spends his time on non-being..." (160, book 11)

"...Plato was not far wrong when he said that there are as many Forms as there are many kinds of natural things..." (171, book 12)

በPhysics ድርሳኑ ደግሞ፥

"...I mention Plato because...he alone tried to say what it is..." (53, book 4)

"...Plato alone asserts the creation of time, saying that it is simulaneous with the world, and that the world came into being..." (130, book ...ወዘተ። ስለዚህ አሪስጣጣሊስ የአፍላጦንን እሳቤ የጣለ አድርጎ ከመሳል አሻሽሎና ተግባራዊ (ancient Empircist ሊባል ይችላል) እንዲሆን አድርጎ የአስተማሪውን ሥራ በውበት የገለጸ ተማሪ ቢባል መልካም ነው።

4.3) ስለ ፍርድ ሥርዓቱና የሶቅራጠስን ኹኔታ ከክሪቶ በተጨማሪ በዩቲፍሮና አፖሎጂ በደንብ ቢከሸኑና ቢቀርቡ ሙሉ ምስሉን ማግኘትና ይበልጥ ታሪኩን ከፍልስፍናው ጋር ማጣጣም ይቻል ነበር።

4.4) "ምንም እንኳን የሚሰጡት መልስ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የማይመጥን ቢመስልም..." (ገጽ 16)። አውሮፓ ውስጥ ሁለት መጻሕፍትን የማያነብብ "ፋራ" ነው ወይም የአውሮፓን እድገት ምስጢር አያውቅም። እነሱም መጽሐፍ ቅዱስ እና የፕሌቶ ሊፐብሊክ ናቸው (ሁለቱን ካነበብኩ በኃላ እንዴት እንዳደጉ ይበልጥ ገብቶኛል)። አሁንም ድርስ ያላቸው ተጽዕኖ የትዬለሌ ነው (የመካነ-አእምሮ (university) ተማሪዎች የአስተሳሰብ መላሸቅን አስተውሎ ፕሮፌሰር አለን ብሉም The Closing of American Mind መጽሐፉ ላይ የቅዱሳት መጻሕፍትንና የፕሌቶን ሪፐብሊክ ተጠቅሞ ነው የሞገተው)። እና፥ ደቬ፥ የጠቀስኩት አሳብህ አንተም ምታምንበት ይመስላልና ቢስተካከል ባይ ነኝ። እንደየዘውጋቸውና ዐውዳቸው ይነበባሉ እንጂ እንዲህ የታሪክ (ታሪክ ለዋጭ) ሰነዶችን judge ማድረግ ጥሩ አይመስለኝም። እንደ እኔ እምነት እንደ አገርም ሆነ አህጉር መጽሐፍ ቅዱስን፥ የፕሌቶንና የአርስቶትልን መጻሕፍት ብናጠና ፕሌቶ እንዳለው

ከዋሻችን እንወጣለን። እነኚህ መጻሕፍት ያላቸው ግለሰባዊና አገራዊ ፋይዳ ብዙ ነውና። በተጨማሪ የእነሱ መጻሕፍት አሳቢ (ምክንያታዊ፥ ርቱዕና ስምሙ ምክንያት) መሪና ሕዝብ እንዲፈጠርና በተለይም እንደኛ ዐይነት አገር "ሶፊስት ፖለቲከኞች" ለበዙባት እውነትን ከውሸት፥ ትክክል ያልሆነውን ትክክል ካልሆነው ነገር እንድንለይ የሚያግዙ ዘመን አይሽሬ መጻሕፍት ናቸው። በእኔ አመለካከት እነሱ (ሶቅራጠስ፥ ፕሌቶ፥ እና አርስቶትል) በሕይወት ቢኖሩ የእኛን አገር ፖለቲከኞች ሶፊስቶች ናቸውና ተጠንቀቁ እንደሚሉ እርግጠኛ ነኝ።

4.5) ሌላው፥ ዶ.ር፥ ሶቅራጠስን በሚገባ ያወቅነው በፕሌቶ ድርሳናት ነውና የሁለቱን አስተሳሰብ ለያይቶ ማቅረብን እንዴት ታየዋለህ? ማለት በሶቅራጠስ ውስጥ ፕሌቶ አለና።

4.6) በገጽ 23ና 223 ላይ ስለ ድኅረ ዘመናዊነት ነግረኸናል። ዘመኑ የድኅረ ዘመናዊነት ነው ብለህ ታምናለህ፥ ዶ.ር?

ድኅረ ዘመናዊነት ራሱን በራሱ የሚቃወምና መቼም እውነት መሆን የማይችል አመለካከት እንደሆነ በተለይ በAnalytical Philosophy ከ1950ዎቹ ጀምሮ ከወዳጆቹ Logical Positivism እና Verificationism ጋር የተወቃ እሳቤ እንደሆነ አይጠፋህም።

4.7) በገጽ 30 ላይ ቀጥታ ከአሪስጣጣሊስ ወደ ቤንትሃም የUtilitarian እሳቤ መሻገርህ እንዴት ነው? እናም ደግሞ እሱን የዚህ እሳቤ ጠንሳሽ ማድረግ በታሪክ ትክክለኛ ሂደት ነው? (በብዙ ዓመታት ኢፒኩሪያን ይቀድሙታል አይደል?)

4. የእነ ካንት እሳቤ መጠቀሱ መልካም ሆኖ በፖለቲካም ሆነ ሌሎች እሳቤዎች የዲበቁሳዊ ዳራዊ አስተሳሰባቸውን (Naturalist Atheist መሆን፥ Materialist or Scientific Atheist መሆን፥ Agnostic መሆን፥ Deist መሆን፥ Pantheist መሆን፥ Panentheist መሆን፥ Acognostist መሆን፥ Christian or non-Christian Theist መሆንን...) በሰፊው አለመዳሰስህ የአሳባቸውን ጥንስስ መነሻና ምሉዕ ምስሉን እንዳናውቅ የሚጋርድ ይመስለኛል። እሱም ቢታሰብበት ለማለት ነው። ያው ለምሳሌ ያህል ካንት

አግኖስቲክ መሆኑና ሆብስ ደግሞ ማቴሪያሊስት ኤቲስት መሆኑና እነ አኲዬናስ ክርስቲያን ቲይስት በመሆናቸው ስለሰውና ፖለቲካ የነበራቸው አመለካከት ላይ ተጽዕኖ እንደነበረው ከታሪክ አይተናል።

4.9) በገጽ 62 ላይ ቅዱስ ቶማስ አኲዬናስ "ደደቡ በሬ" (the dumb ox) ተብሎ የተጠራበት የአንተ ማብራሪያ ስህተት ያለበት ይመስለኛል። ይህም፥ "...ትምህርት ብዙም ሊዘልቀው ስላልቻለ..." ብለሃል። በመካከለኛው ዘመን ስለ ነበረው ፍልስፍና ታሪክ ያጠናው ሊቅ አንቶኒ ኬኒ (ፕሮፌሰር) እንዲህ ብሏል፥ "...as a student his tacitunity (silence by nature) and corpulence (obese by weight) earned him the nickname 'the dumb ox'. Albert quickly appreciated his astonishing talent, and predicted that the dumb ox would fill the whole world with his bellowing (yelling or roaring)..." ታላቁ አስተማሪው (Albert the Great) እንደመሰከረው ሥራው ዓለምን ሞላ። ለተሐድሶም መነሻ ሆነ።

ብቻ ብዙ የምጽፈው ነበረኝ ወደ ዋናው ነጥቤና ትዝብቴ ልዝለል። ስለ ሶፊስቶች ከገጽ 48-51 በሰፊው አስቃኝተኸናል። ከመጽሐፍህም እንዳስተዋልኩት የእጓለን (ዶ/ር) ጽሑፍና አሳብ በሰፊው ተጠቅመኻል። መቼስ ይህቺን የእጓለ አሳብ አይተኻታል፥ "...የቀድሞ ዘመን ሶፊስቶች የጥቅም አገልጋይ የሆነ ትምህርት በጊዜያችንም ስሙን ለውጦ ፕራግማቲዝም በሚባል የአሜሪካ ፍልስፍና አማካኝነት ዘመናዊ ዳባ ለብሶ ወደ የእልፍኝ አዳራሹ ለመግባት ይጠይቃል..." (የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ፥ ገጽ 93) በማለት ፕራግማቲዝምን (ገቢራዊነትን) ከሶፊስቶች ዕይታ ጋር በማመሳሰል ሞግተዋል።

ይህ እሳቤ ባንተም መጽሐፍ በገጽ 150 ላይ የሆልምስን ፍልስፍና ስትነግረን ስለ ዊሊያም ጄምስም እሳቤ፥ ፕራግማቲዝም ጠቅሰኻል። በተጨማሪ በግልጽ ባይሆንም በተዘዋዋሪ ከገጽ 232-235 ይህን አስተሳሰብ አንተ ከያዝከው (ያው በግልጽ ባይጻፍም የጉድኝታዊ እውነት አመለካከት) የእውነት ነባቤ ቃል (theory) በመነሳት ተችተኃል። እንዲሁም የተስፋዬ ሮበሌ (ዶ/ር) መጽሐፍ፥ ሥነ አመክንዮ፥ አንብበኻልም እንደዋቢነትም

ተጠቅመኻል። እሳቸው በገጽ 121 (በመጽሐፋቸው)፥ "...ገቢራዊነት (ፕራግማቲዝም) የተባለውን የፍልስፍና አካሄድ የሚከተሉ ሰዎች፥ እውነት ከውጤት አንጻር ወይም ከምታመጣው በረከት አኳያ ብቻ መታየት አለባት ባዮች ናቸው...በኢትዮጵያ ውስጥ በቅርቡ የተቋቋመ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፥ ይህን የገቢራዊነት ፍልስፍና እንደሚከተል በግልጽ ይፋ አድርጓል። ርዕዮተ ዓለሞችና አንድምታቸው (ብልጹግና ፓርቲ፤ ጥር 2012 ዓ.ም)፤ ገጽ 99-101። ይህ መቼም አስደንጋጭ አቋም ነው..." በማለት ከገጽ 121-124 ድረስ ገቢራዊነት የተሳሳተ የእውነት ምልከታ ያለው ዕይታ እንደሆነ ይሞግታሉ፥ ዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌ። እና ዴቭ ይህን አስተሳሰብ (ገቢራዊነት) ለምን አልሞገትከውም? በዚህም ከውጪ የተቀዳውን ይህን ርዕዮተ ዓለም አለመሞገትህ የአንተን መጽሐፍ ዓላማ (1ኛውንና 3ኛውን) የሚያጎድል ይመስለኛል። አሁን ፕራግማቲዝም ምንድነው? አሜሪካውያን አቀንቃኞች እንማን ናቸው? የአስተሳሰቡ እድገትና ውድቀት ምን ይመስላል የሚለውን እነሆ፤ (ታሪካዊ ዳራውን ማወቅ ለርቱዕ ምክንያታዊ ሙግትና የተሻለ ርዕዮተ ዓለም ጥቆማ ያግዛል) የፕራግማቲዝም እንቅስቃሴ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎቹ ላይ በስፋት በአሜሪካ የተቀነቀነ ነባቤ ቃል (Theory) ነው። በቻርልስ ሳንደርስ ፒርስ ተጠንስሶ በጆን ዶዊ የተስፋፋው ይህ አመለካከት የተለያየ መልክ (version) ቢኖረውም የጋራ ጭብጡ እውነትን ከሚመጣው ውጤት (consequence) አንጻር የሚፈታ ነባቤ ቃል ነው። በጊዜው የተወደሰ ቢሆንም በተለያዩ ነገሮችና የአሳብ ማዕቀፎች ተሞክሮ ያልሠራ በመሆኑ የወደቀ ነባቤ ቃል እንደሆነ ልሂቃን ይመሰክራሉ (Dr. Geisler, A History of Western Philosophy, p.250, vol.2)።

ፒርስ የእውነትን ጠባይ (the nature of truth) በተለያየ መልኩ ገልጾታል።

1) Transcendental truth፡- የነገሮችን እውነተኛ ጠባይ ያመለክታል።

2) Complex truth፡- የዐዋጆችን ገሃዳዊ እውነታ (reality) ከሥነ ዕውቀታዊ እምነት (epistemological belief) ጋር ያለውን እውነታ (truth) ይመለከታል።

3) Logical truth፡- የዐዋጆችን ከገሃዳዊው ዓለም ጋር ያለው ዝምድና እውነትነት ይመለከታል።

በዚህም ለፒርስ አንድ ዐዋጅ (proposition) እውነት ወይንም ውሸት የሚሆነው ከልምድ ወይም ሙከራ (experience) ጋር ባለው ቁርኝት ነው። ልምዱ አፍራሽ ነገርን የማይሰጥ ከሆነ ዐዋጁ እውነት ነው። የሚሰጥ ከሆነ ግን በተቃራኒው። በዚህም አንድ ዐዋጅ እውነት የሚሆነው empirically falsify የሚደረግ ካልሆነ ብቻ ነው።

ለዊሊያም ጄምስ (ሌላኛው አሜሪካዊ Radical Empiricist or Pragmatist) የአንድ አሳብ እውነትነት የሚረጋገጠው (testing of idea) ለአሳቡ እውነትነትም ሆነ ግብረገባዊ ኹነት "ነገሩ ይሠራል?" ("Does it work?")ን ሲያሟላ ነው። ወይንም አንድ አሳብ በራሱ እውነት ነው የሚባል ሳይሆን ያአሳብ እውነት እንዲሆንና በገሃዱ ዓለም ላይ የሚፈጥረው ልዩነት ምንድን ነው የሚለው ላይ የሚያተኩር ነባቤ ቃል ነው። በጄምስ ንግግር፥ "What concrete difference will its being true make in one's actual life?" ሌላው ግብረገባዊ (Moral belief) ጉዳይም የነገሩ ትክክለኝነትና ስህተት የሚለካው የሚያስከትለው (consequence) ነገር ታይቶ፥ ማለትም በረዥም ጊዜ ያመጣል ተብሎ የሚታሰበው መልካም ነገር ተሰልቶ ነው። ይህ የጄምስ አንድን ነገር ከውጤቱ የመመልከት እሳቤው በሐይማኖታዊ ጉዳይም ላይ ተንጸባርቋል። ለእሱ በሐይማኖት ውስጥ አንገብጋቢው ነገር የእምነቱ አስተምህሮት ሳይሆን ልምምዱ ነው (ይህ ከፒቲይዝም እሳቤ ጋር ይጣጣማል)። እውነት ጉድኝታዊ (correspondence፡ which agrees with the reality) ሳይሆን በሰው ልጆች አሳብና ልምምድ የሚታይ ባሕርይ ያለው ነው። እውነት ለጄምስ ወደፊት ከሚደረጉ ነገሮች ጋር የተቆራኘ ነው። ይህም ከሚመጣው ነገር ጋር እና ከሚሰጠው እርካታ ጋር የተሳሰረ ነው። ጄምስ እንደ ገቢራዊነት አቀንቃኝ በሰው ልጆች በዓለም ላይ ተጽዕኖ ማምጣት መቻልና ነጻ መሆናቸው ላይ አጽንዖት ይሰጣል። ጄምስ እሳቤው እንደጠበቀው የሚሠራ አይደለም። ምክንያቱም ገቢራዊነቱ እንዲሠራ ለእያንዳንዱ ተግባር የሚያስከትለውን ውጤት ሁሉ ለማወቅ የሰው ልጆች አይችሉምና!

ሌላኛው አሜሪካዊ የፕራግማቲዝም አፋፉሚ ጆን ዶዊ ሲሆን የHumanist Manifesto አቀንቃኝ፥ የትምህርት ጉዳይን ወደ Secular Humanism ለመለወጥ በተደረገው ጥረት መሪም ነበር። እሳቤው ገንዘብ-አድራጊነት (ቁሳዊነት) (Instrumentalism) ወይንም ተራማጅነት (Progressivism) ወይም ገቢራዊ ነበር። ይህም በማኅበራዊና ፖለቲካዊ ፍልስፍናም ላይ ገቢራዊ እሳቤውን በማስረጽ ማኅበረሰባዊ ችግርን ለመፍታትና ለማደስ ነባቤ ቃሉን እንዲጠቀሙ ነው።

ለዶዊ ቁሳዊነት (መገልገያነት) እሳቤ በአንድ ማኅበረሰብ እንዲያድግ ትምህርት ነው። በትምህርት (Instrumental ነው) አንደኛ፥ ያለውን ሳይንስ ወይንም ማንኛውንም አጀንዳ ለመተቸት፥ ከዛም፥ ሁለተኛ ላይ አሁን ያለውን ማኅበረሰባዊ ኹኔታ (ጉዳይ) ለመድረስ አሮጌውን ከአስፈላጊው በመለየት አሻሽሎ መገንባት (reconstruct ማድረግ) ነው። ለመገልገያው ቁልፍ ነገር ደግሞ ለምምድ ነው። በዚህም ዶዊ ያለውን ነገር በመተቸት አዲስን አሳብ (ርዕዮተ ዓለም) በማስረጽ ወይንም በድጋሚ ትርጉም በመስጠት (reinterpretation) ምንም የማይለወጥ እውነት እንደሌለ ማሳየትና የለውጥና ልምምድ ቅጥልጥሎሽ እንደሆነ ማንጸባረቅ ግቡ ነው። በዚህም ዶዊ Meliorist ሲሆን ዓለም በሰዎች ጥረት የምትሻሻል ናት ይላል"...there are no absolutes and no unchangeable truths because there is a continuum of change and experience...".

Reflecting Thinkingን የሚያበረታታ ሲሆን ይህም አርጅተዋል ለሚባሉ ችግሮች አዳዲስ መፍትሔዎችን ለማበጀት ነው። ይህ አስተሳሰብ አምስት ደረጃዎች ሲኖሩት፡- 1) ለሆነ ወጥ (particular) ችግር ብዙም ግልጽ ያልሆነ (vague) አማራጭን ማሰብ፥ 2) ችግሩን በዕውቀታዊ መንገድ ጠቃሚ (pros) እና ጎጂ (cons) ጎኑን መገምገም፥ 3) አግባብ አላቸው ተብለው የሚታሰቡ መላምቶችን ማሰብ፥ 4) በቀደሙት ልምዶች በመንተራስ ምንጨታዊ ዐዋጅን መጠቀም (deduction)፥ እና 5) እነኚህን መላምቶች መስተጋብአዊ በሆነ መንገድ በልምድ መሞከርን ይገልጻል።

ጋይዝለር እንየሚሉን የዶዊ የትምህርት ሥርዓት ተሞክሮ ከሽፏል። አልሠራም። በብዙ ትውልዶች ብዙ ጊዜ ተሞክሮ የገቢራዊነትንም እሳቤ

ገደል የከተተ አስተሳሰብ ነው። በግብረገብና እውነት ያለው የአንጻራዊነት አመለካከት ራስን በራስ የሚቃወም (self-defeating) ነውና እንደማያስፈልግ ታይቷል። የዶዊ ማኅበረሰባዊ ሽግግር (ሂደት) (social progress) ትርጉም አልባ ነው። ምክንያቱም ሊለካበት የሚችል የማይለወጥ ግብረገባዊ መለኪያ የለውምና። ይህም progressivism የተመሠረተው በምኞት ላይ እንደሆነ አሳይቷል። ዶዊ "ስኬት" ወይም "ለውጥ" በፍልስፍናዊ መንገድ ያልተረጋገጡ ናቸው። እንዲሁም ለሰው ልጆች ስኬትና ለውጥ ምክንያት ይሆኑ ዘንድ ያቀረባቸው ልምድ (experience) እና ሳይንስ ምኞት ናቸው (ከምኞት አልዘለሉም)። ይባሱን ሳይንስና ልምድ ባደገ ቁጥር የሰው ልጆች ግብረገባዊ ኹኔታም እየላሸቀ መምጣቱ ገቢራዊነት ከምኞት እንዳያልፍ አድርጎታል።

ሰለ ገቢራዊነት አይተናል። ብልጽግናም ይህን ርዕዮተ ዓለም እንደሚያቀነቅን ተመልክተናል። ከዚህ በታች ደግሞ በመደመር መጽሐፍ የተብራራውን የዚህን ነባቤ ቃል መልክ ተመልክተን። ያልሠራበትን አንድ ትልቅ ምሳሌ ጠቅሰን ለመፍትሔ የሚሆን አሳብ ተጠቅሶ አሳቤን እጠቀልላለሁ። አሁንም አንባቢ እንዲረዳ የምፈልገው ይህ የርዕዮተ ዓለም ሙግት እንጂ የብሔር ወይንም የሐይማኖት ንትርክ እንዳልሆነ ልብ ይልሏ! ዐብይ አህመድ (ዶ/ር) በመደመር መጽሐፋቸው ከገጽ 13-34 አዲሱን አሳባቸውን (መደመር) ለማስዋወቅና ለመገንባት (reconstruct ለማድረግ) በኢትዮጵያ ውስጥ ቀድመው የተሞከሩትን ርዕዮተ ዓለማት ያስቃኙናል። ከዛም አብዮታዊ ዴሞክራሲ፥ ሶሻሊዝምና ሊበራል ዴሞክራሲ በአገራችን ተሞክረው ለምን እንዳልሠሩ ይጠቁማሉ። በተለይም ከገጽ 32-34 ድረስ "መደመር"ን ከማብራራታቸው በፊት የእነዛን ርዕዮተ ዓለማት ድካም ይዘረዝራሉ።

ያው ፕራግማቲዝም ራሱን በራሱ የሚቃወም አሳብ ነውና እሳቸው በጊዜውም በጊዜው ሂደትም ርዕዮታቸው ሌሎችን በተቹበት ማዕቀፍ መግባቱን የሚያሳይ ጽሑፍ በዚህ መልኩ ሰድረዋል።

1) "...ባለፉት አምስት አሥርት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ትርምስ ከውጪ ያገኘነውን ዕውቀት ከሀገራችን ሁኔታ ጋር በደፈናው

ስናላትመው የተፈጠረ ችግር ነው...” (ገጽ 33) በዚህ የእሳቸው ገቢራዊነት እሳቤ ይህ ትችት አይመለከተውም?

2) “...በምዕራብ ፖለቲካ እየማልንና እየተገዘትን የሀገራችንንና የሕዝባችንን ችግር ከፈረንጆቹ ማሕቀፎች ወጥተን ማሰላሰል አልቻልንም...” ይህ ትችት የእሳቸው ፕራግማቲዝምን (የአሜሪካ ውልድ የሆነው ርዕዮትን) አይመለከትም? (መሞከር ባይኖርበትም) ተሞክሮ ሠርቷል?

3) “...ርዕዮቶቹን በእኛ አገር ተግባራዊ ብናደርጋቸው ምን ሊፈጠር ይችላል?” ብለው በምናባቸው ለመሳል እንኳን አልሞከሩም።” (ገጽ 34) የእሳቸው ገቢራዊነት ይህን ያህል ታስቦበታል? ከታሰበበትስ ይህ ሁሉ (ስፍር ቁጥር የሌለው) ችግር ከየት መጣ? የገቢራዊነት መሞከር ውጤት አይደለምን? (ሁለም ባይሆንም)

4) “...በዓለም ላይ የሚቀነቀኑ ፍልስፍናዎችን በመዳሰስ ቁምነገራቸውን ብቻ እንደ አስፈላጊነቱ እየወሰድን ራሳችን የምንፈትለው ችግር ፈቺ እሳቤ ያስፈልገናል።” (ገጽ 34) የገቢራዊነት እሳቤን ከዚህ በፊት ያሉት ርዕዮቶች ምንም እንኳን ባይሠሩም ይህ ያዋጣል ብለው እንደተጠቀሙት ግልጹ ነው። ይህ አሳብ “አዲስ ርዕዮት” በሚል እንደ ርዕዮት ዓለም ትውውቅ ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይነት ያለው እንጂ ችግር ፈቺነቱ ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ ብዙ ዳፋ ያለው አይደለምን?

5) በመቀጠልም የፕራግማቲስቶች አካሄድ የሆነውን የቀደመውን አስተሳሰብ ተችቶ አዲስን አሳብ የማስተዋወቅንና የመሞከርን መንገድ በገጽ 35-36 የመደመርን እሳቤና ዓለማ ያስተዋውቁናል።

በዚህም፥ “...መደመር ከችግር ትንተና አንጻር አገር በቀል ነው። ከመፍትሔ ፍለጋ አንጻር ደግሞ ከአገር ውስጥም፥ ከውጭም ትምህርት በመውሰድ የተቀመረ ነው።” ይሉንና ከገጽ 36-76 ድረስ የመደመርን ዓላማ፥ መሠረታውያንና ሳንካዎች ይዳስሳሉ። በተለይም ከገጽ 77-90 ድረስ ትልቅ ችግር ብለው የሚያስቡትን ጭቆና ከአገረ መንግሥት ግንባታ ጋር እንዴት እንደታየ በመግለጽ ገጽ 91 ላይ “ጭቆናን በሁለንተናዊ መልኩ አስወግዶ ሕዝብን የአገር ባለቤት በማድረግ የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት

የሚያረጋግጥ ሥርዓት ያስፈልጋል።” በማለት ወደ መፍትሔ አሳባቸው ይዘልቃሉ። በገጽ 103 ላይ ምን ዐይነት ዴሞክራሲ ያስፈልጋል? በሚለው ርዕስ ሥር፥ “የምንዘረጋው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሰው ልጆችን ተደማሪ ፍላጎቶች ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል...” በማለት ልክ እንደ ዊሊያም ጀምስ ደግሞ ስለሰው ልጆች ነጻነት ያላቸውን አመለካከት ይግልጻሉ፥ “...በመደመር እሳቤ መሠረት የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታውን የመበየን ዕምቅ ዐቅምና ነጻ ፈቃድ ያለው ፍጥረት ነው...” ይሉናል።

በስተመጨረሻም በገቢራዊነት የተቀመረውን አሳባቸውን መሳካት በመመኘት (ምኞት በመግለጽ) አሳባቸውን ይጠቀልላሉ። “...የመደመር እሳቤ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ገብቶ ሁላችንም ተደምረን መለወጥና ማረጋገጥ እንችል ዘንድ መሠረታዊ ሐሳባችን በየደረጃው በተለያየ መንገድ ማዳረስ ያስፈልጋል...እንደ አንድ ሕዝብ ተባብረን ከፈጸምናቸው በእርግጠኝነት በኢትዮጵያ ሰማይ ሥር ነገ ከዛሬ የተሻለ ይሆናል...” ብለው ምናልባትም የጎደለ ነገር አለና አሳቦት ምሉዕ እንዲሆን ምን እናድርግ ብለን ብንጠይቃቸው፥ “...ሁሉንም እሴቶቻችን ደምረን፥ ያለፉትን ጥፋቶችን እያረምን በይቅርታ በማለፍ፥ የወደፊቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት በፍቅርና በአንድነት እንነሳ።” (ገጽ 270)።

አንባቢ እንግዲህ የእሳቸው አሳብ ከአሜሪካውያኑ ገቢራዊ አስተሳሰብ አቀንቃኞች ጋር ምን ያህል ተመሳሳይነት እንዳለው ለመጠቆምና ለመረዳት አይቸገርም። የቀደመውን መተቸት፥ አዲስ ገቢራዊ አሳብ ማስተዋወቅ፥ በአፈጻጸም ሂደት ገቢራዊነት ላይ መመሥረት፥ ውጤቱን በመመልከት መንቀሳቀስ፥ እና ትልቅ ምኞትን (የሁሉንም ሰው መደመር) መግለጽ።

የዚህ ርዕዮት (ገቢራዊነት) ትግበራ ላይ ከታየው ድካም አንድ ምሳሌ እንጥቀስ። እሱም የፌደራሉ መንግሥት ከሕወሓት ጋር ባለመስማማት የተፈጠረውን ጦርነት መጥቀስ ይቻላል። (ይህን ስጠቅስ አንድም ለሞቱት የሰው ልጆች ቤተሰቦች መጽናናትን እየተመኘሁ። በጦርነቱ የተጎዱትን ሁሉ እግዚአብሔር ልባቸውን እንዲጠግን፥ ለመሪዎችና ለአገራችን ሕዝቦችም ሁሉ የሁለንተና ፈውስና ጥበብ እንዲበዛ እየተመኘሁና እየጸለይኩ ነው) ይህንን ውጊያ ቅድመ-ጦርነትና ድኅረ-ጦርነት ብለን ብንከፍል።

የገቢራዊነት እሳቤ ባይሞከርና (ፍትሕ ከኩድኝታዊ እውነት ጋር ተስማምቶ የቀረበ ቢሆን)፡-

1) ቀድሞውንም የሕዋሓትን ጥቂት አመራሮች ብቻ ምንም ዐይነት ጥቃት ከመካሄዱ በፊት ሠርተዋል ተብለው በሚታሰቡት ወንጀሎች ይቅርታው ለእግዜር ፍትሕ ለሰው ተብሎ ተጠያቂ ማድረግና ያ ጦርነት ከመከሰቱ በፊት መከላከል ይቻል ነበር፥ ገቢራዊነት ያንን አልፈቀደም፥

2) ከጦርነቱም መገባደጃ ማግስት አቦይ ስብሓት የመፈታታቸው ሚሥጥር ግልጽ ባልሆነበት በገቢራዊነት ውጤት ተኮር እሳቤና ለዚህ እሳቤ አፈጻጸም የቀረበው "የይቅርታ" መስፈጸሚያ መንገድ በሚያስገርም መልኩ ተንጸባርቋል።

በሁለቱም ነጥቦች የገቢራዊነት እሳቤ በትልቁ ታይቷል። በሁለተኛው ነጥብ ላይ እሳቸው ከእስር ሲለቀቁ የይቅርታውን አሳብ ሕዝቡ በተለያየ መንገድ ሊመለከተውና ሊቀበለው ይችላል።

2.1) አንደኛ የመንግሥት ውሳኔ ስለሆነ ይህን (እንደ ቀደመው ሥርዓት) መጠየቅ ምንም ዋጋ የለውም በማለት፥

2.2) ያው "ይቅርታ" በአማኙ ልብ ያለውን ከፍተኛ ሥፍራ በማሰብ "እንደው በሞት ከሚቀጡ በይቅርታ ይኑሩ" በሚል ቅቡልነት ሊኖረው ይችላል በሚል፥

2.3) "ታሪካዊ ተውኔቶች" በሚለው በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተውን የጸጋዬ ገ/መድኅን (ሎሬት) ጽሑፍ ከገጽ 151-159 ድረስ "አንኮበር፤ 1875 ዓ.ም.፤ ችሎት" ላይ የአጼ ዩሐንስ ቁልፍ ሰው የሆኑትን መሸሻ ሰይፉን የአጼ ሚኒልክ ወታደሮች ማርከው ሸንጎ ባቆሟቸው ጊዜ የፍርድ ሂደቱ ምን ሊሆን ይገባል ብለው ሲጠይቋቸው አብዛኛዎቹ ከባባድ ቅጣት እንዲሰጥ ሲጠይቁ፥ የአጼ ሚኒልክ የቅርብ አማካሪ የሆኑት ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) መሸሻን ለዲፕሎማሲያዊ ስምምነት እንዲውል አሳብ ያቀርባሉ። ማለትም መሸሻን በመግደል ምንም እንደማይጠቀሙና ይልቁን ለአጼ ዩሐንስ በመመለስ እሳቸው ያቀረቡትን መሣሪያ መለዋወጥ ይሻላል በማለት አሳብ ሲያቀርቡ ሚኒልክም (አጼ) ይስማማሉ።

ምናልባትም የአቦይ ስብሓት መፈታትና በተፈቱ በማግስቱ የጆ ባይደን ስልክ መደወል (ምናልባትም የአግዋን ጉዳይ ለመነጋገር) ትልቅ ዲፕሎማሲያዊ ልውውጥ ለማድረግ ይሆናል ብሎ የሚያስብም ይኖራል።

ይህም ሆኖ የዚህ ርዕዮተ ዓለም አስተሳሰብ ድካም እንዳለበት ተሞክሮ ታይቷል። ስለዚህም እንደ አማኝና መኃል ከተማ እንዳደገ ወጣት ዴሞክራሲን በመደመር ስም ከገቢራዊነት ጋር አዳቅሎ ከመሞከር ከጉድኝታዊ (correspondence theory of truth) ጋር የእውነት አስተሳሰብ ጋር ሥራ ላይ እንዲወል ማድረግ ለአገራችን ደኅንነትና ሰላም ትልቅ መፍትሔ ያመጣል። በእሳቸው አሳብ አሳቤን ልቋጨው፥ "...ማንኛውም ርዕዮተ ዓለም ትምህርት የምንቀስምበትና መልካሙን ወስደን ሌላውን ራሳችን የምንሞላው እንጂ የማሰቢያ ማሕቀፋችን ሆኖ ምለን የምንገዛበት መሆን አይገባውም (33)...ስለዚህም ከኢትዮጵያውያን መሠረታዊ ሥሪት የሚነሳ፥ ችግሮቻችንን ሊፈታ የሚችል...ኢትዮጵያዊ ፍልስፍና ያስፈልገናል።" (ገጽ 34) ስለዚህ ገቢራዊ ዴሞክራሲ የሚያዋጣን አይመስለኝም። የሚያዋጣን ነባራዊ እውነታ ላይ በመመሥረት የሚታወቀው ጉድኝታዊ የእውነት እሳቤ ያለው ዴሞክራሲ ያስፈልገናል።

Reviewer:- **የኬሚካል ኢንጅነሪንግ ምሩቅና የሥነ-መለኮት ተማሪ፥ የሺጥላ ይገዙ።**

*የመፅሐፉ ርዕስ:- የኢትዮጲያ ረቂቅ ፍልስፍና*
*ደራሲ:- ወልደጊዮርጊስ ይሁኔ*
*አሳታሚ:- ፀጋ ማርያም ማተሚያ ቤት*
*የገፅ ብዛት:- 260*

በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የፍልስፍና ፕሮፌሰር የነበረው ካናዳዊው ክላውድ ሰምነር ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጲያ ፍልስፍና በሚል በሁለት ቅፅ ሰንዶ አቅርቦልናል። ነገር ግን ይህ ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ ሰነባብቷል። ክላውድ ሰምነር የስነፅሁፍ ተመራማሪ ሲሆን የኢትዮጲያን የስነፅሁፍ ዘመን በሁለት በመክፈል ያጠና ምሁር ነው። ከእነሱም ፍልስፍናዊ ይዘት አላቸው ካላቸው ድርሳናት የሀተታ ዘርአያቆብ እና ሀተታ ወልደህይወት ይጠቀሱበታል። ሆኖም ሁሉንም በዘርፉ ያሉ ምሁራን የሚያስማማ ጉዳይ አልሆነም። ገሚሱ ክላውድ የምዕራባዊ ዕሳቤ ላይ የተመሰረተ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ማለትም እንደምዕራባውያኑ ለማሰብ የሚሞክር ኢትዮጵያዊ አለ ለማለት ታስቦ እንደተጠና እንስተው የኢትዮጲያን ፍልስፍና የምናጠናበት የራሳችን ስነዘዴ ሊኖረን ይገባል ብለው የሚተቹ አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ እውነትም ዘርዓያዕቆብ በ16ተኛው ክፍለ ዘመን ተከስቶ የነበረ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ነው በማለት የሚከራከሩም አሉ። ኢትዮጵያ የራሷ ፍልስፍና የላትም የሚሉም አልጠፉም።

የመፅሐፉ ደራሲ ይህን መፅሐፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳውን ገፊ ምክንያት ሲናገር...አንደኛ የፕሮፌሰርነት እና የዶክተርነት ማዕረግ ከስማቸው ፊት አንጠልጥለው ለነገሮች የተሻለ ግንዛቤና አረዳድ አላቸው ተብለው በማህበረሰቡ ትልቅ ግምት የተሰጣቸው አንዳንድ አካላቶች ለሀገራችን ችግር ምንጩ ኢትዮጲያ የራሷ የሆነ ፍልስፍና ስለሌላት ነው ብለው በድፍረት በየሚዲያው ሲናገሩ በመስማቴ ነው ይላል።

ሁለተኛው ረዥም ታሪክ ባስቆጠረው የሀገረ መንግስት ምስረታን መሰረቱን ለመናድ የተለያዩ የውሸት ትርክቶችን በመፍጠር የኮሎኒያሊስቶቹን ከፋፍለህ ግዛው እሳቤ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጥሩ አካላትን በመቃወም እንደሆነ የመፅሐፉን አላማ በመቅድሙ ይነግረናል።

## ፍልስፍና የሌለው ህዝብ ከቶውኑ ሊኖር አይችልም!

መፅሀፉ በአራት ምዕራፎች እና በአስራ ሶስት ንዑስ ርዕስ የተከፋፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ የፍልስፍና ምንነት እና የተለያዩ ሀገራት የፍልስፍና መሰረቶችን ያጠናል። ለዚህም እንደ አብነት ከፍልስፍና ጋር አብሮ ስሟ የሚነሳው የጥንታዊት ግሪክ ፍልስፍና እና ጥንታዊ የሮማውያን ፍልስፍና በማለት በሁለት ንዑስ ርዕስ ከፋፍሎ ይዳስሳቸዋል። እንደሚታወቀው አሁን ላለው የዘመናዊ ትምህርት፣ የመንግስት አስተዳደር ስርአት መሰረት የሆነውን የጥንታዊት ግሪክ ፍልስፍና ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ካሳረፉ ፈላስፎች ዋነኛው ሶቅራጠስ ነው። በሥነ ምግባር የአስተምህሮት ፍልስፍና ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ናቸው ይላቸዋል። በዋነኝነት ነፍስን መሰረት ያደረገው የሶቅራጠስ አስተምህሮ በጎ ህይወት መኖር ደስታን እና እርካታን ለማግኘት አስፈላጊ እንደሆነ ያምን ነበር። ጥሩ ህይወት ለመኖር እንደ ጥበብ፣ ፍትህ እና ራስን መግዛትን የመሳሰሉ በጎነቶች አስፈላጊ እንደሆኑ እና እነዚህን በጎ ምግባራት ማሳደድ የእውነተኛ ደስታ መንገድ እንደሆነ ያምን ነበር እነዚህ እውነተኛ እሴቶች ከውጫዊ ነገሮች የሚመነጩ ሳይሆኑ ከነፍስ ሀብቶች የሚመነጩ ናቸው። ስለሆነም የሰው ልጅ መልካም ምግባር፣ እሴት ከእውቀት እንደሚመጡ ይነግረናል።

በጥንታዊቷ ሮማ የነበረው የፍልስፍና መገለጫ የሆነው የህግ እና የፍትህ ስርአታቸው ነው። ይህ ጥንታዊ ስርአት በዋናነት በሁለት የሚከፈል ሲሆን የህዝብ ሕግ እና የግል ሕግ በማለት ያብራራቸዋል።

የመፅሐፉ ሁለተኛ ክፍል የኢትዮጵያ ፍልስፍና በሰፊው የሚዳስስበት ነው። ኢትዮጵያ የራሷ ፍልስፍና ነበራት? የሚለውን ጥርጣሬ አዘል ጥያቄ በመፋቅ የኢትዮጲያ የመንፈሳዊነት ፍልስፍና በስርአቱ ተጠንቶ ስያሜ ተሰጥቶት በተደራጀ መልኩ ስላልቀረበ እንጂ ይህቺ ጥንታዊት ሀገር የራሷ ፍልስፍና የነበረው ህዝብ እንዳላት ያስታውሳል። ለአብነትም የአኗኗር ይትባህላችንን በመጥቀስ በሀዘን በደስታ ወቅት ማህበረሰቡ የነበረው ጠንካራ መስተጋብር፣ የሰላምታ አለዋወጥ ስርአት፣ እርስ በእርስ የመከባበር እሴቱን በማብራራት የኢትዮጵያ ፍልስፍና መሰረቱ ቁሳዊ ሳይሆን መንፈሳዊ እንደሆነ ይነግረናል።

በሶስተኛው የመፅሀፉ ክፍል የኢትዮጵያ ፍልስፍና ትሩፋቶች ምን ይመስላሉ የሚለውን ለመቃኘት የሞከረ ሲሆን ሥነ-መንግስት እና የአስተዳደር ሥርአቶች ከአክሱም አንስቶ የተለያዩ የታሪክ ዋቢ መፅሀፍትን በማጣቀስ ለማስቃኘት ይሞክራል። የጥንት የኢትዮጲያ ነገስታት በንፁህ ህሊናቸው እየተመሩ ሀገራችውን በህግ እና በስርአት ለማስተዳደር ያደርጉት የነበረውን ጥረት እንዲሁም በዚሁ ክፍል አከራካሪውን የብሄረ ኢትዮጲያን ምስረታ ከስሩ ለመናድ እና ፍልስፍናውን ዋጋ ለማሳጣት የሚሞክሩትን አካላት ይወቅሳል። ለዚህም በዋነኝነት የሚጠቅሳቸው በአፄ ሀይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ወደ ተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት የትምህርት እድል አጊኝተው በመሄድ በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጠንሳሽ የነበሩትን ያነሳል። ሆኖም ሀገሪቷ ከተመሰረተችበት መንፈሳዊ ፍልስፍና ጋር የሚጋጭ እና የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ እና በሊኒን እና በማርክሲዝም አስተምህሮ የሰከሩ የተማሪዎች ማህበር አብዮታዊ እንቅስቃሴ የሀገሪቱ ህግና የፍትህ ስርአት ላይ ትልቅ ችግር እንደፈጠረ ብሎም የአለም ስርአትን ወደ ኢትዮጵያ ማስገባቱ ለብሄርተኝነት ህግ ማርቀቅ ጅማሬ ነው በማለት ያስረዳል። ፀሀፊው በኢትዮጲያ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያ መሰረታዊ ህግጋቶች የጠፉባት ሀገር ሆናለች ብሎ በገፅ (123) ላይ እምነቱን ይነግረናል። በተለያየ ጊዜ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በመድፈር አንድነቷን ጠብቃ እንዳትቆም እጃቸውን ሲያረዝሙ የነበሩ እና የተለያዩ አላማዎችን ይዘው በሀይማኖት ሽፋን አንድነቷን የጠበቀች ጠንቃራ ሀገር እንዳትመሰረት ለማድረግ ሲሞክሩ የነበሩትን ሀገራቶችን በነፃነታቸው የማይደራደሩ ነገስታቶች ነፃነቷን ጠብቀው ለማቆየት ያደረጉትን ጥረት ኋላ ላይም አለም የሚያውቀው በአፍሪካ የነፃነት ምሳሌ እስከመሆን ያደረሳትን የአድዋ ድል የጀግንነት ታሪክ የህዝቦቿን ታላቅነት በማውሳት በዚህም ታላቅ ድል የሀገሬውን ህዝብ በማስተባበር በታላቅ ሀገራዊ ፍቅር ቆራጥነት እና ጀግንነት ሲመሩ የነበሩትን የአፄ ሚኒሊክ ታላቅነትም ይመሰክራል። በአፄ በቴዎድሮስ ሁለተኛ ተወጥኖ ሳይሳካ የቀረውን አሁን ኢትዮጵያ ያላትን ይዞታና አሰፋፈር ህዝቡን አንድ አድርጎ በመግዛት ላሁኒቷ ኢትዮጵያ መሰረት ትተው አልፈዋል በማለት ያወሳቸዋል። ቢሆንም በተለያየ አጋጣሚ የውጪ ሀገራቶች ጣልቃ ገብነት ሀገሪቷን ሲያምሳት እና ይዛ የቆየችውን ባህል እሴት ሲያናጉት እንደነበር እንገነዘባለን።

## የወደቀው የት/ት ስርአት

ትምህርት ችግር መፍቻ መሳሪያ በመሆን ፈንታ በራሱ ችግር ሊሆን አይገባም በማለት የመፍትሔ ሀሳብ ያቀርባል። የሀገራችን የባህላዊው ትምህርት የቤተ ክህነት ትምህርት አሰጣጥ ምን እንደሚመስል በደረጃ ያስቀምጣቸዋል። ይህም የንባብ ትምህርት ፣ የዜማ ትምህርት ፣የቅኔ ትምህርት ፣የትርጓሜ ትምህርት ብሎ በደረጃ ከፍሎ ያሳያል። በተለይም በትምህርት አሰጣጡ ላይ አንድ ተማሪ የመጀመርያ ደረጃ የሆነውን የንባብ ትምህርት ከጨረሰ እና ወደ ሁለተኛው የተሸጋገረ ተማሪ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀማሪው ያስተምረዋል። ይህም ስርአት በአሁኑ ጊዜ (students center) እንደሚባለው ነው። በማለት በገፅ 163 በባህላዊው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ኢትዮጵያውያን ሲጠቀሙበት የነበረ ስርአት እንደሆነ ገልጿል።

የኢትዮጵያ የዕውቀት ምንጭና መሰረት ሥነ መለኮት ነው የሚለው ፀሀፊው ይህ እውቀት የመንፈሳዊነትን እሳቤ የሚያሰርፅ ነው በማለት አያይዞ ይነግረናል።

ስለ ኢትዮጵያ ፍልስፍና ሲነሳ መቼም ስሙ ቀድሞ የሚነሳው የሬኔ ዲካርትን ዘመን የሚጋራው ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ ነው። ዘርዓያዕቆብ በ1599 የተወለደ ሲሆን በንጉሱ ገብረመስቀል ዘመነ መንግስት እንደኖረ ይነገራል። ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ተብለው በታወቁት ሊቅ ከግዕዝ ወደአማርኛ ተተርጉመው የኢትዮጵያውያን ፊሎሶፊዎች፤ ሐተታ ዘርዓያዕቆብ አክሱማዊ ወወልደ ሕይወት እንፍራዝዊ ብለው አሳተትመውልናል።ሊቁ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ለመጀመሪያ ጊዜ ለኢትዮጵያውያን ስለመምህሩ ዘርዓያዕቆብና ስለ ደቀመዝሙሩ ስለ ወልደሕይወት ጽፈው የተዉልንን ሁለት የፍልስፍና መጻህፍት በአንድ መጽሐፍ አካተው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቅ ጥረት አድርገዋል።

በዚህም መፅሀፍ የዘርዓያዕቆብ እና የወልደ ህይወት ታሪክ በጥቂቱ ካስቃኘ በኋላ ከ15 አመት በኋላ የተነሳው ጀርመናዊ ፈላስፋ ፍሬድሪክ ሄግል (Frederick Hegel) አፍሪካውያን የራሳቸው ባህል፣ ታሪክ እና ህይማኖት የሌላቸው የዕውቀት የስነ ምግባር እንዲሁም የሕግ ስልጣኔ እንደሌላቸው ስሁት የሆነ አስተምህሮት በዓለም ላይ በማስተማር አሰራጭቷል። (ገፅ 173)

በማለት ይህን የቀኝ ግዛት ዕሳቤ ሳይንሳዊ ለማድረግ ከመሰሎቹ ጋር የሄዱበት መንገድ ከሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ጠባይ ጋር የሚጋጭ ነው ሲል ይተቻቸዋል።

በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ለፖለቲካ ለአስተዳደር በአጠቃላይ ለማህበራዊና ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንደ ዋና ምክንያት የሚሆነው በመንፈሳዊነት ፍልስፍና የተመሰረተ የትምህርት የዕውቀትና የምርምር ሥርአትን ከዘመኑ ጋር ከማዋሀድ ይልቅ ሀገር በቀሉን ትምህርትም ሆነ ስርአት ወደ ጎን በመግፋት የምዕራብያንን የትምህርት ስርአት ተግባራዊ ለማድረግ የተሞከረው ሙከራ እንደሆነ ይገልፃል። ይህም ስርአት የቀድሞ ሶፊስቶችን አስተምህሮ የተከተለ በዘመነኛው ስያሜው Pragmatism የተባለውን ፍልስፍና የተከተለ ነው ይላል። የዚህም አስከፊ ውጤት በተማሪው፣ በመምህሩ፣ በመሀንዲሱ እና በጤና ባለሞያው ላይ ያመጣውን አሉታዊ ተፅእኖ ያነሳል። በውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ተከታትለው ለሀገራቸው የስነ ጥበብና የኢኮኖሚ እድገት መሻሻል ከፍተኛ ስራን ሰርተው አልፈዋል የሚላቸውን የመንግስቱ ለማን እና የገብረሕይወት ባይከዳኝ አስታውሷቸው መፍትሄ ነው ያለውን የሊቁ የእጓለ ገ/ ዮሀንስን በተዋህዶ ከበረ ፍልስፍናዊ እሳቤ በማንሳት ዘመነኛውን እውቀት ከሀገር በቀል እውቀት እና ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማዛመድ እንዳለብን ጠቆም አድርጎን ያልፋል።

በመጨረሻው ምዕራፍ ጥንታዊ የቁሳዊ ስልጣኔ ትሩፋቶችን የመገበያያ ገንዘቦች፣ ስለ አክሱም፣ ጎንደር፣ ላሊበላ የኪነ ህንጻ ጥበብ የተለያዩ ማህበረሰቦች የስልጣኔ አሻራ ያረፈባቸው ናቸው በማለት እንደምሳሌ የአክሱም ስልጣኔ ላይ የአገው ህዝብ የነበረውን አስተዋፅኦ ያብራራል።

በሥነፅሁፉም ትልልቅ አሻራቸውን ያሳረፉ ቅዱስ ያሬድ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ህይወት እና ስራዎችን በጥቂቱ የሚዳስስ ሲሆን መፅሀፏ አነስ ያለች ብትሆንም ዳጎስ ያሉ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ሀሳቦች የያዘች ልትነበብ የሚገባ ቆንጆ መፅሐፍ ነች።

አንዳንድ ነገሮች…

ታሪክ አሻሚ እና አወዛጋቢ እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ መረጃዎች እንደዋቢነት ስንጠቀምም ሆነ ስናስተላልፍ በጣም ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን አስባለሁ በተለይም እንደኛ ሀገር በአግባቡ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል የሚያስማማ በስርአቱ የተጠና ወጥ ታሪክ ተሰንዶ ላልቀረበላት ሀገር ..

በመፅሃፉ ከደርግ በፊት የነበሩት የኢትዮጵያ ነገስታት ፍፁማዊ አይነት ስብዕና ተላብሰዋል። ይኸውም የተማሪዎች ጥያቄ እና የስርአት ለውጥ መሻትን ተመስርቶ ብሎም በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የአመፅ መነሻ የነበሩት ጥያቄ ፍፁማዊ ስህተት እንደነበሩ እና በንጉሱ ዘመን ሀገሪቱ ምንም አይነት ችግር ውስጥ እንዳልነበረች ያስመስላል። ይህም የመፅሀፉን ሚዛናዊነት በማሳጣት አንባቢ ፀሀፊው ወደ አንድ ወገን እንዳዘነበለ እንዲሰማው የሚያደርግ ነው። ኋላ ላይ መልኩን የቀየረው ስርነቀል ለውጥ አስተሳሰብ መጀመሪያ ሲጀምር ለዘብተኛ እና ስርአቱን ባለበት የማዘመን ሀሳብ እንደነበር የምናውቀው ነው ሆኖም በባላባቱ ስርአት ግብዝነት፣ በተማሪው እና በወታደራዊ ደርጉ አርቆ አለማሰብና ከልምድ ማጣት፣ የስልጣን ሽሚያ የተነሳ ሀገሪቱን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንደመራት ልብ ይሏል። ይህም አንዱን ፃድቅ አንዱን አጥፊ ከማድረግ የፈራጅነት ሚናውን ትተን ታሪክን በአግባቡ እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የምንረዳበት እና የምንማርበት ሆኖ ቢቀርብልን የተሻለ ነበር እላለሁ።

አንዳንድ የቃላት ግድፈቶች እና የዓመተምህረት በገፅ 78 ጥቅምት 25/1982 የተባለው በስህተት ይመስለኛል።

ሌላኛው በታሪክ አከራካሪ እና በቂ ማስረጃ ያልተገኘባቸው አንደ አፈ ታሪክ የሚነገሩ ከመላምት ያልዘለሉ ለምሳሌ የካህኑ ዮሀንስ ግዛት ጉዳይ በመፅሀፉ ውስጥ ተካቶ በማየቴ ጥያቄ ጭሮብኛል።

በተረፈ ይህን መፅሐፍ ሰንዶ ላቀረበልን ለደራሲ ወልደጊዮርጊስ እጅ ነስቼ እንድታነቡት ጋበዝኩኝ።

Reviewer : Yodit Ammanuel is an associate editor at Think Ethiopia

*ርዕስ፡ Borrowing Freedom*
*ደራሲ፡ ፕሮፌሰር ምንዳርያለው ዘውዴ*

ፕሮፌሰር ምንዳርያለው ዘውዴ የፃፉት "Borrowing Freedom " የተሰኘ የፍልስፍና ድርሳን ካነበብኩት ረጅም ጊዜ ቢሆንም አንድ ነገር ይባልበት ዘንድ ወደድኩ። መፅሐፉ "Magnum Opus " እንዲሉት ታሪካዊ ድርሳን ብቻ ሳይሆን እስከዛሬም መሰል ጥልቅ ስራ በሀገራችን የተሰራ አይመስለኝም። መፅሐፉ ልቦለድ ቢሆንም በውስጡ ግን ብዙ የፍልስፍና "Golden nuggets" የተነሰነሱበት ነው። አንባቢ ጥቅጥቅ እና ዳጎስ ያለ በከባባድ የእንግሊዘኛ ቃላት የተዋቀረ ልቦለድ ለማንብብ ብቃቱ ካለው እንጋብዘዋለን። ድርሳኑ አምባገነኖች የሚቀጠቀጡበት ነው። እስቲ ይቺን አንቀጽ ይመልከቱ "አምባገነኖችና ነፈዝ ጀሌዎቻቸው እንዲሁም ስናዳሪ አንፋሽ አከንፋሾቻቸው፣ ከእውነትና ከእውነታ አራት ጊዜ የራቁ ናቸው። በመጀመርያ እንደግለሰብ ራሳቸውን ይዋሻሉ ሲቀጥል እንደጉዋደኛ፣ አለቃና ምንዝር፣ መሪና ተመሪ ወዘተ ክስ በክስ ይወሻሻሉ። ከዚያም እንደቡድን፣ ፓርቲ፣ መንግስት ወዘተ ተጃምለው ህዝብን ይዋሻሉ። በመጨረሻም፣ ወዶ በእሽክሜ፣ ሳይወድ በአርጩሜ የተጋተውን ውሸት፣ የሀቅ ስብሀት የእውነት ጥሉላት ብሎ በድጋፍ ሰልፍ ህዝቡ ራሱንም ሆነ እነሱን መልሶ እንዲዋሽ ይጠብቁበታል" ይህ አንቀጽ ራሱ ደራሲው ወደ አማርኛ ከመለሰው ጾሑፍ የተገኘ ነው።

መፅሃፉ ሲጀምር አንድ አጎዶ ኢ. የተባለ ወጣት በሌላ ከተማ የሚኖር ጠቢብ ወ ሊቅ "The Sage"ን ሊጎበኝ ዕቃውን ሸክፎ ለመሻገር ሲጥር በሀገሪቱ ፖሊሶች ሲፈተሽ ነው። ፓሊሶቹ ያንገላቱታል፣ እሱ ወይ ፍንክች ነው። ቆይቶ ቦርሳው ሲፈተሽ "Borrowing Freedom" የተሰኘ ድርሳን ረቂቅ ይገኝበታል። በዚህ ምክንያት የከተማው ከንቲባ ነገሩን ለማጣራት ይመጣል፣ ከንቲባው ስሙ ኤክሲጁል Exjule ሲሆን ከተማዋን በራሱ ስም ኤክሲጁል ብሎ የሰየመ የለየለት አንባገነን ነው። ከተማዋ በድህነት የደቀቀች ምድረበዳ ብትሆንም ስለ ዕድገቷ ሲያወራ ዓይኑን አያሽም ከተማዋ ያለችበት ሀገር ደግሞ ሳቁ ሲለን Freedom Justice and Democratic Republic of Ajeebux ይባል እንጂ ደም የጠማቸው ነፍስ በላዎች የሚንፈለሰሱበት

ሀገር ነው። መፅሐፉ ትንሽ የ1984 እና Brave New world ዘይቤ ያለው ቢሆንም ድህነት እና ጭቆና የተብራራበት በመሆኑ አፍሪካዊ ቃና አለው። ዋናው ጉዳይ ሰው የራሱን ነፃነት ለአንባገነኖች አሳልፎ ከሰጠ በኋላ መልሶ ነፃነቱን ከእነሱ መልሱ እንደመበደር አሳፋሪ ነገር የለም የሚል ነው። በየመሃሉ ይህን ታሪክ በ580 ገፅ ሲተነትን ብዙ ሃሳብ ያነሳል። Kingdom of Irrationaldom, Borrowing Freedom, recycling poverty, immediacy of Time, Inapproximation etc አሽተን የተባለች ሴት ቆይቶ አጎዶ እንደተገደለ ለጠቢቡ The Sage ትነግረዋለች። የመፅሐፉም አብዛኛው ክፍል በሁለቱ መሃል ያለ ወይይት ነው።

ደራሲው ትዕምርታዊ በሆነ መንገድ የጻፉት የራሳቸውን ታሪክ ነው። በ1985 ባንድ ጀምበር አለ ምንም ምክንያት ከአዲስ አባባ ዩንቨርስቲ 41 ፕሮፌሰሮችን ተባረሩ። ሌሎቹ ከሀገር ወጡ። ከሀገር አንወጣም ያሉትን የትም ቦታ እንዳይቀጠሩ ሰርኩላር ዞረ። የዚህ ሰለባ አንዱ ፕሮፌሰር ምንዳር ያለው ዘውዴ ናቸው። ምንዳርያለው ዘውዴ ያለ ምንም ምክንያት ከዩንቨርስቲው ቢባረሩም ሀገር ጥሎ መውጣት መሸነፍ አድርገው ስለቆጠሩት ከሀገር አልወጡም። እዚህ ኢትዮጵያ ሆነው ሕዝባቸውን በማስተማር ማገልገል ጽኑ ምኞታቸው ነበር። ፕሮፌሰሮች በጣት በሚቆጠሩበት በዛ ዘመን ረብ ያለው ሥራ ሊያገኙ አልቻሉም። ሥራ ማግኘት ያልቻሉት - የትም ቦታ እንዳይቀጠሩ ሰርኩላር ለሁሉም የግልም ሆነ የመንግስት ተቋማት በመበተኑ ነበር። ኢንተርቪው ያደረጋቸው ተቋም ሁሉ በሳቸው ብቃት ደስተኛ ቢሆንም ማንም ሊቀጥራቸው አልቻለም። ፕሮፌሰሩ ግን እጅ አልሰጡም። ወደ ትውልድ ሀገራቸው አርሲ ተመልሰው እርሻ ውስጥ ገቡ። ቀን ቀን ያርሳሉ፣ ያርማሉ፣ ያጭዳሉ። ማታ ማታ ደግሞ ያነባሉ ይጸፋሉ። ነጻነቴን አላበድርም የሚል ሰው እንዲህ መሰሉን መሰዋዕትነት ይኸፍላል።

## Reviewer : Dawit Bezabih is the managing Editor of Think Ethiopia

*Title: የእከይ እና ስቃይ ጣጣ*
*Author: Alex Zetseat*
*pages: 462*

What can an Ethiopian author write about the origin of evil and suffering? Ethiopians breathe suffering from birth to death but Alex Zetseat (Alemu Shimelo) claims to say something new. Unfortunately or fortunately, "The problem of evil" (**ነገረ እኩይ**) has been the most contentious philosophical and theological question in the entire human history. The book is supposedly Philosophical, theological and Pastoral but has tilted towards the pastoral part because the author is a Minister of the Gospel or may be a future pastor.

The Problem of Evil can be succinctly summarized in the following logical form:

1. **If God is omnipotent (all-powerful), then He should be able to prevent evil.**
2. **If God is omniscient (all-knowing), then He should be aware of all evil and suffering.**
3. **If God is perfectly benevolent, then He should desire to prevent evil and alleviate suffering.**
4. **However, evil and suffering exist in the world.**

Therefore, the existence of evil and suffering appears to be logically inconsistent with the existence of an omnipotent, omniscient, and perfectly benevolent God. The author talks about God and the universe, Man and creation untill page 61 as he begins to define the problem of evil.The above

logical puzzle has been a focal point for discussions about the nature of God, the problem of human suffering, and the overall coherence of theistic worldviews. The Problem of Evil has prompted deep reflection, various responses and extensive debate.

It is my belief that it is a purely philosophical concept and should be dealt with the utmost intellectual integrity. However, Alex's Pastoral tendencies have shadowed his insight from the intricacies of the subject. He seems to shield his readers from the horrors of evil up until page page 61 by telling them about God's Goodness and providence. Christians believe and think Suffering came into the world because of our disobedience resulting in the creation of the original sin.Original sin stems from within the Christian doctrine and refers to the idea that humanity inherited a fundamental state of moral corruption or deprivation as a result of the disobedience of the first humans, Adam and Eve in the Garden of Eden. The author beautifully narrates this fall and genetically transferrable sin from page 47 to 60.

This disobedience, often symbolized by the consumption of the forbidden fruit from the Tree of Knowledge, is traditionally portrayed as the moment when humanity fell from a state of innocent communion with God and became burdened with a tendency towards sinfulness, moral frailty and doing evil things. But, God being all knowing of all things past and future is supposed to know or predict our fall (page 82 - 87). That is why I say the problem of evil is exclusively a philosophical question and not a theological one.Original sin posits, due to Adam and Eve's transgression

all subsequent generations inherit a moral taint or predisposition towards wrongdoing. This inherited moral flaw is seen as a foundational aspect of human nature, contributing to the prevalence of moral evil and the perpetuation of human suffering in the world. The book outlines different kinds of evils and sufferings (page 91-120) but concludes by defending God (p. 121 - 127) even in a chapter alloted to define the problem of evil.

Through the years, theologians have designed ways to defend God against this Paradox, their attempt is called Theodicy. Theodicy deals with questions regarding the existence of evil and suffering in a world that is allegedly governed by an omnipotent, omniscient and benevolent deity. The term "Theodicy" was coined by the German philosopher Gottfried Wilhelm Leibniz in the 18th century and is derived from the Greek words "theos" (God) and "dike" (justice).

In essence, Theodicy aims to reconcile the perceived existence of evil and suffering with the notion of a just and loving God. It gets into philosophical, theological, and ethical inquiries seeking to provide explanations and justifications for the presence of evil in a world created by a benevolent God. One common argument is that the existence of evil and suffering is a result of human free will. The ability to make choices, even morally wrong ones, is viewed as a fundamental aspect of human autonomy and dignity. This perspective posits that God allows for the possibility of evil as a consequence of granting humans free will, choosing to prioritize autonomy over a world devoid of moral agency. Another line of thought within Theodicy suggests that evil

and suffering serve as opportunities for soul-building and moral growth. Adversity is viewed as a means through which individuals can develop virtues such as compassion, resilience and empathy (page 255-346). From this perspective, suffering is not devoid of purpose; it is an integral part of the human journey towards spiritual and moral maturity.

Some Theodicies posit that the existence of evil and suffering is part of a larger divine plan that ultimately leads to a greater good. This can involve the idea that suffering serves as a means of character refinement, the establishment of contrast to appreciate goodness, or as a test of faith and perseverance. Alvin Plantinga pointed out that God, though omnipotent, could not be expected to do literally anything. God could not, for example, create square circles, act contrary to his nature, or, more relevantly, create beings with free will that would never choose evil. Taking this latter point further, Plantinga argued that the moral value of human free will is a credible offsetting justification that God could have as a morally justified reason for permitting the existence of evil. The problem of evil originates from the existence of human free will. So that's where Molinism enters the scene as a theological and philosophical perspective that seeks to reconcile divine omniscience, human free will, and the occurrence of contingent events. Named after the 16th-century Jesuit theologian Luis de Molina, Molinism posits the existence of God's knowledge not only of what humans will do (simple foreknowledge) but also of what they would do under any circumstance (middle knowledge). This middle knowledge encompasses God's

knowledge of counterfactuals, or what humans would freely choose in various hypothetical scenarios. The interplay between free will and determinism forms a significant point of contention in philosophical discourse. Compatibilists argue that free will and determinism are compatible, contending that even if actions are determined by antecedent causes, they can still be considered free if they align with the individual's desires and motivations. In contrast, incompatibilists assert that determinism and genuine free will are inherently incompatible, as the presence of causal necessity seemingly undermines the authentic volitional agency of individuals.Open theism posits that since God and humans are free, God's knowledge is dynamic and God's providence flexible. Whereas several versions of traditional theism picture God's knowledge of the future as a singular, fixed trajectory, open theism sees it as a plurality of branching possibilities, with some possibilities becoming settled as time moves forward.

Thus, the future, as well as God's knowledge of it, is open (hence, "open" theism). Other versions of classical theism hold that God fully determines the future, entailing that there is no free choice (the future is closed). Yet other versions of classical theism hold that, though there is freedom of choice, God's omniscience necessitates God's foreknowing what free choices are made (God's foreknowledge is closed). Open theists hold that these versions of classical theism do not agree with the biblical concept of God; the biblical understanding of divine and creaturely freedom; and / or result in incoherence.

The author seems to be worried a great deal as to how believers should confront evil. He dedicated half of the book for it, evidenced by his constant mentioning of Philip Yancey, C. S Lewis, Viktor Frankl or even Ellie Wiesel. But, for Ethiopians evil and suffering has been their companion through out their history. I have found no mentioning of the political, economical, social suffering we had to endure at the hands of our rulers, nature and the culture of our making. Even as an African fighting Colonization and its evil we have to ask God as to why he allowed the transatlantic slave trade or let white missionaries travel across africa as colonial agents in his name.The book seems to be highly theoretical, which is not a bad thing altogether but we can't pray or think our way out of evil and suffering but can only endure it in a stoic fortitude. As the author comfort the reader (page 422 - 437) by mentioning the Armageddon and our eschatological destiny, I am left wondering as to what an African thinks of the end of times since we live under "the threat of a violent death" everyday.

**Reviewer: Dawit Bezabih has two Masters in Law and Philosophy and has authored three books on legal philosophy, he is also the Chief Editor of Think Ethiopia**

## ምዕራፍ ሶስት

# ጥናት እና ምርምር

*የመፅሐፉ ርዕስ:- ምሁሩ*
*ደራሲ:- ዶ/ር አለማየሁ አረዳ (PHD)*
*የገፅ ብዛት:- 274*

ዶ/ር አለማየሁ አረዳ ይህንን ምሁሩ የተሰኘውን መፅሀፍ ሲያበረክቱልን አንደኛም ምስቅልቅል እና ፈር ያልያዘው የሀገራችን አምባገነናዊ ማህበረ ፖለቲካ ሥርዓቱን በማፍረስ እና ህዝብን መሰረት ያደረገ ስርዓት በመገንባቱ ዙሪያ የምሁራኑ ድርሻ ላቅ ያለ ቢሆንም ግን እነኚህ ምሁራን እውን ሀላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ነው? የሚለው ጥያቄ እንደሆነ በመፅሀፉ መቅድም ይነግሩናል።ሀገራችን ለገባችበት ችግር መነሾ የሆነው የብሄር ፖለቲካ እና የዲሞክራሲ አተገባበር መፋለስን ተከትሎ የሀገሪቱ ምሁራን ድርሻ እና ሀላፊነት ምንድነው? የሚለውን ለመጠቆም በመጀመሪያም በፅንሰ ሀሳቦች ላይ ያለንን መረዳት ለማጥራት እና መሰረት ለማስያዝ ይሞክራሉ። በዚህ መፅሐፍ የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ምዕራፎች የምሁር ምንነት እና አደምታ፣ በምሁራን ላይ የተሰነዘሩ ወቀሳዎችን እና ከምሁሩ የማህበረሰብ ክፍል የሚጠበቀውን ሀላፊነት እና ሚናውን ያብራራሉ።

በመሰረቱ ምሁር ሲባል ሁሉም በአእምሮው የሚመጣለትና የሚታየው ምስል ይለያያል። በተለምዶ ቃሉን እየተቀባበልን የተለያዩ ወቀሳዎችን መሰንዘራችን የተለመደ ነው። ይህን ተከትሎ ከተለያዩ የአለማችን ክፍሎች በምሁሩ ላይ የሚሰነዘሩትን ወቀሳዎች ምን ይመስላሉ የሚለውን ካስቃኙ በኋላ ወደ ሀገራችን ተመልሶ እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ከተለያዩ ፀሀፍት እና በተለያዩ ዘርፎች ከሚገኙ ወጣት ባለሞያዎች የተሰነዘሩ ትችቶችን በመፅሀፉ ይዳስሳሉ።

በጠቅላላው እውን በሀገራችን ምሁር አለ ወይ እስከማለት ያደረሳቸው እና እንደውም ለሀገሪቱ ፖለቲካ መሻሻል ድርሻቸውን ከመወጣት ይልቅ ሀገሪቱን ምስቅልቅል ፖለቲካ ቅርፅ በማስያዝ እና አንድ ብሄር ውስጥ በመወሸቅ ማህበረሰቡን በማወናበድ ረገድ ትልቅ ሚና እንደተጫወቱ የሚጠቁሙ አስተያየቶች በርከት ያሉ ናቸው። አያይዘውም ዶ/ር አለማየሁ በተወሰነ መልኩ እነዚህን አስተያየቶች የመቀበል አዝማሚያ ቢያሳዩም በመሰረቱ ምሁር በሚለው ፅንሰ ሀሳብ የጋራ የሆነ የሚያግባባን መሰረት ከሌለን በትክክልም

የትኛውን የማህበረሰብ ክፍል እየወቀስን እንደሆነ ግልፅ አይደለም በማለት ከጅምሩ የምንጓዝበትን መንገድ ለማጥራት ይሞክራሉ።

## ለመሆኑ ምሁር (Intellectual) ስንል ምን ማለታችን ነው?

በመጀመሪያው ምዕራፍ ምሁር የሚለው ቃል ቀጥታ ማሰብ ከመቻል ጋር ብቻ የሚገናኝ ሳይሆን ሀሳብ ከማመንጨት እና ከሰብአዊ ተፈጥሮ ጋር የተጣመረ እንደሆነ ከBill mathew (what's to be human) እና ከAyn Rand (For the new Intellectual) ከተባሉ መፅሀፍቶች እያጣቀሱ በሰዎች እና በእንስሳቶች መሀከል ያለውን የንቃተ ህሊና ደረጃ ያስረዳሉ። ቀጥሎም የምሁርን ፅንስ ሀሳብ አስመልክቶ በተለያየ ዘመን ተከስተው የነበሩትን ፀሐፍት ምልከታ እያሰባጠሩ አንድ የጋራ ትርጉም ሊያስጨብጡን ይሞክራሉ። ለዚህም እንደ አብነት የቶማስ ሶዌልን፣ አንቶንዮ ግራምሺ፣ አሊሬዛ ጀላኒ ፋርኒ እና ሌሎችም ስለ ምሁር ያላቸውን እሳቤ በማብራራት ምሁር ማለት "በመማርም ሆነ በህይወት ልምድ የጨበጠውን እውቀትና የአይምሮ ብቃት ተጠቅሞ በራሱም ሆነ ባለበት ማህበረሰብ አስተሳሰብና አመለካከት ላይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በሚያቀርባቸው ሀሳቦች ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚችለውን ወይም የቻለውን ግለሰብ ወይም የማህበረሰብ ክፍል ነው።" ገፅ(25) ወደ ሚለው አስታራቂ ትርጉም ይመሩናል።ሌላው በመፅሐፉ የምሁርነት ዓበይት መገለጫዎች የሚዳስሱ ሲሆን በዋናነት የሚጠቅሷቸው ከመደቡ ጋር የተዋሀደው ምሁር፣ ባለሙያው ምሁር፣ ለምሁርነት የሚኖረው ምሁር፣ ለሰበአዊ ነፃነት እና ለዕውቀት የሚኖረው ምሁር፣ የአደባባይ ምሁር፣ ሀሳብ አፍላቂው እና ለገበያ አቅራቢው ምሁር፣ ሀያሲው ምሁር፣ አሳቢው ምሁር በማለት ሁሉንም በየፈርጃቸው በጥልቀት ይዳስሷቸዋል።ስለዚህ ዘመኑን የዋጀ ምሁር እንደ ምን ያለ ነው?

እዚህ ላይ በዋንኛነት ዶ/ር አለማየሁ አረዳ አንድ ምሁርን ምሁር የሚያስብሉትን ሶስት መሰረታዊ ነገሮች አሉ እነሱም እውቀት፣ ክህሎትና በጎ ፍቃድ እንደሆኑ እና አንድ ሰው እውቀትና ክህሎት ቢኖረው እንኳን በጎ ፍቃድ ከሌለው ከምሁራን ምድብ ውስጥ ማካተት እንደማይቻል አበክረው ይነግሩናል። ምሁር መንበሩን ዋጀ የሚያስብሉትን ሀላፊነቶች እና ዋና ዋና

ሚናዎች በሰፊው ካብራሩ በኋላ አተገበባበሩ ላይ ግን ከሀገሪቱ ነባራዊ ማህበረሰባዊ እሴት እና ባህል ጋር የተቃኘ መሆን እንዳለበት ያስጠነቅቃሉ።

አራተኛው ምዕራፍ ላይ የኢትዮጵያ ምሁራን ቅኝት ከቅድመ አክሱም አንስቶ፣ የመካከለኛው ዘመን ምሁራን የሚሏቸውንም (የቅዱስ ቃል ኪዳን ዘመን ምሁራን፣ የእስልምና "ቅዱስ ጦርነት" ሰባኪ ምሁራን፣ የገዳ ስርአት ምሁራን) እና የዘመናዊው ምሁራንን በየዘመናቸው የተጫወቱትን ሚና ምን ይመስላል የሚለውን በሰፊው ያስቃኙናል። በተለይም የዘመናዊ ምሁራን ማቆጥቆጥን ተከትሎ በአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩትን ምሁራን ደም አፋሳሽ ትግላቸውን እና ክፍተቶችን ለማሳየት በተነሱበት ሀሳብ መነሾና አላማቸው መሰረት ከፍለው ለማየት ይሞክራሉ። በንጉሱ ዘመን መታየት የጀመሩት እነኚህ ምሁራን ኋላቀር የሆነውን ስርአት በመቃወም የመሻሻያ ሀሳቦችን ያቀረቡ በኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ የተቀጣጠለውን ቀዳሚ የለውጥ ችቦ የለኮሱት የሚሏቸው የለውጥ ፋና ወጊ ምሁራን ሲሆኑ ኋላ ላይም ንጉሱ እነዚህን ጥያቄዎች በማጤን እና መልስ በመስጠት ፈንታ ከድፍረት እንደወሰዱባቸው ይነግሩናል።

ከጣልያን ዳግም ወረራ በኋላ ከንጉሱም ከስደት መልስ በኋላ ደብዛው ጠፍቶ የነበረው ምሁር ማቆጥቆጥ የገባር ስርአት ይፍረስና ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም የሚል አመለካከት የሚያራምዱ ስርነቀል ምሁራን ናቸው። በጊዜው ለሀገራቸው ባዳ ያሏቸውን እነዚህ ምሁራን ስርአቱን በማፍረስ ላይ እንጂ ለወደፊቱ framework ማበጃጀቱ ላይ የነበራቸው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ትግሉ ውጤታማ አይደለም ይሉናል።

በብሄረ ኢትዮጳያ እና ነገዳዊ ፓለቲካ አመለካከታቸውን አንስቶ ይተቻቸዋል። ካፒታሊስታዊ ስርአት በመተቸት ማርክሲስታዊ ስርአትን እንደ ቅዱስ መፅሀፋቸው አድርገው የተቀበሉ እነኚህ ምሁራን ከዋለልኝ መኮንን የብሔር ጥያቄን አስመልክቶ በዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ኀብረት ልሳን "ታገል" መጽሄት ላይ ይዞት የቀረበው ፅሁፍ ተማሪው ስለ ብሄር እና በኢትዮጵያም ስለነበረው የብሄሮች ፖለቲካ ተዛምዶ የተለየ ግንዛቤ አድርጎታል የሚል አመለካከት አለ ይሉናል በገፅ (89) ይህን ፅሁፍ ዋለልኝ የዩንቨርስቲው ተማሪ በተሰበሰበበት አዳራሽ በንባብ አቅርቦት ነበር። በተለይም ይዟቸው

ከወጣው ፅሁፎች ሀገራዊ ብሄርተኝነት የይስሙላ ብሄራዊነት (Fake Nationalism) የሚለውን አመለካከት መሰረት አድርጎ የዋለልኝ የሀገረ ኢትዮጵያ ምስረታን ፋርሽ ማድረጉ ሌሎች የአለም ሀገራቶች የተመሰረቱበትን ሂደት የአለም ታሪክን ለመገንዘብ ፍቃደኛ አይመስልም ይላሉ።ከዛም በኋላ ነገዳዊ ብሄርተኝነት (Ethno-nationalism) አቀንቃኝ ምሁራን ስብስብ በመጠናከሩ ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላም የመደብ ትግል ይቅደም የሚል እሳቤን አስቀድመው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ድርጅቶች በመኖራቸውም የመገንጠል ጥያቄ የሚያስነሱ ኋይሎች እየተበራከቱ ምጣት በመሀከል ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል። ምንም እንኳን ተመሳሳይ አላማ አንግበው የተነሱት ድርጅቶች እነ ኢህአፓ፣ ህወሀት፣ መኢሶንን ጨምሮ በመተባበር ፈንታ በትንሽሽ ልዩነቶች ምክንያት እርስ በእርስ መሳሪያ እስከመማዘዝ ያደረሳቸውን አጋጣሚ በቁጭት ይገልፃሉ። ዛሬም ቢሆን ከዚህ የታሪክ ክስተት መማርና ጉዳዩን ማጤን እንዳለብን ያስገነዝቡናል።

የኢትዮጵያ ምሁራን የታሪክ አረዳድ ህፀፅ እና አንደምታው በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ታሪክን በምን መልኩ መረዳት አለብን የሚል ሀሳብ ቀርቧል። እንደ ዶ/ር አለማየሁ ምልከታ ታሪክ በባህሪው ምንዳና ፍዳን አዝሎ የሚፈስ የኩነቶች ዥረት ነው። በመሆኑም ታሪክ ያስከተለውን ፍዳ ተምረንበት ምንዳውንም ተጋርተን ወደ ፊት እንዳንጓዝ ቀፍድደው ከያዙን ሁለት ተቃራኒ አመለካከቶች አንደኛው ባልኖረበት ዘመን የተሰራን ታሪክ ይዞ "የተጎዳሁት እኔ ነኝ" ሂሳብ ካላወራረድኩ የሚል አቋም ያለው በሌላ መልኩ ደግሞ "ባለፈው ታሪክ ባለ ድል እኔ ነኝ" በሚል ባልዋለበት ጦር ሜዳ ራሱን ሲያሞካሽ የሚውለው በሁለት ጎራ የተከፈለው አመለካከት እንደሆነ ይነግሩናል። በተጨማሪም የብሔረ ኢትዮጲያ አመሰራረት በአራት ዋና ዋና ካስማዎች ከፍሎ የአክሱማዊት የኢትዮጵያ አስተዳደራዊ ስርዐትና የክርስትና እምነት ከሰሜን ወደ መላ ሀገሪቱ የመስፋፋት ታሪክ፣ የእስልምና እምነት ከምስራቅ ወደ መላ ሀገሪቱ የመስፋፋት ታሪክ፣ የኦሮሞ ማህበረሰብ ከደቡብ ወደ መላ ሀገሪቱ የመስፋፋት ታሪክ እና የዘመናዊት ኢትዮጵያዊ ግንባታ ታሪክ በማለት በሀገር ምስረታው ላይ የተጫወቱትን ትልቅ ሚና ይዳስሳል። በዋነት አራቱን ያንሳ እንጂ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ የሚኖሩ ልዩ ልዩ

ማህበረሰቦች ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ መፈጠር የራሳቸውን አሻራ ማኖራቸውንም ይነግሩናል።

በመቀጠል በምሁሩ መንደር የሚዘወሩ የብሄርተኝነት እና የዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለማዊ ሀሳቦች ላይ የተሳሳተ መረዳት በዴሞክራሲያዊ ግንባታው የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅእኖ ሁለቱን ሀሳቦች እያነፃፀረ ልዩነታቸውን እና የብሔርተኝነት ርዕዮተ አለም እንዴት የዴሞክራሲያዊ ግንባታው ላይ ተግዳሮት በመሆን ሂደቱን እንደሚያደናቅፈው ያስረዳሉ። አያይዞም የነዚህን ፅንሰ ሀሳቦች ምንነት አይነታቸውን እና መልካቸውን በጥልቀት በመዳሰስ ምሁራኑ ስለሚያራምዱት ርዕዮተ አለም ምንነት ግንዛቤን በመፍጠር የጠራ እይታን ለመፍጠር ይሞክራሉ።

## በመጨረሻም ታድያ የኢትዮጵያ የ21ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ያላቸው ሚና ምን መምሰል አለበት?

ከዛ በፊት ሀገሩቱ ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ በማጤን እና ነገድ እና ቋንቋን መሰረት ያደረገው ፌደራላዊ መንግስታዊ አወቃቀር የዴሞክራሲ ትግበራውን የሚያደናቅፍ እንዳልሆነ መፈተሽ ያስፈልጋል ብሎ ያስታውሳሉ። ይኸውም ደራሲው የቡድን ጥያቄ ላይ የሚያተኩረው ብሔርተኝነት የግለሰብ ጥያቄዎችን በመመለስ ደረጃ ውጤታማነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው። ይልቅስ የግለሰብ ጥያቄን መሰረት ያደረገው ዴሞክራሲን በማስፈን የቡድን ጥያቄዎችን መመለስ ይቻላል ብለው ያምናሉ። በመጨረሻም ኢትዮጲያ ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የምሁራኑ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊ ሚናዎች ምን መምሰል እንዳለባቸው ይጠቁማሉ። በዚህ አጋጣሚ ይሄ መፅሀፍ ሀገራችን የተዘፈቀችበትን ችግር ከስረ መሰረቱ በማጤን ብዥታ የፈጠሩ ምልከታዎችን በማጥራት የችግሩንም ጥልቀት በማስረዳት መፍትሄ ይዞ ለዘመኑ ትውልድ የቀረበ ሰነድ ነው። መነበብና የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተው ብዙ ሊያወያይ የሚችል ጥራዝ ነው።

ለዶ/ር አለማየሁ አረዳ ስጦታ እጅ ነስቼ መፅሀፉን እንድታነቡት ጋብዛለሁ።

Reviewer :- Yodit Ammanuel is an associate editor at Think Ethiopia

*የመጽሐፍ ርዕስ፦ሆህያተ ጥበብ፤ ለጸሐፊያን፥ ለተርጓምያንና ለአርታዕያን*
*ጸሐፊ፡- ተስፋዬ ሮበሌ (ዶ/ር)*
*የመጽሐፍ ዘውግ፡- የምርምር መጽሐፍ*
*የገጽ ብዛት፡- 205*

መጽሐፉ ሁለት ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን እሱም ሆህያተ ጥበብንና የሰዋሰውን ማብራሪያ ከጥቂት ክፍሎቹ ጋር ያትታል። ይህን መጽሐፍ ከሁለት አጽቆች አንጻር መቃኘትን መርጫለሁ። አንደኛው የመጽሐፉን ጭብጥ (ይዘት) በማስተዋወቅ አንባብያንን ለንባብ መጋበዝ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ቋንቋን ለፍልስፍና (በተለይም ለሥነ-አመክንዮ) ያለውን ጠቀሜታ ማሳየት ነው። "ምክንያትና ተምኔት" በሚለው መነሻ አሳብ ሥር መጽሐፉ ለአንባቢያን እንዲደርስ የተፈለገበትን (ጥንስስ አሳቡን) ወይንም ዓላማውን ይገልጹልናል፥ ተስፋዬ ሮበሌ (ዶ/ር)። እሳቸው ለሚያገለግሉበት ማኅበር (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር) የዐማርኛ ቋንቋ ሰዋሰውና የሥነ-ጽሑፍ ቅርጽ ጠብቆ የትርጉም ሥራን በሚገባ ለማሳለጥ እንዲቻል አጋዥ ምንጭ እንዲሆንና የድርሰት ሥራዎች መብዛታቸው ከጭብጥ ይልቅ "ለሥነ ጽሑፍ ለዛቸው" ትኩረት አለመሰጠቱ ለዚህ መጽሐፍ መወለድ መነሻ ምክንያቶች እንደሆኑና ይህም "ለወጣት ተርጓምያን፥ አርታዕያንና ጸሐፍያን" የተሰጠ በረከት (አቅጣጫ ጠቋሚ) መጽሐፍ ነው (ከገጽ 1-2)። የተጠቀሙት የአጻጻፍ ስልት "ሱታፌአዊ" ሲሆን ይህም አንዱ ከአንዱ ጋር በመተባበር መልካም የሆነ ተዋስኦን የሚጋብዝ የመማማሪያ (ትምህርት የመቅሰሚያ) መንገድ ነው።

በዚህም "ጤፍ ከነወንድሟ ጎተራ ትሞላለች" እንዲሉ አበው፥ በተጨማሪ ከበደ ሚካዔል (ጋሼ) የዕውቀት ብልጭታ በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ እንዳሉት፥

"...ሲተጋገዝ እንጂ ፍጡር የሚድነው፥
ምንም ብርቱ ቢሆን አንድ ሰው አንድ ነው..."

በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በርከት ያሉ አሳቦችንም ለማስተናገድ የሚጋብዝ አካሄድ ነው።

በዚህም መሠረት ከገጽ 8-14 የዚህን መንገድ፥ ሱታፌአዊ፥ አተገባበርን ያስቃኙናል። ማለትም የሰውነት ገደባችንን በማሳየት ትሑታንና ለመማማር (ትምህርት ለመቅሰም) የቀና ልቡና እንዲኖረንና የዚህ ሂደት ጥቅም የትዬለሌ እንደሆነ ይገልጻሉ። ለጥቀውም ከገጽ 15-22 ድረስ "ምስኪኑ ዐማርኛ" በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ሥር የዐማርኛና ግእዝ ቋንቋዎች እንደ ጊዜ ርዝማኔያቸው ያለማደጋቸውን ወይንም በጥቂት ልሂቃን ብቻ ትኩረት ተሰጥቷቸው በብዙኃኑ የተነፈጉበትን ምክንያቶች በመዘርዘር ቁጭታቸውን ይገልጻሉ። ከእነኚህም ውስጥ፥ በገጽ 15 የኢሕአዴግ ፖለቲካዊ አመራር በቋንቋው ላይ ያደረገው ተጽዕኖ፥ እንዲሁም በዚሁ የፖለቲካ እርሾ በትልልቅ የትምህርት ተቋማት (መካነ-አእምሮ ስፍራዎች) የትምህርት ዘርፎች በቋንቋችን አለመሰጠታቸው፥ በቤተክህነት ያሉ መጻሕፍት ለብዙኃኑ በኃላፊነት ትኩረት ሰጥቶ በንቃት የሚንቀሳቀስ ክፍል አለመኖሩ (ቢያንስ በብዛት)፥ በተጨማሪ አንዳንድ የቋንቋው ሊቃውንት በጽሑፎቻቸው ለሞክሼ ሆህያትና ዋሕድ ድምፆች ትኩረት መንፈጋቸው የጥናቱና መፍትሄው መንደርደሪያ መጠቁሞች ናቸው።

በምዕራፍ አንድ ክፍል አንድ "ፍኖተ ፊደል መሠረታውያን" በሚለው ርዕስ ሥር ስለ ሞክሼ ሆህያት፥ ፍንፅቅ ፊደላት፥ ገቢርና ተገብሮ፥ ዋሕድ ድምፅ ፊደላትና አስፈላጊነታቸው በሰፊው ተብራርቷል። በመቀጠልም የክቡር ሐዲስ አለማየሁን አሳብ ለሞክሼ ሆህያት ጥናት መነሻነት በመጠቀም ማለትም ሞክሼ ሆህያት የማያስፈልጉ እንደሆኑ ያብራሩበትን የእሳቸውን ጽሑፍ ከ"ፍቅር እስከ መቃብር" በመጥቀስ ሞክሼ ሆህያት ምን እንደሆኑና አስፈላጊነታቸውን በደደረ ሙግት ያስቃኙናል፥ ተስፋዬ ሮበሌ (ዶ/ር)።

በዚህም ፯ ሙግታቸውን ከገጽ 30-41 ዘርዝረዋል። በተጨማሪም እነኚህን ሙግቶችም ተመልክተው ያላረካቸው (sufficient argument ላልመሰላቸው) እናም ለሞክሼ ሆህያት "ሕግ ማቆም" (ሕግ መስጠት) እንደማይቻል ለሚሞግቱም ሦስት የመልስ ምቶችን ከነ መደምደሚያቸው ከገጽ 42-45 ተንትነዋል። ከገጽ 46-49 ደግሞ ፍንፅቅ ፊደላት ምን እንደሆኑና በእነሱም ላይ የሚቀርበው ትችት ከመልስ ምት ጋር ተሰንዷል። ፍንፅቅ ፊደላት፥ "...በከንፈርና ትናጋ ቅንጅት የሚፈጠሩ ድምፆችን ወካይ ናቸው...ሷ ሟ..." (ገጽ 46)። ሌላው አድራጊና ተደራጊ ግሦችንም ከገጽ

49-51 አስቃኝተዋል። ከገጽ 51-54 ደግሞ የዋሕድ ድምፆችንና አስፈላጊነታቸውን ይተነትናሉ። ዋሕድ ድምፅ፥ “ሁለት አናባቢ ሆህያት ተዋሕደው፥ አንድ ድምፅና ቀለም ሲሰጡ...” የሚፈጥሩት ድምፅ ነው። በመቀጠልም በምዕራፍ አንድ ክፍል ሁለት የሞክሼ ሆህያት የትርጉም ልዩነት እንደሚያመጡ ከገጽ 56-90 በሰፊው ያብራራሉ። በዚሁ ምዕራፍ ክፍል ሦስት ሥር ደግሞ ሞክሼ ሆህያትን በቀላሉ ገንዘብ የሚያደርጉበትን መንገድ በመጠቆም ከገጽ 95-122 ድረስ፥ “እነዚህን ቃላት ማስተዋወቅ እንዲሁም ሰዎች እንዲያጠኗቸው ማበረታታት...” (ገጽ 94) በሚለው ግባቸው በሰንጠረዥ ለጥናት ይጋብዙናል።

በአራተኛው ክፍል “ጓዘ ብዙ ፊደላት” ከዋሕድ ድምፅ ፊደላት ጋር ያላቸውን መቀራረብ፥ በሙግትና ምክረ አሳቦችን በመስጠት እንዲሁም በሰንጠረዥ ማብራሪያዎችን በመሰደር ከገጽ 124-147 ለጥናት እንዲመቹ አቀናብረው ያቀርቡልናል። በሁለተኛው ምዕራፍ የሰዋሰው ክፍል የሆነውን ሥርዓተ ትእምርት ይዳስሳሉ። ከነቁጥ (.) ጀምረው እስከ አራት ነጥብ በሰፊው ከገጽ 150-166 ምንነታቸውንና አስፈላጊነታቸውን ይዘረዝራሉ። በዚሁ ምዕራፍ ስለ አበዛዝ ሕጎችና አስፈላጊነታቸው እንዲሁም ከግእዝ ፊደላትና ቃላት ጋር ያላቸውን ቁርኝት ከገጽ 168-199 ይተነትናሉ።

የገደፉ ቃላትና አንዳንድ አማራጭ የዐማርኛ አቻ ፊደላት፥

፩) ማውጫው ላይ “ሆህተ ጥበብ” ይላል። ልዩ ትርጉም አለው ወይስ “ሆህያተ ጥበብ” ለማለት ነው?

፪) “አዲስ 1879 ፩፰፯፱” ቅጽ ፫ መጽሐፍ ጸሐፊው (ግርማይ ነቅዓጥበብ) ከገጽ 80-86 “ሞክሼ ሆህያት” ከማለት “ድምፀ-ሞክሼ ሆህያት” ይላል። እርሶም ስለዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ያብራሩበት ጽሑፍ ላይ የተዘረዘሩት ቃላት ለምሳሌ:- “ሕብር ወይም ኅብር” ተመሳሳይ ድምፅ አላቸው። በዚህም “ድምፀ-ሞክሼ ሆህያት” የሚለው የተሻለ አገላለጽ አይመስሎትም?

፫) በግርማይ መጽሐፍ ላይ በገጽ 22 ስር "ዩኒቨርሲቲ" አቻ የዐማርኛ ፍቺው “መካነ አዕምሮ” እንደሆነ ይገልጻል። እና እርሶ ደግሞ በተደጋጋሚ

በገጽ 2፥ 17፥... ላይ በቀጥታ ይጠቀሙታል። ታዲያ እንደ ዐማርኛ ጽሑፍ ይህን "መካነ አእምሮ" የሚለውን መጠቀሙ መልካም አይደል?

፬) የምጠቀመው FynGeez በመሆኑ የዋሕድ ድምፆችን እንዳልጠብቅ አድርጎኛል። (የኔው ድካም)

## ሆህያተ ጥበብና ፍልስፍና (የቋንቋ ፍልስፍና)

በተደጋጋሚ ከተጠቀሱት ማለትም ሞክሼ ሆህያትን የመጠበቅ አስፈላጊነት ውስጥ ከተብራሩት ነጥቦች አንዱ የትርጉም ልዩነት መፍጠሩ ነው። ይህም በአሪስጣጣሊስ Organon ከሚባሉት ሥራዎቹ ውስጥ በተለይም የቃላት አሻሚነት የሚታይባቸውን የቃላት አጠቃቀሞች ከሥነ-አመክንዮ መርሆች ጋር በማቀናበር ያሳየበት "Sophistical Refutation" የሚለው መጽሐፍ ተጠቃሽ ነው። በዚሁ መጽሐፍ አፈ-ቀላጤ ሶፊስቶች የሰውን ትኩረት በመሳብ በንግግራቸውና ጽሑፎቻቸው መካከል አሻሚ ቃላትን እንደሚጠቀሙ ልብ በማለት አስራ ሦስት የሚሆኑ ከቃላት ጋር የተያያዙ ተፋልሶዎችን ያስተዋወቀበት ነው።

በዚሁ መጽሐፉ ላይ ቋንቋን ተገን አድርገው የሚፈጸሙ ወይንም ግራ መጋባትን የሚያጭሩ፥ በዋናነት፥ ተፋልሶዎች ስድስት እንደሆኑ ያብራራል። እነሱም "Homonymy (equivocally), Ambiguity, Combination, Division, Accent, Form of expression." (p.4) እነዚህንና የተቀሩትን በተከሹኑ የዐማርኛ ቃላት በዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌ መጽሐፍ፥ ሥነ አመክንዮ፥ ከገጽ 223-236 ድረስ ገልጸውታል። አሪጣጣሊስም ለቃላት (የፊደላት አጠቃቀም በቋንቋ ላይ) ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚገባና በቃላት ጨዋታ (hair splitting) እንዳንሸወድ Categories እና On Interpretation በሚሉት መጽሐፍቱም ስለ ገቢርና ተገብሮም ይተነትናል። በዚህም ድምፀ-ሞክሼ ሆህያትን ማወቅና መጠበቅ በቃላት ከመጥፋት ይጠብቀናል ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ሌላው የፍልስፍና ዕውቀት ላይ ጥብስቅ ያለ ጥናት ያካሄዱ እንደመሆኖት በዚሁ መጽሐፍ ላይ ቋንቋ ነው አስተሳሰብን (አእምሮን) የሚገዛው ወይስ አእምሮ ነው ቋንቋን የሚገዛው? የሚለውን የዘመናት ጥናት የእነ ረስልን፥

ጎትለብ ፍሪጌን፥ ቪቲንግስታይንንና አልቪን ፕላንቲንጋን ዕሳቤ አስተዋውቀውን የእርሶንም አሳብ ሰፋ አድርገው ቢያቀርቡት መልካም ነበር። ያው አንድም ይኸው አሳብ በመጽሐፎት ስለተጠቀሰና ሆህያተ ጥበብ የሚለው የመጽሐፎት ርዕስ ሰፋ ያለ ስለሆነ ቢተነትኑልን እንመኛለን። በተጨማሪ ቋንቋ (ፊደላት፥ ቃላት፥ ዐዋጆች) ከአእምሮና ዓለም ጋር ያላቸውን ቁርኝት ቢያሳዩን መልካም ነው። እንዲሁም አፍላጦን በ Cratylus መጽሐፉ ስለ ቃላት (ሰሞች) የትመጤነት እንዳስቃኘን እርሶ ስለ ቋንቋ ምን ያስባሉ? ማለት ቋንቋ (ቃላት) የሰዎች ሰምምነቶች (Conventional) ናቸው ወይስ በተፈጥሮ ያሉ (Natural)? የሚለውን ቢዳስሱልን መልካም ነው። ያው እርሶ እንደሚያውቁት ቋንቋ “Mind-dependent” ነው ወይስ አይደለም የሚለው ሙግት ከፈጣሪ መኖር አለመኖር ሙግት ጋር ስለሚያያዝ ጥቅሙ ብዙ ነው። በስተመጨረሻ የሁልጊዜም አክባሪዎት ነኝ! እግዚአብሔር ቤተሰቦትንና አገልግሎቶን ይባርክ!

**የመጽሐፍ ዳሰሳ በየሺጥላ ይገዙ (የኬሚካል ኢንጂነሪንግ ምሩቅ፥ የአራተኛ ዓመት የሥነ-መለኮት ተማሪ፥ የአዲስ አበባ ነዋሪ)**

*ርእስ፡ ድብቁና ያልተነገረው የአይሁዳውያን እና የኢትዮጵያውያን ታሪክ*
*ደራሲ፡ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ*
*የታተመበት ዘመን፡ 2010 ዓ.ም.*
*የገጽ ብዛት፡ 238*

የአንድ ሀገር ህዝብ የተሻለ ምግብ እንዲያገኝ፣ ጤናው የተጠበቀለት፣ሰላሙና ደህንነቱ ተረጋገጦለት ምቹ ኑሮን እንዲመራ፤ በአጠቃላይ ደስተኛ እንዲሆን የሚያደርጉት ምክንያቶች በርካታ ቢሆኑም በዋናነት ግን በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊ፣ በፖለቲካና በባህላዊ ሁኔታዎች ከማደግና ካለማደግ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ካላደገ ችግሮቹ ለቁጥር ከመብዛታቸው የተነሳ ለመፍታትም አስቸጋሪ ይሆናሉ። የእነዚህ ችግሮች መነሻ ደግሞ የተማረና የሰለጠነ፣ ሰብዓዊነትን የተላበሰ ህዝብ ሲያንስ፤ የፍቅር ማጣት፣የፍትህና ርዕትህ ጉድለት ተከትሎ ከፍተኛ የስልጣን ጥምና ስግብግብነት በማህበረሰቡ ገዢ ሀሳብ ሆነው ችግሩን ከድጡ ወደ ማጡ ያደርጉታል። ለምን ካልን ምንጩ የመንፈስ ዝቅጠት እና የማንነት ቀውስ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህ ደግሞ ሌላ ምንጭ አለው። የመንፈሳዊነትና የስብዕና ዝቅጠት ነው።ይህም ታሪክን ካለማወቅ፣ ካለመረዳት እንዲሁም ለማወቅና መርምሮ የራስ ለማድረግ ካለመቻል የሚመጣ ክፉ በሽታ ነው።

በፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ ተደርሰው ለአንባቢ ከቀረቡት መጽሀፍት መካከል “ትክክለኛው የአማራ እና የኦሮሞ የዘር ምንጭ” በሚል ርዕስ የቀረበው እና ‹‹ድብቁና ያልተነገረው የአይሁዳውያን እና የኢትዮጵያውያን ታሪክ›› የሚሉትን የማንበብ ዕድሉ ገጥሞኝ አንብቢያቸዋለሁ።አንብቤ ለራሴ ብቻ ጥቅም ላይ ማዋል ስግብግብነት መስሎ ስለታየኝ፤ ሌሎችም እንዲያነቡትና የራሳቸውን ምልከታና መረዳት እንዲኖራቸው በማሰብ (ተጽዕኖ ፈጣሪው ፈረንሳዩ ፈላስፋ፣ የስነ-ጽሁፍ ሀያሲ፣ የማህበረሰብ ጥናት ተመራማሪና በዘርፉ አዳዲስ ርዕዮቶችን (ቲዎሪ) ለዓለም ያበረከተው ሮናልድ ባርተዝ(ስ) ‹The death of the author and the birth of the reader, Ronald Barthes› በሚለው መጽሀፉ እንደገለጸው) እኔም ካለኝ ጥልቅ ፍላጎት ተነስቼ “ድብቁና ያልተነገረው የአይሁዳውያን እና የኢትዮጵያውያን ታሪክ” የተሰኘውን መጽሀፍ በቻልኩት አቅም

እንደሚከተለው ለመዳሰስ ሞክሪያለው። የዳሰሳዬ ትኩረት ከይዘት አንጻር (Thematic Approach) እንደሆነ በቅድሚያ ማሳሰብ እፈልጋለሁ።

መጽሃፋን ለመዳሰስ የምሞክረው ደራሲው ባስቀመጠው የንዑስ አርእስትን ቅደም ተከተልን ትቼ ለኔ በተመቸኝ መልኩ ከፊትም ከኋላም የተነሱትን ሀሳቦች በማንሳት ነው። ይሄን ያደረኩት በታሪካዊ ጽሁፍ ላይ የግዜና የሁነት ቅደም ተከተል (ክሮኖሎጂ) አስፈላጊነት ባለማወቄ ወይም ዘንግቼ ሳይሆን ለመጽሐፍ ዳሰሳየ የግድ ስላልሆነና ለኔም ምቹ ስላልሆነልኝ( ስላልፈለኩት) ነው።በመጽሀፉ ስለ አይሁዳውያን እና የኢትዮጵያውያን ግንኙነት ለማስረዳት ደራሲው የግንኙነት ጅማሮ ነው ብሎ ያስቀመጠው ከዛሬ 3500 ዓመት በፊት አካባቢ እንደሆነ ነው። በገጽ 176 ላይ "የአይሁዳውያን ወደ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ፍልሰት የተፈጸመው ሙሴ ራሱ በህይወት እያለ የዛሬ 3500 ዓመት አካባቢ ነው። እሱም የዮቶር አብ የልጅ ልጅ ኢትዮጲስ አንድ የጽላተ ሙሴን ግልባጭና ሙሴ ቀይ ባህርን የከፈለበት በትረ-ሙሴን ይዞ ከምድያም ተነስቶ ኢትዮጵያ ላይ ሊነግስ ሥርዓተ-ንግሥናውን ለማስፈጸም ወደ ኢትዮጵያ በገባበት ዘመን ነበር።" ብሏል። እዚህ ሀሳብ ላይ ጥያቄ ያጫረብኝ ነገር ደራሲው በገጽ 91 ላይ ሙሴ ለዮቶር አብ ልጅ ለአባ ብሄር በትረ-ሙሴን ለወዳጅነት ማስታወሻ እንደሰጠው በመግለጡ፤ ሙሴ እንዴት በትረ-ሙሴን ለሁለቱም እንደሰጠ ነው።

ደራሲው በገጽ 76 ላይ ስለ ሁለተኛው ግንኙነት እንዲህ አስቀምጦታል "ሁለተኛው ፍልሰት የተከሰተው ወጣቱ ቀዳማዊ ምኒልክ ዋናውን ጽላትና 40000 እስራኤላውያንን ይዞ በመጣበት ጊዜ ነበር።" ስለ ሶስተኛው በገጽ 177 "ሶስተኛው ደግሞ የዛሬ 2500 ዓመት በእስራኤል ሊቀ-ነብያት በነበረበት ሰዓት የባቢሎን (የዛሬው ኢራቅ) ንጉስ ናቡ-ከደነጾር እስራኤልን ወርሮ የሰለሞንን ቤተመቅደስ አፈራርሶ መጽሀፍቱን አቃጥሎና ህዝቡን በሰንሰለት አስሮ ወደ ባቢሎን ባጋዘበት ወቅት ነበር።" በማለት ነው።

ከመጀመሪያው የግንኙነት ሂደት አንስቶ እስከ ሶስተኛው ባለው ሂደት ሁሉ የሁለቱ ሀገራት ህዝቦች ግንኙነት በአስተዳደር፣ በስነ-መለኮት፣ በህግ እና በደም የተሳሰረ እንደሆነ በመጽሀፉ ላይ ተገልጾ እናገኛለን። ይህንንም ለመረዳት በገጽ 187 "የኦሪት ሀይማኖት መስራቹ ነብዩ ሙሴ ራሱ

እግዚሃብሄር እስከሚጠራው ድረስ ስለ ስነ-መለኮት የተማረው ከአማቱ ከዮቶር አብ ነው።” በገጽ 52 ላይ ሙሴ 40 ዓመት ከዮቶር አብ (ከዓማቱ) ጋር እንደኖረ፤ ዮቶር አብ ደግሞ የመልከ ጼዴቅ ዝርያ እንዳለው ተጽፏል። በገጽ 187 ላይ ከኦሪት በፊት እነ መልከ ጼዴቅ በፈጣሪ ያምኑ እንደነበር ሌሎች የዓለም ህዝቦች ግን ከጣኦት በቀጥታ ወደ ክርስትና ነው የተሸጋገሩት በማለት ያስረዳል። በገጽ 186 ላይ ከላይ ያለውን ሀሳብ የበለጠ ሲገልጽ “ኢትዮጵያ ስርዓተ ኦሪትንም ስርዓተ ሀዲስን፣ ወይም ወንጌልን ከነታቦቱ በመቀበልዋ በዓለም ካሉት ቤተክርስቲያናት ሁሉ ልዩ ሆነች።” በማለት ነው። ስለ ኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን “ተዋህዶ” ተብሎ የተሰየመበትን ሁኔታ ሲገልጽ በገጽ 186-187 “እግዚሃብሄር እየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ወርዶ ከቅድስት ማርያም ተወልዶ ከስጋ ስለተዋህደ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተዋህዶ ተብሎ ተጠራ።” ካለ በኋላ ቀጥሎም ‹ኦርቶዶክስ› የሚለው ስም የተቀጠለበት ኦርቶዶክስ ግብጾች በሀሰት ኢትዮጵያ የራስዋን ጳጳስ ልትሾም እንደማይገባት ባልተሳተፈችበት በኒቂያ ጉባዬ ላይ ተበይኖባታል ብለው አጭበርብረው በደካማ ንጉስ የጦር ድጋፍ ፓትሪያሪክነትን ከኢትዮጵያ ከነጠቁ በኋላ ነው።” በማለት ነው።

ከዚህ ላይ ያለኝ ጥያቄ ከጉባዬው በፊት ኢትዮጵያዊ ጳጳሳት እነማን እንደነበሩ ደራሲው ለምን እንዳልጠቀሳቸው ነው። የተረዳውት ነገር ደግሞ ከጥንት ጀምሮ ግብጽ ለኢትዮጵያ እንደማትተኛላት ነው። ለዚህ እምነት ያበቃኝን ሌላ ሀተታ በገጽ 193 ላይ ያገኘሁት ሀሳብ ነው። “የግብጽ ‹ጳጳሳት› እና ‹ፓትሪያሪኮች› የኢትዮጵያን ነገስታት በሴራ እያጠመዱና እየተቆጣጠሩ፣ ለእነሱ ታዛዥ ካልሆኑ በስተቀር ያወርዷቸው ነበር። ኢትዮጵያውያንን በተለይም ቅዱሳን፣ ቀሳውስትን፣ሊቃውንትን፣ከያኒያን፣ የታሪክ አዋቂዎችን እና ፈላስፎችን አረዱ። ጨፈጨፉ። አካል አሰናካሉ።” እዚህ ላይ አጤ ቴዎድሮስ ሁለተኛ የግብጽን (የአቡነ ሰላማን) ሴራ ተረድተው ነበር ማለት ይቻላል። ማህበረሰቡ ግን ንጉሱን ባለመረዳቱና ሃሳባቸውን መርምሮ ሊያውቅ ባለመቻሉ፤ ሊያሳውቀውና ሊያነቃው የሚችሉ ብልህ ሰዎችም ባለመኖራቸው ንጉሱ ለሀገሩ አንድነትና እድገት እንደባከኑ አርፈዋል።

ደራሲው ከላይ ያሉትን ያልተለመዱትን ታሪክ እውነት ነው ብለው ያቀረቡት ከመጽሀፍ ቅዱስ እና ከሌሎች 60 በላይ መጽሀፍትን በመመርመርና መረጃ በመሰብሰብ ቢሆንም ዋናዎቹ ግን በመሪ ራስ አማን በላይ ከግዕዝ ወደ አማርኛ በተተረጎሙት ‹መጽሀፈ (ጃ)ያሻር እና ጃ(ዣ)ንሸዋ› ከተሰኙት ነው። ስለ እነዚህ መጽሃፍት በገጽ 30 ላይ እንደሚከተለው ተጽፏል። “መጽሀፈ ያሻር እና ጃንሸዋ በመልከጸዴቅና የኢትዮጵያውያን ቅድመ አባት በሆነው በኢትዮጵ በኩል ከኖህና ከኩሽ ለኢትዮጵያ የተላለፉ ናቸው።” ይልና በገጽ 34 ላይ “መጽሀፍቶችን ያገኘውና ያሰራጨው አክሱማይ ሲራክ እንደሆነ ያስረዳል። ነገር ግን መጽሀፎችን መሪ ራስ አማን እንዴትና የት እንዳገኙት በመጽሃፉ ላይ አልተብራራም። በዚህ መጽሃፍ ውስጥ የኢትዮጵያውያንን እና የአይሁዳውያን የደም ትስስርን በተመለከተ ደራሲው በዝርዝር ያስረዳል። ታሪኩን ለመረዳት በመጀመሪያ የኢትዮጵያውያን አባት ስለሆነው፣ ካህንና ንጉስ ስለነበረው መልከጸዴቅ እና ከአብርሃም ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ከገለጸበት መንገድ ተነስቶ ማየት የተሻለ መረዳትን ስለሚፈጥር ስለጅማሮው በገጽ 59-60 የተገለጸውን ሀተታ እንይ፤ “የሳሌሙ ንጉስ መልከጸዴቅ ንጉስ ላልሆነው ሰገደ። ምክንያቱ ደግሞ የዓለም ቤዛ ከአብርሃም አብራክ እንደሚመጣ ትዕንቢት በመበሰሩ፣ በአብርሃም አብራክ ውስጥ ተሰውሮ ለነበረው መድህዓኔአለም በአብርሃም ፊት መስገዱን ተከትሎ ሌሎች ነገስታት በመልከጸዴቅ ላይ በዘመቱበት ሰዓት አብርሃም ለመልከጸዴቅ ወግኖ ድል አድርጓል።” የሚል ሲሆን ገጽ 38 ላይ መልከጸዴቅ የኖህ ቀጥተኛ ተወላጅ እንደሆነ ተጽፎ ይገኛል። በገጽ 54 ላይ መልከጸዴቅ እናታችን ሳሌምን አግብቶ ኢትኤልን (ኢትዮጵ)ን እንደወለደና ኢትኤል (ኢትዮጵ) ደግሞ (ገጽ 62 እና 65 ላይ እንዲህ ተጽፏል።) “ኢትኤል” (የእግዚሃብሄር ስጦታ ማለት ነው።) የተባለውን ስሙን ‹ኢትዮጵ› አለው። ትርጉሙም (ቢጫ ወርቅ ስጦታ ለእግዚሃብሄር) ማለት ነው። ከእስራኤል ተነስቶ ጣና ደሴት ሲደርስ፣ ጥንት ‹ኩሽ› ትባል የነበረችውን ‹ኢትዮጵያ› አስባላት።... የኢትዮጵ የልጅ ልጆች የኢትዮጵያን ስጦታዎች ጭነው፣ ወደ እስራኤል ሄደው ለመሲሁ እንደሚሰግዱለት እግዚሃብሄር የተነበየው እና ያዘዘው ቃሉም በኋላ በትክክል በተግባር ዉሏል። ‹ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ

እግዚሃብሄር ትዘረጋለች› (መዝሙረ ዳዊት፣ 67፣ 31) የሚለው ትዕንቢትም ተፈጽሚል” ይላል።

እዚህ ላይ የኔ ጥያቄ ትዕንቢቱ ከተፈጸመ አሁን ላይ ኢትዮጵያውያን እጆቻቸውን ወደ እግዚሃብሄር አይዘረጉም በቃቸው ማለት ነው ወይ? የሚል ነው።ምክንያቱም አማኝ ሁልግዜም ቢሆን እጁን ወደ ፈጣሪው መዘርጋት ይገባዋል በሚል እሳቤ ስለማምን ነው።ሌላውም ቢሆን አማኝ ከሆነ በዚህ ሀሳብ የሚስማማ እንደሆነ አስባለሁ።

ደራሲው ስለአብርሃም ዘር በመጽሀፉ ገጽ 55 ላይ ሲያወሳ፤ ሌላው የኖህ ልጅ ኢቦር የሚባል እንደሆነና እሱም አብርሃምን እንደወለደ እንዲሁም በገጽ 56 ላይ ደግሞ አብርሃም ሳራን አግብቶ ይስሃቅን እንደወለደና በይስሃቅ ዘር መሲሁ እየሱስ ክርስቶስ እንደተወለደ በማተት ነው።ከዚህ ጋር በተያያዘ በገጽ 82 ላይ ሙሴ ከመልከጻዴቅ ዝርያ ካለው ከዮቶር አብ ወንድ ልጅ ከሆነው ከራጉኤል ልጅ፣ ከሲፓራ ጋር ተጋብቶ ወንድ ልጅ እንደወለዱ ይናገራል። በተጨማሪም የሰለሞን እናት የዳዊት ሚስት ኩሻዊ ጥቁር እንደሆነች በገጽ 117 ተጽፏል።

በአጠቃላይ በመልከጻዴቅ ዘርና በአብርሃም ቤተሰብ ትዉልድ መሀል የመጀመሪያው የጋብቻ ግንኙነት የተጀመረው የኢትዮጵ ሁለት ሴት ልጆች የአብርሃምና የሎጥን ሁለት ወንድ ልጆች አግብተው ዘር ባፈሩ ግዜ ነበር። በማለት በገጽ 80 ላይ ደራሲው አስፍሮት ይገኛል። ከላይ በትንሹ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ደራሲው የሁለቱ ህዝቦች ትዉልድ የደም ዝምድና ካነሳ በኋላ ገጽ 38፣9 ላይ “በመጽሀፍ ቅዱስ ስለ ኩሽ አባት የዝክረ ትዉልዱ አወራረድ ተዛብቷል” ይሉና በኛ ታሪካዊ ምንጭ አቀራረብ ግን እውነታው የተለዬ እንደሆነ መጽሀፍ ቅዱስን እና ምንጭ ነው ያለውን በንጽጽር መልክ አቅርቦታል።ከዚህ አንጻርም በመጽሀፍ ቅዱስ ያለው መረጃ የተሳሳተ እንደሆነ ይነግረናል። ከዚህ ላይ እኔን ግር ያለኝ ነገር መጽሀፍ ቅዱስ የተሳሳተ ነገር እንዳለው ቢገልጽም እሱን እንደ ዋቢ መጥቀሱ ነው። ከዚህ አንጻር ደራሲው ክፍተት አለበት ለማለት ዳዴ ስል ‹ተው !› ያስባለኝን ሀተታ በገጽ 19 ላይ በመግቢያው እንደሚከተለው ስለገለጸ ሀሳቤን ተውኩት። ሀተታው “አይሁዳውያን ስለቅዱስ ዳዊትና ቤተሰቡ በደንብ አለመዘርዘር መፈለጋቸው

‹ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ እንደሚባለው ሆነብኝ›› የሚል ነው። ደራሲው በገጽ 64 ላይ "የእየሱስ ክርስቶስ ‹አምሳል› ከሆነው ከትልቁ የእግዚሃብሄር ካህን ከመልከጸዴቅ ዘር በኢትዮጵያ የተወለዱት ሁሉ ነገስታት ዲበ-ሰብእ ሆነዋል። ልክ እን አባታቸው የሳሌሙ ንጉስ መልከጸዴቅ ንግስናን እና ክህነትን (ፖለቲካን እና ቅስናን) አጣምረው ይዘው ህዝቦቻቸውን በፍትህ እና ርትህ ያስተዳድሩ ነበር። በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ የነገሱት ሁሉ የኢትዮጵ ዝርያዎች በጣም ትልልቅ ነበሩ። ከእነዚህ ታላላቅ ሰዎች መሀል የኦሮሞ እና የአማራ ግንደዘር የሆነው ፈላስፋው ደሸት (ደሴትም ይሉታል) ይገኝበታል።"

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ የተረዳሁት ፍሬ ነገር የቀደሙት አያቶቻችንና አባቶቻችን በህዝባቸው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ፣ በፍትህና በርትዕ ይመሩ የነበረው ሀይማኖትን እና ክህነትን አጣምረው የያዙ ስለነበሩ ነው የሚል ነው። ነገሩ አሳማኝ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በመንፈሳዊነት የሚኖሩ ነገስታት (መሪዎች) ለስጋዊ ምኞት የሚታትሩ፣ ለአድሎአዊነት፣ ለስግብግብነት እና ለስልጣን ጥም የመጋለጥ ዕድላቸው ዝቅተኛ ወይም ዜሮ ስለሚሆን ነው።ነገር ግን የኔ ጥያቄ በታሪክ ችግራችን ላይ እና አሁን ባመጣብን ግራ መጋባት እንዲሁም አገራችን ላለችበት ሁለንተናዊ ችግሮችና ማሳካት ስለምትፈልገው ዓለማዊ ዓላማ (secular) የሆነውን ጉዳይ የስነ-መለኮት አስተምህሮ እና ሀይማኖታዊ ነክ በሆኑ ማስረጃዎች ላይ ተመስርተን እንዴት መፍታት እንችላለን? (ምንም እንኳን ይሄን መጽሀፍ ለማዘጋጀት ከስልሳ በላይ መጽሀፍቶችን ደራሲው ዋቢ በማድረግ የተጠቀመ እንደሆነ በመግቢያው ላይ ቢነግረንም።) እንዲሁም በኔ እምነት መጽሀፍ ቅዱስ ለስነ-መለኮት እውቀት፣ ለታሪክ እና ለስነ-ጽሁፍ ዓላማ የሚውል መሆኑን ብገነዘብም ማለት ነው።

በዚህ መጽሀፍ በገጽ 97 ላይ ... ስመ ክህነቱ እስያኤል የተባለው፣ በምድር ላይ ከኖሩ ንጉሰ ነገስታት ሁሉ የላቀው ነው። በሰው ልጆች ፈንጠዝያ ላዕለ-ሰብእ (superman) ወይም ዲበ-ሰብእ ተብሎ ሊታሰብ የሚችል እሱ ብቻ ነው። የተወለደው የዛሬ 3480 ዓመታት ገደማ ነው። እሴ እንደ ነገስታት አባቶቹ ነብይና ካህን ከመሆኑም በላይ፣ የመድብለ ዘር ወይም መሀንዲሰ-ዘር (ጄኔቲክ ኢንጂነር) የዕጽዋት ተመራማሪና የማዕድናት አዋቂ ነበር። ደፋርና በጣም ብርቱ ነበር።... ስነ መንግስትን፣ የፍትሃብሄር

ህግጋትን፣ የመንግስትን ስነ ምግባር መመሪያ ጽፎ ለሁሉም ይሰሙት ዘንድ በኢትዮጵያ ሀገራት ሁሉ አውጇል። ገጽ 98...አጼ እስኤል ዛሬ የምትውለበለበውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ፈልስፎ ሁሉም ንጉሶችና ንጉሰ ነገስታት በፈረሶቻቸው፣ በሰረገላዎቻቸው በቤተ-መንግስታቸው ላይ እንዲያውለበልቡ ያዘዘው እሱ ነው። የስልጣን ዘመን 10 ዓመታት እንዲሆን ገድቧል። ገጽ 98 እሴ በትውልዱ የዮቶር አብ ቅም አያቱ ነበር።... የኢትዮጲስ ሚስት ሩት አማን፣ ማለትም የእሴ አያት አይሁዳዊት ነበረች። ... አጼ እስያኤል ፈረሶችንና አህዮችን በማዳቀል ለመጀመሪያ ጊዜ በቅሎን ያስገኘው እሱ እንደሆነ ተገልጾ ይገኛል።

ከላይ ስለ እስያኤል ደራሲው ያቀረበውን የታሪክ ሀተታ አሁን በታሪክ መጽሃፍቶቻችን በማስፈር እንዴት ማስተማር እንዳለብን እና ምን ማድረግ እንደሚገባን በመጽሀፉ በግልጽ አልተቀመጠም። ከዚህ በተጨማሪም የበቅሎን ጉዳይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የባለቤትነት (የፓተንት) ጥያቄ ማንሳት እንደሚገባን ደራሲው ምንም ያለው ነገር የለም። በመሆኑም ታሪኩን የንባብ ባህል (ልምድ) ያላቸው ብቻ አንብበውት ስለሚያልፉ ታሪኩን የእኛ ማድረግ እና ለትውልዱም ማስተማር እና ማስተላለፍ ያለበት ሌላ አካል ያስፈልጋል ማለት ነው። ከዛ ውጭ ባክኖ መቅረቱ አይቀርም ብየ እሰጋለው።

በአጠቃላይ በመጽሀፉ ገጽ 97፣ አባ ብሄር (የዮቶር አብ ልጅ) በአባቱ ዙፋን እንደተተካ። የይሁዳ ነገድ ተወላጅ የአሚናዳብን ሴት ልጅ ሩት አሚንን አግብቶ እርሷም በኢትዮጵያ ግዛት እና በዓለም ዙሪያ ቀዳማይቱ የአይሁድ ንግስት ለመሆን እንደበቃች። ኢዮጲስንም እንደወለዱ፤ 193፣ ላይ ግዕዝ ያልጠፋው ራሷን በጦር ሀይሏ ባነገሰችው ንግስት ዮዲት ጥረት እንደሆነ፤ እሷ እንደ አጥፊ ሆና በታሪካችን መገለጹ ስህተት እንደሆነ፡ 228፣ ከእግዚሃብሄር በታች ኢትዮጵያውያን አይሁዳውያንን በእግራቸው ስለማቆማቸው፤ ከነብዩ ሙሴ ጀምሮ ኢትዮጵያ አይሁዳውያንን ወደ ግዛትዋ እያስገባች ጥገኝነት፣ መሬት እና ንግስና ሳይቀር እየሰጠች ማስተናገዷን፤ 229፣ እየሱስ ክርስቶስ፣ ቅድስት ማርያም እና ቅዱስ ዮሴፍ በኢትዮጵያ ግዛት በግብጽ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ጥገኝነት አግኝተው እንደኖሩ፤ 229፣ እየሱስ ራሱን ለአይሁዳውያን ሳይገልጽ በ22 ዕድሜው ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ቅድሚያ ሰጥቶ ራሱን ለኛ ገልጾ እስከ 25 ዕድሜው ድረስ ሲያስተምርና

ሲፈውስ ሀገራችን ውስጥ እንደኖረ፤ እየሱስ ክርስቶስ በህይወቱ እያለ በዓለም የመጀመሪያውን ቤተ-ክርስቲያን ሀገራችን መመስረቷን፤ 14፣ ኢስላም በዓለም ላይ እስኪጠራ ድረስ ለነብዩ መሐመድ ቤተሰቦች ጥገኝነት የሰጡት እና በተዘዋዋሪ እስልምና እንዲስፋፋ ያደረጉት ክርስቲያኖቹ ንጉስ አርማህ እና ልጁ እንዲሁም የቀድሞ አባቶቻችን እንደነበሩ፤ 188፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አባላት እግዚሃብሄር እና አብርሃም የተዋዋሉበትን የብሉይ ኪዳን ለማስታወስ ወንድ ልጆቻቸውን እንደሚገርዙ፤ ሌሎች ኦርቶዶክሶቹ ግን እንደኛው አስበው እንደማይተገብሩት፡ ከምግብ እና ከታቦት አንጻር ሁሉ እንደሚለያዩ፤ 204፣ የአፍሪቃ የስም ስያሜ ከአፋር ሰዎች ተርሴስ፣ ‹አፍሪስካውያን› ከሚለው ስያሜ እንደሆነ፤ የዛሬ 130 ዓመት በፊት አትላንቲክ እና ህንድ ውቅያኖስ በጀርመንም፣ በፖርቱጋልም፣ በእንግሊዝ አሳሾች ሁሉ የኢትዮጵያ እንደነበር መገለጹን፤ እንዲሁም 232፣ እጅግ የሚያኮራን በእየሱስ ክርስቶስ ደም ስር የዕኛ የኢትዮጵያውያን ደም መፍሰሱ ነው። እንዴት ቢሉ፣ እየሱስ ክርስቶስ የቅዱስ ዳዊት ዘር በመሆኑ እና የእሱም እናት አይሁዳውያን አዶልያ ወይም አዴል የሚሏት እኛ ደግሞ ሀብሌ የምንላት ኢትዮጵያዊት በመሆኗ እንደሆነ ተጽፏል። የመጽሀፍ ዳሰሳየን ሳጠቃልል ደራሲው በመጽሀፉ ላይ ካነሳቸው ሀሳቦች በመነሳት አሁን ባለንበት ወቅት እና ለታሪካችን ባለን እይታ ሀሳቦችን ለመቀበል ይከብዳል ብየ አስባለሁ።

በመሆኑም ይሄ ነገር የፋንታሲ ዘውግ ያለው ልብ ወለድ ነው እንዴ ብየ ራሴን ጠየኩት፤ ግን የልቦለድ አላባውያንን በጭራሽ አልያዘም። ታሪኩ በአንድ ሀይማኖት ላይ ያተኮረ ነው። አሁን በሀገራችን ደግሞ የሀይማኖት ብዝሀነት ስላለ እንዴት ሁሉንም ባይሆን እንኳን አብዛኛውን ሊያስማማ እና ለአንድነታችን እንደ አንድ የመፍትሄ አካል ልወስደው እችላለሁ? ብየ ሳሰላስል ታሪኩ የተፈጸመው ሀይማኖት የሚባል ጉዳይ ባልነበረበት ዘመን በመሆኑና የታሪኩ ባለቤቶች ደግሞ አያቶቻችን እና አባቶቻችን ስለነበሩ የሁላችንም ታሪክ ከመሆን የሚያግደው ነገር እንደሌለው አሰብኩ።አፈ-ታሪክ ነው እንዳልል የኢትዮጵያ ታሪክ አፈ ታሪክ ነው የሚሉትን ኢትዮጵያውያን ላይ ስለማልስማማ ነው። ምክንያቱም ከአፈ - ታሪክ ነው ‹ታሪክ› ተብሎ የሚጻፈው ከነጉድለቱ። አለበለዚያማ ያልተጻፈ ታሪክ ማለትም የጽሁፍ ዘዴ

ከመፈጠሩ በፊት የነበሩ ታሪኮች፣ (የሰው ልጆች ኑሮ) ‹ታሪክ› ተብሎ ባልተጻፈ ነበር። ደግሞስ አፈ-ታሪክ ቢሆንስ? አፈ-ታሪክ እኮ ለአንድ ሀገር የአንድነት መንፈስና ለጥንካሬአቸው መሰረት መሆኑ አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም። ደራሲው እኛ ኢትዮጵያውያን ለጠቢቦቻችን እና ለሊህቆቻችንን ያለን ቦታ ዝቅተኛ በመሆኑ ማንም እየተነሳ ኢትዮጵያዊነታችንን ዝቅ ዝቅ እንድናደርገው፣ ሚስጢራችንን እንዳናውቅና እንዳንመረምር ሆነናል። በመሆኑም መግባባትን፣ ፍቅርን፣ ፍትህና ርዕትህ እንዲሁም ቅን ልቦና እንዳይኖረን አድርጓል። ግን ይህ ታሪክ እጅግ አስደናቂ በመሆኑ ለመቀበል ቢከብደንም፤ የእኛ ታሪክ ግን እውነት ነው ይለናል።

**ዳሰሳ አቅራቢ: ወልደጊዮርጊስ ይሁኔ የ "ረቂቅ ኢትዮጵያ ፍልስፍና" ደራሲ**

*ርዕስ:- The Teshome Habte Gebriel Reader*
*ጸሐፊ:- Teshome H. Gabriel*
*ገፅ ብዛት:- 299*
*አሳታሚ:- AAU press*

ይህን መጽሐፍ የገዛሁት ሌሎች መጻሕፍትን ገዝቼ በተረፈኝ ጥቂት የኢትዮጵያ ብር ነው። አንዳንዶች መጽሐፋቸውን በምርቃት ወቅት በሚደረግ "ጨረታ" በሚሸጡበት a Vanity ሀገር እንዲህ በመዘንጋቱ ለማላውቀው ደራሲ ሐዘን እንዲሰማኝ ስላደረገኝ የገዛሁት ነበር። ሳላነበው ጥቂት ዓመታት ተቆጠሩና Think Ethiopia ን በድጋሚ ሳንቀሳቅስ ልጎበኘው ወደድኩ። በቅድሚያ እንዲህ ዓይነት ዘጊ ርዕስ እና አስቀያሚ የገፅ ሽፋን የሰራለትን AAU press እከስሳለሁ። በመሠረቱ የመጣጥፎቹ ስብስብ "Reader" ሊባል ይችላል ወይ የሚል የራሴም መከራከሪያ አለኝ።ይህን አልፋችሁ ወደ ውስጥ ስትገቡ ግን ተሾመ የሚባል አስገራሚ ሰው ያጋጥማቹኃል።

ተሾመ ኃ/ገብርኤል (መስከረም 24፣ 1939 – ሰኔ 14፣ 2010, እ.ኤ.አ) ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሲኒማ ምሁር እና በሎስ አንጀለስ በሚገኘው የUCLA ቲያትር፣ ፊልም እና ቴሌቪዥን ትምህርት ቤት ፕሮፌሰር ነበር። ተሾመ በሲኒማ እና በአፍሪካ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ፊልም ላይ እንደ ኤክስፐርት ይቆጠር ነበር። የ UCLA ባልደረባው “የሶስተኛው ዓለም ሲኒማን ወሳኝ በሆነ መንገድ ከመሰረቱት የመጀመሪያዎቹ ሊቃውንት አንዱ ነው” ይላል።ተሾመ በ1962 ወደ አሜሪካ ከፈለሰ በኋላ በ1967 በፖለቲካል ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪውን ያገኘ ሲሆን በ1969 በትምህርት ሚዲያ ሁለተኛ ዲግሪውን ከUtah ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል። በዩሲኤልኤ ትምህርቱን በመቀጠል በ1976 በቲያትር ጥበባት የማስተርስ ዲግሪ፣ በ1979 በፊልምና በቴሌቪዥን ጥናት የዶክትሬት ዲግሪ አግኝቷል። ከተሾመ የምርምር ስራዎች መሃከል Third Cinema in the Third World: The Aesthetics of Liberation in 1982 እንዲሁም Third Cinema: Exploration of Nomadic Aesthetics & Narrative Communities ,Otherness and the Media: The Ethnography of the Imagined and the Imaged, 1993 የሚሉት ዋንኞቹ ናቸው። በአርታዒነት ከሰራባቸው መሃከል

ደግሞ Emergences: Journal for the Study of Media and Composite Cultures እና "ጧፍ" የተሰኘ እና በአማርኛ የሚታተም የስነ ጽሑፍ ጆርናል ናቸው።

መጽሐፉ ደራሲው በተለያየ ጊዜ የጻፋቸውን ጦማሮች አሰባስቦ የሰነደ ነው። አንዳንዶቹ ስለ ሦስተኛ ሲኒማ (Third Cinema) ሐተታ የቀረበባቸው ሲሆኑ ቀሪዎቹ ስለ ግል ሕይወቱ የተጻፉ ናቸው። ሰውዬው በተማሪዎች እንቅስቃሴ ቁንጮ የደረሰ ሲሆን እዚህ ከሚታሰር ወጥቶ እንዲማር በንጉሱ የተሰጠውን "የማርያም መንገድ" በአግባቡ የተጠቀመ ነው። በመሰረቱ "ሶስተኛ ሲኒማ" በ 1960 ዎቹ መጨረሻ ላይ በፊልም ሰሪዎች ፈርናንዶ ሶላናስ እና ኦክታቪዮ ጌቲኖ "ወደ ሶስተኛ ሲኒማ" በሚል ርዕስ ከተዘጋጀ ማኒፌስቶ የተገኘ ቃል ነው። በታዳጊ አገሮች በተለይም በላቲን አሜሪካ፣ አፍሪካ እና እስያ ለሆሊውድ እና ለአውሮፓውያን ሲኒማ የበላይነት ምላሽ ሆኖ የታየውን የሲኒማ እንቅስቃሴ ያመለክታል።ሶስተኛው ሲኒማ በማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በተለይም ከ"ሦስተኛው ዓለም" ወይም ከግሎባል ደቡብ አገሮች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት ትኩረት በመስጠት ይገለጻል። ፊልም ሰሪዎቹ ውበትን ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ እና በፖለቲካዊ ግንዛቤ ውስጥ ያሉ ስራዎችን ለማጉላት ሞክረዋል። ዓላማቸው የንግድ ሲኒማን በመተቸት እና በማፍረስ አማራጭ እይታን ማቅረብ ነበር።

በሶስተኛው ሲኒማ እንቅስቃሴ ውስጥ የተሰሩ ፊልሞች እንደ ቅኝ ግዛት፣ ኢምፔሪያሊዝም፣ ማህበራዊ እኩልነት እና የነጻነት እና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ትግልን የመሳሰሉ ጉዳዮችን በማንሳት ጠንካራ የፖለቲካ ቁርጠኝነት አሳይተዋል። ሦስተኛው ሲኒማ ከሲኒማ የንግድ እና የኢንዱስትሪ ደንቦች ለመላቀቅ ይጥራል። በዚህም የአካባቢውን ማህበረሰቦች እና ተራ ተዋናዮችን የሚያሳትፍ አቀራረብን ይመርጣል። እንቅስቃሴው ብዙውን ጊዜ ቀጥተኛ ያልሆኑ ትረካዎችን እና የሙከራ የፊልም ቴክኒኮችን በመተግበር የግሎባል ደቡብን( Global South) ውስብስብ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ እውነታዎች ለመግለፅ ይሞክራል። በአጠቃላይ ተመልካቾችን ለማሳተፍ እና ለማንቀሳቀስ ያለመ ሲሆን አደንዛዥ መዝናኛዎችን ከመስጠት ይልቅ ወሳኝ ማህበራዊ እርምጃዎችን በመቀስቀስ ላይ ያተኩራል። ሦስተኛ ሲኒማ ጠንካራ እና ተደማጭነት ያለው እንቅስቃሴን በመፍጠር በዓለም ዙሪያ ያሉ የፊልም

ሰሪዎች የፊልሙን ሚዲያ የማህበራዊ ለውጥ መሳሪያ አድርገው እንዲጠቀሙ ይሰብካል።

ተሾመ የሃይሌ ገሪማ ዘመን ተጋሪ ቢሆንም ብዙም ሰው አያውቀውም። በመጽሐፉ ሶስተኛ ክፍል (233- 297) ተሾመ የግል ሕይወቱን ከፍልስፍናው ጋር እያያዘ ይነግረናል። እኔ ኤዲተር ብሆን እነዚህን መጣጥፎች ከፊት አመጣቸው ነበር። አንባቢ ሰውዬውን ካወቀ በኃላ ስራውን መገንዘብ ይችላል። ባለፉት አመታት፣ የተሾመ ተሰጥኦ እና አስተምህሮዎች ቁጥር ስፍር የሌላቸው ተማሪዎች እና መምህራን ላይ ተፅእኖ አሳድሯል። የፊልም እና የማህበራዊ ለውጥ ንድፈ ሃሳቦች ግንባር ቀደም፣ አብዮታዊ ምሁር፣ ጥልቅ አርቲስት እና ታላቅ ሰው እንደነበር ይታወሳል። ተሾመ ትሑት እና በሰፊ ልቡ ታዋቂ ነበር። ተሾመ ጁን 14 ቀን 2010 በልብ ህመም በ70 ዓመቱ ቢያርፍም ከባለቤቱ መድሃኒት የምትባል ሴት እና ፀጋዬ የሚባል ወንድ ልጅ አፍርቷል። የተሾመ ፍልስፍና የThink Ethiopia እህት የሆነች Cinema Ethiopia የተሰኘች የሀገርኛ ፊልም ዳሰሳ የምናደርግባት ገፅ እንድንከፍት ምክንያት ሆኗል።

The Reviewer **ዳዊት በዛብህ** is the managing editor of Think Ethiopia

## ምዕራፍ አምስት

# የሕይወት ክህሎት

*ርዕስ :- "የፈረንጅ ሚስት"*
*ደራሲ፡- እስከዳር ግርማይ (የ "ሰውነቷ›" እና "ጥቁር እንግዳ" ፊልም ደራሲ እና ተዋናዬት)*
*ዘውግ:- Memoir*
*Rating:- 8.9*

**ንቁ፤**
**......ብቁ፤**
**ቁጡ፤**
**......ቅንጡ፤**
**ጥንቁቅ፤**
**......ምጡቅ፤**
**ድንብልቅ፤**
**......ፍልቅልቅ፤**

*(ለእስከዳር ግርማይ)*

---

**#መነሺያ፡-**

ሪዛሙ ደራሲ በርናንድ ሾው ‹‹Major Barbara›› በሚል ድርሰቱ አንዲት ልባም ሴት አስተዋውቆናል። በበኩሌ የበዓሉ ግርማ ሴቶችም ለእኔ ጉምቱ ናቸው፤ እነ ሒሩት፣ ሉሊት፣ ፊያሜታ......ካለፈው ዓመት (2014 ዓ.ም.) አንስቶ የሴት ደራሲያን ቁጥር እየተበራከተ መምጣት ለሥነ-ጽሑፋችን ጉልህ አበክሮ ይኖረዋል፤ በጣም ደስ ተሰኝቼአለሁ፤ ለመሆኑ ሴት የሌለችበት ነገር ምኑ ይጥማል?.......ከእነዚህ መካከል እስከዳር ግርማይ አንዷ ናት፤ "ኢትዮጵያዊ ሀገሩ የት ነው?" በተነበበ በወራቶች ልዩነት "የፈረንጅ ሚስት"ን አስነበበችን፤ ለአሁን ስለ "የፈረንጅ ሚስት" እናውጋ፡-

"የፈረንጅ ሚስት" በተሰኘ ድርሰት እስከዳር ግርማይ በፈረንጅ ሚስትነት-የእራስዋን ተሞክሮዎች፣ ገጠመኞች አሳዛኝ ወላ አስደሳች ቀናት፣ ሞግታ የረታችባቸውን አጋጣሚዎች - ከሌሎች - ከወዳጅ ጓደኞችዋ

(ከፈረንጅ ሚስቶች) ጋር እያጣቀሰች የተረከችበት ድርሰት ነው፤ ቋንቋው ግልጽ ግና ውብ እና ትረካው ፈጣን ድርሰት ነው፤ ሳነበው እንዲህ ሆነ፡-

**#1ኛ**. ነገረ መቃን/Frame-work - አንድን የድርሰት ወላ የጥናታዊ ጽሑፍ ሀሳብ ለማስኬድ መቃን ሁነኛ ዘዴ ነው፤ ፎቶ በመቃን ሲሆን ውበት ይኖረዋል። እስከዳር የታላቁን ባለቅኔ የጸጋዬ ገ/መድኅንን ‹‹አድባር›› የሚል ግጥም እና ከቲያትሮቹ መካከል ደግሞ ‹‹ማነው ምንትስ?›› የሚል ሴቶችን የሚያበቃ ሀሳብ ላይ ተመርኩዛ፣ ወይም መቃን አድርጋ በመገልገል ሀሳቧን ትተርካለች። በእርግጥ ድርሰቱ በተለያዩ ገጠመኞች፣ ትንታኔዎች፣ መዘርዝሮች እና ምሳሌዎች የተሞላ ቢሆንም ሲቋጭ ከመቃኑ ፈቅ አይልም፤ ሴቶች በማኅበረሰቡ ዘንድ አበክሮ እንዳላቸው ይጠቁማል የሚል ዕምነት አለኝ። አልቆጨኝም፤ ረክቼአለሁ!!

**#2ኛ**. ነገረ ጥናታዊ ጽሑፋዊነት - ድርሰቱ ለቀለም ትምህርት ብሎም ለዓለም-አቀፍ ንባብ መዋል የሚችል ጥናታዊ ጽሑፍ ነው ብዬ አምናለሁ፤ ደራሲዋ ተሳታፊ ቀጂ እና የጥናቱ አካል በመሆን/participant observant በመሆን በፈረንጅ ሚስትነት የገጠማትን ዕክል፣ መድሎ፣ ኢ-ፍትሕ እና ሌላም ነገር ትተርካለች፤ ትረካው ደግሞ በሁኔታዎች እና በሰዎች አኳኋን ላይ መሠረት ያደረገ interpretive analysis ነው (እመለስበታለሁ)። እናም ድርሰቱ ሴቶችን በተመለከተ ለሶሾሎጂ፣ ለሥነ-ልቡና፣ ለምጣኔ-ሀብት እና ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ሁነኛ ምንጭ በመሆን ያገለግላል ብዬ አምናለሁ። “Challenges that Hampers Yeferenj Mist” በሚል ርዕስ ለዓለም እንደምታስነብብ አልጠራጠርም።

**#3ኛ**. ነገረ ቁጣ - በወንዴ ጾታ በኩል ትክክል የሚመስሉ ግና መረንና መቀጮ የሆኑ ድርጊያዎች፤ በትንሹ አላስፈላጊ፣ ወይ፣ መናኛ፣ ወይ፣ ክብረ ነክ ቃላት አጣጣላችን ምን ያክል የሴትዋን መንፈስ እንደሚያስቆጣ፣ አልፎም ጫና እንደሚያሳድርባት የሚያስገነዝብ ድርሰት ነው፤ መረንና ፈር ከሳቱ አባባሎች እስካልተቆጠብን ድረስ የሴቶቹን ሥነ-ልቡና እንደምናለምሽ የሚያስጠነቅቅ ድርሰት ነው፤ ለምሳሌ፡-

በገጽ፡- 23፣ 34 እና በሎሎች የቀረቡ ተረኮችን ማየት ይቻላል።

**#4ኛ**. ነገረ ትንተና/interpretive analysis - በqualitative research መስክ ተመራጩን የትንተና ዘዴ interpretive analysis በመጠቀም፣ የሰዎችን ፊት በመፈተሽ ብሎም የቃላት አጣጣልን ከግምት በማስገባት እና ከሁኔታው/ከጉዳዩ በማናበብ የሚከናውን ትንተና ማለት ነው፤ ለምሳሌ፡-

በገጽ 32፣ 33 ላይ ከአንድ ጋዜጠኛ ጋር የምታደርገውን ውይይትና ትንተና እና ሌሎችንም ማየት ይቻላል፤

**#5ኛ**. ነገረ ፍካሬ - እውነትን በሥነ-ውበት መፈከር የዚህ ድርሰት በጎ ጎኑ ነው፤ አንዳንድ ውበታም ቃላት፣ ገላጭ ሐረጋትና ዓረፍተ-ነገሮች በብዛት ይስተዋላሉ። የዓረፍተ ነገር አጀማመርዋም ቢሆን መሳጭና ሁሉን አቀፍ ነው።

ማሳያ፡- ገጽ 36 "የሰይጣን ጆሮ ይደፈንና ከባለቤቴ ጋር ተፋትተን ንብረት ክፍፍል ውስጥ ብንገባ፣ ባለቤቴ መቀመጫዬን ከራሱ ድርሻ ንብረት ጋር ሳይደምረው አይቀርም...."

**#6ኛ**. ነገሬ ሚዲያ እና ክብረ-ነክ ጋዜጠኞች - በድርሰቱ አንዳንድ የሚዲያ እና የሚዲያ ባለሙያዎች ክፍተት ተቃኝቷል፤ መረን እና ለሙያቸው ክብር እና ግንዛቤ የሌላቸው ጋዜጠኞች ምን ያክል የሴትዋን መንፈስ እንደሚያስቆጡ ያሳስባል፤ ለምሳሌ፡-

ከገጽ 32-41 ያለውን ውይይት መመልከት ተገቢ ነው።

**#7ኛ**. ነገረ ተጽዕኖ - ድርሰቱ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ (በውጭም በአገር ውስጥም) በሚገባ ያስቃኛል፤ የሞራል፣ የአካል፣ የመንፈስ፣ ኢ-ፍትሐዊነት...ወዘተ ጫናዎች በፈረንጅ ሚስቶች ላይ ሲደርሱ እናያለን።

**#8ኛ**. ነገረ ተራ ግምት/wild-guess - የውጭ አገር ብሎም የአገራችን ሰዎች ለፈረንጅ ሚስት ያላቸውን ተራ እና መናኛ ግምት ከዚህ ድርሰት መገንዘብ ይቻላል፤ የፈረንጅ ሚስት በራስዋ ጥረት እንደማትኖር አድርጎ መሳል አንዱ ክፍተት እንደሆነ በመረጃ አስደግፋ ትሞግታለች።

**#9ኛ. ነገረ ሙግት/discourse - በዚህ ድርሰት ያልተገባ ንግግር እና ተራ ግምት ሲገጥማት ከተሳሳተው ግለሰብ ጋር ቀጥተኛ እና ግልጽ ውይይት በማድረግ የተሳሳተ ግንዛቤን መቀየር እንደሚቻል ያሳየችበት መጻሕፍ ነው፤ ሴቶች በምክንያታዊነት ላይ ተንተርሰው ክርክር እና ሙግት ሲገጥሙ ታስቃኛለች፤ ሴቶችን ማብቃት ነው ይኼ! ለአብነት፡-**

**ገጽ 74 ላይ ደራሲዋ/ተራኪዋ ከአንድ የአረብ ሰው ጋር ስትሞግት ወላ ስታሳምን እናገኛለን!**

**#10ኛ. ነገረ መሰናሰል እና የፍሰት ወጥነት - ድርሰቱ ከምዕራፍ ምዕራፍ የተያያዘ እና በቂ መዘርዝሮችን ያቀፈ ነው። በተጨማሪም ምሳሌዎችና ምዕራፎቹ ከዋናው ሀሳብ የማይጋጩ ናቸው፤ ረክቼአለሁ!!**

**#11ኛ. ነገረ ምክረ-ሀሳብ/recommendations - ደራሲዋ በተለያዩ ጊዜያት የገጠምዋትን ክስተቶች ወ ገጠመኞች ተንትና ካቀረበች በኋላ ‹ከእጇ ውጪ› ብላ አትገላገልም፤ ለጠቀሰቿው ችግር መፍትሔ ይሆናሉ ብላ ያሰበችውን (ሚዛን የሚደፋ) የምክር ሀሳቦችን ትለግሳለች። እንዲያ ይሻላል!!**

**#መውጫ፡-**

**በጥናታዊ ጽሑፍ አንድ የተለመደ አባባል አለ፤ ‹‹Publish or Perish›› ይሉት ብሒል ነው ታዲያ። የምርምር ወላ የድርሰት ሥራዎች ለውጥ እንዲያመጡ ከተቻለ ለኅትመት እንዲበቁ ማስቻል፤ አሊያ ወዲያ መጠቅለል። በአጠቃላይ፣ አንድ ድርሰት ወላ ጥናታዊ ጽሑፍ በተደራሲው ወይም በተጠኚው ላይ ፈጣን አሉታዊ ጫና ማሳደር ከቻለና ትክክለኛወን መንገድና መፍትሄ እንዲመርጥ ካስቻለ ግቡን መቷል ማለት ይቻላል፤ ‹‹የፈረንጅ ሚስት›› በእራሴ ላይ ፈጣን እርምጃ እንድወስድ አድርጎኛል፤ ምናልባት ከዚህ በፊት ለፈረንጅ ሚስቶች ወላ ለሴቶች የነበረኝን ተራ እና መናኛ ግምት እንድከልስና ትክክለኛወን እሳቤ እንድፈትሽ አስችሎኛል ብዬ ብናገር ከሕሊናዬ አልጋጭም!!**

**ሒሳዊ ዳሰሳ፡- Yonas Tamiru Gebre , associate editor at Think Ethiopia**

*ርዕስ: የልብ ጠጋኙ ማስታወሻ*
*ደራሲ: ዶ/ር ፈቀደ አግዋር*
*ገፅ ብዛት: 213*
*ዘውግ: ማስታወሻ*

የሰው ልጆች በሥራ ገበታ የሚገጥማቸውን ፈተና በሙሉ በትምህርት ቤት ተምረው ይወጣሉ የሚል ዕምነት የለኝም። ነገር ግን ጽኑ እምነቴ ሁሉም በየሙያው የሚማረው ሁሉንም ማሸነፍ የሚችልበት የማሰቢያ መንገድና basic Principles ነው ብዬ አምናለሁ።” የልብ ጠጋኙ ማስታወሻ ገጽ 47በዶ/ር ፈቀደ አግዋር እንደተነበበኝ። (ይኽ ዳሰሳ ከአንድም ሁለት ጊዜ ጽፌው ከፋይል ጋር ተደጋጋሚ የመጥፋት አደጋ ገጥሞታል።እጅ መስጠት አልፈለግኩምና እነሆ በድጋሚ ልጭረው ወደድኩ።

**ማንደርደሪያ**

በመጀመሪያ በሬድዮ የዜና እወጃ አንድ ረጅም ሰዓት የፈጀ ቀዶ ጥገና እሱና ባልደረቦቹ አካሂደው ስኬታማ መሆኑን አስመልክቶ ሲያብራራ አደመጥሁ። ተደሰትኩ። በመቀጠል በማህበራዊ ድረ ገጽ በኩል በተለይም በፌስቡክ የተለያዩ ሐሳቦችና ምስሎችም ሲዟዟሩ አየሁ። በመጨረሻም የልብ ቀዶ ጥገና አጀማመሩንና ተሞክሮዎቹን በተመለከተ ማስታወሻ ማሰናዳቱንና የመፅሐፉ የሽፋን ምስልም ተመለከትኩ። ደስም አለኝ። (የውጮቹ ከፈረሱ አፍ እንዲሉ መሆኑ ነው። ወይም አገርኛው ማን ይናገር ... ብሂል።) መረጃውንና የሽፋን ምስሉን ያለማመንታት የፌስ ቡክ ገጼ ላይ በማጋራት ለወዳጆቼ መረጃውን ማካፈል ጀመርኩ። ቀስ በቀስ በሂደት እዛው ፌስቡክ መንደር የወዳጅነት ጥያቄዬን ሰድጄ ይሁንታን በማግኘት ተወዳጀሁት። ደስታዬ እጥፍ ሆነ። ዕድለኛ ነኝ ማለቴንም አልደብቅም ከተወዳጀሁት ከጥቂት ጊዜ በኋላ የወዳጆቹ ብዛት 5ሺህ በመሙላቱ የወዳጅነት ጥያቄን የማያስተናግድበት ሁኔታ ላይ ተገኝቷልና።

ስለ ማስታወሻ መጽሐፉ የመገናኛ ብዙሃን ላይ ቀርቦ ሐሳብ ሲሰጥ፣ ሲያብራራ ጉጉቴ ወደር አልነበረውም፤ ደግሞም ያለው መረጋጋት የሚጋባ ዓይነት ሆኖኝ አቦ ይሄ ሰው ብያለሁ በአግራሞት። እያደር የፌስቡክ ገጽ

መግለጫ /ፕሮፋይል/ ምስል ረጅም ጊዜ ያኖርሁትን የአገሬ ጉምቱው የጥበብ ሰው ምስል ተክቶ የመፅሐፉ ሽፋን አደረግሁ። ጉጉቴ ጉጉት ብቻ ሆኖ አልቀረም። ከንቱም አልነበረምና መጽሐፉ ለአንባቢያን ደረሰ። በወቅቱ ክፍለ አገር ነኝና (ከአዲስ ውጪ የቅርብ ሩቅ ነገር፤ አፍንጫ ስር እንዲሉ ያለ) መፅሐፉ እንደወጣ አልደረሰኝም። ተንቆራጠጥኩ፤ አልዋሻችሁም በጣምም ሰፍ አልኩ። በወቅቱ ቤሳ ርቆኛልናም ጠንከር ብዬ ከአዲስ አበባ አምጡልኝ ማለትም አልቻልኩም። ብቻ ጉጉቴን ያየው ወዳጄ መጽሐፉን መግዛቱንና የሚመጣ ሰው ካገኘ ሊልክልኝ ቃል ገባ። ይኼኔ ጻድቃን አይቀጣጠሩም ነውና ለአንድ ጉዳይ ወደ አዲስ የምደርስበት አጋጣሚ ተፈጠረ።

ይኸው ወዳጄ ቤት ነውና ያረፍኩት ዓይኖቼ ከመፅሐፉ ላይ ሊነቀለ አልቻሉም። ቆይቼ መቼም አምሮትና ይሉኝታ አይደፋኝ ብዬ - እስቲ ማስታወሻውን አቀብለኝ ማለት። እሱም አውቆብኝ ነበረና ከእንግዲህ ሊያቆየኝ አልወደደም። ወዳጄን ወደ እንቅልፉ እየሸኘሁት ንባቤን ተያያዝኩት። ሳያንቀላፋ አንድ ሁለት (2) ታሪክ ፉት ብዬለት ከዕንባዬ ጋር ትግል ላይ ነኝ። እንዳይወርድ የዓይኔን ዳር ዳር እያበስኩ - ወደ ጣራም እያንጋጠጥኩ ለማሳለፍ እየጣርኩ ነገር። ግን የሆዴን ትግል ማዳፈን አልተቻለኝና አፍንጫ ሲመታ ዓይን ማልቀሱ፤ ዓይን ሲያነባ አፍንጫም ዝም አለማለቱን' ሊያግዝ/ ቀጠሮ እንዳለው ማን አውቆት። ብቻ ወዳጄም ወደ ዕንቅልፉ እኔም ወደ ንባብና ቁዘማዬ ... ቁዘማህን ደግሞ ምን አመጣው ባይ አይጠፉም መቼስ የዶክተር እንግልት- በየህክምና ትንቅንቆቹ ውስጥ የሚያሳየው ከልብ የሆነ መሰጠት፤ ምንም ኩሸት ያልተቀላቀለው ሰውኛ የሆነው አቀራረቡ፤ እንዲሁም ለሰው ልጅ ያለውን ክብር።

ከታማሚ/ ታካሚዎቹ ጋር የሚታመምበትን መንገድ አክሚቸው ድነው ህመሙ ትንፋሽ አሳጥሮባቸው፤ ምግብ መመገብ አቅቶአቸው የነበረውን እፎይ ሲሉ ሲያይ የተሰማቸውን ራስ ምታት ድካማቸውን ሲኖረው ሳይ በእውነት ምን ዓይነት ሰብዕና ነው እያልኩ እየተደመምኩም ነበረና ንባቤ ቁዘማ ሲያንሰኝም አይደል? ማሳያ ይሆነኝ ዘንድ ደጋግሜ ባነበብኩት ቁጥር እንደ አዲስ የሚያስነባኝ ታሪክ መዝጊያው ላይ ትንሽ ልቀንጭብልህ/ሽማ ... ይኸን አስቸጋሪ ጊዜ ባለፈች አመት ከስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ይኸች ወጣት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ተኝታ እንደገና ደወለችልኝ። ሆዴን ባር ባር

እያለው ደግሞ ምን ተፈጠረ በማለት ጥያቄዬን አቀረብኩ። ነገር ግን ዛሬ ይኸች ወጣት የደወለችልኝ የወንድ ልጅ እናት መሆኗን ልትነግረ ነበር።"ጊዜ አላጠፋሁም ነበር፤ በሩጫ ከልብ ማዕከል ወጥቼ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስድስተኛ ፎቅ በፍጥነት ሄድኩኝ። አቅፌ ሳምኳት። ሕጻኑንም ባለማመን መንፈስ ገብቼ አየሁት። ትልቅ ሸክም የቀለለኝ መስሎ ተሰማኝ። ያሰብኩት ተሳካ፣ ያለምኩት ደረሰ፤ የሚለውን ዘፈን ማን ነበር የዘፈነው?"(ገጽ:21/2) ከአስጨናቂ ምጥ በኋላ ጣዕም እየፈጠረ፣ እያሰሰ። እያንዳንዱ ታሪክ ዳኅስ ያለ ጥራዝ ይወጣዋል። እያንዳንዱ የቀዶ ጥገና ቆይታ ተዓምር ተመዝግቦበታል። እንዘልቅ:ሥራዎቹ ላይ ለሚገጥሙት ጉዳዮች መፍቻነት፣ ለማመሳከሪያነት፣ መንገዱን በዕውቀት ለመደገፍ ዓለም አቀፍ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ይጠቀማል። ከመፅሐፉ ጀርባ ለማጣቀሻነት ከቀረቡት መሀል አንድ ሁለቱን ለማየት ሞክሬአለሁ።እነዚህን ውስብስብ የሳይንስ ጆርናል አርቲክሎች ተጠቅሞ የሰራውን ረቂቅ ሥራ - ለአገሬ አንባቢ ያቀረበበት መንገድ እጅግ ያስገረመኝ ነው። ረቂቅ ጽንሰ ሐሳብን አቅልሎ ማቅረብ በዘርፉ ያለውን የጠለቀ ዕውቀት ማሳያ ይመስለኛል። ከዚህ አልፎም የማስታወሻው አቀራረብ ትልቅ የስነ ጽሑፍ ስጦታ ጭምር እንዳለው ያየሁበት ነው።

የጋዜጠኝነትና ስነ ተግባቦት የትምህርት ዘርፍ ላይ ስንማር የሳይንስ ጋዜጠኝነት እጅግ ከባድ መሆኑን መምህራችን የነገሩንን አስታውሳለሁ። ምክኒያቱም የምርምርና የጥናት ውጤቶች የሚዘገቡባቸው ጆርናሎች ጠንከር ያሉ ቃላትን፣ የሙያ አገላለጾችን አልፎ ተርፎም ጽንሰ ሐሳቦች፣ መላ ምቶችና ድምዳሜዎች በከባድ አገላለጽ የሚቀመጡባቸውና ዘርፉም ቴክኖሎጂና አዳዲስ ግኝቶች በብዛት የሚዘዋወሩበትና የሚተዋወቁበትም እንደመሆኑ ከሐሳቦቹና አገላለጾች ጋር መላመድን ከባድ ያደርገዋል። በተወሰኑ ዓመታት የጋዜጠኝነት ቆይታዬም መታዘብ የቻልኩት ይኸንኑ እውነት የሚያጠናክር ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የዶ/ር ፈቀደ የልብ ጠጋኙ ማስታወሻ በዚህ ረገድ ሳደንቅ ከፍ ብዬ የጠቀስኩትን ተግዳሮት የተሻገረ ሆኖ በማየቴም ነው።

መፅሐፉ በሀገራችን የሳይንስን ዘርፍ ለዋነኛው ባለቤት /ለተገልጋዩ ሕዝብ በማድረስ በኩል በተለይም በህክምናው ረገድ ያለውን የተግባቦት መንገድ አታካችና ሩቅነት communication disparities/ በደንብ የተገነዘበ መሆኑን ያሳብቃል። በህክምናው መስክ ያለው የተግባቦት አግባብ ሩቅ ነው ብሎ የዚህ

ዳሰሳ አሰናጅ ያምናል። የተለያዩ ገፌ ምክኒያቶች ለአብነትም የስራ ጫና፣ የተገልጋዩ የሚነገሩትን ጉዳዮች በትክክል አለመተግበርና ከህመም ጋር የሚታገል ቢሆንም የራስን ስሜትና ድካምን ብቻ የማድመጥ አባዜ እንዳለ ባይዘነጋም/ ይኸንን ከተፈቀደልን በሌላ ጊዜ እንመለስበት ዘንድ እንደ ቀብድ ይያዝልንና አሊያም በዚህ መልኩ የሚያፍታታው ሰው ቢገኝ እየተመኘን ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ ...እናልን በህክምናው መስክ ለዚህ የተግባቦት አግባብ የሰመረ አይደለም የሚለው የጸሐፊው ሐሳብ ዶ/ር ፈቀደም ስምም የሆነ አስተያየት ያለው መሆኑን ማጤን ይቻላል። ታሪኮቹ ላይ አገራችን ላይ ያለውን የታካሚና የህክምና ባለሙያው የተግባቦት ርቀት ጠቆም የሚያደርጉ ነጥቦችንም እናገኛለን። ተከታዩን ለምሳሌ ያኸል እንይ

"ለምን እንደሆነ አላውቅም" አለችኝ። እስካሁን የበሽታዬ ምንነት ማንም ሊያስረዳኝ አልቻለም። አሁን ግን ልቤን ለዚህ ለከፋ ደረጃ ያደረሰውና የልብ በሮቹ እንዲጠቡና እንዲያፈሱ የሆኑት ከልጅነቴ ጀምሮ ያጠቃኝ በነበረው የቶንሲል በሽታ ምክኒያት መሆኑን ተረድቻለሁ። በደፈናው የልብ በሽተኛ' እየተባልኩ የልብ ክፍል እየመጣሁ በየወሩ እነዚህን መድሃኒቶች ከመውሰድ ውጪ ምን እየሆንኩ እንደሆነ አልገባኝም። ....." ገጽ 158 እንግዲህ ይህ በአገራችን ካሉት ዩኒቨርሲቲዎች በአንዱ የ3ኛ ዓመት ተማሪ የሆነች ወጣት የገጠማት ነው። ስለ ጤንነቷ ሁኔታ ተገቢውን መረጃ አግኝታ በራሷ የምታደርገው ተጨማሪ ክትትልና ራሷን የምትንከባከብበት መንገድ አንብባም ይሁን ከተለያዩ የዕውቀት ምንጮች እንዳትጠቀም የሁኔታዎች የቅርብ ሩቅነት ምን ያኸል ዋጋ እንደሚያስከፍለን አንዱ ማሳያ ነው።

ከዚህ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች በአንዳንድ የተወሰኑ ንባቦቼ እንዳስተዋልኩት እና መፅሐፉም እንደሚያስረዳን ከቶንሲል ጋር ተያይዞ የሚከሰተው የግራ የልብ በር ህመም /mitral stenosis/ ሚትራል ስቴኖሲስ በምዕራቡ ዓለም ችግር የመሆኑ ጉዳይ ያበቃለት ነው። ያውም ከ30ና 40 ዓመታት በፊት። ምክኒያቱ ደግሞ የቶንሲል ህመም ከመጀመሪያው ጀምሮ ተገቢውን ክትትል ከተደረገበትና አስፈላጊውን አንቲባዮቲክ መድሃኒት ከተሰጠው ይህ ቆይቶ የሚከሰት ህመም አይከሰትምና። እኛ ጋር የባሕል መድሃኒት ዝንጅብልና ደረቅ ነገር ብላበት/ብዬበት ይተውሃል እየተባባልን በወጉም ሳንታከመውና ሳናስታምመው የሚከርመው ህመም ስር ሰዶ የከፋ

ደረጃ ያደርሰናል። ባለሙያውም ቁሱም መፅሐፉም ዝም' ሆኖ ሰዶ ማሳደድ ሆኖብን እንዲችው አለነው። ልብ ብለን ካስተዋልን ይኸንንና መሰል የሚያሙ እውነቶችን መፅሐፉ ያስዳስሰናል፣ ይፈነትውልናል።

የሠው ልጆች በሥራ ገበታ የሚገጥማቸውን ፈተና በሙሉ በትምህርት ቤት ተምረው ይወጣሉ የሚል ዕምነት የለኝም። እኔም ብሆን ይኸን ዓይነት ዕጢ በዓመት ከ7000 – 8000 የልብ ቀዶ ጥገና ከሚሰራ ቤት ተምሬ (ህንድ አገር በትምህርት ሳለ መሆኑ ነው።) እንኳን ልንሰራው ቀርቶ ሠምተነው አናውቅም ነበር። ነገር ግን ጽኑ እምነቴ ሁሉም በየሙያው የሚማረው ሁሉንም ማሸነፍ የሚችልበት የማሰቢያ መንገድና basic Principles ነው ብዬ አምናለሁ። (ገጽ47) በማለት ከከባድና ፈታኝ የቀዶ ጥገና ቆይታው ጋር አዛምዶ ጽኑ እምነቱን የሚያጋራን ዶ/ር ፈቀደ መሰል ፈታኝ ገጠመኞች በእሱ አጋፋሪነት በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄዱት የተለያዩ የልብ ቀዶ ጥገና ወቅት እንዳጋጠሙ ታሪኮቹ ላይ እናነባለን። ጉዞው ምን አድካሚና ፈታኝ ቢሆን፤ የቁሳቁስ፣ የሀብትና በዘርፉ ዕውቀት ዕጥረት (የሉም ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ መሆኑንም አይደብቀንም)፤ ጥልቅ የሙያ ፍቅር፣ ረፍት የለሽ ማንነት፣ በትጋት የሚገለጽ የህሙማንን ችግር ጫማቸው ውስጥ ቆሞ የመረዳትን ትልቅ አቅም እነዚህ ፈታኝ ጉዞዎች ፍሬያማ ሆነው ዛሬ ላይ በኩራት የሚነገር ታሪክ እንዲኖራቸው አድርጓል።

## ስናጠቃልል

መፅሐፉ ዶክተር ፈቀደ አግዋር በጠቅላላ ቀዶ ጠጋኝ ሀኪምነት ከሚሰራበት የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ኮምፕርሄንሲቭ ሪፈራል ሆስፒታል ወደ ልብ ቀዶ ጠጋኝነት የትምህርትና የሙያ ጉዞ ከመታጨት እስከ ት/ት ሂደት ቀጥሎም ሙያውን የጀመረበትን መንገድ በመግቢያው በማስተዋወቅ፤ እጅግ ሰፊ ልምድ የያዙና ተለያይነት /ቫራይቲ ያላቸው 17 የቀዶ ጥገና ታሪኮችን፤ በታሪኮቹ ውስጥም መጠነ ሰፊ ትምህርት - ልብ ያለው ልብ ይበል የሚያሰኙ አኳቷል።እነዚህን ታሪኮች እየዕለት ውሏችን ውስጥ ተርጉመን በየሙያችን ለሚኖረን አበርክቶ ኃይልን የሚለግሱ - ከዶ/ር ፈቀደና የሙያ አጋር ባልደረባዎቹ አልሸነፍ ባይነት- ሙያን ይዞ ራስን በዕውቀት በማጎልመስ እስከምን ድረስ አሻፈረኝ ማለት እንደሚቻል ያየሁበት ሆኖኛል። ዶ/ር ፈቀደ

አግዋር በማስታወሻው ባስነበበኝ ታሪኮች በኩል- ከሰዎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት በኩል አጮልቄ አርአያ የምለው ሰብዕናዬ ሆኗል። ደግሞም በማዕከል ደረጃ የጀመሩት በአገር ውስጥ የልብ ህሙማንን የቀዶ ጥገና ህክምና የማድረግ ጥረት ከፍ ያለ ሰብዕናቸውን የማይበት ነውና ሁሉም ዓላማችሁ መር ባይ ነኝ።

**ቪቫ ዶ/ር**

"የኔነቴን አሻራ በምድሪቱ ሳልጥል በዕውቀቴ ሳልሰራ ለመኖር ሳልታገል ለሙት ሙት ሆኜለት መች እቀመጣለሁ እሮጣለሁ ሮጣለሁ፣ እሮጣለሁ ሮጣለሁ" የሚለውን እንደ መዝሙሬ የማየውን የእዮብ መኮንን ዘፈን የሚመጥን ሕይወት ስላየሁ ባንተ ደስይለኛል!

**ዳሰሳ አቅራቢ፡ አንዋር ሙሰማ (የአስካለች እና የመሐን)**

*የመጽሐፉ ርዕስ፡- የኔ ማስታወሻ*
*ሰናጅ፡- ስንዱ አበበ*
*የታተመበት ዓ.ም፡- 2013 ዓ.ም*
*የገፅ ብዛት፡- 111*

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስንዱ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ጓደኞቼ የፃፉልኝ ደብዳቤዎች ብላ ያካተተቻቸው ጽሁፎች እጅግ መሳጭ ናቸው። ጸሐፍያን ወገጣምያን ጋዜጠኛን ጨምሮ የሚጽፉትን ሃሳብ ሆነው በገሀዱ ዓለም ገሃድነታቸውን አምነው ሲጽፉ ለካ እንዲህ ናቸው። ለካ ሁላችንም የየራሳችን ማስታወሻ እንዲህ ይሰነድ ኖሯል። ቤተሰብ አልያም ሌላ እንዳያየው ተብለው የእሳት እራት የሆኑ ደብዳቤዎች ትውልድ ይቁጠራቸው። ስንዱ ደፋር ናት። ያመነችበትን ትፅፋለች። ስልጣን፣ ጉልበት ሳያስፈራት ትጋፈጣለች። ድፍረት ብቻውን አይበቃም። ስንዱ ድንቅ የስነጽሑፍ ችሎታ አለት። ለጋዜጣ የፃፈቻቸው መጣጥፎች ተቆጥረው አያልቁም። ስንዱ ከሃገራችን ትልልቅ የስነጽሑፍ ስብእናዎች ጋር የቅርብ ወዳጅነት ነበራት።

በዚህ "የኔ ማስታወሻ" በተሰኘ መጽሐፍ ሰው ሰው የሚሸቱና፣ ይዘታቸው ለነፍስ የቀረበ የሀገራችን ገናና ጸሐፊያንና የጥበብ ሰዎች ለስንዱ አበበ የፃፏቸው ደብዳቤዎች በተዋቡ ሥነ ጽሑፋዊ ይትበሃሎች ተከሽነው ቀርበውበታል። ግጥሞችም እንዲሁ። የሰውኛ ለዛን የተላበሱ፣ ያልተድበሰበሱ፣ ማስመሰል ያልነካካቸውና ከነድካም ብርታታቸው ሳይሸፋፈኑ ሰዎቻችንን ተገላልጠው ቆመው የሚታዩበት ነው። ስብሐት ገብረእግዚአብሔር፣ ደረጀ ደስታ፣ ስዩም ተፈራ፣ ሚካኤል ሽፈራው፣ ሙሉጌታ ተስፋዬ፣ ብርሃነ መስቀል ደጀኔ፣ መስፍን አሸብር፣ ሞገስ ሀብቱ፣ ታገል ሰይፉ፣ መስፍን ገብረማርያም፣ መስፍን ካሣና ፍሬዘር አድማሱን ታገኙዋቸውአላችሁ። ነፍሴን የገዙኝ የባሴ ሀብቴና የግፋወሰን አክሎግን መሳጭ ደብዳቤዎችም ትኮመኩሙበታላችሁ። ለስም ያህል ደብዳቤ አልነው እንጂ መሳጭና ክላሲክ ሥራዎች ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስንዱ - ጉኖዬ.ንግስት ናት። ጉኑ ቅኔ ናት። ጉኑ ጥበብ ናት ጉኑ አድባር ናት። ጉኑ የፍቅር አምላክ የፍቅር አድባር ናት። እንዲህም ናት ብንል........እንዲያም ናት ብንላት......እግዜር የዘረፋትስንዱ ቅኔ ናት። ይላታል ፍሬዘር አድማሱ..!!

እስኪ ቀጣዩን የመስፍን ገብረ ማርያምን ጽሑፍ ላስነብባችሁ...!!

"ጥሬ አይደለች አትጎመዝዝ አልወየበች አላረፈች አልሰከነች ተፈላጊም ፈላጊም ናት ተመኝተው የሚመኟት። ብትለኮስ የምትነድ ካወቁላት የማትበርድ ሚስጢር ያላት ውስጠ ወይራ በጠረኗ የምትጠራ። ተፈልጋ ለመዳኒት ለልብ ሳንባ ለኩላሊት ማገገሚያ የሚያደርጓት።"

*መስፍን ገ/ማርያም 1979 ዓ.ም*

ይቀኙታል የፍቅሯን ቅኔ ብቻ ስንዱ ወርቀ ዘቦ ናት ....!! ቀጣዩን የስብሐት ገ/እግዚያብሔርን ጽሑፍ ልቀጥል፦

"ለስንዱ ነብሴ አፈር ድሜ ውስጥ ያዝማሪ ዘፈን እየሰማሁ - አቤት ደስ ማለቱ! ከድንገተኛ ፈገግታሽ እኩል! ሲመጣልኝ ላንቺ "እንግዲህ መጣብኝ ያ ሁሉ ሳቅና ያ ሁሉ ማዘን ያ ሁሉ ግዴለሽ ያ ሁሉ ስንዱ አንዲትም ቃል የለች፤ አንቺን የምታክል አንቺን የምትወክል አጀብ! ማየቱ ይበቃል! ፩ ቀን ካንቺ ጋር ሆኖ ማለፉ ይበቃል!! አትጠገቢም እንጂ!"

ስብሐት ገ/እግዚያብሄር ይሏታል ራሷን ስንዱን ቅኔዋን እየተቀኙላት እየዘረፏት። ስንዱ አበበ (Senedu Abebe) የኢትዮጵያ ዕንቁ ጸሐፊያን ሥራዎቻቸውን የኅትመት ብርሃን በማብቃት ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እድገት ትልቅ ድርሻ አብርክታለች። ለአሁኑ ትውልድ እንዲደርስ የእያንዳንዱ ጸሓፊ ሥራዎች ለማሳተም ሀብትና ንብረቷን በሙሉ ለኅትመት ወጪ በማድረጓ ትልቅ መስዋዕትነትን ከፍላለች። ይህን የሚያውቀው መጽሐፍ አሳትሞ የሚያውቅ ብቻ ነው። ስንቱ መጻሕፍት ነጋዴ የደራሲያን ገንዘብ በአግባቡ የሚከፍለው?

ሙሉጌታ "ጉኖዋ" ስብሃት ደግሞ "ሻህራዛድ" የሚሏት "ጠቢባን የከበቧት ጠቢብ" ስንዱ አበበ እጇን ያስገባችባቸው መፅሀፍት የሙሉጌታ ተስፋዬ የባለቅኔ ምህላ፤ የባሴ ሃብቴ ሲራኖ ትርጉም እና የባሴ ሃብቴ ወንድም ጌታ ወጥ ስራ፤ የተድባበ ጥላሁን መሃልየ መሃልይ ዘካዛንቺስ፤ የመስፍን አሸብር ጠብታ ፍቅር የግጥም መድብል፤ የራሷን ከርቸሌ እና የአርተር ራምቦን የሕይወት ታሪክ ራምቦ መፅሀፍት ደራሲ ናት።

አያ ሙሌ - የልቤ ሰው ለስንዱ አበበ (ጉኖ ዘበናይ)

"ከወሎ ልጅ ውሎ"
ከወሎ ልጅ ውሎ
አንድም ተወልውሎ አንድም አስተውሎ
ልጅትማ ልጅት ናት ...
የወንድ ልጅ ቅናት ...
ስትስቅ ስቅስቅ ...
ስታኮርፍ እርፍ ...
ስትቀኝ ዝስፍ ...
እርግብግብ ...
ዓይነ ርግብ የንስሐ ምግብ ...
የትንሳዔ ግብ ...
ዙፋን ነው ማህፀኗ ...
አብቦ ያፈራ ...
በዘሩ የፀዳ ልዕልት የጥበብ ስልት ...
የለይል የምዓልት ...
ሲወዷት አንድዳ ...
ሲጠሏት ታዝባ ...
ጥዑም ናት ዝምብላ ...
የሕይወት ዘምባባ ...
የበርሃ ተምር ...
የደጋ ተአምር ....
እምቡር እምቡር ስትል ...
እንዳው እምር እምር ድንገት ሳይታሰብ ...
ሰብሰብ እንደክምር የተንሳይ ምሳውን ...
ላጉርሰው ወንድሜን ...
እንዲባርክልኝ ...
ብዕርና ድምድሜን...

ለስብሐት ስንዱ ክርስቶስና መሐመድ አስተማሩ እንጂ አልጣፉም። የእነርሱ አስደማሚ አስተምሮት ሐዋርያቱና ሱሐባዎች ጥፈው አስነበቡን። ፐሌቶ ባይኖር ሶቅራጠስን ለማወቅ ባልታደልን ነበር። ሙሉጌታም እየጣፈ

ይበትን ነበር እንጂ፣ ሰብስቦ አላስነበበንም። ስንዱ አበበ ግን ስራዎቹ በመድብል ሰብስባ ለተደራሲ አቅርባለች፤ ለአንባቢ ጀብታለች። ጉኖ ዘመናይ በግሏ የሐዋርያት፣ የሱሐባዎችና የፕሌቶ ድርሻ ተወጣች። አዎ እሷ ከሐዋርያት፣ ከሱሐባዎችና ከፈላስፎች ተቀመመች።እንደ ሸህ ጫሊ የብዙ ሰው ቅዋ ተሰጣት። እቴጌ … አማልክቱ ለርስዎ ያደላሉ። እስካሁን የሰባት ሰው ቅዋ የተሰጠው ሸህ ጫሊ ብቻ ነበር እማውቃቸው። የክርስቶስ ሐዋርያት፣ የመሐመድ ሱሐባዎችና የግሪክ ፈላስፎች አንድ ላይ ተጨምቀው ባንቾ በኩል ተገልጠው ማየት መታደል ነው።

**Reviewer: A permanent staff editor at Think Ethiopia**

*ርዕስ : ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ*
*ደራሲ: ብላቴን ጌታ ኅሩይ: ወ / ስላሴ*
*የሕትመት ዓመት: 1910 ዓ.ም*

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ለኅትመት የበቁ በርካታ መጻሕፍትን ደርሰዋል። ልጃቸው ላቀች ኅሩይ ከመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያዊ ሴት ደራሲያት መካከል አንዷ ናት። ሌላኛው ልጃቸው ሲራክ ኅሩይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉ ልብወለዶች መካከል የሳሙኤል ጆንሰን "ራሴላስን" ወደ አማርኛ ተርጉሞ በማሳተሙ የመጀመሪያው የሀገራችን ተርጓሚ ያደርገዋል። ይህ "ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ" የተሰኘው መጻሕፋቸው፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ለልጃቸው ፈቃደሥላሴ ኅሩይ የጻፉት ነው። ይህ መፅሀፍ የተደረሰለት ልጃቸው ፈቃደ ስላሴ በጣልያን ወረራ በምዕራቡ ኢትዮጵያ በኩል ከልዑል ራስ ዕምሩ ሀይለስላሴ ጋር ሆኖ ሲዋጋ ተማርኮ ታስሮ ነበር። የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ግራዚያኒ ካስፈጃቸው ወጣቶች አንዱ ነው።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ በተለይ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመርያ ሩብ በሥነ ጽሑፍና በሌሎች የአስተዳደር ጉዳዮች ስማቸው ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ ነበሩ። ከአዲስ አበባ ከንቲባነት እስከ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት በብቃት አገልግለዋል። በሸዋ መርሐ ቤቴ ጊቦ ገዳም በተባለ ሥፍራ በ1871 ዓ.ም. የተወለዱ ሲሆን ከሥራዎቻቸው መካከል “ኢትዮጵያና መተማ (የአፄ ዮሐንስ ታሪክ ባጭሩ)”፣ “የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ የዓድዋ ድል”፣ “ወዳጄ ልቤ፤ የሰውን ጠባይና ኑሮ በምሳሌ የሚገልጽ”፣ “የልዕልት ወይዘሮ መነን መንገድ በኢየሩሳሌምና በምስር”፣ “በኢትዮጵያ የሚገኙ በግዕዝና በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ የመጻሕፍት ካታሎግ”፣ “ማኅደረ ብርሃን ሀገረ ጃፓን”፣ “ለልጅ ምክር ለአባት መታሰቢያ”፣ “የልብ አሳብ፤ የብርሃኔና የጽዮን ሞገስ ጋብቻ”፣ “ጎህ ጽባሕ”፣ “አዲስ ዓለም፤ የቅኖችና የደግ አድራጊዎች መኖሪያ” ይገኙበታል።

መጽሐፉ ልጄ ሆይ እያለ አጫጫር ምክሮችን ይለግሳል:-

"ልጄ ሆይ፤ ሮጠህ ለማታመልጠው ነገር አትሸሽ። እርሱም ሞት ነው። ደጋ ብትወጣ፣ ቆላ ብትወርድ፣ ወንዝ ተሻግረህ ብትሔድ፣ በዋሻ ብትደበቅ፣

ጠመንጃና መድፍ ይዘህ ብትሰለፍ ምንም ቢሆን ከሞት ለማምለጥ አትችልም።"

ልጄ ሆይ፤ በልተህ ስትጠግብ ረኃብን፣ ስትበለፅግ ድህነትን፣ ስትሾም ሽረትን [መሻርን] ... አትርሳ።

ልጄ ሆይ፣ ይህ ዓለም ቀድሞ ከወዴት መጣ ኋላስ ወዴት ይሄድ ይሆን ብለህ ለመመርመር አትጨነቅ። እንኳን የዓለምን ነገር የራስህንም ነገር መርምረህ ለማወቅ አትችልም።

ልጄ ሆይ፤ ወዳጅ ማለት ሰው አይምሰልህ። ነገር ግን ወዳጅ ማለት ጊዜ ነውና በጊዜህ ሁሉ ይወድሃል፣ አለጊዜህ ግን ወዳጅህ እንኳ ይጠላሃል።

ልጄ ሆይ፤ ጠላትህ ሲሞት ወይም ሌላ መከራና ጭንቀት ሲያገኘው ደስ አይበልህ። እርሱ ሞቶ አንተ በዚህ ዓለም አትቀርምና። አንተ ደግሞ በሠራኸው ሥራ እንደ እርሱ መከራና ጭንቀት ሳያገኝህ አይቀርም፤ በመከራና በሞትም የሰው ሁሉ ድርሻው ትክክል እንደሆነ እወቅ።"

ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ዕውቀትን ለመሸመት አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅ ያደርጉት የነበረውን እንቅስቃሴ ሰዎች የተለያዩ ፍረጃዎችንና ትችቶችን ይሰነዝሩባቸው ነበር። ለአብነትም ዓረብኛ ቋንቋን ለመማር ሲሞክሩ “ይኼ ሰው ሊሰልምነው እንዴ”፣ “ፈረንሣይኛና እንግሊዝኛ ለመማር ሲጥሩ ደግሞ ካቶሊክ ሊሆኑ ነው” በማለት ያሚቸው ነበር። የጉዞ ማስታወሻ በሚጽፉበት ወቅት ጃፓን፣ ኢየሩሳሌም፣ ግሪክ፣ ፈረንሣይና ለንደን ሲሄዱ ያጋጠማቸውን ልክ እንደ መዕዋለ ዜና ዘጋቢ የገጠማቸውን ገጠመኝ፣ የተደረገላቸውን አቀባበል፣ ያዩትንና የሰሙትን ይከትቡ ነበር። የጠቅላላ ዕውቀት መጻሕፍትን በሚያዘጋጁበት ወቅት ደግሞ ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ አገር በሚሄዱበት ወቅት በዕውቀት ጉድለት ምክንያት አገርን እንዳያሰድቡ አስቀድመው ምን ማድረግ እንዳለባቸው አሳይተዋል፣ በዚህም አንድ ኢትዮጵያዊ ወደ ውጭ አገር በሚሄድበት ወቅት ከዚህ ቀድሞ ያላየውን አዲስ ነገር ሲመለከት ትልልቅ ሕንፃዎችን፣ ትልልቅ የምግብ ገበታዎችን በሚመለከትበት ወቅት አንድ ጊዜ ካየ በኋላ ዝም ማለት ወይም ደግሞ ደጋግሞ አለማፍጠጥ እንዳለበት ምክር ይሰጡ ነበር። ይህም ወደ ውጭ አገር

የሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ስህተት ሠርተው የአገርን ክብር እንዳያበላሹ በማሰብ የፃፉት ምክር አዘል ጽሑፍ ነው።

የሀገራቸውን ልጆች እንደራሳቸው ልጅ እያዩ ይመክራሉ:-

"የተወደድህ ልጄ ሆይ:- ሰው ሁሉ በዚህ ዓለም የሚኖርበት ዘመኑ እጅግ አጭር ነው። ከዚያውም የሚበዛው በመከራና በሀዘን ይፈፀማል። ይህንንም መከራና ሀዘን አንዳንድ ሰዎች በገዛ እጃቸው ያመጡታል አንዳንድ ሰዎች ግን ሳያስቡት በድንገት ይመጣባቸዋል።"

"ልጄ ሆይየሆነውን ነገር ተናገር እንጂ ገና የሚሆነውን ነገር አትናገር። ለሌሎችም ሰዎች ገና የሚሆነውን ነገር ቢነግሩህም አትመናቸው ክፉ የሚሰራ እንዲጎዳ ደግ የሚሰራ ግን እንዲጠቀም የታወቀ ነውና ደግ ስራ ብቻ እየሰራ ወደ ፊት የሚሆነውን ጠብቅ። ነገር ግን ሁሉ ጊዜው ሲደርስ በግድ ይፈፀማል እንጂ ገዜው ሳይደርስ አይፈፀምምና ለማናቸውም ነገር ቢሆን አትቸኩል።"

"ልጄ ሆይጊዜ ማለት ቀንና ለሊት አይምሰልህ። ነገር ግን ጊዜ ማለት የፈጣሪ አሳብ የሚፈፀምበት ነው። ስለዚህ በሆነውም በሚሆነውም ነገር ሁሉ የፈጣሪ ፍቃድ ይሁን እያልክ ተቀመጥ። ለባሕርይ የሚያስፈልግህን ሁሉ አድርግ ለሌላውም ሰው ለባሕርዩ የሚያስፈልገውን አትከለክል። ለሰው ባህርይ ከሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ዋነኞቹ ሶስት ናቸው ፩ ምግብና መጠጥ ፪ ልብስ ነው ፫ ሚስት ናት። ሰው አነዚህን ሶስቱን ካላገኘ ኑሮው ሁሉ ጎዶሎ ይሆናል። ሰው ምንም ብልህና አዋቂ ቢሆን በራሱ ስራ ብቻ ራሱን ችሎ እንዳይኖር አወቅ። ነገር ግን ሁሉም በየስራው ፀንቶ እርስ በርሱ በስራ ይፈላለጋል። ስለዚህ ሰውን ሁሉ አክብረህ ኑር እንጂ ሰውን አትናቅ። ስራውንም አትንቀፍ።"

"...ልጄ ሆይምንም የሹመት ፍቅር ቢኖርብህ የፈረድህበት ሰው ጠላትህ ይሆናልና የዳኝነት ሹመት አትፈልግ። አንተ ሳትፈልግ ለዳኝነት ሹመት የተመረጥህ እንደሆነ ግን እውነተኛ ፍርድ የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነውና በዳኝነት ነገር ጠላትህን ለመጉዳትና ወዳጅህን ለመጥቀም እንዳታስብ ተጠንቀቅ። እውነትን በሐሰት ለውጠህ የፈረድህ እንደ ሆነ ግን

የእግዚአብሔርን ገንዘብ ማጥፋት ነው። ይህንም በማድረግህ ባንተ ላይ ከሁሉ የበለጠ ፍርድ ይፈረድብሃል።”

ኅሩይ ወደ አገር ቤት የሚመጡ አዳዲስ ነገሮችን ለመሞከር የሚቀድማቸው አልነበረም። ስልክ አዲስ አበባ በገባበት ወቅት በግላቸው (በቤታቸው) አስገብተው ሲጠቀሙ ከነበሩ አራት ሰዎች መካከል እሳቸው አንዱ ነበሩ። በሌላ በኩል ሴት ልጆቻቸውን ወደ ውጭ አገር ልከው ማስተማር ከቻሉ የመጀመርያዎቹ ሦስት ሰዎች መካከል አንዱ ነበሩ። በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ሴት ልጅ አግብታ መውለድ፣ ሙያም መማር እንጂ እንዴት ለትምህርት ተብሎ ወደ ውጭ አገር ይልካሉ በማለት ይተቹ ነበር። በፋሺስት ጣሊያን የወረራ ዘመን (1928-1933) ከንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር በእንግሊዝ በስደት ሳሉ በ1931 ዓ.ም. ያረፉት ብላቴን ጌታ ኅሩይ፣ ቀብራቸው በባዝ ከተማ ሉግዘምበርግ ሲፈጸም፣ በሥርዓተ ቀብር ላይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባሰሙት ዲስኩር እንዲህ ብለው ነበር፡-

“ታላቅ ነህ ሳልልህ ብቀር ሥራዎችህ ቀድመውኝ ይናገራሉ። ይህ የአዳም ልጆችን ወግ ሲቀበል የምታዩት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በሀገራችን ሥርዓት በመልካም አያያዝ ያደገ፣ ከኢትዮጵያም ከፍ ከአሉት ሊቃውንት የሚቆጠር ነው። ብልኃቱንና ትጋቱንም ለመልካም ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ስላደረጋቸው በመንግሥታችን ሥራ ለመመረጥና ወደ ታላቁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ለመድረስ ችሏል። በጊዜውም የጻፋቸው መጻሕፍት ከፍተኛ ባህሪውን የሚገልጹ ይልቁንም በቤተ ክህነትና በታሪክ ዕውቀት በዓለም ሊቃውንት ዘንድ የታወቀና የተከበረ አደረጉት። ለምታውቁት ሰው ከታሪኩ ከዚህ የበለጠ ልነግራችሁ የሚያስፈልግ አይመስለኝም።” ጣሊያን ሲወገድ በ1940 ዓ.ም. አፅማቸው ፈልሶ በአዲስ አበባ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል።

የብላቴን ምክር ይቀጥላል:-

“ልጄ ሆይ ከኃይለኛና ከነገረኛ ሰው ጋራ አትጣላ። ከነገረኛና ከኃይለኛ ሰው ጋር መጣላት በሚነድ እሳት ላይ ገለባ እንደመጨመር ነውና ተጠንቀቅ። ”

“ልጄ ሆይ ለጌታህ ገንዘብ አታበድር። ክፈለኝ ባልኸው ጊዜ ነገር ፈልጎ ወደ ዳኛ ይወስድሃልና።”

"ልጄ ሆይ ጠላት በዛብኝ ምቀኛ አሴረብኝ ብለህ እጅግ አትጨነቅ። በዓለም ይሚኖር ፍጥረት ሁሉ ጠላትና ምቀኛ አለበት እንጂ ባንተ ብቻ አይደለም። ከዚሁም በጥቂቱ እጽፍልሃለሁ።”

“በፍየል ነብር፣ በበግ ተኩላ፣ ባህያ ጅብ፣ በላም አንበሳ፣ በዓይጥ ድመት፣ በዶሮ ጭልፊት አለባቸው። ይህንንም የመሰለ ብዙ አለ። ሰውም እርስ በርሱ እንዲሁ ነው...ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባነት፣ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት፣ በቀይ መስቀል፣ የውጭ ዜጎችን በሚዳኝ ልዩ ፍርድ ቤት፣ በኢትዮጵያ ባንክ አስተዳደር ምክር ቤት ውስጥ በፕሬዚዳንትነት፣ ከሃያ በላይ መጻሕፍትንም በማሳተም ለአገር ልማት አገልግለዋል። ኅሩይ ኢትዮጵያ ወደ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ስትቀላቀል ልዑክ በመሆን፣ በመጨረሻም በጣሊያን ስትወረር አቤቱታዋን ለማሰማት ከቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር ሰፊ ጥረት ያደረጉ የአገር ባለውለታና በጥንታዊ የአገር በቀል ዕውቀቶችና በዓለም አቀፋዊ ጉዞና ንባብ የተቀረጹ ነበር።”

Reviewer : A Permanent Staff editor at Think Ethiopia

*ርዕስ: የትዝታ ፈለግ*
*ደራሲ: አሰፋ ጫቦ*
*ዘውግ: የመጣጥፎች ስብስብ*
*የሕትመት ዓመት: 2008 ዓ.ም*

አሰፋ ጫቦ ‹የትዝታ ፈለግ› በሚል ርዕስ ለንባብ ያበቃው እና 28 መጣጥፎችን የያዘው መጽሐፍ ወደማናቃቸው ጊዜያት እና ቦታዎች ከመውሰዱም ሌላ የአጻጻፍ ውበቱ እጅግ ያስደንቃል። አቶ አሰፋ ጫቦ ከአባቱ ከጫቦ ሣዴ ሃማ ያሬና ከእናቱ ከማቱኬ አጀን ከተራራ አናት ላይ ከሚገኝ ሜዳማ ቦታ ላይ ጨንቻ ከተማ ነው የተወለደው። ከጋሞ ሰንሰለት ተራራዋች አንዱ ጫፍ ላይ የሚገኝ ጠረጴዛ ነው ይላታል ጨንቻን ሲገልጣት ከ2-6ኛ ክፍል እዚያው ጨንቻ የተማረ ሲሆን በዘጠኝ ዓመቱ የጨንቻ ገብርዔል ዲያቆን በመሆንም አገልግሏል።

በድቁናው ባገኘው ካፒታልም ጥቂት የዶሮና የበግ ግልገል ገዝቶበታል። ሐሙስ ሐሙስን እየጠበቀ ኤዞ ገበያ ዶሮና እንቁላል እየነገደ ይውል ነበር። ከእነሱም ውስጥ ት/ቤት ድረስ እየተከተሉ ያስቸግሩት የዶሮና የበግ ግልገልም ነበረው። የ 8ኛ ክፍል ትምህርቱን በሻሸመኔ በኋላ ታሪኩን ሲያውቅ ስሙን ካላስቀየርኩ ብሎ ከታገለበት ከአጼ ናኦድ ት/ቤት ከ39 ተማሪዎች አንዱ በመሆን ነበር የተከታተለው። የተዋቀረበትን ዋልታና ካስማ ያየበት ቆይታው በጋሞ ውስጥ ካሉ 40 ከሚሆኑ ‹ካዎ›ች አንዱ በሆኑት በዘመዱ በቀኛዝማች ኢሌታሞ ኢቻ ቤት በኖረበት ወቅት ነበር።

ሲገልጻቸውም ‹በኢሌታሞና በሰዋች መሀከል የግንኙነት አጥር የለም። ወግ ሳያበዙ ለሕዝብ አሳቢና ተቆርቋሪ ናቸው ነው የሚላቸው የጋሞ ካዎ የሚፈራ ሳይሆን የሚከበር ነው ይለናል። ገና በልጅነቱ ለሕዝብ በመስራት እርካታ ማግኘት እንደሚቻልም የተገነዘበው በጉሌታ-አንዱሮ ግብር ተቀባይ ተደርጎ በቀኛዝማች ኤሌታሞ ሲመደብ ነው።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ከአዲስ አበባ ከኮከበ ጽባህ አቋርጦ ሲቪል አቪዬሺን ተቀጥሮ ባህር ዳር ሄደ። ሀ ብሎ የመጀመሪያውን ስራውንና የመጀመሪያ ልጁንም ያገኘው ጎጃም ነበር። ‹ጎጃሜ ተነቀለ› ብሎ ፖሊስና

እርምጃው ላይ ጽፎ ጠፍቶ እስከወጣ ድረስ እዚው ነበር። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሕግ ት/ቤት LLB አግኝቶ የተመረቀ ሲሆን በዓለም አቀፍ የህግ ተማሪዋች ውድድር ከውጭ የምስክር ወረቀት ከንጉሱም የወርቅ ኦሜጋ ሰዓት ተሸልሟል። በ1960 የሕግ ተማሪ ሆኖ በአፍሪካ አዳራሽ የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር ስብሰባ ላይ ከመጮህ ጀምሮ ይህው እስከእልፈተ ሞቱ ድረስ ለአገርና ለወገን ዋይታውን አላቋረጠም ነበር። በአጠቃላይ የአጥቢያ ፍ/ቤት ጸሐፊ፤ የበጅሮንድ ጽ/ቤት ተላላኪና ጸሐፊ የአየር መርማሪ (metrology) የሕግ አማካሪ ሆኖ ሰርቷል።

በፖለቲካው መስክ ከተማሪዎች ንቅናቄ ባሻገር የሁለት ድርጅቶች መስራችና መሪ ሲሆን ከ1966-1967 የልጅ እንዳልካቸው አዲሱ ካቢኔና የደርግ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆኖ ጋርዱላ ሄዶ ነበር። በጄኔራል መብራቱ ፍስሃ ታስሮ እስከተባረረ ድረስ የፖለቲካ ድርጅት መስራችና መሪ፤ የአውራጃ አስተዳዳሪ የመንግሰትና የባለስልጣን አማካሪ፤ የሕዝብ ተከራካሪ በመሆን በለውጡ ውስጥ ሰርቷል።

በኋላም በራሱ ከግቢ የመራቅ ጥያቄ አነሳሽነት “በችሎታው መጠን ሥራ ይሰጠው” የሚለውን ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ የፈረመበትን ደብዳቤ ይዞ መገናኛ ሚኒስቴር ወረደ። ከዚያ ነው እንግዲህ በየካቲት 1971 ዓ.ም መጀመሪያ ወደ ደርግ ጽ/ቤት ታፍኖ ተወስዶ ከዚያም በማዕከላዊ ታስሮ ከ10 ዓመት ከ6 ወራት ከ6 ቀናት በኃላ የተፈታው፤ ማዕከላዊ እስር ቤት የሰው ገበያ ነበር ብሎ ሲገልፀው በ10 ዓመት የእስር ዘመኔ ውስጥ ከ100.000ሺ በላይ ሰው አይቼበታለው ይለናል ካያቸውም ውስጥ በባህርይ፣ በቁመና፣ በአለባበስና በስነምግባራቸው ጥሩ አድርጎ በመጽሐፉ ውስጥ ይገልጻቸዋል።

ዋታካዳ እንደሚጠሩት “ጋንታይናው” ‹ጋትዬ› አሰፋ ጫቦ ዛሬ አብዛኛው እየፈራ እየሸሸ ምክንያቱን በሚደረደርበት ወቅት እሱ ምን አቅብጦኝ ከደርግ ጋር ገጠምኩ ብሎ አያውቅም አምኖ እንጂ ምናምን ፍለጋ ወይም ሰው ገፍቶት እንዳልገባ በግልጽ አስቀምጦልናል እንዲያውም ‹በመሸ በጠባ ቁጥር በጥሼ የምቀጥለው ማተብ› የለኝም ይል ነበር። በንባብ የዳበረ የበሰለ መሆኑን ከማሳየቱም ሌላ ስለ አሜሪካ መምጣትና መኖር ያካፈለው ምክር በቀላሉ የሚታይ አይደለም ስለስደቱ ዓለም ችግርና ውጥንቅጥ ሲጽፍም ስደተኛው

በሃብት ድህነትና በአእምሮ ድህነት መሃከል ያለው ልዩነት የጠፋበት መምሰሉን ፍንትው አድርጎ አቅርቧል። በአጠቃላይ ጆሮ ጠገብነት ማወቅን አለመተካቱን ያሳውቀናል ጀግና ፍለጋ ጦር ሜዳ መሪዋች አምባ የፖለቲካ ሰዋች አምባ እንኄዳለን። ጋሞ ግብር ገበረ እንጂ ሥርዓቱን አልገበረም በማለት ጥፋቱን ስህተቱን በማመን መቀበልና ባደባባይ ይቅርታ መጠየቅ የጋሞነት ገላጭ አብሮ የተወለደ የውስጥ ባህርይ መሆኑን በመተንተን ለየት ስላለው የአገርና የህዝብ አስተዳደር ሥርዓት ሲያጫውተን አንዳንዶቻችን በአገራችን ውስጥ ይህ መኖሩን ባለማወቃችን እንቆጫለን ወደዛሬያችን ለማምጣት በምኞት እንጋልባለን።

"እነታጋይ መለስ የኢትዮጵያ ታሪክ የ100 አመት ነው ሲሉ አብዛኛው ሰው ኡኡ! አለ። የ3ሺ፣ የ5ሺ ታሪክ የት ሄደ? ለማለት ነው። ነገሩ ግን በመሠረቱ እውነት አለው። ከአፄ ዮሀንስ ወዲህ ማለታቸው ይመስለኛል። ከሚኒሊክ እስከ ደርግ ማለታቸው ነው። ይቺ አገር የዛሬ መልኮን በአመዛኙ ያገኘችው ከሚኒሊክ ወዲህ መሆኑ አይካድም።

የወያኔ አቀራረብ ታላቅ ስህተት ያለው መንፈሱ ላይ ነው። ከጀርባው ባለው አጀንዳም ላይ ነው። ይህም ናፖሊዮን ስለ ጣሊያን አለ የተባለውን ያስታውሰኛል። "Italy is a geographic expression" (ጣሊያን ስም እንጂ አገር አይደለም ማለቱ ነው) ወያኔም ኢትዮጵያ የጎሳዎች ጥርቅም እንጂ አንድ አገር አይደለችም ነው የሚለው። በአገሩ ሙሉ መንደርተኛ እንጂ ኢትዮጵያዊ የሚባል ነገር (Ethiopian personality) አልወጣም ነው የሚሉት። "ይሄ እንዴት ይሆናል!!? እኔ ጋሞ ነኝ። ኢትዮጵያዊም ነኝ። ሁለቱ ተጣልተው ለማስታረቅ ተቀምጬ አላውቅም። የኔ ቢጤ በሺዎች የሚቆጠሩ አውቃለሁ። የማላውቃቸውም ሚሊዮኖች ይኖራሉ።" ገፅ 132

በአዲስ አበባ የሚኖሩ ጋሞዎች በአንድ ወቅት እለተ ሰኞን በየሳምንቱ ይቀድሷት ነበር። ሰኞን እንደ ቅዱስ ቀን ይጠቀሟታል፥ ለእርቅ አላማ ያውሏታል። የቁጣ እሳት አብርደው የፍቅር ኩራዝን ይለኩሳሉ።አሰፋ ጫቦ "የትዝታ ፈለግ" በሚለው መፅሐፉ ሰኞ 'ዶርዜ ማራም' ትባል እንደነበር ጠቅሷል። የዶርዜዎች ማሪያም እንደማለት ነው። ቅዳሜ እና እሁድ በማህበር ጠላ፥ በሰፈር አረቄ፥ በድግስ ጠጅ ወዘተ ተገፋፍተው የሚጣሉ ይኖራሉ።

ፀበኞቹ እንዳቸው በሌላ አካላዊ ጉዳት ያደርሱ ይሆናል። በፀብ ንብረት ቢወድም፥ አካል ቢጎዳ ከዶርዜ ማራሞ ፀቡ አያልፍም። አዲሳባ ያሉ የጋሞ ሰዎች በእለተ ሰኞ ለእርቅ ይቀመጣሉ። ጋሞ ሆኖ የተጣላን ሁሉ ያስታርቃሉ። በዳይ ይቅርታ ይጠይቃል፥ ተበዳይ ይቅርታ ያደርጋል። ሽማግሌዎች እርቅን ያፀናሉ። ሰኞ የስራ መጀመሪያ ቀን ነው። ጋሞዎቹ ግን ሰኞን በስራ አይጀምሩም። “ሳምንቱ መጀመር ያለበት የተጣላን በማስታረቅ ነው። ስራ ከእርቅ በኋላ ይደርሳል” ይላሉ። የትዝታ ፈለግ መፅሐፍ ደራሲው አሰፋ ጫቦ በዘመነ ደርግ ስልጣን ነበረው። በእርሱ የስልጣን ዘመን ቤቱ የሚመጡ የጋሞ ተወላጆች ነበሩ። “አሴፓ ከሰው ጋር ተጣልቶ የታሰረ የጋሞ ሰው አለ። ና ዋስ ሁን” ይሉታል። ዋስ ሊሆን ይሄዳል። ከሰው ተጣልቶ የታሰረውን ዋስ ሆነው ካስወጡት በኋላ ወደ ቤቱ አይሰዱትም። ከተጣለው ሰውጋ ያስታርቁታል። በየሳምንቱ ሰኞ ጋሞዎች ተሰባስበው እርቅ ይፈጥራሉ። ያቺን የእርቅ ቀን “ዶርዜ ማራሞ” ወይም “የዶርዜዎች ማሪያም” ይሏታል።

“ማንኛውም ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ መለኪያ፣ መመዘኛ የፀና የማይለወጥ ዘላለማዊ አይደለም። ጊዜ፣ ቦታ፣ ወቅት፣ ዘመን አይቶ እንደሁኔታው የሚለወጥ ነው። በእጃችን የያዝነውን፣ በፊታችን የተደቀነው ችግር መፍትሄ የሚሻ መሆን መቻል ያለበት ይመስለኛል። ፖለቲካ ባዶ ሕዋ (vacuum) ላይ የሚሰራ ትርዒት አይደለም። ዛሬ ያለንበት ሁኔታ የዛሬ መለኪያ፣ የነገን መፍቻ ቁልፍ ይጠይቃል። የትናትናውን ሙሉ በሙሉ አውልቀን አንጥልም። ትምህርት እናገኝበታለን። ፋይሉ ታይቷል፤ ይቀመጥ፤ ይደር፤ እንላለን። የቢሮከራሲ ቋንቋ መጠቀሚያ ነው። ትናንት ከዛሬ፣ ከወቅቱ፣ ከተደቀነብን “እውነት” ጋር ታርቆ ባይታረቅም፤ ተቻችሎ መሄድ ያለበት ይመስለኛል።” (ገጽ 55)

ይህ መጽሐፍ የተለያዩ መጣጥፎችን ብቻ የያዘ ሳይሆን የአሰፋ ጫቦንና ጨንቻ ጋሞን ጠብሰቅ ያለ ታሪክ የያዘ ግለታሪክ ነው ብለን መውሰድም እንችላለን። ጋሻ አሰፋ ስለጋሞና ስለ ትውልድ ቦታቸው ጨንቻ አንስቶ አይጠግብም ሰለጨንቻና ስለ ጋሞ የአኗኗር ዘይቤና ፍልስፍና አንስተው በትዝታ ሲነጉዱ ብቻቸውን ሳይሆን አንባቢውንም ይዘው ነው።

*"ይቅርታ ለማድረግ የሚሳነን እንኳ ቢመስል ፖለቲካ የመቻቻል ጥበብ መሆኑን ልብ ልንለው የሚገባን ይመስለኛል። በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ በፊትም ደርግ ኢሠፓ ጥፋቱ ብቻ ጠፍቶኝ አያውቅም። ኢትዮጵያን ከፊውዳሊዝም ማላቀቁ አብሮ ይታየኛል። "ከመሬት ላራሹ" ጋር አብሬ አየዋለሁ። ከባሮ፣ ከአባይ ድልድይ፣ ከመልካ ዋከና፣ ከግልገል ጊቤ ኃይል ማመንጫ፣ ከሙገር ሲሚንቶ ፊብሪካ...ከአርባ ምንጭ የውሃ ቴክኖልጂ ኮሌጅ...ከበደሌ ...ከሃረር...ቢራ ፋብሪካ ...ከነዚህ ጋር ሁሉ አየዋለሁ። በጦፈ ጦርነት መሃል የተሰሩ በመሆናቸው የበለጠ ክብደት እሰጠዋለሁ። ደርግን የመላው ደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብ በስምም በግብርም ኢትዮጵያዊነታቸው እንዲረጋገጥ እንዳደረገ አድርጌ እቆጥረዋለሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ በአገራቸው ሥልጣን፣ ቦታ የያዙበት ዘመንና ሥርዓት ነው። ቃዲና ፓትርያርክ ጎን ለጎን ከአገሪቱ መሪዎች ጋር እኩል የተቀመጡበት ስርዓት ነው። የደርግን የኢሠፓን "ወንጀል" ስመለከት እኔ ከነዚህና እዚህ ያልተጠቀሱ ሌሎችንም "ቅጣት ማቅለያዎች" ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ያ እኔ ነኝ። ሌላውም እንደዚያ ቢያደርግ ደስ ይለኛል።"* (ገጽ 58 )

እንዲህ ያለ የይቅርታና ሚዛናዊ ልብ ያለው ከአሰፋ ውጪ የለም ብንል ምንም ውሸት አይኖረውም። አሰር አመት በእስር ያሳቃየህን መንግስት በዚህ መልኩ ጥሩ ጎኑን ለመጻፍና ለመመስከር የግድ አሰፋን መሆን ይኖርብሃል። ያለፉትንም ሆነ አሁን ያለውን መንግስት በጥላቻ ስናነሳ ለምንውልና ፍጹም ጨለምተኞች እና ዘረኞች ለሆንን ሰዎች ይህች የአሰፋ አንቀጽ ብዙ ነገር ታስተምረናለች:-

*"....ወደ እኛ ቤት የሚወስደውን የመንገድ ካርታ ልስጣችሁ።.... አባቴ ዳና ሳዬ፣ ሀማ፣ ያሬና፤ እናቴ ማቱኮ አጆ ሙሉ ጋሞ ናቸው። ታላቅ ወንድሜ 12 ልጆች ወልዷል። የስምንቱ እናት ታየች በዛብህ የጋሞ ነፍጠኛ አማራ ናት። የአራቱ እናት ትግሬ ነች።"*

የእኔ ልጆች 3ቱ እናት ጎንደሬ መስላኝ ነበር። እናቷም እሷም ጎንደር ስለተወለዱ ጎንደር ስላገባኋት። ጠጋ ብዬ ሳይ የእናቷ እናት ካፊቾ ናቸው። በሚኒሊክ ወረራ ተማርከው ከወጡት ከከፋ ልዕልቶች ውስጥ ነበሩ። የጋኪ

ሻረቾ ዘመድ ነበሩ። በ1956 እኔ ሳናግራቸው ዕድሜያቸው ከ100 አመት በላይ መሰለኝ። አማርኛ አይችሉም። ድንገት ካሬቾ ቢችሉ ከማን ጋር ሊነጋገሩ? የባለቤቴም አባት አዘዞ ተመድቦ የነበረ ወታደር የሸዋ ኦሮሞ ነው ተባለ። አንዱ ልጄ ¼ኛ ጉራጌ ነው።

የእህቴ ባል ኦሮሞ ነው። ባሏ ደግሞ የሄደው ከሰላሌ ነው። አምስት ወልደዋል። አንዱ ወንድሜ ሶስት ልጆች አሉት። ትልቋ ግማሽ ኩኩዩ ነች። የሁለቱ እናት እንግሊዛዊት ነች።

“የሻቱ በዛብህ ሚስት ንግስቲ መረፅ ስመ ጥር ሀማሴን የሻሸመኔ ልጅ ነች። ሻሸመኔ ከወንድሟ ከኢትዮስ መረፅ ጋር አጼ ናዖድ ትመህርት ቤት አብረን ነበርን። ሻቱ የታየች ወንድም ነው። አማራ የጋሞ ነፍጠኛ ነው። ወልደው ከብደዋል። የእኔ ልጆች ሁለቱ አግብተው ወልደዋል። ትልቁ ባህርዳር የተወለደው ልጄ ሚስቱ ኤርትራዊት ነች። የሀረር ኤርትራዊት። ትንሿ ልጅ ያገባችው ግማሽ አማራ የሆነ ልጅ ነው። ኧረ ተውን! እንዲህ ተወሳስቦ እያለ አትከልክሉን! ማሩን! ኢትዮጵያዊ በሉን! የእኛ ቤት መቀላቀል ገና አንድ ሁለት ትውልድ ነው። ለአስር ትውልድ ያህል የኢትዮጵያ ውብ ጥበብ (ሞዛይክ) ገጽታ የፈጠሩ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን አሉ።” ገፅ 148

በተፈጥሮው ሰው መጥላት የማይፈልገው አንጋፋው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች፣ ቀጥተኛው፣ ብዕረኛው አቶ አሰፋ ጫቦ በ73 ዓመት ዕድሜው የአራት ልጆች አባትና የዘጠኝ ልጆች አያት ሆኖ በአሜሪካ ቴክሳስ ሀገረ ግዛት በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ ሕይወቱ አልፏል።

Reviewer : A Permanent staff editor at Think Ethiopia